አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ሥራ ቁሶች በደጋ ዳሞ ወረዳ

በ
በአስማማው እስተዚያ ዘለቀ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር
ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ከሚጠበቁ ግዴታዎች ከፊሉን
ለማሟላት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

የካቲት 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ሥራ ቁሶች በደጋ ዳሞት ወረዳ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በ
አስማማው እስተዚያ ዘለቀ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር
ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ከሚጠበቁ ግዴታዎች ከፊሉን
ለማሟላት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

አማካሪ
ሰላማዊት መካ (ረ/ፕሮፌሰር)

የካቲት 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ሥራ ቁሶች በደጋ ዳሞት ወረዳ

በ

አስማማው እስተዚያ ዘለቀ

ILS LIBRARY

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

LIBRARY

አማካሪ

ፈራማ

ፈታኝ

ፈርማ

ማውጫ

ርዕስ **ገጽ**

ምስጋና ---------- I

አጠቃሎ ---------- II

የሰንጠረዥ ማውጫ----------III

የደጋዳሞት ወረዳ ካርታ----------IV

ምእራፍ አንድ 1

1. መግቢያ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ 1

1.2. የጥናቱ ዓላማ 5

1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ 5

1.4.የጥናቱ ወሰን 6

1.5. የጥናቱ ዘዴ 7

1.5.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ 7

1.5.2. የመተንተኛ ዘዴዎች 11

1.6.የመስክ ተሞክሮ 11

1.7. ያጋጠመ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች 14

ምእራፍ ሁለት 17

2. ክለሳ ድርሳን 17

2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት 17

2.2. ትውራዊ ዳራ 23

2.2.1. የቁሳዊ ባህል ምንነት 23

2.2.2. ቁሳዊ ባህሎችን የመመደቢያ መስፈርቶች 30

2.2.3. ቁሳዊ ባህልን የመተንተኛ ሞዴሎች /አንባሮች/ 33

2.2.4. የቁሳዊ ባህል በመጥፋት ላይ መሆንና ያሳደሩ ተፅዕኖዎች 36

ምእራፍ ሦስት 44

3. የደጋ ዳሞት ወረዳ ዳራዊ መግለጫ 44

3.1. የደጋ ዳሞት አሰያየም ታሪካዊ አመጣጥ 44

3.2. መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥና የአየር ፀባይ 46

3.3. የህዝብ ብዛት፣ የቋንቋና የሃይማኖት ሁኔታ 47
3.4. ማህበራዊ ግንኙነት 48
3.5. የህዝቡ የኑሮ መሰረትና መስህብነት ያላቸው ቦታዎች 51
3.6. የቁሳዊ ባህል ሰሪዎችና ማህበራዊ ደረጃ 53
ምእራፍ አራት 56
4. የመረጃ ገለፃና ትንተና 56
4.1. በመጥፋት ላይ ያሉ ባህላዊ ቤቶች 56
4.1.1. የባህላዊ ቤቶች አይነትና መስሪያ ጥሬ ቁሳቸው 56
4.1.2. የባህላዊ ቤቶች የአሰራር ሂደት 68
4.1.3. ባህላዊ ቤቶቹ በመጥፋት ላይ ለመሆናቸው ተፅዕኖ ፈጣሪዎች 73
4.1.4. የደጋ ዳሞት ወረዳ ባህላዊ ቤት ሰሪዎችና ማህበራዊ ደረጃ 76
4.2. በመጥፋት ላይ ያሉ የእጅ ስራ ቁሶች 77
4.2.1. የድንጋይ ወፍጮዎች 78
4.2.2. ከቆዳ የሚሰሩ ቁሶች 90
4.2.3. ከሳር አይነት የሚሰሩ ቁሶች 105
4.2.4. ባህላዊ የስፌት እቃዎች 113
4.2.5. ባህላዊ የእጅ ስራ ቁሶች በመጥፋት ላይ ለመሆናቸው ተጽዕኖ ፈጣሪዎች 126
4.2.6. የደጋ ዳሞት ወረዳ ባህላዊ የእጅ ስራ ሰሪዎች ማህበራዊ ደረጃ 135
ምዕራፍ አምስት 139
5 ማጠቃለያና ይሁንታ 139
5.1 ማጠቃለያ 139
5.2 ይሁንታ 140
ዋቢ ጽሑፎች 142

ምስጋና

በመጀመሪያ እኔን ለዚህ ደረጃ ላበቃኝ ለእግዚአብሄር ምስጋና ይድረሰው። ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ውድና የተጣበበ ሰዓታቸውን ሰውተው ጽሁፌን በማንበብ፤ ስህተቶቼን በማረምና አቅጣጫ በማሳየት ቀና ድጋፋቸው ላልተለየኝ ለአማካሪዬ ለረ/ፕሮፌሰር ሰላማዊት መካ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በመስክ ቆይታዬ መረጃ በመስጠት ጥናቱ እንዲሳካ ቀና ትብብር ያደረጉልኝን በአባሪው ክፍል ስማቸው የተጠቀሰውን መረጃ አቀባዮቼንና የደጋ ዳሞት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊና ባለሙያዎችን ከልብ አመሰግናለሁ። በትምህርት ቆይታዬ ወቅት የማይጠገብ እውቀታቸውን ለለገሱኝ መምህሮቼ ዶ/ር ዮናስ አድማሱና ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ የከበረ ምስጋናዬ ይድረሳቸው። በተለይ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ በቁሳዊ ባህል ዙሪያ ያሉ የቲዎሪ መጻሕፍትን በመጠቆም ያደረጉትን ትብብር ልረሳው አልችልም።

ይህን ጥናት በማጠናበት ወቅትም ሆነ በምማርበት ጊዜ ሁሉ ልጆቻችንን የመንከባከብ የጋራ ኃላፊነት ደርባ በመውሰድ ላደረገችው ተጋድሎ ውድ ባለቤቴን አለም ድልነሳን፣ እንዲሁም ተናፋቂ ልጆቻችን ሳሙኤልና አቤል አስማማው የመዝናኛ ጊዜያችሁን ሰውታችሁ በፍቅር ትመለከቱኝ ስለነበር ከልቤ ውስጥ በክብር ትኖራላችሁ።

ይህንን ጥናት ለመስራት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቂ ባይሆንም ላደረገልኝ የገንዘብ ድጋፍ አመሰግናለሁ። እንዲሁም የትምህርት እድል ለሰጠኝ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ (በተለይ የትምህርት ቢሮው ኃላፊ አቶ ዲላሞ አቶሬ) ምስጋናዬ ይድረስልኝ። መቅረፀ ድምፅ በማዋስና በማበረታታት ድጋፉን ለቸረኝ ለፀጋዮ ሽንብር፤ የሁልግዜ ጉትጎታቸው ላልተለየኝ ለያለው ዘለቀ፤ ለመንግስተአብ ተሾመ፣እንዲሁም ለመላው ለኤፍ ኤም 94.7 ሬዲዮ ጣቢያ ሰራተኞች ምስጋና ይገባቸዋል።

የቪዲዮና የፎቶ ካሜራ ላዋሰኝ ለአቶ የሮም ገሰሰ፤እንዲሁም ጹሑፌን ኤዲት አደርግ ዘንድ ላፕቶፕ የሰጠኝን ተማሪ ደረጀ መርሻ ከልብ አመሰግናለሁ። የክፍል ጓደኞቼ (አሻግሬ ዳምጤ፤ሞገስ ጀምበሩ፤ምህረት ተስፋዬ፣ሃፍታይ ገ/እግዚአብሄርና ቤተልሄም ኃይሉ) ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

በመጨረሻም ይህን ጥናት መልክ በማስያዝና ፎቶግራፎቹን ወደ ጽሑፉ በማስገባት የተባበረችኝን የስራ ባልደረባዬ ትዝታ ዘውዱ ምስጋናዬ ይድረስሽ።

I

አጠቃሎ

ይህ ጥናት "በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ሥራ ቁሶች በደጋ ዳሞት ወረዳ" በሚል ርዕስ ሲዘጋጅ በወረዳዋ በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ሥራ ቁሶች አሰራር፣ ብሎም በምን ተጽእኖና እንዴት እየጠፉ እንዳሉ በመግለፅ የማሳየት ዓላማን ይዞ ነበር።ዓላማውን ማሳካት ይቻል ዘንድ አጥኝው የቃል መጠይቅንና ምልከታን በዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት፣ የጽሁፍ መጠይቅን፣ የናሙና ጥናትንና የተተኳሪ ቡድን ውይይትን በአጋዥነት ተጠቅሟል። በነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙትን መረጃዎች በምዕራፍ ሁለት በቀረቡት ንድፈ ሃሳቦች መሰረት ገለፃና ትንተና መስጠት ተችሏል። ከገለፃና ትንተናውም የተለያዩ ውጤቶች ተገኝተዋል።

በጥናቱ የተተኮረባቸው ባህላዊ ቤቶች (ደርብ፣ አዳራሽ፣እልፍኝና ጎጆ ቤት) እና የእጅ ሥራ ቁሶች ማለትም የድንጋይ ወፍጮ፣ የቆዳ ውጤቶች፣ ከሳር ዓይነት የሚሰሩና የስፌት እቃዎች ናቸው። እነዚህ ባህላዊ ቁሶች በአካባቢው በሚገኙ ከእንጨት፣ ከሳር፣ ከድንጋይ፣ ከጭቃ፣ ከሀረግ፣ ከቀርከሃና ከውሃ ኃይል ጥሬ ቁስ የሚሰሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል። ባህላዊ ቁሶቹ የመሰራታቸው ምክንያትም ለመጠለያነት፣ ምግብ ለመመገቢያነት፣ እህልን ለመፍጨት፣ ለልብስነት፣ ለምንጣፍነት፣ ለግብርና ሙያነት፣ ለመጫኛነትና ጓዝን ወይም ምርትን ለማጓጓዣነት፣ ለዝናብና ለፀሃይ መከላከያነት፣ እህልን ለመሰፋፈሪያነትና ለማቀራረቢያነት፣ እህልን ለመንፊያነትና ለማበጠሪያነት እንዲሆኑ የተሰሩ ናቸው።

በሌላ በኩል ለአገልግሎት ተግባር መፈፀሚያነት ከሚውሉበት ዓላማ ውጪ የተመረጡ ቁሶች በተመረጡ የስነቃል ግጥሞች ተተንትነዋል። እነዚህ ባህላዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች ይዘውት የነበረውን ቅርፅ፣ ይሰጡት የነበረውን አገልግሎትና ጥበባዊ እሴት ከነተፈጥሯዊ አውዳቸው በተለያዩ ተፅዕኖ ፈጣሪ ምክንያቶች የተነሳ ጨርሶ የመጥፋት፣ የቅርፅና የጥሬ ቁስ፣ እንዲሁም የአገልግሎት ለውጥ ተከስቶባቸዋል። ጥናቱም ከዚህ ድምዳሜ ላይ ደርሷል።

ይህን የጥናት ድምዳሜ ከግንዛቤ በመውሰድ የወረዳዋ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤትም ሆነ የአካባቢው ማህበረሰብ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋትም ሆኑ የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች እንዲሁም የሀገሪቱ ዘመናዊ የምህንድስና ባለሞያዎችና በየደረጃው ያሉ አካላት ሀገረሰባዊ ቤቶችንና የእጅ ስራ ቁሶችን በመጥፋት ላይ የመሆን አደጋን በማሳየት በጋራ እንዲንከባከቡ የሚያሳስቡ ይሁንታዎችን በመስጠት ጥናቱ ተጠናቋል።

ማውጫ

ርዕስ **ገጽ**

ሰንጠረዥ-1 የደጋ ዳሞት ወረዳ ባህላዊ ቤቶች አማካይ መጠን ---------- 68

ሰንጠረዥ 2- የቤትና የውሃ ወፍጮ አማካይ መጠን ማሳያ ሰንጠረዥ---------- 90

ሰንጠረዥ 3 የስፌት ዕቃዎች አማካይ መጠን ማሳያ ---------- 126

የዲጋ ዓለም ዐቀፍ ወረዳ = ካርታ

ምእራፍ አንድ

1. መግቢያ

ይህ ጥናት በአማራ ክልል፣ በምእራብ ጎጃም ዞን በደጋ ዳሞት[1] ወረዳ በመጥፋት ላይ ባሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። ሀገረሰባዊ ቤቶቹና የእጅ ስራ ቁሶቹ የቁሳዊ ባህል ጉዳይ አካል ሲሆኑ የወረዳውን የቀደመ አስተሳሰብና የፈጠራ ጥበብ የሚያሳውቁ ናቸው።

እነዚህ የቁሳዊ ባህል ጉዳዮች የወረዳዋን ማህበረሰብ የቀደመ ማንነት የሚያሳውቁ ቢሆኑም በአሁኑ ሰአት በመለወጥ ደረጃ ላይ ይገኛሉ። በተለይ ሀገረሰባዊ ቤቶች፣የዕጅ ስራ ቁስ የምንላቸው የቤትና ውሃ ወፍጮዎች፣ የቆዳ ውጤቶች ፣ ከሳር ዓይነት የሚሰሩ ቁሶች ናቸው።በመጥፋት ላይ ያሉትን ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች አሰራር፣እንዲሁም እንዴት እየጠፉ እንዳሉ በመግለጽ በዚህ ጥናት ማሳየት ይሞከራል።

ጥናቱ አምስት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን፣ምዕራፍ አንድ መግቢያ፣ ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን፣ ምዕራፍ ሦስት የደጋ ዳሞት ዳራዊ መግለጫ፣ ምዕራፍ አራት የመረጃ ገለፃና ትንተና እንዲሁም ምዕራፍ አምስት ማጠቃለያና ይሁንታ ናቸው። በመጀመሪያ ጥናቱ በመግቢያው ሰባት ንዑሳን አርዕስተ ጉዳዮችን ያካተተ ሲሆን በዋናነት የጥናቱን የትኩረት አቅጣጫዎችና የአጠናን ዘዴዎች ለማስተዋወቅ፤ የመስክ ተሞክሮንና ያጋጠሙ ችግሮችን እንዲሁም የተወሰዱ የመፍትሄ ሀሳቦችን ለመጠቆም የተዋቀረበትን እናስቀድም።

1.1 የጥናቱ ዳራ(Background to the study)

የቁሳዊ ባህል ጥናት ከፎክሎር የጥናት ዘርፎች ውስጥ አንዱ ሲሆን በተለያየ የሙያ መስክ የተሰማሩትን ባለሞያዎችም የሚጋብዝ እንደሆነ ይታመናል። ለዚህ ምክንያቱ ቁሳዊ ባህል የሰው ልጅ ራሱን በተለያየ አተያይ እንዲመለከት የማድረጉ ጉዳይ ድርሻው የጎላ በመሆኑ ነው። የተለያዩ የሙያ ባለቤቶች የሚሰበሰቡበት የሙያ መስክ መሆኑን ሄኒሪ, ግላሲ ማቴሪያል ካልቸር በሚለው መጽሐፋቸው የሚከተለውን ብለዋል።

> *The study of material culture gathered historians, art historians, architectural historians, geographers, folklorists, archeologists, anthropologists, sociologists,*

[1] ስለደጋ ዳሞት አጠቃላይ ስዕል በዳራዊ መግለጫው "ምእራፍ 3" ላይ መመልከት ይቻላል።

artists curators, dealers, and collectors in a common cause... the cause was understanding human beings through their culture... (ግላሲ: 1999: 71-72)

እንደ ግላሲ ከሆነ በዚህ የ"ቁሳዊ ባህል" ጥናት የታሪክ አጥኝዎች፣ የጥበብ ታሪክ ተመራማሪዎች፤ የመልክዓ ምድራዊ ጥናት ባለሞያዎች፣ የፎክሎር መስክኞች፣ የጥንታዊ ታሪክ /ቅርስ/ አጥኝዎች፣ የስነሰብዕ ተመራማሪዎች፣ የማህበራዊ ሳይንስ አጥኝዎች፣ ጥበበኞች፣ የሙዚየም ኃላፊዎች፣ ነጋዴዎች እንዲሁም የቁሳዊ ባህል ሰብሳቢዎች የጋራ ጉዳያቸው ያደርጉታል:: የጋራ ጉዳይ የመሆኑ ምክንያትም የሰው ልጅን በፈጠረው ባህል ውስጥ መረዳት ማስቻሉ ነው::

"ቁሳዊ ባህል" ከፎክሎር ዘርፎች አንዱ ሲሆን ዘመናዊ ኢንዱስትሪ ከመጀመሩ በፊትም ባሁኑ ወቅትም የሚሰሩ በዓይን የሚታዩና በእጅ የሚዳሰሱ ቁሶችን የሚያጠና ነው:: ይህን የጥናት ዘርፍ አስመልክተው ፈቃደ አዘዘ የሚከተለውን ብለዋል::

> *ቁሳዊ ባህል በዓይን የሚታየውን በእጅ የሚዳሰሰውን ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፣ እነዚህ ቁሳቁሶች የተገለገሉበት ዘዴ ወይም ቴክኒክ፣ የልዩ ልዩ ምግቦች አሰራር፣ የቅመም አቀማመም ብልሃትን፣ የልብስ የቤት፣ የአጥር ወዘተ አሰራርን ሰዎች ልዩ ልዩ ስራዎች የሚያከናውኑባቸውን መሳሪያዎችና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ያጠናል ማለት ነው::* (ፈቃደ፣ 1991፣ 15)

ከዚህ የምንረዳው ቁሶችን ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ከምን ቁሳቁስ እንደተሰሩና እንዴት እንደተሰሩ ነው:: የሰው ልጅ በወቅቱ የፈጠራቸው ቁሶች ለራሱ አካባቢያዊ ውጤቱና መገለገያዎቹ ናቸው፤ አካባቢያዊ መጠሪያም ያደርጋቸዋል:: አካባቢያዊ ቁሶቹ እንደ ግልጋሎታቸውና ስያሜያቸው ባህልን የመፍጠር ሚና ይስተዋልባቸዋል:: የቁስና የባህል ቁርኝትም የጠበቀ ነው:: ቁስንና ባህልን ነጣጥሎ ማየት ስለማይቻል ይመስላል "ቁሳዊ ባህል" የሚል መጠሪያ የተሰጠው:: በዚህ ላይ ግላሲ የሚከተለውን ብለዋል:: "Material culture is culture made material. It is the inner wit at work in the world. Beginning necessarily with things, but not ending with them. The study of material culture uses objects to approach human thought and action" (ግላሲ. 1999፣41)

የሰው ልጅ በምድር ላይ ሲኖር ለራሱ መገልገያ ይሆኑት ዘንድ ቁሶችን በራሱ ፈጠራ ይሰራል:: ቁሶችን ከተለያዩ ቁሶች ለመስራት ይጀምራል:: ሲጠናቀቁ ግን ሌላ የተለያዩ ቁሶችን ይፈጥራሉ:: በዚህ ሁኔታ የ"ቁሳዊ ባህል" ጥናት በተሰሩት ቁሶች የሰውን ልጅ የቀደመ አስተሳሰብና ድርጊት ለማወቅ ይጥራል ማለት ነው::

> Material culture is the study through artifacts of the beliefs- values, ideas, attitudes, and assumptions- of a particular community or society at a given time. The term material culture is also frequently used to refer to artifacts themselves, to the body of material available for such study (ፕሮን, 2009:1)

ከፕሮን ሀሳብ "ቁሳዊ ባህል" የአንድ የተወሰነ አካባቢ ወይም ማህበረሰብ በኖረበት ዘመን የሰራቸውን የራሱን የጥበብ ውጤቶች በማጥናት የዚያን አካባቢ /ማህበረሰብ/ በወቅቱ የነበረውን እምነት፣ ዋጋ፣ አስተሳሰብና አመለካከት የምናጠናበት ዘርፍ እንደሆነ ያስረዳል:: በተያያዘም "ቁሳዊ ባህል" የሚለው ሐረግ በተደጋጋሚ እንደሚወሳው ከሆነ ጥበባዊ ስራዎቹን ለማጥናት የተሰሩባቸውን ቁሳቁሶች አስቀድሞ መመልከትና ማጤን እንደሚገባ ይጠቁማል::

የ"ቁሳዊ ባህል" ጥናት የአንድን የተወሰነ አካባቢ ወይም ማህበረሰብ በኖረበት ዘመን የሰራቸውን የእጅ ስራ ውጤቶች የሆኑትንና ባህላዊ ጉዳዮችን[2] መሰረት አድርጎ ቁሶች ከምንና እንደምን ባለ ብልሃት ይሰራሉ ሲል የሚጠይቅና ምርምራዊ ምላሽ የሚሰጥ መስክ እንደሆነ መረዳት ይቻላል:: እነዚህን የቁሳዊ ባህል ጉዳዮች በመመርመር የሰው ልጅን አስተሳሰብ እምነትና የፈጠራ ብልሃት ከመረዳት በዘለለ ቁሳዊ ባህሎቹ በቋሚነት የመለወጥ ጉዳይ ስለሚገጥማቸው ተሸቀዳድሞ ማጥናትና ማሳወቅ ከአጥኝዎች ይጠበቃል:: ይህን ማድረግ ካልተቻለ የአንድን ማህበረሰብ /አካባቢ/ የቀደመ ማንነት መረዳት ያዳግታል::

በሌላ በኩል ሮበርት, ውስጥ ዶርሰን (1972 :431) የበርካታ ትውልዶችን የፎክሎር ባለሞያዎች ስጋት ገልፀዋል:: የስጋታቸው ምንጭ የፎክሎር አይነቶቹ ምንም አይነት አሻራ ሳይተው

---

[2] ባህላዊ ቁሳቁስ የምንለቸው ሀገረሰባዊ እጅ ስራ፣ ሀገረሰባዊ ምህንድስና፣ ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ሀገረሰባዊ ስዕልና ሀገረሰባዊ ምግብ ናቸው /ፈቃደ፣1991፣15/

እየጠፉ መሆናቸውን ነው:: በተለይ በቁሳዊ ባህሎች ላይ የጠነከረ ማስጠንቀቂያ አቅርበዋል:: በአብዛኛው የእጅ ሙያ ውጤቶችና የአሰራር ቴክኒካቸው /ዘዴዎቻቸው/ ሳይታወቁ ወይም ሳይቀረሱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመጣው በዘመናዊ የቴክኖሎጂ ውጤት እየተቀየሩ በመጥፋት ላይ ናቸው ይላሉ ሮበርት:: እየተረሱም የሄዱበት ሁኔታ ተፈጥራል የሚል ስጋታቸውን አስተጋብተዋል::

“ቁሳዊ ባህሎች” የሰው ልጅን የቀደመ አስተሳሰብና የአሰራር ጥበብ የሚያሳውቁ በመሆናቸው እየጠፉ ያሉበትን ሁኔታ ማሳየት ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ ነው::

ደጋ ዳሞት በአማራ ክልል በምዕራብ ጉጃም ዞን ውስጥ የምትገኝ ወረዳ ስትሆን፣ ከአዲስ አበባ በ401 ኪሎ ሜትር ርቃ ትገኛለች:: በወረዳዋ በርካታ ቁሳዊ ባህሎች አሉ:: ቁሳዊ ባህሎቹ በነበረ አሰራራቸውና ግልጋሎታቸው የቀጠሉ ቢሆንም የተወሰኑት በተለይ ባህላዊ ቤቶችና ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁሶች በመጥፋት ሂደት ላይ እንዳሉ ቤተሰቦቼን ለመጠየቅ ወደ ወረዳዋ በሄድኩበት ወቅት ተመልክቻለሁ::

ሀገረሰባዊ የምህንድስና ውጤት የሆኑት ባህላዊ ቤቶች /አዳራሽ፣ እልፍኝ፣ ጎጆና ደርብ/፣ የእጅ ስራ ውጤት የሆኑት ቁሳቁሶች ማለትም የቆዳ /ደበሎ፣ ለምድ፣ አቁማዳ፣ ስልቻ፣ ገርጋዲ፣ ላምነት፣ መጫኛ፣ ጠፍር፣ ማንጠቢያ፣ ምናር/፤ የሳር አይነት ውጤቶች /ገሳ፣ ዳውጋ፣ የሸቆ ጥላ/፤ የድንጋይ ውጤቶች /የቤትና የውሃ ደንጋይ ወፍጮ/፤ የስፌት ውጤቶች /ሞሰብ፣ ሞሰበወርቅ፣ ቀለምሻሽ፣ ወስከንቢያ፣ ወራንታ፣ ላዳን፣ ቁና፣ ወንፊት፣ ሰፌድ፣አገልግል/ በአሁኑ ሰዓት በሌላ እየተተኩ በመጥፋት ላይ ናቸው:: የእነዚህ ቁሶች በመጥፋ ሂደት ላይ መሆን የወረዳዋ ተወላጅ እንደመሆኔ ትኩረቴን ስቦታል::

ይህ በተፈጥሮም ይሁን በኢኮኖሚ እንዲሁም በባህል ሳቢያ የመጣው ለውጥ በወረዳዋ ያሉ ባህላዊ የቤትና የእጅ ስራ ቁሶችን ሳይጠኑ ሊያጠፋቸው ይችላል የሚል ስጋት አለኝ:: ስለሆነም በወረዳዋ በመጥፋት ላይ ያሉ ቁሶች አሰራራቸውን እንዲሁም እንዴትና በምን ተጽእኖ እየጠፉ እንዳሉ በዚህ ጥናት ለማሳየት እሞክራለሁ::

1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓላማ በደጋ ዳሞት ወረዳ በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች አሰራር፣ ብሎም በምን ተጽእኖና እንዴት እየጠፉ እንዳሉ በመግለፅ ማሳየት ነው:: ጥናቱ በውስጡ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎችም ያካትታል::

1. በወረዳዋ በመጥፋት ላይ ያሉትን ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች መለየት፣
2. ሀገረሰባዊ ቤቶቹና የእጅ ስራ ቁሶቹ በመጥፋት ላይ ለመሆናቸው ተፅዕኖ ያሳደሩ ጉዳዮችን መጠቆም፣
3. የሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶችን የመስሪያ ቁሳቁስ፣ የአሰራር ሂደታቸውን፣ አገልግሎታቸውንና ሰሪዎችን መግለፅ፣
4. ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች የወረዳዋን ማህበረሰብ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሃይማኖታዊ ገፅታ በምን ሁኔታ እንደሚገልፁ በስነቃሎች ተንትኖ ማቅረብ፣
5. ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች ደብዛቸው ከመጥፋቱ በፊት በፎቶግራፍ፣ በቪዲዮና በቴፕ መረጃቸውን ማስቀረት::

1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

"ቁሳዊ ባህል" በውስጡ በርካታ ባህላዊ ጉዳዮችን የያዘ ሲሆን፣ ያለፈውንም ሆነ ያሁኑን ትውልድ የአስተሳሰብ አድማስ፣ የፈጠራ ችሎታና የአጠቃቀም ደረጃ በማሳየት ጉልህ ድርሻ አለው:: በዚህ የጥናት መስክም የማስተማር ዘዴን በማጎልበት፣ ባህላዊ ጉዳዮችን በመቅረስ፣ ማህበራዊ ችግሮችን በመፍታት፣ የአኗኗር ሁኔታን በማሻሻል፣ እንዲሁም ባህል ፈጣሪ ማህበረሰቦችን በማነቃቃትና በማበረታታት ረገድ ሊጠቅም ይችላል:: ይህ ጥናትም የቁሳዊ ባህል ጥናት በመሆኑ፣

- ከቁሳዊ ባህሎች ውስጥ በተለይ በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች እንዴት እየጠፉ እንዳሉ፤ እንዲሁም አሰራራቸውንና አገልግሎታቸውን መረጃ ይሰጣል::
- የጥናቱ ውጤትና ትንታኔ ወደፊት በፎክሎር ገፅታዎች ላይ ጥናት ለሚያደርጉ በተለይ ይህ ጥናት አዲስ በመሆኑ በመነሻነት ይጠቅማል::

- በወረዳዋ ውስጥ ከሚገኙ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች ጋር በተያያዘ ሀገረሰባዊ እውቀቶችን ቀርሶና ሰንዶ በማቆየት ረገድ ጥናቱ የራሱ ፋይዳዎች አሉት::
- በየደረጃው ያሉ የስራ ክፍሎችና አካላት በመጥፋት ላይ ያሉትንም ሆነ በአገልግሎት ላይ ያሉትን ቁሳዊ ባህሎች በምን ሁኔታ መስራትና መታደግ እንደሚችሉ የሚያሳውቅ ስለሆነ ጠቀሜታ አለው::
- የቁሳዊ ባህል ጥናት የአካባቢውን ህብረተሰብ ባህል፣ አስተሳሰብ፣ የፈጠራ ችሎና የአኗኗር ዘይቤ፣ እንዲሁም የእርስ በርስ ግንኙነት የሚያሳይ ስለሆነ ለልማት መሰረት ሊሆን ስለሚችል ፖሊሲ ለሚያወጡ አካላት መነሻ ሀሳብ ስለሚሆን ጠቀሜታው የጎላ ነው::

1.4.የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከአራቱ የፎክሎር ዘርፎች[3] ውስጥ አንዱ ከሆነው "ቁሳዊ ባህል" ላይ የተወሰነ ነው:: ጥናቱ ከ"ቁሳዊ ባህል" ውስጥ መጠናት ካለባቸው ባህላዊ ጉዳዮች መካከል በሀገረሰባዊ ምህንድስናና የእጅ ስራ ቁሶች ላይ በማነጣጠር በተለይ በመጥፋት ላይ ያሉትንና ከሌሎች ባህላዊ ቁሶች ይልቅ የተሻለ መረጃ ይገኝባቸዋል ብሎ ባመነባቸው ላይ ተወስኗል::

የጥናቱ ተተኳሪ ቁሶች በጥናቱ ዳራ ላይ የተዘረዘሩት ናቸው:: ከሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁሶች ውስጥ ከሸክላ አፈር የሚሰሩ የቤት ቁሶች፣ ከብረታብረት የሚሰሩ ቁሶች፣ ከእንጨት የሚሰሩ የግብርና ቁሶችና ከጭቃ የሚሰሩ የቤት ቁሶች አጥኝው ለጥናት በሄደበት ወቅትም ሆነ ቤተሰብ ለመጠየቅ ጎራ ባለባቸው ጊዜያት ባደረገው ምልከታ ለጥናት ከተመረጡት ቁሶች በተሻለ ግልጋት ላይ ያሉ መሆናቸውንና በሌላ መተካታቸውንም በተጨባጭ ማረጋገጥ ስላልቻ ከጥናቱ ወሰን ውጪ ሊደረጉ ችለዋል:: እናም ጥናቱ በመጥፋትና በመኖር ህልውና ላይ ያሉትን ነጥሎ በማውጣት በማጥናት ማሳየት በሚቻልበት መልኩ ተወስኗል::

---

[3] የፎክሎር ዘርፎች፣ ስነቃል፣ ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ሀገረሰባዊ ትውንጥበባትና ቁሳዊ ባህል ናቸው:: (ዶርሰን፣ ውስጠ ፍቃደ፣ 1991፣15)

በሌላ በኩል የጥናቱ ተተኳሪ ቦታ በአማራ ክልል በምዕራብ ጎጃም ዞን ውስጥ ከሚገኙት ወረዳዎች ውስጥ አንዷ የሆነችው ደጋ ዳሞት ወረዳ ናት:: የወረዳዋን የአየር ፀባይ ተከትሎ ደጋማ፣ ወይና ደጋማና ቆላማ ከሆኑት ሰላሳ ሁለት ቀበሌያት ውስጥ አስሩ ቀበሌያት ላይ በመወሰን የጥናቱን መረጃዎች ማሰባሰብ ተችሏል:: የመወሰኑ ጉዳይም በሰላሳ ሁለቱ ቀበሌያት ያሉ ሀገረሰባዊ ምህንድስናና የእጅ ስራ ቁሶች ምንም ልዩነት ሳይታይባቸው በአስሩ ቀበሌያት ሊካተቱ የሚችሉ በመሆናቸው ነው:: ከዚህ ባሻገርም የወረዳዋ የመሬት አቀማመጥ ወጣ ገባና ሰፊ በመሆኑ ከጉልበትም ሆነ ከጊዜ አንፃር አድካሚነቱ ታሳቢ ተደርጓል:: ስለዚህ ይህ ጥናት በደጋ ዳሞት ወረዳ በመጥፋ ላይ ካሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች ይበልጥ አደጋ የገጠማቸውን በመምረጥ ሊወሰን ችሏል::

1.5. የጥናቱ ዘዴ

1.5.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ዋና ዓላማ በደጋ ዳሞት ወረዳ በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች አሰራር፣ ብሎም በምን ተጽእኖና እንዴት እየጠፉ እንዳሉ በመግለፅ ማሳየት እንደሆነ በ1.2 ተገልጿል:: ይህንንም ዓላማ ማሳካት ይቻል ዘንድ መረጃዎችን በቀዳማይና ካልኣይ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መጠቀም ተችሏል::

በመጀመሪያ ለዚህ ጥናት ቀዳማይ መረጃዎች የተሰባሰቡባቸውን ዘዴዎች በተለያዩ መንገዶች የተዛዱባቸው ቢሆኑም በመረጃ ማሰባሰቡ ወቅት ከነበራቸው አስተዋፅኦ አንፃር በሁለት ዓይነት ከፍየ ለማሳየት እፈልጋለሁ:: መረጃ ለመሰብሰቡ የተሻለ አስተዋፅኦ የነበራቸውን "ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች" ያልኳቸው ሲሆኑ፣ እነሱም የቃል መጠይቅና ምልከታ ናቸው:: ሁለተኛዎቹና በአጋዥነት ወይም መረጃ በማሟያነት የተገለገልኩባቸው ዘዴዎች ደግሞ የጽሑፍ መጠይቅ፣ የናሙና ጥናት (case study) እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት ናቸው::

የቃል መጠይቅ ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ በዋናነት ተመርጧል:: ይኸውም ቁሶቹ ከምን እንደሚሰሩ፣ እንዴት እንደሚሰሩ፣አገልግሎታቸው ምን እንደሆነ፣ ሰሪዎች እነማን እንደሆኑ፣ ተጠቃሚዎች እነማን እንደሆኑ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳቸው እንዴት እንደሚገልፅ፣ ከመቼ ጀምሮ ግልጋሎታቸው እየተቋረጠ እንደሄደ፣ በመጥፋት ላይ

ለመሆናቸው ተፅዕኖ ያሳደሩ ጉዳዮች፣ እንዲሁም በምን ቁሳቁሶች እየተተኩ እንደሆነ ለማወቅ የቃል መጠይቅ ተመራጭ ነው::

ለነዚህ ጉልህ ጉዳዮች መረጃ ማግኘት ይቻል ዘንድ የእጅ ሙያ እውቀት ያላቸውና በሙያው ለረዥም ጊዜ የቆዩ፣ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የባህልና የታሪክ እውቀታቸው የተመሰከረላቸው፣ በቁሶች ተገልጋይ የሆኑ፣ ከቁሶቹ ጋር የተለየ ቁርኝት /የሕይወት ገጠመኝ/ ያላቸው ወጣቶች፣ እናቶች፣ አባቶችና ካህናትን የቃል መጠይቅ ማድረግ ተችሏል:: መረጃ አቀባዮችን አንድም የወረዳዋን ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ባለሞያዎችንና የተለያዩ ሰዎችን በመጠየቅ በሌላ በኩልም በአጋጣሚ ማለትም ገበያ ላይ፣ መንገድ ላይ፣ እንዲሁም /እኔ የማውቃቸውን/ በማካተት ነው:: በአብዛኛው ከ30 ዓመታት በላይ ዕድሜ እና የተለያየ ዶታ ካላቸው 20 ዋናና 14 ተራ በድምሩ 34 የወረዳዋ ነዋሪዎች ጋር የቃል መጠይቁ ተከናውኗል:: መረጃ አቀባዮችን በፊደል ቅደም ተከተል ስማቸውን፣ አድራሻቸውን፣ የመረጃቸውን ዓይነት፣ መረጃ የሰጡበትን ጊዜ በአባሪ ክፍል ማያያዝ ስለተቻለ ከዚያ መመልከት ይቻላል::

መረጃውን ከመረጃ አቀባዮች ማሰባሰብ ይቻል ዘንድ በሁለት መንገድ ተከናውኗል:: አንደኛው መንገድ መስከኛውና መረጃ አቀባዮች ከመገናኘታቸው በፊት ቀደመው በተዘጋጁ ጥያቄዎች (Structured interview) የተተገበረ ሲሆን፣ የእጅ ባለሞያዎችን፣ ታሪኩንና ባህሉን የሚያቁ ታዋቂ ሰዎችን እንዲሁም ተጠቃሚዎችን ሳነጋግር ተጠቅሜበታለሁ:: ሌላውና ሁለተኛው መንገድ በንግግር ወቅት ድንገት ብልጭ የሚሉና አውዱም የሚፈጥራቸውን መረጃዎች ለማሰባሰብ ግልጋሎት ላይ የዋለው የቃል መጠይቅ (unstructured interview) ነው::

የቃል መጠይቁ የተካሄደው እንደመረጃ አቀባዮች ማንነትና ሁኔታ ሰፈር ውስጥ ባሉ የእጅ ስራ መስሪያ ቦታዎች፣ መኖሪያ ቤቶች፣ ቤተ እምነቶች፣ በግብርና ስራ ላይ፣ በገበያ ቀን መጠጥ ቤት፣ ቁሶች በሚሸጡባቸው ገበያዎች፣ እንዲሁም የሚያልፉ አጋጣሚዎች በተከሰቱበት ወቅት ለአብነትም መንገድ ላይ ሊከናወን ችሏል::ከመረጃ አቀባዮች የተሰበሰበው መረጃ የተቀረፀው በቴፕ መቅረፀ ድምፅ ነው:: ስለሆነም ወደ አስር ካሴቶች በቀረጻ ወቅት መጠቀም ተችሏል::

ምልከታ ሁለተኛው ካልኣይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዋነኛ ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን ለዚህ ጥናት በቃል መጠይቅ የተሄደባቸውን ቁሳቁሶች አካላዊ ቅርጽ በፎቶግራፍና በቪዲዮ ለመሰብሰብ ያስቻለ ዘዴ ነው:: ለጥናቱ ትኩረት ወደተደረገባቸው አስር ቀበሌያትና ገበያዎች በመዘዋወር ምልከታ ለማድረግ ተችሏል:: በምልከታው መረጃ አቀባዮች በቃል ምልልሱ ወቅት፣ በቃል የተናገሯቸውን ቁሳቁስ ዓይነትና በመጥፋት ላይ ያሉበትንም ሁኔታ ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ማከናወን የተቻለበት ሁኔታ አለ:: ዋናው የምልከታው ዓላማም በወራዳዋ ያሉት ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች እርግጥ እየጠፉ ናቸው? ግልጋሎታቸውስ ይሄ ነው? አካላዊ ቅርፃቸው ይሄ ነው ለካ? የሚሉትንና ተመሳሳይ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ተጠቅሜበታለሁ:: በተያያዘም እየጠፉ ያሉትን ቁሶች እየተኳቸው ያሉት የዘመኑ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን በምልከታው ለማረጋገጥ አጋጣሚው ተፈጥሯል:: ሌላው በወረደዋ የነበረውን የደን፣ የውሃ ተፋሰሶች፣ ለሳር ቤት ክዳን የሚሆነውን የስርስራ ሳር ሁኔታ በምልከታው ወቅት ማትኮር ተችሏል:: ምክንያቱም በአንዳንድ ቁሳቁሶች ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር የመቻላቸው ሁኔታ ያመዘነ በመሆኑ::

ምልከታው በሁለት ዙር የተከናወነ ሲሆን በመጀመሪያው ለሃያ ስድስት ቀናት በሁለተኛ ዙር ደግሞ አስራ ዘጠኝ ቀናት በድምሩ አርባ አምስት ቀናት በመቆየት ለጥናቱ መሰረት የሚሆኑ በፎቶግራፍ /58 የታተሙ ምስሎችንና 2 ሲዲ ያልታተሙ ፊልሞችን/፤ በቪዲዮ /2 ቪዲዮ ካሴቶች/ እንዲሁም በጽሑፍ /ማስታወሻ በመያዝ/ በማሰባሰብ ለመጠቀም ተችሏል::

በሌላ በኩል ለዚህ ጥናት የጽሑፍ መጠይቅ ተጠቅሜያለሁ:: የጽሑፍ መጠይቅ የተጠቀምኩበት ዋናው ዓላማ የመንግስት አካል የሆነው የወረዳዋ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ፣ ለቁሳዊ ባህሎቹስ ምን ያህል ትኩረት እንደሰጡ፣ በመጥፋት ላይ ያሉትን ለይተው ማወቃቸውን፣ ለቁሶች በመጥፋት ላይ መሆን ተፅዕኖ ያሳደሩትን ማወቃቸውን፣ ቁሶችን የሚንከባከብ ራሱን የቻለ ባለሞያ መኖሩን፣ በወረዳዋ የቁሶቹ ማከማቻ ሙዚየም መኖሩንና የመሳሰሉትን በምን ሁኔታ ላይ እየሰሩ እንደሆነ ለማወቅና ለይሁንታ ሀሳበነትም እንደመነሻ እንዲሆነኝ ከማሰብ ነው::

ይህንን ጥናታዊ ጽሑፍ በመረጃ ለማበልፀግ ሲባል ናሙና ጥናትን(case study) መጠቀም ተችሏል። በተለይ የእጅ ባሞያዎችን /ቆዳ ሰሪዎችን፣ ወፍጮ አውጪዎችን፣ የስፌት ቁስ ሰፊዎችን፣ ዳውጃ ሰሪዎችን፣ የሣር ቤት ሰሪዎችን/ ሙያውን ከማን እንደተማሩት፣ እንዴት እንደተማሩት፣ በሙያው ምን ያህል ተጠቃሚ እንደሆኑ ለምን ያህል ጊዜ በሙያው እንደቆዩ፣ በቆይታቸውም ምን ችግር እንደገጠማቸውና ምን መፍትሄ ለመውሰድ ጥረት እንዳደረጉ፣ በሌላ መልኩም እነዚህ ቁሶች እንዴትና በምን ምክንያት እየጠፉ እንዳሉ ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ የተሰጠባቸውን መረጃዎች ለማካተት ተችሏል:: ከእጅ ባለሞያዎች ባሻገር ከተጠኚ ቁሶች ጋር በተያያዘ ልዩ ግንዛቤ ያላቸውንና ግንዛቤያቸውን ለማካፈል ፈቃደኛ የሆኑትን ሌሎች ሰዎችም ለማካተት ጥረት ተደርጓል::

በቀዳማይ መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴ ውስጥ የተተኳሪ ቡድን ውይይትን ለመረጃ ማበልፀጊያነት በአጋዥነት የተጠቀምኩት በወረዳዋ በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች እንዴትና በምን ሁኔታ እየጠፉ እንደሉ ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ /በቁጥር 5/ የእድሜ ባለፀጋዎችንና ታሪኩንና ባህሉን ያውቃሉ ያልኳቸውን መረጃ አቀባዮች አንድ ላይ ተሰባስበው እንዲወያዩ በማድረግ ነው:: በጋራ ውይይታቸውም የባህላዊ ቁሶቹ እየጠፉ መሄድና የዘመኑን መለወጥ በማጤን ለወደፊቱ በጋራ ማሰብ እንደሚጠበቅባቸውና ቁሶቻቸውንም ባሉበት እንዲቀጥሉ ለማድረግም ሆነ በቅርስነት ለማቆየት ፍላጎታቸውን አሳይተዋል:: ለጥናቱም የባህላዊ ቁሶቹ እየተለወጡና እየጠፉ መሄድ ታሪካዊ ዳራን በተላበሰ መልኩ መረጃዎችን ማግኘት ተችሏል::

ከቀዳማይ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቀጥሎ ለጥናቱ ወደመስክ ከመሄዴ በፊትም ሆነ በኋላ ካልዐይ መረጃዎችን ከቤተመጻሕፍትና ከዓለም አቀፍ ድረገፆች ለማሰባሰብ በዘዴነት ለመጠቀም ችያለሁ:: ይኸውም የተለያዩ ትውሮችንና ወረዳዋን የሚመለከቱ ጥሬ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የታተሙ መጻሕፍትን፣ ያልታተሙ ጽሑፎችንና ከኢንተርኔት በማንበብ ማስታወሻ መያዝ ተሞክሯል:: በካልአይ መረጃ ዘዴ የተሰበሰቡት መረጃዎችም በቃል መጠይቅና በምልከታ የተገኙ መረጃዎችን ለመተንተን ግልጋሎት ላይ ይውላሉ::

1.5.2. የመተንተኛ ዘዴዎች

የመስኩ ምሁራንን ዋቢ በማድረግ የተሰባሰቡ መረጃዎችን በምድብ በምድብ በማስቀመጥ፤ በምራፍ ሁለት የተነሱትን ትዉሮች በመጠቀም በተለይም የስከለረት ዘጠኝ ሞዴሎችን (2.2.3) በማስተምስ በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችንና የጅስራ ቁሶችን ለመተንተን ተሞክሯል። ከዘጠኙ ሞዴሎች በተጨማሪ የፕሮን ሦስት ሂደቶችን በማዋሐድ ለመስራት ጥረት ተደርጓል።

1.6.የመስክ ተሞክሮ

የፎክሎር ምርምር ስራ በቤተመጻሕፍት ብቻ የሚወሰን አለመሆኑ ይታወቃል። እንዲያውም አብዛኛውን ወይም በዋናነት በመስክ ላይ የተመሰረተ ነው። እናም ይህን ጥናት ከመጀመርና የመስክ ጉብኝቴን እስካጠናቅቅ ድረስ የመስክ ተሞክሮ ሂደቶች ይኖሩኛል።

ወደ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የኢትዮጵያ ስነጽሑፍና ፎክሎር የድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለመማር በ2001 ዓ.ም ከጀመርኩበት ወቅት አንስቶ በአዕምሮዬ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ማጤን መጀመሬ አልቀረም። እናም በዚሁ ዓመት ቤተሰቦችን ለመጠየቅ ወደ ጥናቴ የትኩረት ወረዳ በሄድኩበት ጊዜ በልጅነቴ የነበረውንና በአሁኑ ወቅት ያለውን የአየር ሁኔታ፣ የደን ተጨፍጭፎ መጥፋት፣ የሳር ቤቶች በቆርቆሮ የመለወጥ፣ የቤት መገልገያ ቁሳቁስም የዘመኑ ቴክኖሎጂ ባፈራቸው ቁሳቁሶች እየተተኩ መሆናቸውን ለማጤን ችዬ ነበር። ይሄን ጉዳይ በአዕምሮዬ ይዤ ልስራበት ወይስ አልሰራበት ብዬ ለመወሰን በማወጣ በማወርድበት ወቅት በአጎራባች ወረዳ በማቅ አሰራር ላይ ጥናት ካደረጉት አቶ መኮንን ባይህ ጋር ተገናኘን።

ርዕስ ለመምረጥ በተዘጋጀሁበት ጊዜ ነበርና አቶ መኮንንን ያገኙኋቸው "ለምን በመጥፋት ላይ ያሉ ቁሳዊ ባህሎችን አትሰራም። እኔ ቢቡኝ ወረዳ ላይ የማቅ አሰራርን ሳጠና በርካታ ቁሶች እየጠፉ መሆናቸውን ተመልክቻለሁ። ጥናቱም አዲስ ነውና ሂድበት አሉኝ።" የእሳቸው ጥቁምታም በቀደም ያደረጉትን ምልከታዬን አጠናከረውና ወደዚህ ጥናት ልገባ ችያለሁ።

ከዚህ በኋላ ርዕሱ ፀድቆ ወደ መስክ ጉዞዬ ከመሄዴ በፊት በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተለያዩ የትውር መጻሕፍትንና ተዛማጅ ስራዎችን እንዲሁም በወረዳዋ ዙሪያ የተጠኑ ስራዎች መኖራቸውን ለማወቅ በቤተመጻሕፍት ውስጥ ማንበብና ማስታወሻ የመያዝ ሙከራ አድርጌያለሁ:: በሌላ መልኩም ከወረዳዋ ወደ አዲስ አበባ የመጡትን ተወላጆች በተለይ ከአቶ አሳምነው ደስታ ጋር በውሃ ወፍጮ ዙሪያ በመወያየት ማረጋገጫ ለማግኘት ችያለሁ:: ምክንያቱም አቶ አሳምነው የውሃ ወፍጮ ለቤተሰባቸው ነበርና::

ከዚህ በላይ የጠቋቆምኳቸው ተሞክሮዎች ወደ መስክ ከመሄዴ በፊት ነው:: በመቀጠል ከየካቲት 25 ቀን 2002- መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ በቆየሁባቸው የመጀመሪያ ዙር የመስክ ተሞክሮዬ የሚከተሉትን ለመጠቃቀስ ልሞክር:: ይኸውም ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፉ ትምህርት ክፍል ያጻፍኩትን የትብብር ደብዳቤ በመያዝ ለወረዳዋ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት አስረከብኩ:: በዚህን ወቅት በወረዳዋ ዋና ከተማ ፈርስ ቤት የሚሰራ የባለቤቴ ወንድም/አቶ አበበ ድልነሳ/ን ይገዬ ነው የተንቀሳቀስኩት:: አቶ አበበን መያዜም ቢሮክራሲያዊ ውጣውረዱን ቀንሶልኛል:: ከባለሞያዎቹ ጋርም በቀላሉ እንድግባባ አድርጎኛል:: እናም ከባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት መረጃ ለማሰባሰብ ለምንቀሳቀስባቸው ወረዳዎች የትብብር ደብዳቤ በማጻፍ ተረከብኩ:: በተያያዘም የጽ/ቤቱን ባለሞያዎች በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ እነማንን ማነጋገር እንዳለብኝም አወያየኋቸው:: እነሱም የሚፈልገውን መረጃ ሰጡኝ::

የጽ/ቤቱን የትብብር ደብዳቤ በመያዝ ቀጥታ ወደተመረጡ ቀበሌያት ተንቀሳቀስኩ:: ስንቀሳቀስ ግን በተለይ ከዘመዶቼና ከሚያውቁኝ ሰዎች ውስጥ የሚተባበሩኝን በመያዝ ነበር:: ይሄም እነማንን ማነጋገር እንዳለብኝ፣ እንዴት ማግኘት እንዳለብኝ፣ ቀጠሮ የመያዝና የማመቻቸት ተግባር በመፈፀም ጉልህ ድርሻ ተወጥተውልኛል:: በእነሱ በመታገዝም መረጃ አቀባዮችን ያለምንም ስጋት የቃል መጠይቅ ማድረግ ችያለሁ:: በተወለዱበትና በሚያውቁት ቦታ ጥናት ማጥናት ስሜታዊነት እንደሚንፀባረቅ በተለያዩ የመስኩ ባለሞያዎች ቢጠቀስም ሊጋረጡ የሚችሉ ችግሮችን ከማስወገድ በዘለለ ስራን ለማቀላጠፍና ጊዜን ለመቆጠብ የማይናቅ አስተዋፅኦ ማድረጉን ማረጋገጥ እችላለሁ:: በተቻለ መጠን ከስሜታዊነት ለመራቅ ጥረትም አድርጌያለሁ::

የመጀመሪያ ዙር የመስክ ጉዞዬን አጠናቅቄ ከመጣሁ በኋላ በቴፕ የቀረፅኳቸውን የካሴት መረጃዎች ወደ ስክርፕት የመቀየርና የተጓደሉትን የማሰብ ስራ ሰራሁ:: የመስክ ሪፖርቴንም ለአማካሪዬ በማቅረብ እንዴት እንደሄድኩበትና ወደሁለተኛው ዙር የማሚላት ስራ ለመሄድም እንዴት እየተዘጋጀሁ እንደሆነ ተወያየን:: ከአማካሪዬም ምን ማድረግ እንዳለብኝ ገንቢ ምክር ተቀበልኩ::

በመቀጠል ለሁለተኛ ዙር የመስክ ጉዞ ከሚያዚያ 16 ቀን 2002- ግንቦት 4 ቀን 2002 ዓ.ም ወደ ወረዳዋ ሄድኩ:: በእነዚህ ቀናትም በተጨማሪ መታየት ያለባቸውንና በማሚያነት የሚፈለጉትን መረጃዎች ለማሰባሰብ ቻልኩ:: በተለይ አብዛኞቹን ቁሳቁሶች ፎቶግራፍ ያነሳሁኝ በዚህ ዙር ነበር:: በመስክ ስራዬም የፎቶግራፍና የቪዲዮ ካሜራ፤ የቴፕ መቅረፀ ድምፅ፤ አንዳንድ ቁሶችን ለመለካት የሜትር እና አንዳንድ መረጃዎችን በጽሑፍ ለመያዝ እንዲያመቸኝ የማስታወሻ ደብተር ተጠቅሜያሁ::

የመስክ ስራ እጅግ አድካሚ እንደሆነ ተረድቻለሁ:: በተለይ ወቅቱ በጋ ስለነበር የወረዳዋ መሬት በአራሾቹ ቡንግልግል ብሎ የታረሰ ስለነበር ካንዱ መንደር ወደአንዱ መንደር:: ከአንዱ ቀበሌም ወደ ሌላው ቀበሌ ለመዘዋወር በዚያ ላይ መጓዝ መቻል እጅግ አስቸጋሪ ነበር:: በዚያ ላይም የበርሃማነት መስፋፋቱ የመጠለያ ዛፍ ማጣት አንዱ ፈታኝ ሁኔታ ነበር:: ሆኖም በታላቅ ትዕግስትና ፅናት የመስክ ተግበሬን ልፈፅም ችያለሁ:: አጥኝ ትዕግስተኛና ሆደ ሰፊ መሆን እንዳለበትም የክፍል መምህሬ ፍቃደ አዘዘ /ዶ/ር/ የሁል ጊዜ ምክራቸው እንደነበር እያስታወስኩኝ:: ሌላው የፎቶግራፊና የቪዲዮ ግራፊ ሙያ ስለነበረኝ የመስክ ስራዬን ለመተግበር አግዞኛል::

1.7. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

ችግሮች አይደለም ለጥናትና ምርምር ቀርቶ በህይወት ውጣ ውረድ ሂደትም መከሰታቸው የተፈጥሮ ባህሪያቸው መሆኑ ግልፅ ነው:: እናም ጥናቴን ይገፉ ወደ መስክ በሄድኩበት ወቅትም ሆነ ወደ አዲስ አበባ ስመለስ ችግሮች ገጥመውኛል:: ሆኖም ችግሮች እንደሚከሰቱ ታሳቢ አድርጌ ስለነበር መፍትሄዎቹንም አያይገፎ መጠቀሜ አልቀረም:: ለችግሮች መፍትሄ ካልሰጠሁማ ምኑን አጠናሁት::

ወደ ወረዳዋ ለምን እንደሄድኩ ከአንድ ስማቸውን ከማልጠቀሳቸው ግለሰብ (ስማቸውን □ንዳልጠቅስ ስለጠየቁኝ) ጋር ስንወያይ /የካቲት 27 ቀን 2002 ዓ.ም/ "ይሄ ተጠና አልተጠና ምን ያደርጋል? ተመልሰን አንጠቀምበት ከንቱ ልፋት ነው::" በማለት ተስፋ አስቆራጭ ሀሳባቸውን አጋፈጡኝ:: ሆኖም በሌላ ጎኑ መምህር እንዳሻው የተባሉ ለአጎታቸው የውሃ ወፍጮ የነበራቸው /መጋቢት 2 ቀን 2002 ዓ.ም/ "እኛ እዚህ ተቀምጠን ምንም ሳናደርግ ከአዲስ አበባ መጥተህ ይሄን ለማጥናት ማሰብህ ልትመሰገን ይገባል" ማለታቸው ተስፋ አስቆራጩን ንግግር ከውስጤ አስወግደውልኛል::

ሌላው በተለይ የመረጃ ሰጪዎቼ ሀሳባቸውን አብራርተው መግለፅ አለመቻላቸው ነው:: እንዲያውም የወረዳዋ ህዝብ ተግባር እንጅ ንግግር አይችልም እንዴ? እስከማለት ድርሼ ነበር:: የቁሶችን ታሪካዊ አመጣጥም ሆነ አገልግሎት ስጠይቃቸው አጭር ምላሽ ነው የሚሰጡት፣ ታሪኩን ያውቃሉ የተባሉትም ሆኑ ቀሳውስቱ:: ይህን ችግር ለመፍታትም የተለያዩ ስልቶችን ለመፍጠር አስጨንቆኛል:: ሆኖም የተለያዩ ትውስታዎችን በመቀስቀስና በመጎትጎት መረጃዎችን ማግኘት ችያለሁ::

በሶስተኛ ደረጃ የገጠመኝ ችግር የዳውጀንና የደበሎን ቁሶች ሁኔታ መረጃ ለማግኘት ወደ ቤተክርስቲያን ሲሄድ በቀሳውስቱና በእቃ ጠባቂዎች መጠርጠር መቻሌ ነበር:: ንዋየ ቅዱሳትን ለመዝረፍ የምሰልላቸው ነበር የመሰልኳቸው:: እናም በጥርጣሬ አይን ተመልክተውኛል:: ቁሶችን ለማሳየትም ሆነ መረጃ ለመስጠት አንገራግረውኝ ነበር:: የስጋታቸው ምንጭ ግን ቤተክርስቲያናቱን ዘራፊዎች እየተበራከቱባቸው የመሄዱ ጉዳይ ነው:: ነገር ግን እኔ የመጣሁት ለዚህ ጥናት መረጃዎችን ለማሰባሰብ ነው:: እኔም የእነ እከሌ ዘመድ ነኝ:: እነሱን አውቃለሁ እያልኩ በአካባቢው የሚታወቁትን ሰዎች በመናገር እንዲያውም አንዳንዶች "አንተማ የእኔ ዘር አይደለህ" እያሉ ጥርጣሬያቸውን አስወግደው የምፈልገውን መረጃ እንዲሰጡኝ አድርጌያለሁ::

በመቀጠል የፎቶግራፍና የቪዲዮ ካሜራዬ ዲጅታል በመሆኑ የሁለቱን ሙያ ይሰራል:: ሆኖም አረፋ መድሃኒያለም ከሚባለው ራቅ ያለ ቀበሌ መረጃ በማሰባሰብበት ወቅት የካሜራው ሚሞሪ በመሙላቱ ፎቶ የማንሳትና ቪዲዮ የመቅረፅ ስራዬ ተቋረጠ:: ወደ ወረዳዋ ዋና ከተማ ፈረስቤት ብመለስም ከሚሞሪው ወደ ሲዲ የሚቀይር ቴክኖሎጂ

ባለመኖሩ በመፍትሄነት ደብረማርቆስ ከተማ የ100 ኪሎ ሜትር የመኪና ጉዞ በማድረግ ችግሬን ልፈታ ችያለሁ:: ሆኖም የሁለት ቀናት የስራ ጊዜያት ተሻምቶብኛል::

በዚህ ጥናት የመስክ ቆይታ በዋና ችግር የምፈርጀው ወቅቱ የምርጫ ጊዜ መሆኑ ነው:: ይኸውም የ2002 ዓ.ም 4ኛው አገር አቀፍ የክልልና የፌደራል ተወካዮች ምርጫ የምረጡኝ ዘመቻ የሚጧጧፍበት ነበረ:: በእርግጥ የምርጫ ዘመቻው በወረዳው የገጠር ቀበሌያት ያን ያክል የጎላ ቅስቀሳ አላስተዋልኩም:: ዝም ዝም ነበረ:: ሆኖም (ሚያዚያ 18 ቀን 2002 ዓ.ም) በዕለተ ሰኞ የገጠር ትልቅ የገበያ ቀን ነው፤ ከጠዋቱ አራት ሰዓት ጀምሮ እስከ ቀኑ ስድስት ሰዓት ድረስ በገበያው እየተዟዟርኩ የስፌትና የቆዳ ውጤት ቁሶችን ፎቶግራፍ ሳነሳ ቆየሁ:: ከስድስት ሰዓት በኋላ ግን የቀበሌው ምክትል ሊቀመንበር አቶ ስለሺ የሚባሉ በመጀመሪያው ዙር መስራቴን እያወቁ የመስሪያ ፍቃድ አምጣ አሉኝ:: እኔም ተወልጄ ያደኩበትና በህፃንነቴ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስማር የቆርቆርኩት ገበያ ስለነበር የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የሰጠኝን የትብብር ደብዳቤ ይገፍ አልሄድኩም ነበርና የምሰጠው አጣሁ:: በዚህን ጊዜ አቶ ስለሺ "እንዲያውም የቅንጅት ተወካይ ነህ:: ፍቃድ ሳታመጣ እንዳትሰራ" በማለት ለቁም እስር ዳረጉኝ:: ዘመዶቼና የማውቃቸው ሰዎች ቢለምኗቸውም አሻፈረኝ አሉ:: በተለይ ማግኘት የማልችላቸው የእጅ ባለሞያዎችን የቃል መጠይቅ የከሰዓተ ቀጠሮ እንዳልፈጽም አድርገውኛል:: ይህን ችግር መፍታት እችል ዘንድ ስልክ ደውዬ ከወረዳዋ ዋና ከተማ የትብብር ደብዳቤውን አስመጥቼ በማሳየት ነፃ ወጥቼ ማግኘት የቻልኳቸውን ለመስራት ችያለሁ:: በዚህ አጋጣሚ ምንም እንኳን ተወልዳችሁ ያደጋችሁበት ቦታ ቢሆንም ለጥናትና ምርምር ስትንቀሳቀሱ የትብብር ደብዳቤና ማስታወቂያ እንዳይለያችሁ ለመጠቀም እወዳለሁ::

በችግርነት የምጠቅሰው ሌላው ጉዳይ በቁሶቹ ዙሪያ የሚነገሩ ስነቃሎችን /ቃል ግጥም፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ወጎች፣ ተረቶች፣ ወዘተ/ እንዲነግሩኝ የምጠይቃቸው መረጃ አቀባዮቼ "አይ ይሄማ ጠፋቶኛል፣ ረስቸዋለሁ::" በማለት ምላሽ መስጠታቸው ነው:: ለዚህ ችግር በመፍትሄነት የወሰድኩት የአረፋ ደብተራ እና የፊደስ ቤት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን (መ/ር ሽጋው ገበየሁንና መ/ር ሀይማኖት አያሌው)ን ለተማሪዎቻቸው በቤት ስራነት ሰጥተው እንዲያሰባስቡልኝ ማድረግ ችያለሁ:: ይህም አንድን መረጃ አቀባይ ከመጠየቅ ተማሪዎች ቤተሰቦቻቸውን በማወያየት ሙሉም ባይሆን የተወሰኑትን ለማግኘት ጥረት ተደርጓል::

ስነ ቃሎችን እንደልብ ካልማግኘት ችግር በተጨማሪ አንዳንድ ቁሳቁሶች አገልግሎታቸው የተቋረጠ በመሆኑ የአሰራር ሂደታቸውን በፎቶግራፍና በቪዲዮ ማስደገፍ አለመቻሌ ነው:: ለአብነትም የወፍጮ ቁሶች፣ የቤት አሰራር፣ የገሳ አሰራር፣ የስፌት ዕቃዎች አሰፋፍና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል:: በመፍትሄነትም ቁሳዊ አካል የተገኘላቸውን ፎቶግራፍ በማንሳት መሰነድ ችያለሁ

በመጨረሻም እንደችግር የምጠቅሰው በአካሌ ላይ የገጠመኝን ህመም ነው:: ይህም በመስክ ጉዞዬ የተከሰተ ስለመሰለኝ:: ሰኞ ግንቦት 9 ቀን 2002 ዓ.ም ጠዋት ከምኝታዬ ስነሳ አይኔ፣ ፊቴና አፌ ከግራ ወደ ቀኝ ተጣሞ አገኘሁት:: ይሄ አስደንጋጭ ነበር ለኔ:: "በአካል አያመሽ" አይነት ስለሆነብኝ:: ወዲያው ወደህክምና ሂጄ ስመረመር መንስኤው እንደማይታወቅ፣ ሆኖም በርካታ ግምቶችን ዶክተሩ ነገሩኝ:: ከግምቶችም የአየር ድራት መሆኑ ሚዛን ደፋልኝ:: ምክንያቱም ከመስክ ስመለስ አባይ ላይ "አዲሱን የህዳሴ ድልድይ" ፎቶግራፍ ላነሳ መስኮት ከፍቼ አንገቴን ሳስወጣ እንደ እሳት የሚጋረፍ የሙቀት ሞገድ እንደገረፈኝ አስታወስኩ:: እኔም መዳኔን እንጅ የጥናቴ ጉዳይ ለአንድ ወርና ከዚያ በላይ የተዘጋ ፋይል ሆነ:: ሆኖም የህክምና መድሃኒቱ ወይም የማሳጅ መታሸቱ አልያም ፀበሉ ይሁን በውል ባላውቀውም በአንድ ወር ውስጥ ሁሉም ነገር ወደ ነበረበት ተመለሰልኝ:: መዳኔ ቢያስደስተኝም ሁኔታው የፈጠረብኝ ስሜት ግን በጥናቴ ላይ መዘናጋትን ፈጥሮብኝ እንደነበር አልዘነጋውም::

ምእራፍ ሁለት

2. ክለሳ ድርሳን

2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ለዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ በተመረጠው ተተኳሪ ወረዳ ላይ በቀጥታ ቁሳዊ ባህልን መሰረት ተደርገው የተሰሩ ጥናታዊ ጽሁፎች አላጋጠሙኝም:: ሆኖም በትምህርት ክፍሉ የተሰሩ ጥናቶች ቀርበዋል:: ለዚህ ጥናት በተመረጠው የቁሳዊ ባህል ዘርፍ ላይ የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪ ጥናቶች ናቸው:: ከቀረቡት ጥናቶች ውስጥ በብዛት በሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁሶች ላይ ያተኩራሉ:: በእኔ ቅኝት በትምህርት ክፍሉ በሀገረሰባዊ ምህንድስና ላይ ተሰርቶ ያገኘሁት አንድ ጥናት ነው:: በሌላ በኩል ግን ከተለያዩ የጥናት መጽሄቶች ባህላዊ የቤት አሰራርን መሰረት ያደረጉትን መቃኘት ችያለሁ::ቅኝት የተደረገባቸው ጥናቶች በጠቅላላው ሰባት ናቸው::

ቅኝቱን በቅደም ተከተል ማስኬድ ችያለሁ:: በመጀመሪያ በባህላዊ ቤቶች ላይ የተሰሩትን ማስቀደም ሲሆን፣ በሁለተኛነት ደግሞ በሀገረሰባዊ እጅ ስራ ቁሶች ላይ የተሰሩትን:: በተያያዘም የዓመተ ምህረት ቅደም ተከተላቸውን የጠበቀ ነው:: በባህላዊ ቤቶች ከተሰሩት ውስጥ ሁለቱ በዓለም አቀፍ ኮንፈረንስ ላይ የቀረቡ ጥናቶች ሲሆኑ፣ አንዱ በክፍሉ የተሰራ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ነው::

የመጀመሪያው ግርማ ኪዳኔ፣ "The Traditional Ways of Building Houses within Wolayta Society" 1994 ነው:: አጥኝው ይህን ጥናት በ12ኛው ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ጥናት ኮንፈረንስ ላይ ያቀረቡት ሲሆን ለጥናታቸው በመነሻ ምክንያትነት የጠቀሱት ወደ አርባ ምንጭ ጉዞ ሲያደርጉ የወላይታ ቤቶችና የቤት ውስጥ ቁሶች ውበት ስለሳባቸው ነው:: ጥናታቸውን ለማስኬድም የእጅ ባለሞያዎችንና እውቀቱ ያላቸውን ሰዎች በማወያየት እንደሆነ ጠቅሰዋል:: በተያያዘም በ317,800 ሄክታር የመሬት ስፋት ላይ 1.5 ሚሊዮን ህዝብ እንደሚኖር ጠቁመዋል::

አጥኝው የወላይታ ህዝብ የቤት አሰራር ከክልሉ ህዝብ የተለየ ደንብ እንዳለው አሳይተዋል:: ደንቡም አንድ ወንድ ለአቅመ አዳም ሲደርስ ገንዘብ ካለው ትዳር ቢይዝም ባይዝም ቤት

የመስራት መብት እንዳለው፣ ሴቶች ግን ባል ስታገባ ወደ ባሏ መሄዷ ስለማይቀር በግሏ ቤት መስራት እንደማትችል ነው:: አጥኝው አያይዘውም ቤትን ለመስራት በጋን እንደሚመርጡ ጠቅሰዋል:: በጋን የመረጡበት ምክንያትም አዝመራን ሰብስበው ነፃ የሚሆኑበት ወቅት በመሆኑ፣ የቤት መስሪያ ቁሳቁስ እንደልብ ለመቁረጥና ለማሰባሰብ የሚያመች በመሆኑ፣ ለቤት ማሰሪያ ድግስ ለመደገስ እህል የሚገኝበት በመሆኑና ሳሩን ለማጨድም ይህ ወቅት ተመራጭ ስለሆነ ነው:

በወላይታ ማህበረሰብ "ሜሽታ" የሀብታም፣ "ጉላንታ"፣ የመካከለኛና "ቡራሪያ" ዝቅተኛ ደረጃ ያላቸው ሰዎች የሚሰሯቸው ቤቶች በሶስት እንደሚከፈሉ አጥኝው በጥናታቸው አሳይተዋል:: የቤቶችን መጠንም እንዲሁ በሶስት የከፈሏቸው ሲሆን፣ "ጋሾ"፣ "ጊጋ" እና "ካሪ" የሚባሉ ናቸው:: በመጨረሻም በጥናታቸው የወላይታ ማህበረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራር ሂደት ቤት ለመስራት ከማቀድና ከመዘጋጀት ጀምሮ እስከ የቤቱን በር አቁሞ የመቆለፊያ ስልትን እስከ ማከናወን ድረስ አስራ ሁለት ሂደቶችን ማለፍ እንደሚጠበቅ ተንትነው አቅርበዋል::

ከዚሁ ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ በባህላዊ ቤቶች ላይ ጥናት ተደርጎ ያገኘሁት ጽሁፍ ደግሞ ፈቃዱ ገዳሙ፣ "'The Gurage House' Its Construction and Socio- Economic Significance" 2003 የሚለው ነው:: የጥናቱ ትኩረት በጉራጌ ማህበረሰብ ባህላዊ ቤቶች ላይ ሲሆን የቤት መስሪያ ጥሬ ቁሶች ዕድ፣ ወይራ፣ ዘንባባ፣ ሳርና የመሳሰሉት እንደሆኑ ተመልክቷል::

አጥኝው ጉራጌዎች ለባህላዊ ቤቶች የተለየ የአሰራር ብቃት እንዳላቸው፣ ትዳር የመሰረቱ ወንዶች ቤትን በመስራት ሲታወቁ ያገቡ ሴቶችም የተሰራውን ቤት በማስዋብ ማህበራዊ የስራ ድርሻቸውን እንደሚወጡ እንዲሁም ባህላዊ ቤቶቹ ማህበራዊ ትስስርን በመፍጠር አቻ የማይገኝላቸው መሆናቸውን አሳይተዋል::

ሌላው በዚህ ጥናት የተጠቆመው የቤት አሰራር ቅደም ተከተላዊ ሂደት እንዳለውና የቤት ጣሪያን ለመስራት በትልቅና በትንሽ ቤቶች መጠን በሁለት መክፈል ነው:: ቤቱን ለመስራትም የወንዶችና የሴቶች ስራ የጋራ እንደሆነ ጠቁሟል:: ቤቱ ተሰርቶ እንዳለቀም

የቡና ማፍላት ስነስርዓት ይደረግና ይጠጣበታል:: በመጨረሻም አጥኝው በዚህ ጥናት የጉራጌ ባህላዊ የቤት ጣሪያዎች በቆርቆሮ ክዳን እየተቀየሩ መሆናቸውን ጠቁመዋል::

ከላይ ከተቃኙት ጥናታዊ ጽሁፎች ጋር በተመሳሳይ ባህላዊ ቤቶችን በጥናታቸው አካተው፣ ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶችን አብረው በማስኬድ ያቀረቡት አስቴር ሙሉ፣ "ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዘጌ ባህረ ሰላጤ" በሚል ርዕስ በ2000 ዓ.ም ያቀረቡት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ነው:: በዘጌ ባህረ ሰላጤ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶችንና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶችን በሳይንሳዊ የአጠናን መንገድ ከመግለፅ፣ ከመቅረስና ከመሰነድ በተጨማሪ ለማህበረሰቡ ጠቀሜታ የሚያበረክቱበትን መንገድ መጠቆም ነው የሚል ዋና ዓላማ ይዘው በመነሳት በተለይ በባህላዊ ቤቶችና በባህላዊ የቤት ውስጥ ቁሶች (ከሸክላ የተሰሩ) ላይ ትኩረት በማድረግ ጥናታቸውን አቅርበዋል:: አስቴር ባህላዊ የቤት ዓይነቶችን (እሳተ ከላ፣ ፎቅና ምድር፣ ጎጆ ቤት) በማለት በሶስት ከፍለው የተመለከቱ ሲሆን ባህላዊ የቤት ውስጥ ቁሶችንም በተለይ የሸክላ ቁሶችን አሰራርና ሰሪዎችን በጥናታቸው አሳይተዋል::

አጥኝዋ በባህላዊ ቤቶችና በቤት ውስጥ ቁሶች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችን በዝርዝር ከማቅረብ በተጨማሪ እንዴት ለበለጠ ጥቅም የሚውሉበትን መንገድም ጠቁመዋል:: ሌላው የዘጌ ባህረ ሰላጤንና የማህበረሰቡን አጠቃላይ ገፅታ አቅርበዋል:: ጥናታቸውን በዋናነት በቃለመጠይቅና በምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተጠቅመው የተሟላ ለማድረግ ጥረት አድርገዋል::

ከዚህ በላይ የቀረቡት ጥናቶች በዚህ ጥናት የተቃኙት ባህላዊ የቤት ሁኔታን የተመለከቱ በመሆናቸው ነው:: የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ጥናቶች በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ካለመሰራታቸውም በላይ ሁለቱም በደቡብ ክልል ከሚገኙ ብሄረሰቦች የጉራጌንና የወላይታን የቤት አሰራር ትኩረት ያደረጉ ሲሆን፣ በቦታም ሆነ በጥናት ትኩረት ከእኔው የጥናት ርዕሰ ጉዳይ ይለያሉ:: መለየታቸው አንድም ባህላዊ የእጅ ስራ ቁሶችን አብረው አለማየት፣ አንድም ሀገረሰባዊ ቤቶች በመጥፋት ላይ መሆን የጥናታቸው ትኩረት አለማድረግ ነው:: ሆኖም ባህላዊ ቤቶችን ትኩረት በማድረጋቸው የእኔውን ጥናት ግማሽ አካል የሚነኩ ስለሆነ በተዛማጅነት ልቃኛቸው ችያለሁ::

ከነዚህ ጥናቶች ጋር አብሮ የተቃኘው የአስቴር ሙሉ ጥናት በክፍሉ በሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ደረጃ ሀገረሰባዊ ምህንድስናንና ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁሶችን አካቶ የተሰራ በመሆኑ የተሻለ ቀረቤታ አለው። በቦታ ደረጃም ቢሆን የሁለታችንም በአማራ ክልል በምዕራብ ጉጃም ዞን ውስጥ የተወሰነ በመሆኑ ያመሳስለናል። በሌላ በኩልም የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ አድርገው ባይሄዱበትም በቁሳዊ ባህሎች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችን በመጠቆማቸው በተወሰነ ደረጃ ቀረቤታ ይታይበታል።

ይሁን እንጂ በእኔ ጥናትና በአስቴር ሙሉ ጥናት መካከል ልዩነት አለ። ምንም እንኳን በባህላዊ ቤቶችና በሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁሶች ላይ ብናነጣጥርም በጥናታችን የተመለከትናቸው ቁሶች ይለያያሉ። ይኸውም ባህላዊ ቤቶችን ብንወስድ በዓይነትና በአገልግሎት ደረጃ ይለያያሉ። የእሳቸው ቤቶች እሳተ ከላ፣ ደርብና ምድር፣ ጎጆ ቤት ሲሆኑ የእኔዎቹ አዳራሽ፣ ደርብ፣ እልፍኝና ጎጆ ቤት ናቸው። እነዚህም የመስሪያ ቁሳቁስ ተቀራራቢነት ቢታይባቸውም በአገልግሎትና በአሰራር የሚለያዩበት ሁኔታ አለ።

በሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁስም ቢሆን እሳቸው የተመለከቱት በተለይ የሸክላ የቤት ውስጥ ቁሶችን ሲሆን፣ የእኔው ደግሞ ከእሳቸው ትኩረት ውጪ ያሉትን፣ ሆኖም በጉልህ በመጥፋት ላይ ያሉትን መርጨ ትኩረት በማድረጌ ነው። ዋናው ጉዳይም እኔ በመጥፋት ላይ ያሉትን መርጬ ማጥናት መቻሌ ነው።

ከዚህ ቀጥያ የምቃኛቸው ሶስት ጥናታዊ ጽሁፎች ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረቡ የሁለተኛ ዲግሪ ሚሚያ ናቸው። ትኩረታቸው በሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁሶች ላይ በመሆኑ ከእኔው ጥናት ጋር በከፊል ይገናኛሉ። ከዚህ አኳያ "ባህላዊ ሽመናና ቆዳ ስራ በደንበጫና አካባቢዋ" በሚል ርዕስ ሔለን አላምራው በ1999 ዓ.ም ያቀረቡት የሁለተኛ ማሟያ ጽሑፍ አንዱ ነው።

አጥኝዋ በደንበጫና አካባቢዋ የሚገኙ የሽመናና የቆዳ ስራ ባለሞያዎች ለስራቸው የሚጠቀሙባቸውን መሳሪያዎችና የአሰራር ሂደታቸውን ማሳየት በሚል ዓላማ ተመስርተው ጥናታቸውን አቅርበዋል። የባለሞያዎቹን ማህበራዊ ህይወትና ስለነሱ የሚነገሩ ስነቃሎችን ይዘትም በመተንተን አሳይተዋል። የጥናት ትኩረታቸውም በሽመናና

በቆዳ ስራ ባለሞያዎችና የስራ ውጤቶቻቸው እንዲሁም በአሰራር ሂደታቸው ላይ እንደሆነ በዳሰሳው ለመመልከት ተችሏል::

ቀጥሎ ደግሞ ዐቢዩ አስማማው "የአርጎባ ብሔረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች በአማራ ክልል፣ ደቡብ ወሎ ዞን፣ አርጎባ ልዩ ወረዳ" በሚል ርዕስ በ2000 ዓ.ም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረቡት ጥናት ነው:: አጥኝው የአርጎባን ብሄረሰብ ማንነት ከቁሳዊ ባህሎቻቸው አንፃር ለማጥናት ወዲያውም መረጃዎችን በፅሑፍ ከትቦ ለማስቀመጥ የሚል ዋና ዓላማ በመያዝ ከብሄረሰቡ ቁሳዊ ባህሎች ናሙና የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶችን የጥናታቸው ዋነኛ ተተኳሪ አድርገው አጥንተዋል::

አጥኝው ከእንጨት የተሰራ ቁስ (ብርኩማ)፣ ከድጋይ የተሰራ ቁስ (የመብራት ማስቀመጫ) ከአፈር የተሰራ ቁስ የጭስ መሞቂያ (ቦለቅያ)፣ ከቅል የተሰራ ቁስ (መጠጫና ፈሳሽ መያዣ)፤ በሌላ ጎኑም ናሙና የአንገት፣ የእጅ፣ የወገብና የእግር ጌጥ ቁሶችን መርጠው አሰራራቸውንና አገልግሎታቸውን አሳይተዋል::

የጥናት መረጃዎችን ለማሰባሰብ በዋናነት የቃል መጠይቅንና ምልከታን፤ በአጋዥነትም የጽሑፍ መጠይቅ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይትና ናሙና ጥናትን ተጠቅመዋል:: የቴፕ፣ የፎቶግራፍና የቪዲዮ መሳሪያዎችንም ለመረጃ ማጠናከሪያነትና ቁሶችን በቅርስነት ለመያዝ ግልጋሎት ላይ አውለዋል::

የዐቢዮ ጥናት ከእኔ ጋር የሚመሳሰለው የሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁስን ትኩረት ማድረጉ ነው እንጅ ልዩነቱ የጎላ ነው:: አንደኛ ምንም እንኳን የእጅ ስራ ቁሶችን ቢመለከቱም እሳቸው ያተኮሩባቸውን ቁሶች እኔ አልመለከታቸውም:: ሁለተኛው ሀገረሰባዊ የምህንድስና ቁስን አላካተቱም:: ሌላውና ዋነኛው ልዩነታችን የቁሶችን በመጥፋት ላይ መሆን ያልተመለከቱ መሆናቸው ነው::

"በጎባ ወረዳ የኦሮሞ ብሄረሰብ የመመገቢያ ቁሳቁስ አሰራር፣ አገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ ትንተና" በሚል ርዕስ አበበ መርዕድ በ2000 ዓ.ም ያቀረቡት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ በማስከተል ለመዳሰስ ይሞክራል:: አጥኝው በጎባ ወረዳ የኦሮሞ ብሄረሰብ መመገቢያ ዕቃዎች አሰራር፣ አገልግሎትና ፋይዳ፣ የአንዳንዶችንም ታሪካዊና ማህበራዊ ጉዳይ

ተንትነው ማሳየት ዋና ዓላማቸው አድርገዋል:: አጥኝው ከዕንጨት የተሰሩ ቁሶች፣ ከሸክላ የሚሰሩ መመገቢያ ቁሶች፣ የቡና ስርዓት ማከናወኛ ቁሶች፣ ከቅል የተሰሩ ቁሳቁስ፣ የስፌት ዕቃዎች (ትኩረቱ ወተት ማለቢያ፣ ማስቀመጫ፣ መጠጫ፣ መናጫ፣ ማርጊያ፣ ዘመድ ዘንድ መውሰጃ)፣ ከቆዳ የተሰሩ ቁሶች (የወተት ማለቢያ፣ ውሃ መቅጃ ፣ ማር መሰብሰቢያ፣ አገልግል መለኳሚያ) እና ከቀንድ የሚሰሩ እቃዎችን አሰራር ማህበራዊ ፋይዳና ጠቀሜታ ተንትነው አሳይተዋል::

አበበ መርዕድ የጥናት መረጃቸውን በቃል መጠይቅ፣ በምልከታ፣ በፎቶግራፍ፣ በቪዲዮ ግራፍና በቴፕ መቅረፀ ድምፅ መሳሪያዎች ለመሰብሰብ በዘዴነት ተጠቅመዋል:: ይህን ጥናት ከእኔው ጋር የሚያመሳስለው በሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁሶች ላይ መሰረት በማድረጉ ነው:: ከዚህ ውጪ በመሰረታዊ የጥናት ትኩረታችን እንለያያለን:: ዋናው ጉዳይ የቁሶቹ በመጥፋት ላይ መሆን የእሳቸውን ጥናት አይመለከትም:: ዋና ዓላማውም ይሄ አይደለም:: ባህላዊ ቤቶችንም አልተመለከተም:: ከዚህ አኳያ ልዩነታችን በቦታም ሆነ በተተኳሪ የጥናት ቁሳችን እንለያያለን::

በመጨረሻም ዋልተንጉስ መኮንን "የሽመናና የጥልፍ ትውፊት በአክሱም" በሚል ርዕስ በ2000 ዓ.ም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ በዚህ ጥናት ተቃኝቷል:: ዋልተንጉስ ለጥናታቸው በዋና ዓላማነት ይዘውት የተነሱት ነጥብ የሽመናና የጥልፍ ትውፊቶች በአክሱም እንዲከሰቱ ያደረጉና እነርሱንም ከሌሎች ያኗኗር ዘይቤዎች ጋር ያስተሳሰራቸውን የእምነት፣ የአምልኮና የእሴት ገፅታዎች ማሳየት የሚል ነው:: አያይዘውም ትውፊቶቹ ተለይተው የዚያ ማህበረሰብ መታወቂያ እንዲሆኑ ያስቻሏቸውን ማስዋቢያ ስልቶችና የአሰራር ቴክኒኮች መግለፅ፣ የሽመናና የጥልፍ ስራን በተመለከተም የአሰራር ሂደታቸውን ቀርሶ ማስቀመጥና በቅርስነት ማቆየት በሚልም ተመልክተዋል:: አጥኝው ሀገረሰባዊ ዕደጥበብ በማለት የሽመና ሙያንና የሽመና ውጤቶችን ተንትነዋል:: በተጨማሪም የማህበረሰቡን የአስተሳሰብ ለውጥና ትውፊት ለማሳየት ለውጥ ከሳች ምክንያቶችን አቅርበዋል::

የዚህ ጥናት ትኩረት በሀገረሰባዊ ዕደጥበብ ውጤቶች ላይ በመሆኑ ከእኔው ጋር የሚጋራቸው ጉዳዮችን ተመልክቷል:: ነገር ግን እንደተቀሩት ሁሉ ይህ ጥናት ባህላዊ

ቤቶችን ያላካተተ በመሆኑና የቁሶች በመጥፋት ላይ መሆን የትኩረት አቅጣጫው ባለመሆናቸው ከእኔው ጥናት ጋር ይለየዋል:: በዋናነትም በሽመና ቁሱና በማስዋቢያ ስልቱ ትውፊታዊነት ላይ ያነጣጠረ ጥናት ነው::

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በተዛማጅ ፅሁፍነት የተዳሳሱት አምስት የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጽሑፎችና ሁለት ዓለም አቀፍ ኮንፈረንስ ላይ የቀረቡ ጥናቶች ምን ዓላማ ይዘው እንደተነሱና በምን ላይ ትኩረት አድርገው እንደተጠኑ የተጠቆመ ይመስለኛል:: በተያያዘም ከእኔው የጥናት ርዕሰ ጉዳይ ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ለማሳየት ተሞክሯል:: ይኸውም ከተወሰኑት ጋር ከባህላዊ ቤቶች፣ ከሌሎቹ ጋር ደግሞ ከሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁሶች ባለን ይዘት እንመሳሰላለን:: ሆኖም ከሁሉም ጥናታዊ ፅሁፎች ጋር የቁሳዊ ባህሎች በተለይ ባህላዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች በመጥፋት ላይ መሆንን የእኔው ጥናት በብቸኝነት ትኩረት ያደረገበት በመሆኑ በዋናነት ይለየዋል:: ከጥናታዊ ፅሁፎች ዳሰሳ በመቀጠልም ጥናቱን ለመግለፅም ሆነ ለመተንተን እንደማንፀሪያ ወይም እንደመነሻ የሚሆኑትን የትወራ ስራዎች አቀርባለሁ::

2.2. ትውራዊ ዳራ

2.2.1. የቁሳዊ ባህል ምንነት

"ቁሳዊ ባህል" ከፎክሎር ዘርፎች ውስጥ አንዱ እንደሆነ አስቀድሞ ለመጠቆም ተሞክሯል:: "ቁሳዊ ባህል" የምንለው ሰዎች አካባቢያዊ እውቀትንና ጥሬ ቁስን ተጠቅመው የፈጠሯቸውንና ስያሜ ያወጡላቸውን አካላዊ ቁሶች በመላ አካቶ የሚይዝ ነው:: ስለዚህም ነው ማርቼስ, "much has been said about material culture. Every thing man made is part of his material culture, his artifact..." (ማርቼስ ውስጠ ማዮ;1984:16) በማለት መግለፅ የቻሉት::

እንደ ማርቼስ ከሆነ ስለ "ቁሳዊ ባህል" ብዙ መናገር እንደሚቻል ጠቅሰው፣ የሰው ልጅ የሚሰራው ማንኛውም ነገር የቁሳዊ ባህል አካል እንደሆነ ነው:: በተለይም የእጅ ስራዎች ዋና መሰረት የመሆናቸውን ሚስጢር ገልፀዋል:: ስለሆነም ቁሳዊ ባህል እንደሀውልት ወይም ቅርስ በቀላሉ የማይበሰብስ አካላዊ ነገር ነው:: በሌላ በኩል በግለሰቦች የተሰራ በስባሽ አካል እንደሆነም ይታመናል:: ይህ የእጅ ስራዎችን አካቶ የሚይዘው ጉዳይ ለበፊቱና

ለአሁኑ ትውልድ የማይናቅ መረጃን እንደሚሰጥ ማርቼስ አክለው ጠቅሰዋል:: ይህን በተመለከተ ፕሮን (2009:1) ቁሳዊ ባህልን ለማጥናት ሰው ሰራሽ ቁሶች መረጃነታቸው የማይናቅ ነው ይላሉ::

"ቁሳዊ ባህል" በባህላዊ መንገድ የሚሰራ ሆኖ አካላዊ ቁስን የሚያሳይ እንደሆነም The New Encyclopedia Britannica (1768፣463) ላይ ሰፍሮ ይገኛል:: በተጨማሪም ቁሳዊ ባህል በውስጡ ሀገረሰባዊ ምህንድስናን፣ ሀገረሰባዊ ስዕልንና ሀገረሰባዊ እጅ ስራን አቅፎ እንደሚይዝና በነዚህ መሪ ሀሳቦችም የቤት ግንባታን፣ የህንፃና የወጥ ቤት እቃ ንድፍና ጌጥን፣ የአጥር ቅርፅን፣ የአልጋ ልብስን በአጠቃላይ በቤት ውስጥ ኢንዱስትሪ የሚሰሩትን ቁሶች አካቶ እንደሚይዝ ተጠቁሟል::

ይህን በሰው ልጆች ቀያዊ ክህሎት የሚሰራን "ቁሳዊ ባህል" በማጥናት የአንድን ማህበረሰብ ቀርቶ የሀገርን ያለፉ የእድገት ደረጃና የእውቀት መጠን ማወቅ ይቻላል:: ይኸውም የሰው ልጅ መንፈሳዊ ህይወቱን የሚያድስበት አንዱ መንገድ ቁሳቁስን መስራትና በዚያ መጠቀምን እንዲሁም ማንነትን ለመግለጫም መዋሉ ነው:: ለዚህ ይመስላል "The history of American technology begins and ends with our material culture" (ስከለረት 1980) በማለት የፃፉት:: የአሜሪካ የቴክኖሎጂ ታሪክ የሚነሳውና የሚታወቀው በአሜሪካውያን ቁሳዊ ባህል አማካይነት እንደሆነ ጽሁፉ ያስረዳል:: አያይዞም ቁሳዊ ባህል ለየእለት ህይወታችን የሚያገለግለን በተለያየ አይነት ቅርጽ በእጅ የሚሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል:: የአሜሪካ የቴክኖሎጂ እድገት መነሻው የጥንቱ ቁሳዊ ባህል እንደሆነ መገለፁ አንድን ሀገር የዚህ ቁስ ሰሪና ተጠቃሚ ነበረ ብሎ የማንነት መለያነቱን አስረግጦ ማሳየቱ ነው::

ስለሆነም የአንድን ሀገር ታሪክም ሆነ የሰው ልጅን የፈጠራ አድማስ ለማወቅ ከጽሁፍ መረጃዎች የበለጠ ቁሳዊ ባህሎች ገላጮች እንደሆኑ ማረጋገጥ የሚቻል ይመስለኛል:: ይህን አስመልክተው ፕሮን (2009:3) ማዮ (1984:2) ከቃላትና ከጽሁፍ የበለጠ ቁሶች የአንድን ህዝብ ማንነት ለማወቅ እንደቁልፍ የመረጃ ምንጭነት ያገለግላሉ ብለዋል:: ከነዚህ ጋር በተመሳሰለ ግላሲ (1999: 46-47) ቁሳዊ ባህል እውነተኛ እውቀት ነው፤ የልብ ወዳጅ ነው፤ እንደ ቋንቋ ነው፤ ከዚህም በላይ ሀሳብና ድርጊትን በአካላዊ ቅርፅ እንዲቀመጥ

የሚዘግብ እንደሆነ አብራርተዋል:: አክለውም ልክ እንደተረት /ታሪክ/ ሰው ሰራሽ ቁሶች ሰነድ (text) ናቸው ብለዋል::

ግላሲ "ቁሳዊ ባህልን" እውነተኛ እውቀት ነው፣ የልብ ወዳጅ ነው፣ ልክ እንደቋንቋ ነው የማለታቸውን ያህል አሜስ "Material culture as a non verbal communication" (አሜስ, ውስጠ ማዮ 1984:25) ቁሳዊ ባህል ቃላዊ ያልሆነ መግባቢያ ነው በማለት የማጠናከሪያ ሀሳባቸውን አስቀምጠዋል:: በንግግር የሚገለጽ ሳይሆን አካላዊ አሻራውን አይተን ከቃላት በላይ እማኝነቱን እናረጋግጣለን ለማለት ነው:: ከዚህ አኳያ ከቁሳዊ ባህል አራት እውነታዎችን ልንረዳ እንደምንችል ማርቼስ ውስጠ ማዮ (1984:22) ጠቁመዋል::

አንደኛው የተለየ ገላጭና ማብራሪያ ለሚጠይቁ ጥያቄዎች ቁሳዊ ባህልን መጠቀም መቻል፣ ሁለተኛው ደግሞ ወቅታዊ የሆኑና ተከታታየነት ያላቸውን የቁሳዊ ባህል አጠቃላይ ጥያቄዎች በቋሚነት ለመመለስ የሚያስችል ህግ ለመልመድ፣ ሌላኛው ያሁኑንና ያለፈውን የሰው ልጅ ሰፊ የስራ ባህርይ ለማወቅ ተከታታይ ጥያቄዎችን ለማንሳት መርዳቱና በመጨረሻም የአሁኑን ቁሳዊ ነገር ለማጥናት የባህል ዘዴ ሂደትን ማየቱ አጠቃላይ የሰው ልጅን ባህሪ ለመግለፅና ለማብራራት የሚሉት እንደሆኑ ከጽሁፋቸው መረዳት ይቻላል::

ቁሳዊ ባህል ከንግግር የበለጠ የአንድን አካባቢ ወይም ህብረተሰብ ለመረዳት ቁልፍ መረጃ ነው:: ያም ሆኖ ቁሳዊ ባህል በውስጡ አምስት ጉዳዮችን እንደሚያካትት ቢታወቅም ለዚህ ጥናት የተወሰዱት "Folk architecture" (ሀገረሰባዊ ምህንድስና) እና "Folk crafts" (ሀገረሰባዊ እጅ ስራ) ናቸው::

ሀገረሰባዊ ምህንድስና ሲባል በባህላዊውም ሆነ ዘመናዊው በየእውቀት መጠን ሲታይ ከቤት አሰራር ጋር የተያያዘ ነው:: ዘመናዊ ምህንድስና የምንለው ከኢንዱስትሪው አብዮት በኋላ የመጣ ዘመናዊ የቤት አሰራርን ይወክላል:: ሀገረሰባዊ ምህንድስና የምንለው ደግሞ በትምህርት በተገኘ እውቀት የሚሰራ ሳይሆን፣ ትውፊታዊ ፕላኑ በህንፃው በላቤት ወይም በገንቢው የሚለመድ ሆኖ፣ በእጅ መሳሪያዎች የሚሰራ መሆኑ ነው:: ይህን ሀሳብ ሮበርት ውስጠ ዶርሰን (1972:281) ሀገረሰባዊ ምህንድናን ትውፊታዊ ምህንድስና ልንለው እንደምንችል በማጠናከሪያነት አቅርበውታል:: በተመሳሳይም ግላሲ (1999:232)

የምህንድስና ንድፍ አካላዊ ቅርፅን የሚፈጥር ነው ብለውታል:: ከፅንሰ ሀሳባዊ ሁኔታም ካየነው ሀሳብን በፕላን መልክ ቅርፅ የመስጠት ጉዳይ፣ አለፍ ሲልም ፕላኑን የሰው ልጅ በአይኑ ሊያየው በሚችል መልክ አካላዊ ለማድረግም ይመስላል:: ምህሩ አያይዘውም ምህንድስና በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት /ትስስር/ ከማሳወቅ ባለፈ መግባቢያነቱም ያመዘነ እንደሆነ ገልፀዋል:: ምህንደስናን ከባህል ጋር ማያያዙ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህን ለማወቅ ከቁሳቁስ አኳያ ግንዛቤን መፍጠር ተገቢ እንደሆነም አክለዋል::

ሌላው ሮበርት ውስጠ ዶርሰን (1972:283-284) እንዳሉት የምህንድስና ንድፍ የሰሪውን ማንነት መረዳት ለመቻል ቁልፍ ጉዳይ ነው:: እናም ምህንድስና የባህል ልዩነትን፣ በግለሰብና በማህበረሰብ መካከል ያለ ትስስርን፣ የባህል ስርጭትን፣ የባህልን በቋሚነት የመቀጠል ባህሪ፣ አዲስ አካባቢን በቀላሉ የመልመዱ ጉዳይ እንደሚጠናበት አብራርተዋል:: አክለውም ሀገረሰባዊ ምህንድስና በአጠቃላይ ከአካባቢው በቀላሉ በሚገኙ ጥሬ ቁሳቁሶች መስራት መቻልን እንደሚጠቁም ገልፀዋል:: ግላሲ በተጨማሪ "Buildings, like pots and poems, realize culture. Their designers ratinonalize their actions differently... But all of them create out of the smallness of their own experience." (ግላሲ., 1999:227) በማለት አስፍረውታል::

ህንፃዎች ልክ እንደሸክላና ስነ ግጥም ሁሉ ባህልን እውን ያደርጋሉ:: የህንፃዎቹ ሰሪዎች የየራሳቸውን እሳቤ ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ በተለያየ አይነት መግለፅ መቻላቸው ነው:: በሰዎች መካከልም የራስን መንገድ የሚለይ አካሄድ እንዳለ ነው:: ነገር ግን ሁሉም ሰሪዎች ከራሳቸው ትንሽዬ ልምድ ተነስተው እንደሚፈጥሩ ምሁሩ አያይዘው ገልፀውታል::

በሌላ መልኩ ግላሲ (1999:231) የሀገሬውን ምህንድስና ማጥናት አጠቃላይ የተገነባውን አለም የማወቂያ ስልት እንደሆነ ጠቅሰዋል:: የምልዑነት ውለታን ለማሳወቅና ልዩነትን እውቅና ለመስጠት፣ የህንፃዎች ማስረጃነት ይመረጣል:: የሰው ልጅን የታሪክ ቅጅ /ትርጉም/ በተሻለ መልኩ መገንዘብ እንዲቻል ሀገረሰባዊ ምህንድስና ጥቅሙ የጎላ እንደሆነም አመልክተዋል:: የሀገረሰባዊ ምህንድስና ውጤት የሆኑት ባህላዊ ቤቶች በአካባቢው በሚገኙ ጥሬ ቁሶች ይሰራሉ::

በዚህ ላይ ፎስተር(1963:375) ሀገር በቀሉ የምህንድስና ህዝባዊ ሀሳብ የመነጨው በሁሉም የዓለም ክፍል ያሉት ሰዎች ህይወታቸውን ከመጥፎ የአየር ሁኔታ ለመከላከል ሲሉ በራሳቸው እውቀትና በአካባቢያቸው ቁሳቁስ ባህላዊ ቤታቸውን መስራት መቻላቸውን ነው:: የባህላዊ ቤት መስሪያ ጥሬ ቁሶችም እንጨት፣ አፈር ወይም ደንጋይ እንደሆኑ ተጠቅሰዋል:: እነዚህን ጥሬ ቁሶች በራሳቸው እጅ መልክ በመስጠት አንድን ቤት መስራት እንደሚችሉ ፎስተር አያይዘው ገልፀዋል:: ቀስ በቀስም የግብርና ቤቶችንና የገበሬዎች መኖሪያ ቤትን በዛሬው መልክ እንደሚሰሩ አክለዋል:: ስለሆነም ባህላዊ ቤትን ለመሰራት ሀገረኛ እውቀት[4] "Indigenous Knowledge system" ፣ እንጨት፣ አፈር፣ ድንጋይ፣ ሳርና የመሳሰሉትን ጥሬ ቁሶች መጠቀም ይቻላል::

ሌላው ባህላዊ የቤት አይነቶችን አስመልክተው ግላሲ (1999:233) የተለያዩ ሀገራት የቤት ሁኔታን ባጠኑበት ወቅት ባገኙት ቤቶችን የመከፋፈል ልምድ በየሀገራቱ ከተሰጡት ስያሜዎች ተነስተው እንደሆነ ገልጸዋል:: አያይዘውም ከሰዎች ባገኙት መረጃ መሰረት ቤቶችን ወይም ግንባታዎችን በቁሳቁስ አይነታቸውና በተሻለ በጣሪያ ቅርፃቸው ተነስተው መሰየም እንደቻሉ ነው:: ከዚህ አኳያ ለዚህ ጥናት በተመረጠው ወረዳ ያሉት ባህላዊ የቤት አይነቶች በአካባቢው በተሰጣቸው ስያሜ መሰረት አዳራሽ፣ ደርብ፣ እልፍኝና ጎጆ ቤት በመባል እንደሚታወቁ ቃላዊና ምልከታዊ መረጃዎች ያረጋግጣሉ:: በእርግጥ ባህላዊ የቤት አይነቶችን እንደየአካባቢው ሁኔታ የተለያየ ስያሜ መስጠት እንደሚቻል ይታመናል::

ከሀገረሰባዊ ምህንድስና ቀጥሎ ለዚህ ጥናት የተመረጠው ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ነዉ:: ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁሶች በአእምሮ የታሰበ ንድፍን አካል ይሰጣሉ:: በአካል መልክ የተፈጠረውን ቁስም በመኖር ሂደት ላይ እንዲሰምር ያደርጋሉ:: ለዚህም ነው ግላሲ "Artifacts set the mind in the body the body in the world" (ግላሲ., 1999:42) በማለት የገለፁት:: ይህ ብቻም ሳይሆን ግላሲ (1999:44) ቁስ የአለም አካል እንደሆነና ተፈጥሮን አካላዊ አድርጎ እንደሚቀርፅም ገልፀዋል:: የእጅ ሙያ ምርቶች በቋሚነት የንድፍ ሂደቱን ሲያሳውቁ፣ ንድፍም በአእምሮ እንደሚፈጠር አስረግጠው ያስረዳሉ:: የእጅ ሙያ ምርቶቹ ለየቀን ተግባር የሚውሉ መሆናቸውን ብራሲየር የተባሉት ባለሞያ "Folk Crafts Simple hand made objects for every day use" በማለት በድረገፃቸው ጽፈዋል::

---

[4] ሀገረኛ እውቀት የሚለውን የሀገርኛ እውቀት ስርዓቶች በማለት ተርጉመውታል:: (ፈቃደ፣ 1991:11)

ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁሶች እንደምሁራኑ የትውር እሳቤ ከሆነ የሰው ልጅ ለየእለት ተግባሩ መጠቀሚያ ይሆኑት ዘንድ በአካባቢው ባገኛቸው ጥሬ ቁሶች የራሱን ሀገረኛ እውቀት ተጠቅሞ ይሰራቸዋል:: ቁሶቹ ሲሰሩ ባህላዊ ፍላጎትን ባገናዘበ መልኩ እንደሆነ ይገመታል:: ይህን በተመለከተ ፕሮን, "... These natural materials are artifacts- objects modified by man- and are of cultural interest" (ፕሮን; 2009:2) የተፈጥሮ ቁሶችን ሰው ሰራሽነት ጠቅሰው፣ ባህላዊ ፍላጎትን ባገናዘበ መልኩ ተስተካክለው እንደሚሰሩ ጠቁመዋል:: ሮበርት (1972:233) በበኩላቸው ሀገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ትውፊታዊ የእጅ ሙያ ውጤት እንደሆኑ ገልፀዋል::

የየእለት መገልገያ ቁሶቹ በሰው ልጅ አእምሮ ተፀንሰውና አካላዊ ቅርፅ ተሰጥቷቸው ባህልን ባገናዘበ መልኩ ጥቅም ላይ በመዋላቸው የማይረሳ ትውስታን መፍጠራቸው አይቀርም:: ይህም ቁሶቹን በመመልከት የቀደመ የሰዎችን የፈጠራ ችሎታና የባህል መገለጫ፣ ልክ ጽሁፍን የማንበብ ያህል ልንረዳባቸው እንችላለን:: ግላሲ (1999:47) የእጅ ስራዎች አልፎ አልፎ በባህሪያቸው የጠራ ስድ ጽሁፍን ይወክላሉ ማለታቸው ያለነገር አይደለም:: ከእጅ ስራ ቁሶቹ ድርሰታዊ ህብረትን ባካተተ መልኩ ሰነድና አውድን፣ ቅርፅና ፍችን፣ መዋቅርና ተግባርን በአንድ ላይ መግለፅ የሚቻልባቸው መሆናቸውን አያይዘው መጻፋቸውን ማጤን ይቻላል::

የእጅ ስራ ቁሶቹ የማይረሳ ትውስታን የመፍጠራቸው ጉዳይ ከአካባቢያዊ ጥሬ ቁስ መሰራታቸው ይመስላል:: የሀገረሰባዊ የእጅ ስራ አይነቶችና መስሪያ ጥሬ ቁሶች በተመለከተ ፓንክረስት የሚከተለውን ብለዋል::

> *Ethiopia has a long history of handicrafts which stretch as back to the very down of history. It found expression in the countries prehisforic rock paintings and curuings, as well as in the wonders of ancient Aksum, with its beautifully constructed palaces and remarkable stele or obelisks and its fine coins struck for many centuries in gold, silver and bronze.... (ፓንክረስት: 251)*

ከጥቅሱ የምንረዳው የኢትዮጵያ የእጅ ስራ ወይም የእደጥበብ ስራ ረዥም ታሪክ ያለውና እንዲያውም ወደኋላ ተለጥጦ የታሪክ ውልደት ላይ እንደጀመረ ነው:: እንደ ሀገሪቱ ቅድመ ታሪክ መግለጫ ከሆነ የድንጋይ ቅብና ፍልፍል ጽሁፍ ወይም አስገራሚው ጥንተ አክሱም ስራ፣ የሚያምረው የቤተመንገስት ግንባታ፣ የድንጋይ ሐውልትና ከወርቅ፣ ከብርና ከነሐስ የተሰሩ መልካም ሳንቲሞች ተጠቃሽ እንደሆኑ በመጠቆም የኢትዮጵያን የእደጥበብ ውጤት ጠቅሰዋል::

ከኢንዱስትሪ አብዮት በፊት ጀምሮ እንደ ኤሮፖውያን ሁሉ የኢትዮጵያ ህዝብም የየዕለት ፍላጎቱን የሚያሟላባቸው የእጅ ስራ ቁሶችን ይሰራ እንደነበር ፓንክረስት (1964:221) በሌላ ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ አቅርበዋል:: በዚህ ጽሁፋቸው የእጅ ስራ ቁሶችንና የመስሪያ ጥሬ ቁሳቸውን ጨምረው ገልፀዋል:: ይኸውም ከብረታብረት /ቢላዋን፣ ጎራዴን፣ ጦርን፣ ማረሻና ሌሎችን)፤ ጥጥና ሱፍን በመሸመን ተመራጭና ቆንጆ ልብስን፤ የበፊን፣ የበግና የሌሎችን ቆዳ በመፋቅ (የጋሻ ሰገባን፣ የመጽሀፍ ሽፋንን፣ ኮርቻን፣ የፈረስ ልጓምን፣ ጠፍርን፣ ቀበቶን)፤ ከሸክላ (ማሰሮን፣ ጋንንና የመሳሰሉትን)፤ ከቀርቀሃ (ቅርጫትን)፤ ጠቃሚ የቀንድ ቁሳቁስን ከወርቅ፣ ከብርና ከነሀሰስ (ውብ የሆነ ቅርፅ ያላቸው የጆሮና የአንገት ጌጣጌጦችን)፣ የተለያየ ቀለም ያላቸው የስጋጃ ምንጣፎችን፣ ብርሃን ፈንጣቂ ጽሁፎች የሚፃፉባቸውን ብረናዎችና የመሳሰሉትን ሰርተው በየዕለት ተግባራቸው ይጠቀሙ እንደነበር በስፋት ገልፀዋል::

ሲልቨርማን(1999:3) ሸክላ፣ ጌጣጌጥ፣ ቀለምቅብ፣ ቅርጫት ስራ፣ እንጨት ስራ መንፈሳዊ ማዕከላዊነት ይፈጥሩ እንደነበር በጥናታቸው ጠቁመዋል:: ከሁለቱ አጥኝዎቸ መረዳት አንደሚቻለው ዥንዲ፣ ደበሎ፣ ካባ፣ ቦርሳ፣ አቅማዳ፣ ስልቻ፣ ዳውጅና የመሳሰሉትን በሀገረሰባዊ የእጅ ስራ አይነትነት ልንመደባቸው እንችላለን:: በሌላ ጎኑ የስፌት እቃዎች (መሶብ፣ መሶበ ወርቅ፣ ቀለምሻሽ፣ ወራንቻ፣ ላዳን፣ ቁና፣ ሰፌድ፣ አገልግል)፤ ገላና የሸቆ ጥላም የሚጠቀሱ ናቸው::

ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁሶችን ለመስራት በእኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ጥሬ ቁሶችን መጥቀስ ይቻላል:: በዋናነትም ቆዳና ሌጦ፣ እንጨት፣ ሳር፣ የሸክላ አፈር፣ ብረታብረት፣ ቅል፣ የእንስሳት ቀንድ፣ ቃጫ፣ ሞራ፣ ሰም ይጠቀሳሉ:: እናም እነዚህን የጥሬ ቁስ አይነቶች

ባለሞያዎች በያይነታቸውና በአገልግሎታቸው አማካይነት አስማምተው በመስራት ለህብረተሰቡ ለየዕለት የስራ ተግባር ማቅረብ እንደሚችሉ ይገመታል፤ ነውም::

በአጠቃላይ ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ አንዱ የቁሳዊ ባህል ክፍል ሲሆን የሰውን ልጅ የቀደመ አስተሳሰብ፣ እምነት፣ ባህል በጠቅላላው ማንነት መግለጫ በመሆኑ መጠናት እንደላበት ይታመናል:: ለዚህም ነው በጥናቴ ከሀገረሰባዊ ምህንድስና ጋር አያይዤ ቁሳዊ ገላጭነታቸውን ለመተንተን የተነሳሳሁት:: ሆኖም ሁሉንም ቁሶች ሳይሆን በመጥፋት ለይ የሆኑት ብቻ የጥናቴ ትኩረት በማድረግ እንደምሰራ በጥናቴ ወሰን ላይ መጥቀሴን ልብ ይሏል:: የቁሳዊ ባህል ምንነትን ከቁሳዊ ባህል ጉዳዮች ውስጥ ሀገረሰባዊ ምህንድስናና ሀገረሰባዊ የእጅ ስራን ከአይነትና መስሪያ ጥሬ ቁሳቸው ከዚህ በላይ ትዎራዊ ንድፈሀሳባቸውን ለመዳሰስ ሙከራ ተደርጓል:: በመቀጠል ደግሞ እነዚህን ቁሶች እንዴት መመደብ እንደሚቻል የተለያዩ ምሁራንን ንድፈ ሀሳቦች በማጣቀስ ላቅርብ::

2.2.2. ቁሳዊ ባህሎችን የመመደቢያ መስፈርቶች

ቁሳዊ ባህሎች አይነታቸው የበዛ እንደሆነ መገመት አያዳግትም:: የመስሪያ ጥሬ ቁሳቸውም እንዲሁ የተለያየ ነው:: እናም እነዚህን ቁሶች በተግባርም ሆነ በአስፈላጊነታቸው ከፋፍሎ መመደብ የሚጠበቅ ጉዳይ ይመሰለኛል::ምደባ የየሀገሩን ወይም የየአካባቢውን ማህበረሰብ ቁሶች በራስ ሀገራዊ (ከባቢያዊ) እውቀት የመሰራታቸውን ያህል አካባቢያዊ ስያሜ የማይናቅ እንደሆነ በስፋት ተጠቅሷል:: በዚህ ላይ ግላሲ “During architectural field work I have taught my self to concentrate on form, but every where I go the people whose houses I study classify buildings by materials, and especially by roofing.... ” (ግላሲ 1999:33)ያስፈሩትን ማየት ይቻላል::

ከዚህ የምንረዳው በተለይ ባህላዊ ቤቶችን በተለያዩ ሀገራት ባጠኑበት ወቅት ያገኙት ቤቶችን የመከፋፈል ልምድ በየሀገሪቱ በተሰጡት ስያሜዎች ተነስተው ነው:: ይኸውም ከሰዎች ባገኙት መረጃ መሰረት የግንባታዎችን የቁሳቁስ አይነት ወይም ከዚህ በተሻለም የቤቶችን የጣሪያ አይነታቸውን በማየት ለመመደብ እንደተጠቀሙ ገልፀዋል:: በዚሁ ላይ ቤቶችን የመመደብ ጉዳይ አስቸጋሪነት በመጥቀስ የተነሱት ሮበርት ውስጠ ዶርሰን (1972:284) ሀንፃዎችን በተግባራቸው አጠቃላይ ምደባ መስጠት እንደሚቻል ጠቁመዋል::

ፕሮን እንደ ሮበርት ሁሉ ቁሶችን በየወገናቸው ለመመደብ እጅግ የተሻለውና ተስፋ የተጣለበት ስልት በተግባራቸው (በሙያቸው) መሆኑን ንድፈ ሀሳባዊ ልምዳቸውን አካፍለውናል:: ".. The most promising mode of classification is by function." (ፕሮን፣2009፣2) በማለት:: ይህ አባባላቸው ከባህላዊ ቤቶች ውጭ ያሉትን ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁሶችንም ሆነ የቁሳዊ ባህል ጉዳዮችን በተግባር የመመደብ አማራጭነት እንዳለው የሚያስገነዝብ ይመስለኛል:: ፕሮን በዚሁ ገጽ ላይ አክለውም ቁሶች ባህላዊ እምነትን እንደሚያንፀባርቁ ጠቅሰው፣ የዚህ አይነቱ የማሳያ ዋጋ ከቃላዊና ከባህሪያዊ የባህል አገላለፅ ዘዴ በተለየ እንደሆነ ጠቁመዋል::ማለትም ቁሶችን ለመመደብ ቅርፅም ጠቃሚ እንደሆነ ነው::

ማርቼስ ውስጠ ማዮ (1984:11) በጽሁፋቸው እንደጠቀሱት ከሆነ ቁሳዊ ባህል የሰው ልጅን ባህሪ የሚያንፀባርቅ በመሆኑ በሁለት መንገድ ተንትኖ መመደብ እንደሚቻል ነው:: አንደኛው በሳይንሳዊ የምደባ አሰራርና ብልሃት፣ በሁለተኛነትም እንደመሰረታዊ መመሪያ የወሰዱት በቁሳዊ ቅሪቶች ንድፍ (ሞዴል) ልዩነት ተገልፀውና ተብራርተው መመደብ እንዳለባቸው መክረዋል::

ማርቼስ በሌላ መልኩ "... Classification is the means by which artifactual material is categorized subject to manipulation.... Thus, classification is a self- contained techniques for determining artifacts categories and cultural process." (ማርቼስ ውስጠ ማዮ 1984:15) በማለት የእጅ ስራ ቁሶችን ለመፈረጅና ስም ለመስጠት ባህላዊ ሂደትን መሰረት ያደረገ ግለሰባዊ ብልሃትን የሚሻ የመመደቢያ ዘዴን ጠቁመዋል::

ማርቼስ በዚህ ጽሁፋቸው /1984:16/ የእጅ ስራ አይነቶች የሚሰሩት በአካላዊ መለያ ባህሪያቸው ሆኖ በክፍል የመመደቡን ግምታዊ ተግባር ከባህልና ከታሪካዊ ጠቀሜታቸው አኳያ ማየትም እንደአማራጭ ስልት ጠቁመዋል:: ቁሶችን መከፋፈል መረጃን በአጭሩ ለማቅረብና በቀላሉ ለመቆጣጠር እንደሚያመች አስረድተዋል:: "... Classification summarizes data and makes them manageable" (ማርቼስ ውስጠ ማዮ,1984፡19/

በማለት ነው:: በተያያዘም ቁሶችን ለመመደብ አራት የታወቁ አባባሎችን መጠቀም እንደሚቻል አሳይተዋል::

የመጀመሪያው ምድቦች ሆን ተብሎ መለያ ፀባያቸውን መሰረት ባደረገ ትርጉም በመስጠት እንደሆነ፣ በሁለተኛነት ደግሞ የምድቦች መለኪያ የሆነው በጊዜና በቦታ ሳይወሰንና ባህሪያቸውን በተመሳሳይ ሰአት ከአንደ አቅጣጫ በላይ ማየት እንደሚቻል፣ በሶስተኛነትም እንደተፈጥሮ ክስተት ምድቦችን የመደልደል፣ የመመደብ፣ አቅጣጫን የማሳየትና በመጨረሻም ምድቦች ከራሳቸው ተግባር አኳያ ወሰን ሊደረግባቸው እንደማይችል አጠቃለው አቅርበውታል::

ከላይ በተለያዩ ምሁራን ከተሰጡት ንድፈ ሀሳባዊ መረጃዎች ስንነሳ ባህላዊ ቤቶችንም ሆነ ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁሶችን ለመመደብ ከአካባያዊ ስያሜ፣ ከቁሶች አገልግሎት ወይም ተግባር፣ ከቁሶች ቅርፅ፣ ከባህላዊ ገላጭነታቸው፣ ከቁሳዊ ቅሪቶች ንድፍ (ሞዴል)፣ ከግለሰባዊ ብልሃት፣ ከመስሪያ ጥሬ ቁሳቸው፣ ከተፈጥሮ ክስተት አይነታቸው፣ ከትንተናዊ ትርጉማቸው እና ከመሳሰሉት እንደሆነ መረዳት ይቻላል:: የምሁራኑን ንድፈ ሀሳብ መሰረት በማድረግም ለጥናቴ በመረጥኩት ወረዳ ትኩረት ያደረኩባቸውን ቁሳዊ ባህሎች በተለይ ባህላዊ ቤቶችን በአካባያዊ ስያሜ፣ የእጅ ስራ ቁሶችን ደግሞ በመስሪያ ጥሬ ቁሳቸውና በተግባራቸው ከፋፍዬ ለመመደብ እሞክራለሁ::

ቁሳዊ ባህሎችን በምድብ ከፋፍሎ ማስቀመጥ አንድ ሙያ ነው:: ሆኖም በምድብ ከፋፍሎ መሳየቱ ብቻ ግብ አይደለም:: ስለሆነም እያንዳንዱን ቁስ አሰራርና አገልግሎት በገለፃ ማቅረብ ይጠበቃል:: ለዚህም የተለያዩ ንድፈ ሀሳባዊ ትወራዎችን መጥቀስ ይቻላል:: እናም ቀጥሎ ለማቅረብ ተሞክሯል:: እነሱም ቁሳዊ ባህልን የመተንተኛ ሞዴሎች (አንጻሮች) እና ሂደቶች ናቸው::

2.2.3. ቁሳዊ ባህልን የመተንተኛ ሞዴሎች[5] /አንፃሮች/

"ቁሳዊ ባህል"ን በራሱ በማስተዋል ብቻ አካባቢያዊ ተምሰሌትነቱንም ሆነ ማህበራዊ ገላጭነቱን መረዳት ይቸግራል::መረጃን መሰረት ተደርጎ የተሰባሰቡት ቁሶች መተንተን ይኖርባቸዋል:: ሲተነተኑ የተደበቀ ውበታቸው ወይም ገላጭነታቸው ጎልቶ ይወጣል:: ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ገላጭነታቸው የሚታወቀው ሲተነተኑ ነው:: ምሁራን መረጃነታቸውን የሚሹት ከዚህ የተነሳ ነው:: እናም ቁሳዊ ባህልን ለመተንተን የስከለረት (1980) ዘጠኝ ሞዴሎችን መጥቀስ ይቻላል::

- ታሪካዊ ጥበብ ገላጭነታቸው:- ቁሶች በተፈጥሯቸው ውበትን የተላበሱ ናቸው:: እናም ይሄ ሞዴል ቁሶችን በምንተነትንበት ወቅት ከጠቃሚታቸው አኳያ ሳይሆን ጥበባዊ መስህበነታቸውን ማሳየት ነው:: ይኸውም የቁሶችን ቅርጽ፣ ቀለም /የተለየ ውበት/፣ ለስላሳነት /ሻካራነት/ በገለፃ ወቅት አጉልቶ በማውጣት ታሪካዊ እሴት አመላካችነታቸውን ማሳየት ይጠበቃል::
- ተምሳሌታዊነት:- ይሄ ሞዴል አንዳንድ ቁሶች በማህበረሰቡ ዘንድ የተለየ ተምሳሌታዊ ትርጉም የሚያሰጡ መሆናቸውን ማሳየት የሚችል ነው:: ከሃይማኖት ወይም ጀግናዊነት መገለጫ ጋር በተያያዘ የተለየ ክብር ሊሰጣቸው ይችላል:: እናም ቁሶቹን በሚተነተኑበት ወቅት የተለየ ተምሳሌታዊነታቸውን ማሳየት ከአጥኝው እንደሚጠበቅ ሞዴሉ ቀርቧል::
- ባህላዊነት:- ይህ ሞዴል የአንድን ማህበረሰብ፣ ብሄር /ቡድን/ ወዘተ ባህል መገለፅና አለመገለፅ የምንፈትሽበት ነው:: የቁሱ የተለየ ባህሪ አለው ወይ? የተወሰነ ባህልን የሚወክልቡት ሁኔታ ይኖራል? ብሎ በመመርመር ማጤንና መግለፅን ይጠይቃል::
- አገልገሎት ሰጭነት:- ይህ ሞዴል ቁሶችን በምንተነትንበት ወቅት ተቀዳሚ አገልግሎታቸው ምንድን ነው እንዴት አገልግሎት ይሰጣሉ? አሁንም ያን አገልግሎት ይሰጣሉ? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ለአንባቢ ግልፅ አድርጎ ማሳያ ነው::
- መዋቅራዊነት:- ይሄ ሞዴል ቁሱ እንዴት እንደተሰራ፣ ከምን እንደተሰራ፣ መስሪያ ቁሱ ከየት እንደተገኘ ለሚያወሱ ጉዳዮች ትኩረት በመስጠት ትንታኔውን ማስኬድ ይጠበቃል::

---

[5] ሞዴሎች "Art Historical" "Symbolic", "Cultural", "Fictional", "Structural", "Environmental", "Behavioral", "Community", "Social history" ይባላሉ (ስከለረት ከኢንተርኔት: 1980)

- አካባቢያዊነት:- ቁሶችን አካባቢው በራሱ ቅርፅ ያወጣላቸዋል? ቁሱ ተፈጥሯዊውን አለም ይገልፃል /ያንፀባርቃል/? ተፈላጊ ጥሬ ቁሶችንስ ማግኘት ይቻላል? የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አካባቢው በቁሶቹ ላይ ያሳደረውን ጠቀሜታ ወይም ተፅዕኖ መፈተሽ ይገባል:: አካባቢው ወደ በርሃማነት መቀየር በጥሬ ቁሶቹ ላይ ያመጣው ተፅዕኖ መኖርና አለመኖር የምናውቅበት ሞዴል ነው::
- ባህሪ ገላጭነት:- ይህ ቁስ ለህዝቡ ምኑ ነው? በቁሱና በህዝቡ መካከል አንዳች የሚያገናኛቸው ባህሪይ ተፈጥሯል? በማንኛውም መንገድ ሰዎችን ለተለየ ባህሪይ ለውጧቸዋል? የሚሉትን ጉዳዮች ምላሽ በመስጠት ቁሶችን በመተንተን የተለየ በህሪ ገላጭነታቸውን መሳየት ነው::
- ማህበራዊነት:- ቁሱ ለማህበረሰቡ ያለውን ጠቀሜታ ለጥቂቱ ወይም ለብዙሃኑ የማህበረሰብ ክፍል የተለየ ማህበራዊ ጠቀሜታ አለው? ሁሉም የማህበረሰብ አባል ለቁሱ ተመሳሳይ እይታ ይሰጠዋል? በማለት አንዳች ማህበራዊ ጠቀሜታነትና ገላጭነት ማጤን ይገባል::
- ማህበረሰብ ታሪክ ጠቋሚነት:- የቁሱ ታሪክ ምንድን ነው? ስንት ዘመኑ ነው? በባህል የተለየ ሁነት ወይም የተለየ ወቀተን የሚያስታውስ ነው? ማን ነው የሰራው? ባለቤቱ ማነው የሚሉትን መሰረታዊ ነጥቦች በመጠየቅ ቁሱ የአንድን ማህበረሰብ ታሪክ ጠቃሽነት ማሳየት ነው::

በአጠቃላይ ቁሳዊ ባህሎችን በምንተነትንበት ወቅት እነዚህን የመተንተኛ ሞዴሎች በአእምሯችን ማሰላሰል ይጠበቃል:: የትንታኔው ጉልህ ድርሻ የቁሶችን የተለየ ተምሳሌታዊነት፣ ማህበራዊነትና የመሳሰሉትን ጉዳዮች እንዴት እንደሚገልፁ ከቁሶቹ ጋር አብሮ መቅረስ የሚያስችል ነው:: በተለይ በመጥፋ ላይ ያሉ ቁሶች አካላዊ ቅርፃቸው ብቻ ሳይሆን እነዚህን መሰረታዊ የህብረተሰቡ እሴቶች ጨምረው ይዘው የሚጠፉ ስለሆነ መጠናት እንዳለባቸው አያጠያይቅም:: ከዘጠኙ ሞዴሎች ጎን ለጎን ትንተናውን በሶስት ሂደቶች[6] ማስኬድ እንደሚቻል ፕሮን(1999:7-10) ጠቁመዋል::እ

- ገለፃ:- ይህ ቁሳዊ ባህልን የመተንተኛ ሂደት የመጀመሪያ የተንታኙ እይታ ሲሆን፣ የቁሱን ቅርፅ በመያዝ አካላዊ መጠኑን /ርዝመት፣ ቁመት፣ ክብደት፣ ስፋት/ እና

[6] ሂደቶች (Description; (Deduction); (Speculation) በማለት ይጠቅሷቸዋል:: (ፕሮን; 2009"7-10)

የቀለም መስህብነቱን ሌላው ሊመለከተው በሚችል መልኩ መግለፅ የሚያስችል ነው:: የፋብሪካው ተቀዳሚ ተግባር የቁሱን ጥበባዊ ስራና ሌሎች ማስዋቢያ ጉዳዮች እንደመሆኑም ተመራማሪውም በሚያጠናው ጥናት ላይ ብቻ በማተኮር ትንተናውን እንዲሰጥ ምሁሩ ይመክራሉ:: እናም የቁሱን ይዘት ሌሎች ሊረዱት በሚችል መልክ መግለፅ መቻል ነው::

- ትርጓሜ:- በሁለተኛነት የሚመጣው የትንታኔ ሂደት ሲሆን የቁሱን መጠን ወይም ይዘት ከገለፅን በኋላ አንዳች ትርጓሜ መስጠት የሚያስችለን ነው:: ይህም በቁሱ ላይ ብቻ ሳይሆን ሰዎች አለሙን የተረዱበትን መንገድ በትንታኔያችን የምንቃኝበት፣ ቁሱን ከታሪካዊነት አኳያ የተለየ ጠቋሚነት እንዳለው ማሳየት የሚቻልበት ነው:: በዚህ የትንታኔ ሂደት ላይ ተንታኙ ራሱን ለተወከለው አለም በማጋለጥ ስሜታዊነትን በመገደብ ምን እንዳየ፣ እንደሰማ፣ እንዳሸተተ፣ እንደቀመሰና እንደተሰማው ሌሎች እንዲስማቸው ማድረግ አለበት:: በተያያዘም ተመራማሪው እውቀቱንና ልምዱን በመጠቀም ውጪያዊ መረጃን በመያዝ የቁሱን ውስብስባዊነት መተርጎም ይሆናል:: ለቁሱም ያለውን ስሜታዊ ምላሽ ማስገንዘብ እንደሚጠበቅበት ምሁሩ ይመክራሉ::
- ግምታዊ ጥቆማ:- ይህ ሂደት ቁሳዊ ባህልን በመተንተን ሂደት በሦስተኛነት የሚመጣ ነው:: የቁሱን አካላዊ ቅርጽ መጠን /ይዘት/ ከገለፅንና ይህኑ መሰረት ያደረገ ትርጓሜ ከሰጠን በኋላ በተሰማንና በተረዳነው መጠን የራሳችንን ንድፈ ሀሳብ /ከተቻለ/ የምንፈጥርበት ነው:: ይህም ሶስት ግምታዊ የህግ ትንታኔ ደረጃዎች አሉት:: አንደኛው በተቻለ መጠን ምናባዊ ፈጠራን መጠቀም፣ ቀጥሎም ነፃ ሆኖ ሀሳብንና የተረዱትን ብቻ አለዝበ ማቅረብና በችኮላ ሳይሆን በተንታኙ የተለመደ ስሜትና ውሳኔ ግልፅ ያልሆነን ጉዳይ ሊታመን በሚችል መንገድ ማስቀመጥ መቻልን ይጠይቃል:: ተመራማሪው ከቁሱ ውጪያዊ መረጃ ወይም ከቁሱ ተለይቶ በራሱ የአረዳድ ብቃት የሚከወን ነው:: ለባህሉ ባለውም አቋም መሰረት የራሱን ትንታኔ የሚሰጥበት ክፍል እንደሆነ ፕሮን ያስገነዝባሉ::

ከላይ በተጠቀሱት የትንተና ሞዴሎችና የትንተና ሂደቶች አማካኝነት አንድ የቁሳዊ ባህል አጥኝ በመረጃ አስደግፎ ያሰባሰባቸውን ቁሶች በመተንተን ማሳወቅ እንደሚችል መረዳት የሚቻል ይመስለኛል:: ይህም ቁሶችን በራሳቸውም ሆነ ማህበረሰቡ በፈጠረላቸው ስነቃሎች

በመመራት መተንተንና ተምሳሌታዊ ወይም ማህበራዊ ዋጋቸውን ሌሎች ሊረዱት በሚችሉት መንገድ ማስረዳት ነው::

እነዚህ የማህበረሰቡን እምቅ እውቀት ገላጭ ቁሶች አሁን ባለንበት ዘመን አደጋ ላይ የወደቁበት ሁኔታ ተፈጥሯል:: ይኸውም በተፈጥራዊ ሁኔታዎች መዛባትም ይሁን ዘመኑ በወለዳቸው የዘመኑ ቴክኖሎጂ የቅርፅ ወይም የመጠን ለውጥ መከሰት አልቀረም:: እናም በዚህ ጥናት የሀገረሰባዊ ምህንድስናና የእጅ ስራ ቁሶች በመጥፋት ላይ መሆን የሚተኮርበት በመሆኑ በመጥፋት ላይ የመሆናቸውንና ተፅዕኖ ያሳደሩ ጉዳዮችን ቀጥሎ ለማሳየት ይሞክራል::

2.2.4. የቁሳዊ ባህል በመጥፋት ላይ መሆንና ያሳደሩ ተፅዕኖዎች

ለውጥ የማይነካው የተፈጥሮ ክስተት በዚህ አለም ላይ አይኖርም:: ሁሉም ጊዜና ወቅቱን ጠብቆ ይለወጣል:: የለውጥ መዘግየትና መፍጠን ካልሆነ በስተቀር:: እናም የሰው ልጅ አካባቢያዊ እውቀቱንና ጥሬ ቁሱን ተጠቅሞ ለየዕለት የኑሮ ሂደቱ ሲጠቀምባቸው የነበሩት ቁሳዊ ባህሎች ጊዜያቸውን ጠብቀው በተለያዩ ምክንያቶች መለወጣቸው አይቀርም:: እንዲያውም ለውጡ ከራሱ ከሰው አስተሳሰብና ራሱ ከፈጠረው ከባህሉ ይጀምራል::

ለውጥን አስመልክተው ፕሮን (2009:6) የቁሶች በአገልግሎት ላይ የመቆየታቸውን ሁኔታ ተመሳሳይነት ጠቅሰው፣ ነገር ግን የህዝቦችን የባህል ለውጥ በሂደት እንደሚነካቸው በጽሁፋቸው አስፍርዋል:: እንደ ምሁሩ እምነት ከሆነ ጥበባዊ ቁሶቹ በተለያየ መልክ ምላሽ ለመስጠት የሚያነሳሱት በተፈጠሩበት ጊዜ እንጂ በለውጥ ሂደት ላይ ግን የደበዘዘ እንደሚሆን ነው:: እነዚህ ባህላዊ ቁሶች አሻራቸውን ሳየተው የሚጠፉበት ሁኔታ አለ:: በዚህ ላይ ሮበርት የሚከተለውን ብለዋል::

"Traditional crafts that are of great antiquity are on the point of disappearing. They represent an important part of a traditional way of life that is also being submerged by a new and different way..." (ሮበርት ውስጠ ዶርሰን; 1972:442) ትውፊታዊው የእጅ ሙያ ቁስ ወይም የጥንት የምንለው በመጥፋት ላይ

እንደሆነ ሮበርት ይነግሩናል:: ጠቃሚውን ህይወት የሚወክለው ታላቁ የእጅ ሙያ በአዲስና በተለየ ሁኔታ እየተለወጠ ወይም እየተተካ እንደሄደ ያስገነዝባሉ::

ጀኪንስ ውስጠ ዶርሰን (1972:500) በተጨማሪ ሀገረሰባዊ የእጅ ስራዎችና ምርቶች ሙሉ በሙሉ እየጠፉ እንደሆነ ያስገነዝባሉ:: ይህም በአካባቢ መለወጥና ምጣኔ ሀብታዊ ተፅዕኖ ነው:: የአገልግሎት መጠን መቀነስም ተጠቃሽ ነው ይላሉ:: እንደ ጀኪንስ ከሆነ ባህላዊ የሸክላ ስራ ማዕከላት ቁጥር፣ የሽመና መስሪያ ቦታ፣ አናፂዎች፣ ከመዳብ ወይም ከነሃስ ሳንቲሞችን የሚሰሩ ባለሞያዎች፣ ብረታብረት ቀጥቃጮችና የመሳሰሉት እየቀነሱ መሄዳቸውን ጠቁመዋል:: ይህም የሀገረሰባዊ ቁሶች ብቻ መጥፋት ሳይሆን ባህላዊ እጅ ሰሪዎችም ሙያቸውን እየተው መሆናቸውን የሚያስገነዝብ ነው::

በሌላ ጎኑ ሮበርት ውስጠ ዶርሰን (1972:281) ለበርካታ ምዕተ ዓመታት በምዕራብ አውሮፖና በሰሜን አሜሪካ ዘመናዊ ምህንድስናና ባህላዊ ምህንድስና ጎን ለጎን ከመቀጠላቸውም በላይ በተለይ ባህላዊ ምህንድስና የተሻለ ተቀባይነት እንደነበረው ሀሳባቸውን ያጋሩናል:: ሆኖም ከኢንዱስትሪው አብዮት ወዲህ በተለይ በ20ኛው ክፍለ ዘመን የህዝባዊ ምህንድስና ተፈላጊነት እየጨመረ ሲመጣ ሀገረሰባዊ ምህንድስናው እየደበዘዘም ሆነ እየተለወጠ እንደመጣ ያስገነዝባሉ:: ሮበርት (1972:242) አክለውም ለውጡ ሙሉ እቃውን ወይም ቁስን ብቻ ሳይሆን የአሰራር ጥበቡን በሌላ መልክ ቀይሮ ወይም ቅርፁን ሳይቀይር በተለወጠ ቁስ መስራትንም እንደሚጨምር ጠቁመዋል:: ይህም ለውጥ በቁሱ ቅርፅ ብቻ ሳይሆን የመስሪያ ጥሬ ቁሱንም መጥፋት ይጨምራል::

የለውጡ መኖርን ተገንዝበን ቁሶቹ አሻራቸውን ሳይተው ከመጥፋታቸው በፊት በጥናት የተደገፈ አሻራቸውን ማቆየት ከሰሪዎች ብቻ ሳይሆን ከአጥኝዎችም ይጠበቃል:: ለዚህም ነው ግላሲ (1999:85) በጊዜ የመለወጥ ጉዳይ እንደማይቀር ጠቅሰው፣ ነገር ግን የቁሳዊ ባህል ጥናት ትውፊታዊ መስመርን ለማላደግ እንደሚረዳ በጽሁፋቸው አስፍረዋል:: ጥናቱ የጥበብን ሀሳብ ለመጠበቅ ሰፊ፣ ክፍት፣ ዲሞክራሲያዊና ፖለቲካዊ ግልጋሎትን እንደሚሰጥ ያስረዳሉ:: ግላሲ "... The study of vernacular architecture, through its urge toward the comprehensive, accommodates cultural diversity. It welcomes the neglected in to study in order to acknowledge the reality of difference

and conflict. (ግላሲ., 1999:23) በማለት ሀሳባቸውን አክለዋል:: ይህም የቀያዊ ምህንድስና ጥናት የባህል ልዩነትን ለማስተናገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው የሚያሳይ መሆኑን ነው:: የተተወን /የተረሳን/ እና የተናቀን ለማጥናት መፈለግ የእውነታን ልዩነትና ቅራኔ እንዳለ መቀበል እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል::

በአጠቃላይ ባህላዊ ቁሶች በባህል፣ በምጣኔ ሀብት፣ በሙያ፣ በጥሬ ቁሳቁስ ወዘተ ጉዳዮች ተፅዕኖ ምክንያት እየጠፉ እንደሚሄዱ መረጃዎች ያመለክታሉ::በሌላ ጎኑም የኢንዱስትሪ አብዮት መከሰትና የቴክኖሎጂ ምርቶች በገፍ መሰራጨት እንዲሁም ባህላዊ የእጅ ስራ ባለሞያዎች ሙያቸውን ለልጆቻቸው ማውረስ አለመፈለግ ለቁሶች በመጥፋት ላይ መሆን ተጠቃሾች ናቸው:: በባህላዊ ቁሶች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮችን አንድ በአንድ ቀጥሎ ለማቅረብ ይሞክራል::

. የደን መጨፍጨፍ

የአለም ህዝብ ቁጥር ከዘመን ወደ ዘመን በተሸጋገረ ቁጥር በእጅጉ እየጨመረ መሄዱ ይታመናል:: የህዝቡ እየጨመረ መሄድም በአካባቢው የተፈጥሮ ስሪቶች ላይ ተፅዕኖን ማሳደሩ አልቀረም:: ምክንያቱም ለመኖር ሲል የተፈጥሮ ስሪቶችን በገፍ መጠቀሙን ይቀጥላል:: በቀጠለ ቁጥርም ውድመትን ያመጣል:: ለዚህም ነው በአሁኑ ወቅት በአለም አቀፍ ደረጃ የበርሃማነት መስፋፋት ባስከተለው ችግር ሰላማዊ ሰልፎችና ውይይቶች የተበራከቱት:: ለበርሃማነት መንስኤውም የደኖች መጨፍጨፍ ነው:: ደኖች በተጨፈጨፉ ቁጥር በሰው ልጅ ታሪክ እጅግ ግልጋሎት ላይ ይውል የነበረው እንጨት ይጠፋል:: የዚህ መጥፋትም ሀገር በቀል የእንጨት ስራ ውጤት ቁሶች እየጠፉ መሄድን ይደቅናሉ::

የእንጨትን ጠቃሚነት አስመልክተው ሮበርት ውስጠ ዶርሰን (1972:240) በሰው ልጅ የታሪክ ሂደት ውስጥ እንጨትን የመሰለ ጥሬ ቁስ ማግኘት እንደማይቻል ይናገራሉ:: የክብደቱ መቅለል፣ ምቹ የመሆኑ፣ በቀላሉ ለመስራት ማስቻሉ፣ የልስላሴ ጥሩነቱ፣ ድምጽን የመሳብ ብቃቱ እና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች በመስጠት ጥራቱ የሰው ልጅ በርካታ ሙያዎችን እንዲሰራበት አስችሎታል በማለት ያስገነዝባሉ:: ይህን የመሰለ ሙያን የሚጋብዝ እንጨት የሚገኘው ከደን ሀብት ነው:: ሆኖም የደን ሀብት እየመነመነ በመሄዱ በራሱ ባህላዊ የቤትና የእጅ ስራ ቁሶችን ለመስራት አይቻልም:: ስለሆነም የህዝብ ቁጥር

መጨመር የደን ውድመትን ማስከተል፣ ደን በወደመ ቁጥር ደግሞ በርሃማነት መስፋፋት ይመጣል:: በነዚህ ተፅዕኖዎች የተነሳ በርካታ ሀገር በቀል ቁሶችን ለመስራት አይቻልም:: ምክንያቱም ጥሬ ቁሱ ይወድማልና::

. የመስሪያ ጥሬ ቁሶች አቅርቦት መቀነስ

ባህላዊ ቁሶች ከእንጨት፣ ከሳር፣ ከቆዳ፣ ከሸክላ አፈር፣ ከብረታብረት፣ ከቅልና ከመሳሰሉት ጥሬ ቁሶች እንደሚሰሩ አስቀድሞ ለመጠቆም ተሞክሯል:: በዋናነትም ባህላዊ ቁሶች የሚሰሩት ከእንጨት፣ ከሳር፣ ከጭቃና ከቆዳ እንደሆነ ይታመናል:: ነገር ግን ከላይ በተከሰተው ተፅዕኖ የተነሳ የመስራያ ጥሬ ቁሶች አቅርቦት መቀነስ ይታያል:: በአሁኑ ሰዓት እነዚህን ቁሶች በተለየ እንጨትና ሳርን እንደልብ ማግኘት አይቻልም::እንጨትና ሳር እንደልብ ማገኘት ባለመቻሉም ባህላዊ ቤትን መስራት ቀንሷል:: የስፌት እቃዎቸንም እንዲሁ በነበረ ሂዳታቸው ማስቀጠል አቅቷል:: እናም ቁሳዊ ባህሎችን ለመስራት የሚያገለግሉት ጥሬ ቁሶች አቅረቦት እየቀነሰ በሄደ መጠን ባህላዊ ቁሶችም እየጠፉ የመሄዳቸው እጣ ይመጣል::

. የኢንዱስትሪ አብዮት መከሰትና የምርቶቹ በገፍ መሰራጨት

በኢነዱስትሪ ከበለፀጉ ሀገራት ወደተለያዩ ሀገራት የሚሰራጩት የኢንዱስትሪ ምርት ውጤቶች በፈጠሩት ጫና ሀገረሰባዊ የእደጥበብ ቁሶችን መቀነሱ አልቀረም:: በዚህ ላይ ሮበርት ውስጠ ዶርሰን(1972:236) የኢንዱስትሪው አብዮት በፈጠረው ሁኔታ በፋብሪካ የተመረቱ ቁሳቁሶች በ18ኛውና በ19ኛው ክፍለ ዘመን በተለይ ወደ ገጠራማው ክፍል መጉረፍ በባህላዊ ሁኔታ በሚሰሩት የእጅ ስራ ቁሶች ላይ ተፅዕኖ ማሳደራቸውን ጠቁመዋል:: በዚህ የተነሳ በባህላዊ ሰሪዎች ላይ ጉዳት ማድረሱ አልቀረም:: ምክንያቱም በገፍ ከመመረታቸውም ባሻገር በርካሽ ዋጋ መቅረባቸው በተጠቃሚው ዘንድ ተቀባይነትን አግኝተዋልና:: እናም የኢንዱስትሪው አብዮት በባህላዊ ቁሶች ላይ ተፅዕኖ እንዳደረሰ መረዳቱ አያዳግትም::

የኢንዱስትሪ ምርቶች በቁሳዊ ባህሎች ላይ ተፅዕኖ ከመፍጠራቸውም በላይ የተፈጥሮ ትውስታን እንደሚያጠፉ ይታመናል:: በዚህ ላይ ግላሲ (1999:240) የፋብሪካ ምርቶች ተፈጥሮን እንደሚፍቁ ጠቁመዋል:: አያይዘውም ቁርጥራጭ ብረቶችና ለስላሳ የፕላስቲክ

ምርቶች ለተፈጥሮ መነሻነት ምንም ትውስታን እንደማይፈጥሩ ገልፀዋል:: በዚህ የተነሳም ሰዎች የግዴታ ትውስታቸውን እንደሚተው ከዚያ የትውስታ ድባብም እንደሚርቁ አስገንዝበዋል::

ከግላሲ በተመሳሳይም ብራውሴር (1999) የኢንዱስትሪው ተጠቃሚ ማህበረሰብ በቋሚነት በሌሎች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድረው በርካሽ፣ በመናኛ የፋብሪካ ውጤት፣ በብዛት በማምረትና በማቅረብ የሌላውን ማህበረሰብ ባህላዊ የእጅ ሙያ ቁስ ማውደም መቻሉን ጠቁመዋል:: ይህም ሀገረሰባዊ የእጅ ስራዎች ያለፈባቸው ፋሽኖች ናቸው የማለትን ጉዳይ እንደመጣ ያስረዳሉ:: ሮበርት ውስጠ ዶርሰን (1972:282) በሌላ በኩል የህዝባዊ ምህንድስና ውጤቶች በአንባራዊነት በተለይ ከኢንዱስትሪው አብዮት በኋላ እንደመጡ ያብራራሉ:: የህንፃ ቁሶች የፋብሪካ ውጤቶች እንደሆኑ ጠቅሰው የህንፃ ፕላናቸውም በህዝባዊ ጋዜጦች፣ በንግድ አህዝቦቶች እና በመንግስታዊ ኤጀንሲዎች ወደ ተለያዩ ሀገራት እንደተሰራጩ አመላክተዋል::

ዘመናዊ የህንፃ ቁሶችና ፕላኖች በብዛት በተሰራጩ ቁጥር ሀገረሰባዊ የምህንድስና ሙያ በባህላዊ መንገድ በዘመድ ወይም በዘር የመተላለፍ ጉዳይ ከመረሳቱም በላይ የቁሳቁሱ፣ የእጅ መሳሪያዎችና የህንፃቸው አሰራር ጥበብ ትውፊታዊነትም አብሮ እንደሚጠፋ ከምሁራኑ ሀሳብ መረዳት እንችላለን:: ስለሆነም የኢንዱስትሪው አብዮት መከሰትና የምርቶች ወደ ገጠራማውም ሆነ ወደ ተለያዩ ሀገራት በገፍ መሰራጨት በባህላዊው የእጅ ስራ ቁስ ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩን ልብ ማለት ይገባል::

. የገበያ ፍላጎት መቀነስ

የገበያ ፍላጎት መቀነስ በተለይ በሀገረሰባዊ የእጅስራ ቁሶች ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ አይቀርም:: ይህ የሚሆነውም የቴክኖሎጂ ውጤቶች ወደገጠራማው ክፍል መጉረፍና በርካሽ ዋጋ መሸጣቸው የተጠቃሚውን ፍላጎት ይስቡታል "... to buy factory made goods at a price lower than the crafts man could make and sell his proucts most people of course, began buying the cheaper goods." (ሮበርት ውስጠ ዶርሰን; 1972:236)ማለታቸው በርካሽ የቀረቡት የፋብረካ ቁሶች የአብዛኛውን ህዝብ ትኩረት እንዳገኙ ነው:: በዚህን ወቅት የእጅ ስራ ባለሞያው በአካባቢው ቁሳቁስ የሰራቸውን ቁሶች

ለመሸጥ ይችግረዋል:: በፋብሪካ በገፍ ከሚመረቱ ቁሳቁሶች ጋር በእጅ ሰርቶ መወዳደር አይችልም:: በዚያ ላይም ሀገረሰባዊ ቁሶችን ለመስራት በአሁኑ ወቅት በደን መጨፍጨፍ የተነሳ የጥሬ ቁስ አቅርቦት መቀነስ የፈጠረው ጫና አለ:: ጥሬ ቁሶችን በርካሽ ዋጋ ማግኘት ካልቻለና ያለምንም ክፍያ ከራሱ ጫካ ያመጣቸው የነበሩት እየጠፉ ከሄዱ በገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ ባህላዊ ቁሶችን መስራት ይችግረዋል:: በውድ ዋጋ ጥሬ ቁሶችን ሰርቶ በውድ ዋጋ ሸጦ የእለት ኑሮውን ለመምራት ባቃተው ቁጥር ከገበያ ውጪ ይሆንና ከነአካቴውም መስራቱን ያቆማል::

በዚህ አካሄድ ደግሞ በሀገር በቀል እውቀት የተሰሩ ቁሶች አደጋ ላይ ይወድቃሉ:: በእኛም ሀገር ለጳሶ ጌ ድልቦ ብላታ ደሬሳ አመንቴን ዋቢ አድርገው ባቀረቡት አጠቃላይ ሀሳብ /1983 :231/ በኢትዮጵያ የእደጥበብ ምርትና በውጭ አገር እርካሽ የኢንዱስትሪ ሸቀጣሸቀጥ መካከል በተካሄደው የገበያ፣ የፖለቲካና የባህል ጦርነት ከ1933-1966 ድረስ የአገሪቱ የእጥበብ ሙያ ምርት ከጊዜ ወደ ጊዜ ገበያ እያጣ እንደሄደ ያስረዳሉ:: እናም የገበያ ፍላጎት መቀነስ በሀገረሰባዊ ቁሶች ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ የጎላ ይሆናል::

. ባህላዊ ቁሶች የኋላቀርነት ምልክት ተደርገው መወሰዳቸው

ከላይ እንደጠቀምነው አብለጭላጭና ሳቢ የፋብሪካ ምርቶች ከገበያ ላይ በርካሽ የሚገዙ ከሆነና የዘመናዊው ቴክኖሎጂ ውጤት በዘመናዊው ትውልድ የእሳቤ አድማስ ላይ የሚታጨቅ ከሆነ በቀየው ለተመረቱት ቁሶች ቀልቡን ዝግ ያደርጋል:: እንዲያውም በሀገሩ እጅ ሰሪዎችና በሀገር በቀል ጥሬ ቁስ የተሰሩትን የራሱን ማንነት ገለጭ ቁሳዊ ባህሎች "ፋሽናቸው ያለፈባቸውና ዘመናዊነትን የማያንፀባርቁ" በማለት ይንቃቸዋል::

የግድ በባህላዊ ቁሶች መወሰን አለብህ ብሎ ማስገደድ በይቻልም የራስን ደግሞ ማበልፀግና ተወዳጅ ማድረግ ይቻል ነበር:: ዘመኑ ባፈራቸው አብለጭላጭ የፕላስቲክ እቃዎች እንጅ ማን በሰፈት እቃዎች ይመገባል ይላል ዘመንኛው:: ስለሆነም ባህላዊ ቁሶች የኋላቀርነት ምልክት ተደርገው መወሰዳቸው ሀገር በቀል ቁሶችን በሚሰሩት ባለሞያዎች ላይ በሚፈጠረው ጫና የማይመረቱበት ደረጃ ላይ ይደርሳል:: ይህም ቁሳዊ ባህሎች በመጥፋት ላይ ለመሆናቸው አመላካች ጉዳይ እንደሆ መረዳት ይቻላል::

. የባህላዊ ቁስ ባለሞያዎች ሙያውን ለልጆቻቸው ማውረስ ያለመፈለግና ልጆችም ሙያውን መናቃቸው

እንደ ዓለም አቀፍ ተሞክሮም ሆነ እንደ ኢትዮጵያ የጥንቱ ቁሳዊ ባህል የሚሰራው አብዛኛውን ጊዜ በዘር በሚወርስ ሙያ እንደሆነ ይገመታል:: ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣን የእጅ ሙያ አክብሮ መያዝና ማስቀጠል የዘመንኛው ትውልድ ፍላጎት ሲሆን አይታይም:: የዘመንኛው ትውልድ ወላጆችም ይህን ባህላዊ የአሰራር ዘዴና ቁስ ለልጆቻቸው ማውረስን አልፈለጉም:: ምክንያቱም ልጆቻቸው ይህን ሙያ ተምረው ወይም ለምደው በሙያው መሰማራታቸው ከገቢያም ሆነ ከተጠቃሚው የፍላጎት ማጣት ተጠቃሚ ይሆናሉ ብለው ባለመገመት የፈጠረው ተፅዕኖ መሆኑ አያጠራጥርም::

በሌላ ጎኑ የዘመኑ ትውልድ ዘመናዊ ትምህርትን እየተማረ ስለሆነ ትኩረቱም ወደ ዘመናዊ ሙያ እንጅ ወደ ጥንቱ የቤተሰቡ ሙያ ማዘንበል አልቻለም:: ቁጭ ብሎም የአባቱን የእጅ ሙያ እየተመለከተ የሚለምድበት ጊዜ የለውም:: ዘመናዊ ተማሪም ስለሆ ኋላ ቀር ተብሎ በሚጠራው የቤተሰቡ ሙያ ተሰልፎ መታየትን ይጠላል:: ወላጆቹም እየተዋረዱና እየተናቁ እዚህ የደረሱበትን ሙያ ዘመናዊ ትምህርት ለተማረው ልጃቸው ማውረስን አይሹም:: በዚህ ላይም ተጠቃሚነቱ እየቀነሰ በመሄዱ በሌላ ትርፋማ ሙያ ላይ ተሰማርቶ የእነሱንም ሆነ የራሱን የተጎሳቆለ ህይወት እንዲለውጥ ምኞታቸው ነው::

ስለሆነም ወላጆቹ ባህላዊ ሙያውን ማውረስ ባለመፈለጋቸው ልጁም ኋላ ቀር የሚባለውንና ትርፋማ ያልሆነውን ሙያ በመናቁ ቁሳዊ ባህሎች የመጥፋት አደጋ ይጋረጥባቸዋል:: በመካከልም ከትውልድ ወደ ትውልድ ሙያውን የሚያሸጋግሩት አባቶች በሞት በተለዩ ቁጥር ሀገር በቀል እውቀቱን ጨምረው ይዘውት ይቀበራሉ:: ይህም በራሱ መረጃ በመሰብሰብ ወቅት ቁልፍ ወይም ሙያዊ መረጃን የሚሰጥ አካል ይጠፋል:: እናም የቁሶችን የአሰራር ጥበብና ተምሳሌታዊነት ብሎም ማህበረሰብ ገላጭነት ቀርሶ ለማስቀረት ይቸግራል:: በዚህ ተፅዕኖ የተነሳ ቁሳዊ ባህሎች በመጥፋ ላይ ለመሆናቸው አመላካች እንደሆነ መረዳት አያዳግትም::

. ባህላዊ የእጅ ስራዎች እንደተጨማሪ ስራ መታየታቸው

"... At the same time, craftsman were also usually part time farmers who had some land on which they grow crops and raised animals, devoting time to their own farm when they could..." (ሮበርት ውስጠ ዶርሰን: 1972:240) እንደ ሮበርት ከሆነ ባህላዊ የእጅ ስራ ባለሞያዎች የግብርናን ስራ በተጨማሪነት እንደሚሰሩ ነው:: አዝዕርትን በማምረትና እንስሳትን በማራባት የስራ ተግባር ላይ ጊዜያቸውን ስለሚያሳልፉ ለእጅስራ ሙያው ትኩረትን እንደሚነሱት ምሁሩ ያስገነዝባሉ:: በተመሳሳይም ላጵሶ ጌድልቦ/1983:231/ ከእርሻና ከእንስሳት እርባታ ጋር አጣምረው እንደሚሰሩ ጠቁመዋል::

በግብርና የስራ ተግባር የሚያገኙት ገቢ እየጨመረ በሄደ መጠን ትኩረታቸውን ወደ ግብርናው ያደርጉትና ባህላዊ የእጅ ሙያውን እንደተጨማሪ ስራ በማየት በዚህ ዘርፍ የሚገኘውንም ባህላዊ የቁስ ምርት ይተውታል:: በሌላ መልኩም በተደራጀ መልክ የሚያመርቱበትና ከግብርናው መስክ ከሚያገኙት ገቢ የተሻለ ተጠቃሚ የማይሆኑ ከሆነ ከነአካቴውም ሙያውን እርግፍ አድርገው ሊተውት እንደሚችሉ መገመት ይቻላል::

ምእራፍ ሦስት

3. የደጋ ዳሞት ወረዳ ዳራዊ መግለጫ

ይህ ምዕራፍ የደጋ ዳሞት ወረዳን ዳራዊ ሁኔታ ለማስተዋወቅ መከራ ያደርጋል:: ስለሆነም የደጋ ዳሞት አሰያየምና ታሪካዊ አመጣጥ፣ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥና የአየር ፀባይ፣ የህዝብ ብዛት፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ማህበራዊ ግኑኝነትና መስህብነት ያላቸው ቦታዎች፣ እንዲሁም የቁሳዊ ባህል ሰሪዎችና ማህበራዊ ደረጃ የሚሉት ንዑሳን ርዕሶች ይቀርባሉ::

የወረዳዋን ዳራዊ መግለጫ ማቅረብ የተፈለገበት ምክንያት ከተለያየ አቅጣጫ ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎችን መመለስ ስለሚያስችል ነው:: ባህላዊ ቁሶቹ የተሰሩባቸው ጥሬ ቁሶች ሲዘረዘሩም ሆነ በመጥፋት ላይ ለመሆናቸው ተፅዕኖ ፈጣሪ ጉዳዮች ሲተነተኑ በእርግጥ እነዚህ ጥሬ ቁሶች በወረዳዋ ነበሩ? ተፅዕኖ ፈጣሪዎችስ በጉልህ ይስተዋሉባታል? የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ማስቻሉ ነው::ለቁሳዊ ባህሎቹ በመጥፋት ላይ መሆን የወረዳዋ የመሬት አቀማመጥና የአየር ሁኔታ፤ እንዲሁም የህዝቡ የኑሮ መሰረት የራሳቸው ድርሻ ነበራቸው? የወረዳዋ ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ቤቶችንና እጅ ስራ ቁሶችን ሲሰራ፤ የነበረው ማህበራዊ ተሳትፎ ምን ይመስል ነበር? ለሚሉ ጥያቄዎችም ምላሽ ያስገኛል::ስለሆነም በዳራዊ መግለጫው የተጠቆሙትን ንዑሳን ርእሶች በሚከተለው መልክ ለማስተዋወቅ ይሞክራል::

3.1. የደጋ ዳሞት አሰያየም ታሪካዊ አመጣጥ

በታሪክ እንደምንረዳውም ሆነ በግልፅ እንደምናስተውለው የቦታም ሆነ የሰው ስም አሰያየም ራሱን የቻለ ሂደት አለው:: ምናልባት ስምን ወላጆች በተሰማቸውና በገጠማቸው ተነስተው ሊሰይሙት ይችላሉ:: ሀገርንና የተወሰነ የቦታ ስያሜን ግን ከአንድ ቤተሰብ የህይወት ትወስታ ወጣ ብሎ ሊሰየም ይችላል:: ሆኖም የሰውም ሆነ የቦታ ስም በየትኛውም ሀገር ያለትርጉም የሚሰየምበት ሁኔታ እንደሌለ ይገመታል::

"ዳሞት" የሚለው ቃል ወይም የግዛት ስም በታሪክ ውስጥ ጉልህ ሆኖ መታየት የጀመረው ከ6ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደነበር የፈረስ ቤት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 50ኛ

ዓመት የወርቅ ኢዮቤልዮ በዓል አዘጋጅ ኮሚቴ ባዘጋጀው መጽሔት /1994: እ.ኢ.አ/ ያልታተመ ላይ ተጽፎ ይገኛል::

ይህ ያልታተመ መጽሔት አባ ጋስፐረኒ የተባሉ የኢጣሊያ መነኩሴ "የኢትዮጵያ ታሪክ" ብለው የጻፉትን ጥራዝ ዋቢ በማድረግ እንደሚከተለው ብሏል::

> ... አጤ ካልብ ከሂማሪያት ንጉስ ጋር በ525 ዓ.ም ባደረገው ጦርነት በግንባር ከተሰለፉት ጦረኞች መካከል መሸሽ ወይም ወደ ኋላ ማፈግፈግ የመያውቁ ማሸነፍ እንጅ መሸነፍ ፊዕሞ የማይታይባቸው በአንድ ክፍል የተሰለፉ ሰዎች ነበሩ:: እነዚህ ሰዎች አንድ ቀን ግን የጦር ድግስ ለንጉሳችን አናቆይም ብለው የአለቃቸውን ትዕዛዝ ጥሰው ጠላትን ገጥመው አሸነፉ:: የድሉ የምስራች ቃል የደረሰው ንጉስም እነዚህን ጀግኖች አስቀርቦ ከጠየቃቸው በኋላ ለህይወታቸው ሳይሳሱ ባስገኙት ድል በጀግንነት ተዋግተው በከፈሉት መስዋዕትነት ተደስቶ ካመሰገናቸው በኋላ፣ ከእንግዲህ በኋላ የመንግስት ግብርና ዕዳ እንዳይጠየቁ ነፃ ህዝቦች ሆነው በዚያው በጀግንነት ሙያቸው ብቻ ሲጠሩ በግንባር እንዲሰለፉ በማለት አዳቸውና ግብራቸው ውትድርና ወይም ሞት እንዲሆን በመወሰኑ ዕዱሞት ተባሉ በማለት የስሙን አመጣጥ ከጥሬ ቃሉና ትርጉም አስማምተው ጽፈዋል:: ... ለነዚህ ጦር ቀመስ ህዝቦች መኖሪያ ማደሪያቸው እንዲሆን ከአባይ ወንዝ ወዲያ ማዶና ወዲህ ማዶ ያለውን ሀገር ሰጣቸው በማለት የታሪኩን እውነታ ለማቀራረብ ሞክረዋል:: /1994:12/

ከዚህ አኳያ "ዳሞት" የሚለው ቃል ከሞት ግብር ጋር የተያያዘ የጀግንነት ስም እንደሆነ መረዳት ይቻላል:: በአፄ ላሊበላ ዘመንም ዳሞት የተባሉት ጠንቀኞች ወይም ጦረኞች የግዮን ወንዝ ባላደራ ሆነው፤ ከምንጩ እስከ ሀይቁ /ከግሸን አባይ እስከ ጣና ሀይቅ/፣ ከጣና ሐይቅ እስከ ሳሱ (እስከ ዛሬው መተከል አሶሳ ድረስ) ወርቅ፣ ማር፣ ፈረስና ሰንጋ የሚገብረውን ነገድ ሁሉ በበላይነት እንዲጠብቁ በአገው ቤት አዛዥ ላይ ተሰማሩበት /1994:12-13/ በማለትም ተጠቁሟል::

በትውፊታዊ ሥነቃሉም ዳሞት..... ዕደው ሞት
ግብሩ..... ዘመቻ
ሰንቁ..... በስልቻ
ምግቡ... እንጎቻ

እየተባለ ሲነገርለት መኖሩ ከላይ የቀረቡትን ማስረጃዎች የሚያጠናክር ይመስላል:: በአፄ ኃይለ ስላሴ የግዛት ዘመንም ከ1960-1961 ዓ.ም በተጣለው የአንድ ብር ከሃምሳ የመሬት

ግብር የተነሳ የዳሞት ህዝብ ያስነሳው ዓመጽ ለጀግንነቱና ሞትን ያለመፍራቱ ምልክት ነው:: /1994:20/

ይህ "ዳሞት" የሚለው የግዛት ስያሜ ሲሰፋና ሲጠብ የኖረ የነጋሽ ሀገር ሲሆን፤ በኋላ በቆላውና በደጋው ዳሞት መከፈሉን መረጃዎች ያመላክታሉ:: እናም "ዳሞት" የሚለው ቃል ጥቅል መጠሪያ እንደነበር መገንዘብ አያዳግትም:: ደጋውን ዳሞት ስድስቱ መደብ ዳሞት፣ አምስቱ መደብ ዳሞት በኋላም አሁን የያዘውን አራቱ መደብ ዳሞት ሊመሰርት እንደቻለ መረጃ አቀባዬ አረጋግጠዋል።

አቡሀይ መንግስቱ አሰጌ አለባ (16/07/2003/ "በድሮው ስድስቱ መደብ ዳሞት/ደንበጫ፣ ቋሪት፣ እናሞራ፣ በርቀኝ፣ ጠሊም፣ አረፋ/፤ አምስቱ ደግሞ/ቋሪት፣ እናሞራ፣ በርቀኝ፣ ጠሊም፣ አረፋ/ ሲባሉ የነበረ ሲሆን፣ በአሁኑ ግን አራቱ /እናሞራ፣ በርቀኝ፣ ጠሊም፣ አረፋ/" የሚባሉትን እንደያዘ ነግረውኛል:: በአሁኑ ሰዓት ደጋማው ክፍል የበዛበት በመሆኑ "ደጋ ዳሞት" የሚለው ሲያሜ በዚህ ጥናት የሚተኮርበት የወረዳ ስም መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። የወረዳዋን ስም አሰያየምና ታሪካዊ አመጣጥ በጥቂቱ ለማስተማወቅ የተቻለ ይመስለኛል:: ጠለቅ ያለ ታሪኩን ለባለታሪኮቹ ትቼ ወደቀጣዩ ርዕሰ ጉዳይ ላሞራ::

3.2. መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥና የአየር ፀባይ

የዚህ ጥናት ተተኳሪ ደጋ ዳሞት ወረዳ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከሚገኙ 15 ወረዳዎች ውስጥ አንዷ ስትሆን፣ ከፌደራል መንግስት ዋና ከተማ አዲስ አበባ 401 ኪሎ ሜትር፣ ከክልልና ከዞን ዋና ከተማ ባህርዳር 221 ኪሎ ሜትር ርቃ እንደምትገኝ በየሶስት ወሩ የሚፃፈው የወረዳዋ የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት ያልታተመ መጽሄት ያስረዳል:: የወረዳዋ ዋና ከተማም ፈረስ ቤት ትባላለች::

የደጋ ዳሞት ወረዳ አጠቃላይ የቆዳ ስፋት 65,726.68 ሄክታር ሲሆን፣ ለእርሻ የዋለው ማሳ 25,262 ሄክታሩ እንደሆነ መረጃው ያስረዳል:: አለን, ሆብን የተባሉ አሜሪካዊ ምሁር "የመሬት አያያዝና አወራረስ በደጋ ዳሞት አማራ" በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ በ1970 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ጥናት መፅሄት ላይ የመሬቱ ስፋት 1200 ስኩየር ማይልስ እንደነበር ጽፈዋል::

በአሁኑ ሰዓት ወረዳዋ በሰሜን ምስራቅ ከምስራቅ ጎጃም ዞን አካል ቢቡኝ ወረዳ፣ በምዕራብ ከጃቢ ጣህናን ወረዳ፣ በሰሜን ከቋሪት ወረዳ፣ በደቡብ ከደንበጫ ወረዳ ጋር ትዋሰናለች::ደጋ ዳሞት ወረዳ ከባህር ወለል በላይ ከ1500-3400 ሜትር የሚደርስ ከፍታ አላት:: የመሬት አቀማመጧ ከጠቅላላው 35% ተራራማ፣ 30% ወጣ ገባ፣ 20% ሸለቋማ፣ 15% ሜዳማ ነው:: የአየር ንብረትን በተመለከተም 75% ደጋማ 20% ወይና ደጋማ እና 5% ቆላማ እንደሆነ መረጃዎች ያስረዳሉ:: ስለሆነም አብዛኛውን የመሬት አቀማመጧ ተራራማና ወጣ ገባ፤ የአየር ፀባዩዋም ደጋማ እንደሆነ መረዳት ይቻላል:: ተራራማና ሸለቋማ መሆኗን አስተውለው ይመስላል አለን, ሆበን(1970፣70) ከታች በርካታ ወንዞችና ዥረቶች ይበዙበታል ያሉት::

3.3. የህዝብ ብዛት፣ የቋንቋና የሃይማኖት ሁኔታ

የደጋ ዳሞት ወረዳ ደጋማውና ወይና ደጋማው የበዛ በመሆኑ በርካታ ህዝብን መያዙ አያጠራጥርም:: ስለሆነም ከላይ በጠቀስነው ያልታተመ የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት ጽሑፍ መሰረት /1997:4/ የወረዳዋ አጠቃላይ ህዝብ 179,972 ሲሆን ወንድ 89,657፣ ሴት 90,315፣ ከዚህ ውስጥ በከተማ ወንድ 1363 ፣ሴት 1719 በድምሩ 3082፤ በገጠር ደግሞ ወንድ 88,294 ሴት 88,396 በድምሩ 176,690 እንደሆነ ተጽፏል:: በተያያዘም 98.1 በእርሻ ስራ ላይ ቀሪው 1.9% ደግሞ ንግድና የመንግስት ስራ እንደሆነ ተመልክቷል::የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃለፊና ባለሞያዎች ለጽሑፍ መጠይቁ በሰጡት ምላሽ በሌሎች የእጅ ሙያዎች የሚጠቀም ቢኖርም አብዛኛው ህዝብ የሚተዳደረው በግብርና ነው::

በሌላ በኩል እ.ኤ.አ. በ1999 ዓ.ም የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባካሄደው የህዝብና ቤት ቆጠራ መሰረት ጠቅላላው የወረዳዋ ህዝብ 151,121 እንደሆነ ጽፏል:: የክልሉ ህዝብ ብዛትም 17,214,470 ሲሆን፣ ምዕራብ ጎጃም ዞን ለብቻው 2,107,721 ነው:: እናም ከ151,121 የወረዳዋ ህዝብ ውስጥ ወንድ 74,383፣ ሴት 76,738 ነው:: ከህዝቡ ውስጥ በከተማ ወንድ 3491፣ ሴት 3202 በድምሩ 6693 ሲሆን፣ በገጠር ደግሞ ወንድ 70,892፣ ሴት 73,536 በድምሩ 144,428 እንደሆነ የፌደራል የህዝብና ቤት ቆጠራ ኤጀንሲ መጽሄት /2007/ ያስረዳል::

ሁለት ዓመታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በወረዳዋና በፌደራል ህዝብና ቤቶች ቆጠራ ኤጀንሲ መካከል የ28851 የህዝብ ቁጥር ልዩነት ታይቷል:: ይሄ ከምን እንደመጣ የሚታወቅ ነገር የለም:: ይህ በእንዲህ እያለ አለን, ሆበን(1970:70) ከዛሬ አርባ ዓመታት በፊት የወረዳዋን ህዝብ ብዛት የ1960 ዓ.ም እ.ኢ.አ ግምት በመውሰድ 100,000 እንደነበር ጽፈዋል::

የወረዳዋ ህዝብ አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሲሆን በብሄረሰብ ደረጃም ተወላጁ ሙሉ አማራ ነው:: ሃይማኖቱን በተመለከተም አሁን አሁን በተለይ (እንደ አጥኝው ግንዛቤ ከሆነ) ከ1981 ዓ.ም ወዲህ አልፎ አልፎ የፕሮቴስታንት እምነትን የሚከተሉ ሰዎች ብቅ ከማለታቸው ውጪ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ህዝብ ነው:: በዚህ ላይ የዛሬ 40 ዓመት ገደማ ያጠኑት አለን, ሆበን (1970:70) የደጋ ዳሞት ህዝብ ራሱን እንደ አማራና ኦርቶዶክስ አማኝ እንደሆነ የሚቆጥር መሆኑን በጥናታቸው ጽፈዋል:: አያይዘውም በወረዳዋ 223 ሰበካዎች የነበሩ ሲሆን 19ኙ ያለ ቤተክርስቲያን በተራራቀ ቦታ መኖራቸውን ጠቅሰዋል:: ይህ ማለት 204 ቤተክርስቲያናት በወረዳዋ እንደነበሩ ነው:: መረጃው ኦርቶዶክስ እምነት ብቻ እንደነበር የሚያመላክት ነው:: በሰበካው መካከል በአለን, ሆበን ግምት የ3.5 ስኩየር ማይልስ ርቀት ሲኖር፣ በእያንዳንዱ ሰበካ ከ150-1300 በላይ ህዝብ እንደነበረበትም አያይዘው ጠቁመዋል::

በአጠቃላይ በወረዳዋ የነበረው ህዝብ በሶስቱ መረጃዎች መሰረት በ40 አመታት ውስጥ የ51000 ወይም የ79000 ህዝብ ጭማሪ መታየቱን መግለፅ ይቻላል:: ቋንቋ አማርኛ የመሆኑን ያህል ሃይሞኖትን በተመለከተም ከ20 ዓመታት ወዲህ የፕሮቴስታንት እምነት ፈራ ተባ እየተባለ ቢሆንም አያቆጠቆጠ ያለበት ሁኔታ እንዳለ /በእኔ/ እማኝነት ማረጋገጥ ይቻላል::

3.4. ማህበራዊ ግንኙነት

በደጋ ዳሞት ወረዳ ሰርግ፣ ማህበር፣ ሰንበቴ፣ ሰንበታት፣ ፅጌ፣ ወንፈል /ደቦ/፣ ለቅሶ፣ ቤት ስራና የመሳሰሉት የማህበራዊ ግንኙነት መሰረት ናቸው:: በዚህ የማህበራዊ መዋቅር ሂደት መጀመሪያ ከቤተሰብ ይጀምራል:: በአንድ ቤተሰብ አባት፣ እናት፣ ልጆች /ከጋብቻ በፊት ከሌላ ሴትም ሆነ ወንድ የተወለዱትን ይጨምራል/፣ የባልና የሚስት ዘመድ በችግር ምክንያት ከተጠጉ አብረው ይኖራሉ:: በዚህ ቤት ውስጥ ምሰሶው ወይም ኃላፊው ባልየው

ነው:: ባልየው ቢሞት ግን ታላቅ ወንድ ልጅ ቤተሰቡን በማማከርም ይሁን በመምራት ያስተዳደራል:: ሌላው በቤተሰቡ ማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ አለን, ሆበን(1970:70) እንደትልቅ ጉዳይ ያዩት አንድ ወንድ ሚስት ቢያገባ አንድ አመትና ከዚያ በላይ ሚስቱን ይዞ ከቤተሰቦቹ ጋር አብሮ መኖሩ ነው ይላሉ:: ይህም ጎጆ እስኪወጣና እራሱን እስኪችል ማለት ነው::

ሌላው አለን, ሆበን(1970:71) እንዳሉት የመንደሮች ስብስብ በአንድ ሰበካ ይዋቀርና ማህበራዊ ጉዳያቸውን ይከውናሉ:: ይኸውም በቤተክርስቲያን ተሰባስበው የገጠማቸውን ችግር ተወያይተው ይፈታሉ:: ወይም አማጋ ላይ ይሰባሰቡና ድርቅ ቢከሰት፣ የሀገር ጉይን የሚመለከት ችግር ቢመጣ ተሰባስበው ይወያያሉ:: በዚህ ውይይት ላይ ግን ወንዶችን እንጅ ሴቶችን አይመለከትም:: እንዲሁም ቤተክርስቲያንን እምነታቸውን የሚከውኑበት፣ ህፃናት ልጆቻቸውን ክርስትና የሚያስነሱበት፣ ሙታቸውን የሚቀብሩበት፣ ሰንበቴና ፅጌ የሚጠጡበት ነው:: የአሁኑ የመንግስት መዋቅር በዘመናዊ መልክ ተዋቅሮ ከመውረዱ በፊት ማህበራዊ ግንኙነታቸውን ይፈፅሙ የነበረው በቤተክርስቲያን ቅጥርና በክብቶቻቸው መገናኛ አማጋ ነበር::

በወረዳዋ ያሉት ማህበረሰቦች በዋናነት ማህበራዊ ግንኙነታቸውን እንደችግር መፍቻነት የሚጠቀሙት "በዓድቃን" ወይም "በታቦት" ስም በሚጠጡት "ማህበር" ነው:: ይህ "ማህበር" ከ12 እስከ 24 አባወራዎች በአንድ ላይ ተሰባስበው በእያንዳንዱ ግለሰብ ቤት በየወሩ ጠላ፣ የተሟላ ምግብ፣ አረቄ፣ ቡናና የመሳሰሉትን እየጠጡና እየተመገቡ የሚያስተላልፉት ነው:: "ማህበር" በከተማ ደረጃ "እድር" ሊከውናቸው የሚችላቸውን የመተጋገዝ ተግባራት ይፈፅማል:: የአንድ ማህበርተኛ ቤተሰብ ቢታመም፣ ቢሞት፣ ቢታሰር፣ የከፋ ችግር ቢደርስበት እያንዳንዱ ማህበርተኛ በግልም ይሁን በቡድን የግብርና ስራዎችን የማገዝ፣ ቁርባን የማስቆረብ፣ እንዲሁም የገንዘብ እገዛ የማድረግ የውዴታ ግዴታ አለበት:: በዚህ ላይ ግን በየወሩ ተራው በሚደርስበት የማህበር ደጋሽ ቤት በመገኘት የማህበሩ አባል የሚሆነው ባልየው ብቻ ነው:: ሴቶች በጎረቤት ካልሆነ በስተቀር አብረው ሂደው የማህበሩ ድግስ ተካፋይ አይሆኑም:: እነሱ የባለቤታቸው የማህበር ተራ ሲደርስ ድግስ መደገስና በሙያቸው መመስገን ብቻ ነው:: የማህበሩ አባል ቢሞት የመጀመሪያ ወንድ ልጅ ወይም

የመጨረሻ ቤቱንና ሀብቱን የወረሰው ወንድ ልጅ የአባቱን ማህበር ያስቀጥላል:: ምክንያቱም ሲወርድ ሲዋረድ ለመጣው መተጋገዝ ባለዕዳ ነውና::

በሌላ በኩል "ጽጌ" ድግስን የሚከውኑት ከመስከረም 27 ቀን ጀምሮ በአማጋቸው ወይም ቅርብ ደብር ያላቸው ከሆኑ በደብራቸው በየሳምንቱ ለአንድ፣ ለሁለት፣ ለሶስት፣ ለአራትና ለአምስትም ይሆናል እንደ ህዝቡ ብዛት በየሳምንቱ አንዳንድ እንስራ ጠላ፣ አንዳንድ ድስት ወጥ፣ ሃምሳና በላይ እንጀራ፣ በወቅቱ የምትታለብ ላም ያለው ሁሉ "ማሪያም ያየችው ነው" ተብሎ ስለሚገመት በሽንክላ እርጎ ይመጣል:: "ጽጌ" ወንድ ልጆችና አባት ብቻ የሚጠጡበት ነው:: ብዛት ያላቸው ሰዎች በአንድ ቀን የሚያወጡት የጽጌ ድግስ ከህዳር 6 ቀን ማለፍ ስለማይችል ነው:: በዚህ ማህበር ድሃ ካልሆነ በስተቀር ከቤት የሚውል አባወራ የለም:: ሴት እናቶችም ይሁኑ ሴት ልጆች አይሰተፉበትም:: በዚህን ቀን ሴቶቸ ወንድ ልጆች ይዘዋቸው የዋሏቸውን ከብቶች ማስመሸትና ወደ ቤት ማስገባት የስራ ተግባራቸው ይሆናል::

እንዲሁም "ሰንበቴን"ና "ሰንበታትን" በተመለከተ በወረዳዋ የሚከወን ማህበራዊ ድግስ ነው:: "ሰንበቴ" የተባለው ድግስ አሁንም ቢሆን ለወንድ አባትና ልጅ ሲሆን በአንድ ትልቅ ማድጋ ጠላና ነባብሮሽ ቂጣ ብቻ የሚቀርብበት ነው:: አቅርቦቱም በየሶስት ወሩ ነው:: በተመሳሳይ "ሰንበታቴ" የሚባለው እናቶችና አባቶች በጋራ በቤተክርስቲያን ቅጥር ካሉት ዛፎች ጥላ ስር የሚጠጡት ነው:: ይሄ በተለይ ከሌሎች የሚለየው ሴቶችን በመጨመሩ ነው:: ቆይታውም እንደ "ሰንበቴ" ሁሉ ሶስት ወር ሲሞላ ነው:: ጠላና በወጥ እንጀራ ይቀርብበታል::

ከነዚህ ድግስን መሰረት ካደረጉት ማህበራዊ ግንኙነቶች በተጨማሪ የቀብር ስርዓትን እንመልከት:: አንድ ሰው ሲሞት ጥሩ ድምፅ ያለው ሰው ይመረጥና /በከተማ ጥሩንባ ነፊ እንደሚባለው ነው/ ከተራራ ላይ ይወጣና ወደየመንደሮች እየዞረ ድምፁን ከፍ አድርጎ በመጮህ "እከሌ፣ እከሊት፣ የእከሌ ልጅ አረፏልና፣ሞቷልና ተጎዳ" በማለት ይጮሀል:: ይህን የሰማ ስራ ይዞ እንደሁ ስራውን ትቶ፣ ምግብ ይመገብ እንዲሁ ምግቡን አቋርጦ ሬሳው ካለበት ቤት መድረስ የሚችል ከሆነ ቀጥታ ይሄዳል ካልሆነ ጫሂው ከነገረው ቤተክርስቲያን ሂዶ የቀብር ሥርዓቱን ይፈፅማል:: በባህሉ ሬሳው አፈር ሳይቀምስ ምግብ መመገብም ሆነ ስራ መስራትና እጅን መታጠብ አይፈቀድም::

ሰርግ ሌላው የወረዳዋ ማህበረሰብ የሚገናኝበት ማህበራዊ ክስተት ነው:: አንድ ሰው ልጁን ሲድር ከዚህ ቀደም የከፈለውም ሆነ በአዲስ መልክ ዘመድ፣ ጎረቤት፣ ልጁን ክርስትና ያነሳ አበልጅ ሌማት ይይዛል:: ሌማቱ ሶስት እንስራ ጠላ፣ ሶስት ድስት ወጥ፣ መቶና በላይ እንጀራ በማምጣት በአቆልቋይ የሚያበላበት ሁኔታ ነው:: ከሌማት ውጪ አንዳንድ ገንቦ ጠላ፣ አስር እንጀራ፣ አንድ ጠርሙስ አረቄ ሳይዝ የሚመጣ የሰርግ ታዳሚ የለም:: በዚህ ማህበራዊ ተግባርም የሰርግ ስርዓታቸውን አድምቀው ያሳልፉታል::
ስራን በተመለከተም በአካባቢው አጠራር በወንፈል /በደቦ/ በመተጋገዝ ይከውናል:: በዚህም እንደየ ስራው አጣዳፊነት በአንድ ላይ ይወያዩና የእከሌን በዚህ ቀን እንስራ የእከሌን ደግሞ ቀጥለን በማለት የስራ ቀናትን ይወስናሉ:: እናም እርሻን፣ አረምን፣ አጨዳን፣ ውቂያን፣ የከብት መኖ መሰብሰብን፣ የቤት ስራን በዚህ ሂደት ይከውናሉ:: በተለይ የቤት ስራ የሴትም ሆነ የወንድ የጋራ ስራ ነው:: የመስሪያ ጥሬ ቁስ ከመሰብሰብ ጀምሮ እስከ ቤት ምርግ የጉልበትም ሆነ የድግስ መረዳዳት አለ::

በአጠቃላይ በወረዳዋ ያለው ማህበረሰብ በሙሉ በያለበት በነዚህ ማህበራዊ መዋቅሮች ደስታውን፣ ሀዘኑንና ችግሩን ወዘተ በመፍታት ያሳልፍ ነበር:: እንደመረጃ አቀባዮቹ ከሆነ በአሁኑ ሰዓት ይሄ ሁሉ የድግስ ጋጋታ እየቀረ መሆኑን ነግረውኛል:: ይኸውም የኑሮ ውድነት እየተከሰተ፣ ህዝቡም በቁጥር እየጨመረ ሲመጣ በድግስም ሆነ በስራ መተጋገዝ በቤተሰብ እየተወሰነ ነው:: በተለይ የሰርግ ድግስ ቀርቶ ወደ ቤት ስራ ድግስ መቀየሩን ለጥናት በሄድኩበት ወቅት በምልከታዬና በቃል መጠይቅ ላረጋገጥ ችያለሁ:: ሆኖም እንደማህበርና የስራ ወንፈል /ደቦ/ ያሉት አሁንም ቢሆን እየደበዘዙ እንዳልሄዱ መረጃ ሰጪዎች አረጋግጠዋል:: ሰንበቴ፣ ሰንበታት፣ በክፊልም ፅጌ ሙሉ በሙሉ ተቋርጠዋል::

3.5. የህዝቡ የኑሮ መሰረትና መስህብነት ያላቸው ቦታዎች

በ3.3. ለይ 98.1 ህዝብ በግብርና ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ተጠቅሷል:: ይኸውም በአብዛኛው በእርሻ በተወሰነም በከብት፣ በበግ፣ በፍየል፣ በፈረስና በቀፎ እርባታ የሚተዳደር ህዝብ ነው:: እናም፣ በዋናነት መሬት የኑሮ አለኝታ ነው:: መሬትን በርስትነት ዘር ቆጥሮ የትውልድ ሀረግን አያይዞ በተወላጅ መካከል ገብቶ እኩል የመካፈል ሁኔታ የተጀመረው በአፄ ሰርፀ ድንግል የመንግስት ዘመን በዳሞት በተሾሙት ከአፄ ዳዊት የዘር ግንድ የተገኙት የአቤቶ ተክለሃየማኖት ልጅ ደጃች አሰቦ፣ እህቶቻቸውና ወንድሞቻቸው

ነው::/1994:15/:: ይህም እስከ 1966 ዓ.ም የአብዮት ለውጥ ጊዜ ድረስ የነበረ እንደሆነ ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ::

የህዝቡ የኑሮ መሰረት ግብርና በመሆኑ በተለይ በደጋው ክፍል እኗምሬ፣ አተር አበባ፣ ጃናህሌ፣ ቁጭ ብየ፣ ኣዳመ፣ እናት በጓሮና አፈጫት የተባሉት የድንች ዝርያዎች ከምግብነት አልፈው የገቢ ምንጮች ናቸው:: በዚህ ደጋማ ክፍል ከአስራ አራት የገብስ አይነቶች ውስጥ የታወቁትን ጅባሳድ፣ ጥቁር ሰነፍ ቆሎ፣ ነጭ ሰነፍ ቆሎ፣ ወይዘርዮ፣ ጠመጅ፣ መሰኖ፣ ሰመሬታ፤ እንዲሁም የደጋ ገብስ /አውራ ገብስና ጠይም ወይም ጥቁር ገብስ/፤ አሁን ደግሞ "ሆ... በል" የተባለ ስንዴ መሰል ገብስ ይመረታል:: /1997:5/ ከዚህ በተጨማሪ በቆላማና ወይና ደጋማ ቀበሌዎች በልጀ ንጉስና በአረፋ ጤፍ፣ አተር፣ በቆሎ፣ ኑግ፣ ተልባ እና የመሳሰሉት ይመረታሉ:: በወረዳዋ እያንዳንዱ አርሶ አደር በተበጣጠሰ መሬቱ የተለያዩ አዝዕርትን በማምረት ለገበያ ያቀርብ እንዲሁ እንጅ የሚሸምት የለም::

ሌላው በወረዳዋ ደጋማ ክፍል በግና ፈረስ በብዛት ይረባል:: እናም የደጋው የገቢ ምንጭ ከፈረሶቻቸው የሚወለዱት የበቅሎ ግልገሎች ናቸው:: በተጨማሪም የቀርቀሀ ምርት ዋናው የደጋማው ክፍል የገቢ ምንጭ ነው:: ቀርቀሃውን በቁምም ሆነ ቅርጫት ሰርቶ በመሸጥ ተጠቃሚ ናቸው:: በአጠቃላይ የወረዳዋ ህዝብ በእርሻና በከብት እርባታ የመጠቀሙን ያህል በተወሰነ መልኩም እንደመረጃ አቀባዮች (እንደጥኝው ግንዛቤ ከሆነ) በተለያዩ ቀበሌያት ብረት ቀጥቃጮች፣ ሸክላ ሰሪዎች ቆዳ ፋቂዎች ከግብርና በተጓዳኝ የእጅ ስራቸውን ለገበያ በማዋል ይጠቀሙ ነበር:: በተወሰነ መልኩ አሁን እየተዳከሙ ቢሄዱም::

ከግብርና በተጨማሪም በወረዳዋ ለገቢ ምንጭነት ገና ተግባር ላይ ባይውሉም ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ዋሻዎችና ፏፏቴዎች አሉ:: እነዚህ ሰው ሰራሽ ቅርሶች የጋለሞታ ትክል ድንጋይ /ዳሞት ድኩልካና ቀበሌ/፣ ሰነቦ ተክለሃይማኖት ገዳም /በገነተ ማርያም ቀበሌ/ የሰብለ ወንጌል ፍርስራሽ ህንፃ ቤተመንግስት /በጌንስ ተክለ ሃይማኖት ቀበሌ/፣ ጃን ነገስ ዋሻ /አረፋ መድሃኒያለም ቀበሌ/፣ ሸማ ማጠቢያ ዋሻ /ጉድባ ሰቀላ ቀበሌ/፣ ጠቢብ ዋሻ /ጉኡስ ደብተራ ቀበሌ/፣ ጫት ዋርካ ዋሻ /ጫት ወርካ ቀበሌ/፣ ጉድያሜ ዋሻ /ጓንሲት ጉድያሜ ቀበሌ/ እና ጅብ ዋሻ /ሻንጊ ደረቁ ቀበሌ/ በመባል ይታወቃሉ:: /1997:12-13/ እንደሁም

የተፈጥሮ የፏፏቴ ቅርሶች አምቦፌ ፏፏቴ/ አረፋ መደሃኒያለም ቀበሌ/ እና ዋና ተስኬ ፏፏቴ / ዳሞት ሲፋጥራ ቀበሌ/ የሚገኙት ተጠቃሽ ናቸው::

በአጠቃላይ በወረዳዋ ላለው ህዝብ የኑሮ መሰረት ግብርና ነው:: እንዲሁም ገና ለቱሪስት መስህብነት ግልጋሎት ላይ ባይውሉም ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ቅርሶች ታላቅ የገቢ ምንጮች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገመታል::

3.6. የቁሳዊ ባህል ሰሪዎችና ማህበራዊ ደረጃ

ይህን ንዑስ ርዕስ በወረዳዋ ዳራዊ መግለጫ ላይ ያመጣሁት ያለነገር አይደለም:: ምክንያቱም ባህላዊ እጀ ሰሪዎች ሀገራዊ አንድምታን የሚጋሩ ቢሆንም ወረዳዋን መሰረት አድርጌ ለመግፅ ስለፈለኩ ነው:: የቁሳዊ ባህል ሰሪዎች በኢትዮጵያ በተለያዩ ቦታዎች ነበሩ:: ሆኖም እነዚህ ቆዳ ፋቂዎች፣ ሸማ ሰሪዎች፣ ሸክላ ሰሪዎችና ብረት ቀጥቃጮች ጨዋ እየተባለ በሚጠራው ማህበረሰብ የተለየ ስም እየተሰጣቸው ይዋረዱ ነበር:: እነዚህ በውርደት ይኖሩ የነበሩ እጀሰሪዎች በተለይ ሪቻርድ (251) ከአክሱም ዘመን መውደቅ በኋላ ኢትዮጵያ ከማንም ጋር ላለመገናኘት የባህር በሯን ዘግታ በነበረበት ወቅት የኢኮኖሚ መሰረቷ ከእጅ ወደአፍ ሲሆን የኢትዮጵያ የእጅ ሙያተኞች ከእጅ ወዳፍ የበረውን የኢኮኖሚ ባህሪና የህብረተሰቡን በስልጣን ተዋረድ የተደራጀ ልማት በማንፀባረቅ መልኩ የሚታወሱ እንደነበሩ ጠቅሰዋል::

ሪቻርድ (251-252) አክለውም በመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ የእጅ ሙያተኞች በአራት የተከፈሉ እንደነበር ጠቁመዋል:: የመጀመሪያዎቹ በመላ ሀገሪቷ በተራ የኑሮ ሁኔታ ላይ ካሉት ገበሬዎች ጋር አብረው፣ ሁለተኛዎቹ ደግሞ ክርስቲያኖችና ቀላውስት አብዛኞቹ የሃይማኖት ማዕከላዊነትን መሰረት አድርገው ከተሰባሰቡት በጎን፣ በሶስተኛነትም ገዥዎችና ዳኞች ተንቀሳቅሰው በከተሙበት ከተማና በመጨረሻም በወታደራዊ ካምፕ ዙሪያ ከተሰባሰቡት ወንዶችና ሴቶች ጋር በመሆን ቁሳዊ ባህሎችን ያመርቱ እንደነበር በጥናታቸው አመላክተዋል::

እነዚህ በችግር ጊዜም ይሁን በሰላም ጊዜ ባህላዊ ቁሶችን እያመረቱ ያቀርቡ የነበሩ የኢትዮጵያ የእጅ ባለሞያዎች ባሳለፉት ዘመን ሁሉ በውርደት የኖሩበት ሁኔታ ይበልጣል:: ተክለ ፃድቅ መኩሪያ የአፄ ሚኒልክን አዋጅ ዋቢ አድርገው የሚከተለውን ፅፈዋል::

> ... ሰራተኛውን በስራው የምትሰድብ ተወኝ ከዚህ ቀደም ብረት ቢሰራ ጠይብ፣ ሸማ ቢሰራ ሸማኔ፣ ቢጽፍ ጠንቋይ፣ ቤተክርስቲያን ቢያገለግል ደብተራ እያለችሁ... እጁ ምናምን ስራ የማያውቀው ሰነፍ ብልሁን እየሰደበ አስቸገረ:: ቀድሞም ይህን ሁሉ ፍጥረት የተገኘው ከአደምና ሄዋን ነው እንጅ ሁለተኛ ፍጥረት የለም:: ... ለወደፊቱ እንዲህ ብሎ የሰደበ እኔን የሰደበ ነው እንጅ ሌላውን መስደብ አይደለም:: ዳግመኛ ሲሰድብ የተገኘ ሰው መቀጫውን አንዳንድ ዓመት ይታሰራል:: ... ጥር 1900 ዓ.ም /ተክለ ፃድቅ 1983:591/

ይህ እንግዲህ የእጅ ባለሞያዎችን ምን ያህል ጫና እንደነበረባቸው መገመት አያዳግትም:: እናም አፄ ምኒልክ ዘመናዊነትን እየተላበሱ ሲመጡና ለቴክኖሎጂ እድገት የሀገሬው የእደጥበብ ሙያተኛ ቁልፍ መሆኑን ተረድተው ይመስላል አዋጅ ያስነገሩ:: አፄ ቴዎድሮስም ተመሳሳይ አዋጅ አውጥተው እንደነበር ታሪክ ይመስክራል:: ስለሆነም በመላ ሀገሪቱ በቁሳዊ ባህል ሰሪዎች ላይ የነበረው ማህበራዊ ተፅዕኖ በደጋ ዳሞት ወረዳ ባሉት ላይም ተንፀባርቋል::

በተለይ ጋብቻን በተመለከተ ርስትና ዘር እየቆጠረ መወለድን እያስመሰከረ ይኖር ለነበረው የደጋ ዳሞት ህዝብ ከባህላዊ እጀሰሪዎች ጋር ለመፈፀም የማይቻል ነበር:: መረጃ አቀባየ አቶ በላይ አለኸኝ ወንድም (ፈረስ ቤት ከተማ፣ 11-07-2002) "ጋብቻ ቀርቶ ግንባር በምታክል መሬት ብቻ እንድንወሰን ያደርጉን እንደነበር ቅድመ አያቶቼ ሲያወሩ ሰምቻለሁ:: ተወልጄ ካደኩባት ቆላ ሻንጊ ቀበሌም ወደፈረስ ቤት ከተማ የመጣሁት በአካባቢው ሰዎች ጫና ነው::" በማለት አጫውተውኛል:: ሆኖም አሁን እንደ እጅ ባለሞያው የኑሮ ደረጃ፣ ትምህርትና መንግሰታዊ ስልጣን ተመዝኖ አልፎ አልፎ ጋብቻ እየተፈፀመ እንደሆነም ነግረውኛል:: በሌላ መልኩ ግን ሙያቸውን ለማስቀጠልም ሆነ ለልጆቻቸው ለማውረስ አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ እንዳሉም በውይይታችን ወቅት አውርተውኛል::

ባህላዊ እጀ ሰሪዎች ባላባት ነኝ፣ ገዥ ነኝ እያለ የበላይነቱን ሲያንፀባርቅ ለነበረው ጭምር ለልብሱ፣ ለከፈኑ፣ ለእርሻው፣ ለማብሰያው፣ ለመኝታው፣ ለጦር መሳሪያው፣ ለቤት ክዳኑ ወዘተ አገልግሎት በመስጠት ታሪክ የማይሽረው ተገባር ፈፅመዋል:: አሁንም ቢሆን

የተለያዩ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ጫናዎች እያደከሟቸው ቢሆንም:: እናም የወረዳዋን ባህላዊ እጀ ሰሪዎች በተለይ በመጥፋት ላይ ያለውን የቆዳ ቁስ ሰሪዎችን መርጨ የቃል መጠይቅ ማድረግ ችያለሁ:: ሌላው የስፌት ሙያን በተመለከተ ለሴት ተለይቶ የተሰጠ ቢሆንም የክብር እንጅ የውርደት እንዳልነበር ይታወቃል:: ቤት ስራንና ሌሎችን ቁሶች በተመለከተም ችሎታው ያለው ሁሉ ስለሚሰራቸው የተለየ ሰሪ የላቸውም:: የጋራ ስራዎች ናቸውና:: ስለሆነም በተለየ ባለሞያን ወስጀ ያወያየሁበት ሁኔታ የለም::

በአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ የደጋ ዳሞት ስም አስያየመን፣ መልካ ምድራዊና የአየር ፀባይን፣ የህዝብ፣ የሃይማኖትና የቋንቋ ሁኔታን፣ ማህበራዊ ግንኙነትን፣ መስህብነት ያላቸው ቦታዎችን እንዲሁም የቁሳዊ ባህል ሰሪዎችን ማህበራዊ ደረጃ ለመዳሰስ መኩራ አድርጌያለሁ::

ምእራፍ አራት

4. የመረጃ ገለፃና ትንተና

ይህ ምዕራፍ ባህላዊ ቤቶችንና የእጅ ስራ ቁሶችን የአሰራር ሂደትና በመጥፋት ላይ መሆን እንዲሁም አጠቃላይ ገፅታ ማወቅ ይቻል ዘንድ በተከወነው የቃል መጠይቅና በወረዳዋ ናሙና ቀበሌዎች በመሟሟር በተደረገው ምልከታ መሰረት የተሰባሰቡትን የቁስ መረጃዎች መግለፅና የተወሰኑትን ቁሶች በመምረጥ በስነቃላዊ ግጥሞች አዋህዶ መተንተን የሚቻልበት ነው:: ገለፃና ትንታኔውን ለመስጠት የመስኩ ምሁራንን ንድፈ ሀሳብ ዋቢ በማድረግ ቁሶችን በማዋገን ማስቀመጥ ተችሏል:: እዲሁም ባህላዊ ቤቶችንና የእጅ ስራ ቁሶችን በሁለት መልክ ከፍሎ ለመግለፅና ለመተንተን ተሞክሯል:: በሁለት መልክ መክፈል የተቻለውም ሀገረሰባዊ ምህንድስናና ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁሶች የተለያዩ በመሆናቸው ነው::

4.1. በመጥፋት ላይ ያሉ ባህላዊ ቤቶች

4.1.1. የባህላዊ ቤቶች አይነትና መስሪያ ጥሬ ቁሳቸው

ጥንታዊ ባህላዊ ቤቶች ለሰው ልጅ መጠለያነት በተለያየ አይነት ተሰርተው ግልጋሎት ይሰጡ እንደነበር ይታወቃል:: በተለይ ባህላዊ ቤቶችን በመጥፋት ላይ መሆንና አለመሆን፣ እንዲሁም የአሰራር አይነታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ እችል ዘንድ በደጋማ፣ ቆላማና ወይና ደጋማ ቀበሌያት ስዘዋወር የተለያየ መጠን እንዳላቸው መገንዘብ ችያለሁ:: የተለያየ መጠን ያላቸውን ቤቶች ከባቢያዊ እውቀትን መሰረት ተደርገው እንደመሰራታቸው ቀያዊ ስያሜን ተጠቅሜ መመደብ ችያለሁ::

ከዚህ አኳያ ሶስቱም የአየር ፀባይ በሚንፀባረቅባቸው ቀበሌዎች ይሰሩ የነበሩ በመጥፋት ላይ ያሉት ባህላዊ የቤት አይነቶች ደርብ፣ አዳራሽ፣ እልፍኝና ጎጆ ቤት ናቸው:: የቤት አይነቶቹ በዚህ መልክ ይዋገኑ እንጅ መስሪያ ጥሬ ቁሳቸው በተለይ የደጋማ ቤቶች ይለያል:: ይኸውም በደጋማው ክፍል የሚሰሩ ቤቶች ለግድግዳ /ቀርቀሃ፣ ውልክፍ፣ ፅድ፣ ወይራ፣ ኮሶ/፣ ለጣሪያ /ቀርቀሃ፣ ሸንበቆ/፣ ለማገር /ሀረግ፣ ቀርቀሀ፣ ወች፣ ውልክፍ ልጥ/፣ ለክዳን /የገብስና የመስኖ ብዕር/፣ ለምርግ /ጭቃ፣ የገብስ ገለባ/፣ ለወጋግራና ለምሰሶ /ፅድና ኮሶ/ በመጠቀም ነው::

በቆላማና በወይናደጋማው ደገሞ አንዳንድ ጥሬ ቁሶችን ከደጋማው ክፍል በውሰትም ሆነ በግር ማግኘት ቢችሉም በደጋማው የማይገኙ የደን ውጤቶችን ይጠቀማሉ:: መስሪያ ጥሬ ቁሶቹ ለግድግዳ /ወይራ፣ ፅድ/ከደጋ/፣ ደንጋይ ፣ቀንጦ፣ ሰገድ፣ አንቡስ፣ አባሎ፣ ጓምቢሎ፣ ሰሳ/፣ ለጣሪያ፣ /ሸንበቆ፣ ሰገድ፣ ጫት/፣ ለጣሪያ ክዳን /ስርስራና ዘባ ሳር/ ለማገር፣ /አጋም፣ ልጊጣ፣ ቀጨሞ፣ ከሰይ፣ ዘነዘና/ ለማገር ማሰሪያ /ቱቻ፣ ጎድር፣ ሀረግ፣ ወቺ/ከደጋ/፣ /ለምርግ /ጭቃ፣ የጤፍ ጭድ፣ የገብስ ገለባ፣ የአተር ገለባ/፣ ለወጋግራና ለምሰሶ /ፅድ/ከደጋ/፣ ወይራ፣ ሰገድ፣ ቀንጦ/፣ ለድምድማት /ቀጨሞ፣ ከሰይ/፣ ለበርና ለመቃምድራ /የአቫር ወይም ዋርካ እንጨት፣ ዋንዛ/፣ ምሰሶውን ከጣሪያው ጋር የምታገናኘው ገበታ የዋንዛ እንጨት፣ ከምሰሰው ጫፍ ዝናብ እንዳይገባ ከቂጡ የተበሳ ከሸክላ አፈር የተሰራ እንስራ ይቀመጥበታል:: ጠቅለል ባለ መልኩ ስናስቀምጠው በደጋም ሆነ በቆላና በወይና ደጋ ባህላዊ የቤት አይነቶች የሚሰሩት ከእንጨት፣ ከድንጋይ፣ ከጭቃ፣ ከሳር፣ ከሀረግ፣ ከቀርቀሃ፣ ከሸንበቆ፣ ከሸክላ አፈር፣ ከገብስ ብዕርና ከመሳሰሉት ጥሬ ቁሶች በማሰባሰብ ነው:: የሁሉም ጥሬ ቁሶች መገኛ በዚያው በወረዳዋ ውስጥ ነው::
ባህላዊ የቤት ዓይነቶቹ በውስጥ አካፋፈልና በመጠን ይለያዩ እንጅ የግድግዳ ቅርፃቸው ክብ የጣሪያቸው ደግሞ ሾጣጣ (Cone shape) ነው:: እናም በቤቶቹ መጠንና በውስጣቸው የመከፋፈል ብዛት በልዩነት እንዲሰየሙ መደረጉን ማጤን ይቻላል:: እያንዳንዳቸውን ቀጥሎ ማቅረብ ተችሏል::

ደርብ[7] ቤት:- ይህ የቤት አይነት ከደንጋይ፣ ከጭቃ ጡብ፣ ከእንጨት ጣውላ፣ ከሸንበቆ፣ ከሳርና ከሀረግ የሚሰራ ሲሆን አንዳንድ ጊዜም ያለ ድንጋይና ያለ ጭቃ ጡብ በእንጨት ብቻ የሚሰራ ደእንበር መረጃ አቀባዮች ነግረውኛል:: ታሪካዊ አመጣጡ ከመቼ ዘመን ጀምሮ እንደሆነም አይታወቅም:: /አቶ ዳኛው ወርቅነህ ባይነስ 28-08-2002/ ምናልባት አስቱር ሙሉ የዘጌ ባህረ ሰላጤን ባህላዊ ቤቶች ባጠኑበት ጥናታቸው "ደርብና ምድር ቤት" የ15ኛው ክፍለ ዘመን ስሪት መሆኑን መጠቆማቸው ከዚህ ጋር ያመሳስለው ይሆን የሚል (የራሴ ግምት አለኝ):: ግን ከዘጌው ባህረ ሰላጤ ቤት የውስጥ አከፋፈልና አሰያየም ጋር በምንም መንገድ አይገናኝም:: ይሁን እንጂ ዘመን ቢራራቁም የዚያ ቅጅ ይመስላል::

---

[7] ደርብ ማለት በድሮ ጊዜ የሚሰራ ባለ አንድ ፎቅ ቤት ነው:: (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ 1993፣460)

በወረዳዋ ባደረኩት ምልከታና ከመረጃ አቀባዮቹም ባገኘሁት መረጃ መሰረት ወርቅነህ ባይነስ አይቸህ በ1950 ዓ.ም ከድንጋይና ከጭቃ ጡብ የሰሩት ደርብ ቤት ብቻ ነው ያለው:: በዚህ ዙሪያም ሙሉ መረጃውን የሰጡኝ ዋና መረጃ አቀባዬ የቤቱ ባለቤት ልጅ አቶ ዳኛው ወርቅነህ ይባላሉ:: አቶ ዳኛው ወርቅነህ ተወልደው ያደጉት ጨዋኔ ብሀንዴ ቀበሌ ልዩ ስሟ ሸባ ከምትባል ጎጥ ሲሆን የ65 ዓመት አዛውንት ናቸው:: በ1975 ዓ.ም ጀምረው ከወረዳዋ ዋና ከተማ ፈረስ ቤት በንግድ ኑሯቸውን መሰረቱ:: አሁን ቤተሰባቸውን አስተምረው ያለምንም ስራ ቢኖሩም ቤት ሰርተው ያከራያሉ:: እናም ከመኖሪያ ቤታቸው ሂጄ ነው ያነጋገርኳቸው:: ደርብ ቤቱ ግን ያለው ጭዋኔ ማሪያም ቀበሌ ልዩ ስሟ ሸባ ከምትባል ጎጥ ነው::



ፎቶ 1 ደርብ ቤት(አሁን ቆርቆሮ የለበሰ)

ፎቅና ምድር በሚል የተከፈለው ይህ ደርብ ቤት በሚከተለው መልክ እንደተሰራ የባለ ቤቱ ልጅ መረጃውን አጋርተውኛል::

> *ይሄ ቤት ያባቴ ነበር:: ያኔ እኔ ገና ልጅ በነበርኩበት ወቅት በ1948 ዓ.ም አካባቢ ተጀምሮ በ1950 ዓ.ም በሁለት ዓመት ውስጥ ተጠናቀቀ:: በወቅቱ ድንጋዩንና የጭቃ ጡቡን በተለየ መልኩ ለሰራው ሰውዬ ሃያ ጠገራ ብር ተሰጥቶት ነው:: ጡበናው ጭቃ ተበክቶ በጭድ ታሽቶ እየተቆረሰ የሚዘጋጅ ነው:: እና ግድግዳው በጡብና በድንጋይ ከተገነባ በኋላ በምድር ቤቱ ላይ አግድም ወፍራም እንጨትና ጣውላ ይረበረብና በጭቃ ይደረፋል:: ከዚያም የፎቁ ወለል ከተሰራ በኋላ የፎቁ ግድግዳ ደግሞ ወደላይ በጡብና በድንጋይ ይገነባል:: ተገንብቶ ከላቀ በኋላ ባጥ /ጣሪያ/ ይዋቀርና ይማገራል:: ከተማገረ በኋላ በጭቃ ይመረግና ከላዩ ላይ አመድ ይለብሳል:: አሁን እሳቱ የላይኛውን ጣሪያ ይበላና የታችኛውን አይነካውም:: አመዱና ጭቃው ስላለበት ይሄ እንግዲህ የእሳት መከላከያ ነው:: ከዚህ በላይ እንደገና ሌላ*

ጣሪያ ይዋቅርና ተማግሮ ስርስራ ሳር ይከደናል:: ከዚያም ፎቁ ላይ ካለ ታላ የሸንበቆ መከታ ዙሪያውን ይሰራበታል:: /አቶ ዳኛው ወርቅነህ ባይነስ 28-08-2002/

በዚህ መልክ የተሰራው ደርብ ቤት ግድግዳው ክብ ሲሆን ጣሪያው ሾጣጣ (Cone Shape) ነው:: እናም ቤቱ የምድሩና የፎቁ ሁለት በሮች ያሉት ሲሆን፣ ወደ ፎቁ መውጫና መውረጃም ሁለት መሰላል አለው:: በውጨኛው መወጣጫ ማንም ሰው ሊጠቀምበት ሲችል የውስጠኛው ግን ያለቤተሰቡ በተለይ ያለባለቤቱ ማንም የሚያውቀው የለም:: "የውስጠኛውን ባለሀብቱ ነው ሚስጢሩን የሚያውቅ:: ሌላ ሰው አይወጣም አይገባም:: ክልክል ነው:: ማንም አያየውም:: በሚስጢር የተደፈነ ነው:: የተደፈነውን ብድግ አድርገህ አንስተህ ነው የምትገባው::" እንደላይኛው::

የቤቱን አከፋፈል በተመለከተም የፎቁ የእንግዳ መቀበያ ወለል ብቻ ነው ያለው:: በዚህ ክፍል በአመትባልም ሆነ በማህበር ወይም በድግስ ቀን ማንኛውም እንግዳ በውጭኛው መወጣጫ ወጥቶ የሚጋበዝበት ነው:: አረቄውን፣ ጠላውን፣ ቡናውንና ምግቡን መጠጣትና መብላት ይቻላል:: ከፎቁ በረንዳ ላይም ቡና ይፈላበታል:: አነስ ያለ ድስት ተጥዶ ወጥ ይሰራበታል እንጅ ከዚህ ውጪ ሌላ ተግባር አይፈፀምበትም:: ነገር ግን መተኛት ይቻላል::

ምድር ቤቱ ከቤተሰቡ ውጪ ማንም ሰው አይገባበትም:: በውስጡ የእህል ጎታ፣ ቅቤና ማር ወይም በአጠቃላይ ከእሳት አደጋ በእጅጉ የሚጠበቁ እቃዎች የሚቀመጡበት ነው:: በተጨማሪም እናትና አባት ለአመትባልም ሆነ ለሰርግ ራቅ ወዳለ ቦታ ቢሄዱ ልጆች የሚተኙበት የጠፍር አልጋ ይኖራል::

የዚህ አይነት ቤት መሰራት በተጀመረበት ወቅት አዳራሽ ቤቶች በእሳት እንደጋዩ መረጃ አቀባዮቼ በናሙና ጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ውይይት ላይ አንሰተው ተወያይተውበታል:: በውይይታቸውም የእከሌ አዳራሻ በዚህን ቀን ሲቃጠል፣ የእከሌ ደግሞ በዚህ ቀን እያሉ ነበር በትውስታ መልክ ያቀረቡት:: እናም ከውይይታቸው መገንዘብ እንደተቻለው ደርብ ቤት ሰርቶ ከእሳት ቃጠሎ ሳያመልጥ ቤቱን አመድ ላድርግለት የሚሉት የጠላትነት ጥፋት እንደነበር ነው:: ደርብ ቤት ለመስራት የፈለገ ቤተ ሰሪ፣ ሰው ሳይሰማ የአደራሽ ቤቱን ክዳን በሌሊት ገፎት ያድር እንደነበር አጫውተውኛል:: (አቶ

ይታይህ አላምንህ፣ አቶ ዳኛው ወርቅነህ፣ አቶ ፈንቱ አስረስ፣ አቡሃይ ጥሩነህ መርሻ፣ 30-08-2002)

ደርብ ቤቱ የወረዳዋን ማህበረሰብ የወቅቱ ታሪክ ወይም የተለየ ሁነት ጠቃሽ እንደነበር ከመረጃ ሰጪዎች ውይይት መረዳት ይቻላል:: ምክንያቱም በወቅቱ "ደርብ ቤት ሰርቶ ሳያመልጠኝ በእሳት ለጋይለት" በሚሉት ፈሊጥ ማህበረሰቡ በእሳት ቃጠሎ የስጋት ሁነት ውስጥ መኖሩን ይጠቁማልና:: በሌላ በኩልም በማህበረሰቡ መካከል የኢኮኖሚ ልዩነትን የሚፈጥር ስለነበር ደርብ ቤት የሰራ ሰው የተለየ ክብር ይሰጠው እንደነበር ነው:: ደርብ ቤት ለሰራ የነበረውን ክብር ሲገልፁ:-

> *አንደኛ ቤቱን የሚሰራ ሀብታም ነው:: ድሃ አይሰራውም:: እናም የአካባቢው ሰው የተለየ ክብር ይሰጠዋል:: እሱማ ፎቅ ቤት ሰራ አሳት ዳነ ልጆቹን እህሉን ንብረቱን እዚያ አቶ ያድናል ይባላል:: አፍተኛ ክብር ይሰጡታል:: ትልቅ ክብር አለው:: እዋዋ... ትልቅ ክብር አለው:: በብዙ ድካም እኮ ነው የሚሰራው:: በቀን እኮ አስር፣ አስራ አምስት፣ ሃያ ሰው ይውላል:: ግንቡን ሲሰራ:: ለዚህ ሁሉ ሰው ለሁለት አመት መደገስ ቀላል አይደለም:: ወጪው የበዛ ነው:: በወቅቱ በገንዘብ ባይተመንም:: /አቶ ዳኛው 28-08-2002/*

ከዚህ አኳያ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የተለየ ግምት መሰጠቱ የማይቀር ነው:: በአጠቃላይ ደርብ ቤት እሳትን ለመከላከልና ወደ ዘመናዊ የፎቅ ቤት አሰራር ለመለወጥ ፈር የቀደደ እንደነበር መመስከር ይቻላል:: የአባ ወርቅነህ ባይነስ ይህ ደርብ ቤት በአሁኑ ሰዓት ቆርቆሮ ለብሶ ነው ያለው:: ባለቤቱም በህይወት የሉም:: የመጨረሻ ልጃቸው አቶ ልይህ ወርቅነህ ምድር ቤቱን ብቻ እህልና እቃ በማስቀመጥ ይገለገሉበታል:: ፎቁ ላይ ሳርና ለማገዶ የሚሆን የበቆሎ አገዳ ከምረውበታል:: ጣሪያው ላይ የለበሰው ቆርቆሮ ተቆራርጧል፤ የግድግዳው ካብም በጥንቃቄ ባለመያዙ የመፍረስ አደጋ ተጋርጦበታል::

አዳራሽ[8] ቤት:- ይህ ባህላዊ የሳር ቤት እንደ ደርብ ቤት ሁሉ ግድግዳው ክብ ሲሆን ጣሪያው ደግሞ ሾጣጣ (Cone shape) ነው:: ጣሪያው ቀጥ በሎ የቆመ ሾጣጣ ሳይሆን ከወደ ቂጦ ሰፋ ያለ ነው::ማለትም ከጫፍ ወደታች እየሰፋ የሚሄድ ነው::

አዳራሽ ቤት የጥንት እንደሆነ መረጃዎች ያረጋግጣሉ:: ይህ የጥንት ቤት የሚሰራው በዚያው በወረዳዋ በሚገኙ ጥሬ ቁሶች ነው:: መስሪያ ጥሬ ቁሶቹ እንጨት፣ ሳር፣ ቀርቀሃ፣ ሸንበቆ፣ የገብስ ብዕር፣ ሀረግ፣ ልጥ፣ የገብስ ገለባ፣ የአተር ገለባ የጤፍ ጭድና ጭቃ ናቸው:: ይህን ቤት ለመስራት ግልጋሎት ላይ የሚውሉት ቁሶች እንደአየሩ ጠባይ ይለያያሉ:: ማለትም በወይና ደጋውና በቆላው የሚገኙ ጥሬ ቁሶች በደጋው አይገኙምና:: እናም የአሰራር ሂደታቸው፣ ቅርፅና መጠናቸው ቢመሳሰልም በመስሪያ ጥሬ ቁስ ይለያያሉ ማለት ነው::

በደጋማው ክፍል ብቻ የሚገኙ መስሪያ ጥሬ ቁሶች /ጥድ፣ ኮሶ፣ ቀርቀሀ፣ ወች፣ የገብስና የመስኖ ብዕር/ ሲሆኑ፣ በወይናደጋዊውና በቆላው ብቻ የሚገኙት ደግሞ /ቀንጠ፣ ሰገድ፣ ጓንቢሎ፣ አባሎ፣ ደንጎሪታ፣ ልጊጣ፣ ዋንዛ፣ ዋርካ፣ አቫር፣ አምቡስ/ ዋነኞቹ ናቸው:: ሌሎቹ እንደ ወይራ፣ ውልክፉ፣ ሸንበቆ፣ አጋምና ሀረግ ያሉት በወረዳዋ ሁሉም ቀበሌያት እንዲሚገኙ /አቶ ይታየህ አለምንህ፣ 03-09-2002፣ አቶ ዳኛው ወርቅነህ፣ 28-08-2002፣ አቡሀይ ጥሩነህ መርሻ 29-08-2002/ ነግረውኛል:: "ከሰው መርጦ ለሹመት ከእንጨት መርጦ ለታቦት" እንደሚባለው የአበው ምሳሌያዊ ንግግር የተገኘው ሁሉ እንጨት ለቤት መስሪያ አይሆንም:: ለምስጥ በቀላሉ የማይጋለጥና ረዥም አመታትን ለማገልገል እንዲችል ጠንካራ እንጨትን መምረጥ ይጠበቃል:: "የሰገደ እንጨት የእባብ ልብ እንጅ የለውም አንጀት" በማለት ልበደንዳናውና ወንድነቱ በቀላሉ የማይፈታው ጎበዝ ፎካሪ ሲፎክር መደመጡ ራሱን ከጠንካራው የሰገድ እንጨት ማመሳሰሉን ነው:: እናም ይሄ የሰገድ እንጨት ካለው ጥንከሬና ቀጥ ብሎ ማደጉ የቆላና ወይናደጋ ቤቶችን በጣሪያ ማዋቀሪያነት ያገለግላል::

---

[8] አዳራሽ ማለት 1 ሰፊ /ትልቅ ቤት/ /አማርኛ መዝገበ ቃላት 1993፣339/ 2. በመረጃ አቀባዮቼ መሰረት ደግሞ የእህል ጎታው፣ የጋማ ከብቱ፣ ላሙ በሬው፣ በጉ ፍየሉ፣ ጥጃው፣ ቤተሰቡ የሚጠቃለልበት በመሆኑ የሁሉም መዳረሻ ነው በማለት አዳራሽ /ትልቅ ቤት/ ተባለ /ቁስ አጥናፉ ለማ መሸሻ፣ 29-08-2002/

እነዚህን ጥሬ ቁሶች ተጠቅሞ የሚሰራ ይህ አደራሽ ቤት በመጠን ይለያያል:: ይኸውም ባለ 12፣ ባለ 14፣ ባለ 16፣ ባለ 20 እና በለ 22 ክንድ ቤት ተብሎ ይገለፃል:: ይህ የሚሆነው የመጠን ልዩነት መኖሩ ነው:: ከመጠን ልዩነቱ አኳያም ባለ12ቱ ዘጠኝ ወጋግራ፣ ባለ 14ቱና 16ቱ 12 ወጋግራ፣ ባለ 20 እና 22ቱ 16 ወጋግራ መጠቀም እንደሚቻል /አቶ ይታይህ አላምንህ 03/09/2002/ ነግረውኛል:: በምልከታዬ ማግኘት የቻልኩት ባለ 12ክንድ ቤት እንጅ ከዚህ በላይ ያሉት የሉም::



ፎቶ 2. ባለ 12 ክንድ የደጋ አዳራሽ ቤት

የቤቶቹ መጠን መለያየት እንደባለቤቶቹ ፍላጎታና አቅም የሚወሰን ነው:: ለምሳሌ ባለ10 ክንድ ቤት ገና ትዳር ይዞ ጎጆ የወጣ የሚሰራት ናት:: ልጅ ባለመውለዱና የከብቶቹ ብዛትም ውስን በመሆናቸው:: እናም ያለ ወጋግራ ድጋፍ ዝም ብላ በምሰሶው ብቻ የምትዋቀር ናት:: በዚች ቤት ለተወሰኑት ከብቶቹ ጋጣ፣ ለሚስቱና ለባልዬው አንድ የእንጨት አልጋ፣ መደብና የእህል ማስቀመጫ መጠነኛ ጎታዎች /ጎሸጉሾች/ ይኖሩባታል:: ከዚች ቤት በላይ እስከ ሃያ ሁለት ክንድ ድረስ የሚሰሩት ቤቶች የስፋታቸውና የወጋግራ አጠቃቀማቸው ብዛት በባለቤቶች የሀብት መጠን የሚወሰኑ ናቸው:: ያም ሆኖ አዳራሹም ይሁን ከዚህ በታች ያሉት ባለወጋግራ ቤቶች ውስጣዊ የቤት አከፋፈላቸው ተመሳሳይ እንደሆነ መረጃ ሰጪዎቹ ነግረውኛል::

በተለይ ባለ 22 ክንድ ወይም /ከመሀል ምሰሶው እስከ ግድግዳው 11 ክንድ/ ወይም 5 ½ ሜትር መጠን ያለው ትልቁ አዳራሽ ቤት ከሀብታቸው ብዛት የተነሳ ሁሉንም አጠቃለው ለማስገባት ይመቻቸው ዘንድ ባለፀጋዎቹ የሚሰሩት ነው:: አሰራሩም ለየት ይላል:: እንደመረጃ አቀባዮች ከሆነ ከምሰሶው በተጨማሪ ወደ 16 ወጋግራዎች፣ ከምሰሶው 6

ክንድ /ሶስት ሜትር/ ርቀው የሚተከሉና በየባላዎቻቸው ላይ ዙሪያውን በሚሸከሙት ድምድም ባጡ /ጣሪያው/ እንዳይዘጠጥ /እንዳይረግብ/ ወጥረው የሚይዙ አሉት::

ከአዳራሹ ቤት መለስ ያሉትም ወጋግራዎችን መጠቀማቸው ጣሪያውን ወጥረው በመያዝ ለምሰሶውና ለግድግዳው ከፍተኛ ድጋፍ ማድረጋቸውን በማጤን ነው:: ከወጋግራዎቹ ባላዎች ላይ ዙሪያውን የሚደረገው ድምድም ከከሰይ፣ ከዘነዘናና ከቀጨሞ ቀጫጭን ጭራሮዎች እየተሰካኩ ዘንዶ መስሎ በቱቻ ወይም በጎድር ጉንጉን ወይም በወች ወይም በሀረግ ጥምጥም ብሎ ይታሰራል:: እናም ወጋግራዎቹ ይዜን ድምድም በመሸከም ነው ከመሀል ያለውን የጣሪያ ክፍል እንዳይረግብ የሚያግዙት:: ድምድሙ ተዘርግቶ ቢሰራም ወጋግራዎቹ ላይ ሲደረግ ግን ክብ ሆኖ ነው::

ሌላው ከመሀል የሚቆመው ምሰሶ የቤቱን ሾጣጣነት ከማሳየት ባለፈ ለቤቱ ዋልታ ነው:: እናም ከምሰሶው ጫፍ ላይ ከገተም ወይም ከዋንዛ ወይም ከዋርካ ዛፍ ግንድ የተጠረበ ገበቴ ከጫፍና ጫፍ ዙሪያውን በመሮ ይበሳና ይሰካል:: ከዚያም በዚህ የምሰሶ ገበቴ ላይ ደራስ የሰገድ እንጨቶች /በቆላው/ እና ቀርቀሃ /በደጋው/ አካባቢ በማዋቀሪያነት ይበሱና በካስማ ተመትተው በቱቻ ወይም በወች ይታሰራሉ:: እነዚህን ደራስ ማዋቀሪየዎች /በአሁኑ የቆርቆሮ ወራጅ ማለት ነው/ ተከትሎ ጣሪያው ቁልቁል እየሰፉ ይማገራል:: የጣሪያው ስፋት እየጨመረ በሄደ መጠን በደራሶቹ ማዋቀሪያዎች መካከል ሸንበቆና ሌሎች ቀጥ ቀጥ ያሉ እንጨቶች ወይም አጠር አጠር ያሉ የቀርቀሀ ሳጋዎች እየተሳጉ ይሰራል:: የጣሪያው የማገር ብዛት በግምት እስከ ሃያ የሚደርስ ሲሆን፣ የግድግዳው ደግሞ ከድምድማቱ ጋር ወደ አራት ማገር እንደሚኖረው መረጃ አቀባዮቼ ነግረውኛል::

አዳራሹ ቤት ሰፊ የሆነ የክብት ጋጣ፣ ከበሩ መግቢያ በሰተቀኝ በኩል ከምሰሶው ራቅ ብሎ፣ ወጋግራዎችን ግን አማክሎ ይከፈላል:: በክብቶች ጋጣ ላይም ከወዲያ እስከ ወዲህ በደጋ የቀርቀሃ፣ በቆላና በወይና ደጋ ደግሞ ቀጥ ያሉና ረገቾርም እንጨቶች የሚጋደሙበት በርካታ እንግዳና ቤተሰብ የሚያስተኛ ቆጥ ይሰራል:: ከበሩ መግቢያ በስተግራ ደግሞ የበግ፣ የፍየልና የጥጃ ጓዳ(ጉርኖ) ይዘጋጃል:: በበጎቹ ጓዳ ላይም መለስተኛ አልጋ ቢያንስ ሁለት ቢበዛ እስከ አራት ሰው የሚያስተኛ ይሰራል::

ከመግቢያ በሩ ጀምሮ እስከምሰሶውና አለፍ ብሎ ወለልና ከምሰሰው ስር ማብሰያ ምድጃ ይኖራል:: በበሩና በወለሉ መካከል:: ወደ ከብቶች ጋጣና ወደበጎች ጓዳ ማስገቢያ ድረስ የመተላለፍያ ቦታ አለ:: እንደ አቶ ዳኛው ወርቅነህ ከሆነ ምድጃው የሚሰራው እንደሁኔታው ነው:: ከምሰሶው አጠገብ ወይም ከፍ ብሎ ወደ መደቡ ወይም ወደማጀቱ ዘወር ብሎ ይሰራል:: ከወለሉ ከፍ ብሎ እንዲሁም ከበጎች ጓዳ ጀምሮ ቀጠን ብሎ በድንጋይና በጭቃ የሚራ የሰው መቀመጫ መደብ ይዘጋጃል:: ከመቀመጫው መደብ በስተጀርባ እስከ ግድግዳው ድረስ ሰፊ የሆነ የመተኛ መደብ ወይም ለመኝታ የሚሆን የጠፍር አልጋ ማስቀመጫ ይሰራል:: ከዚህ ውጪ ያለው ቦታ ከከብቶች ጋጣ መልስ ከወለሉና ከመደቡ ጀምሮ በሸንበቆ ወይም በመቃ የተከለለ የእህል ጎታ፣ የበርበሬና የዱቄት ጉሽጉሽ፣ የጋን፣ የማድጋ፣ እንዲሁም አጠቃላይ የቤት መገልገያ ቁሳቁስን አሸጎ የሚይዝ ማጀት ይሆናል::

ማጀት በወረዳዋ ማህበረሰብ ባህል መሰረት ሴቶች ብቻ ስራቸውን የሚያከናውኑበት ከመሆኑም በላይ ደጀናቸውም ነው:: ሴትየዋ ከባለቤቷ ጋር ብትጣላና ጥሉ ከሮ ለድብደባ የሚጋበዝባት ከሆነ ወደማጀቷ ዘላ ትገባለች:: ወደማጀቷ ዘላ ገባች ማለት ህጋዊ ከለላ አገኘች ማለት ነው:: ወይም በዘመኑ አጠራር ጥገኝነት ጠየቀች ማለት ነው:: እናም የባለቤቷ ንዴት ወይም ቁጣ መብረዱን ሳታረጋግጥ ወይም ገላጋይ ከጎረቤት ካልመጣ በቀር ከማጀት አትወጣም:: ባልየውም ንዴቱን ውጦ የማስተዋያ ጊዜን እንዲወስድ ይረዳዋል:: በባህሉ ሴትን ማጀት ድረስ ተከትሎ ሂዶ መደባደብ ነውር ነው:: ወንድነቱንም ዝቅ ያደርገዋል:: ከማጀት በተጨማሪም ሴት የቤቱን ምሰሶ ተጠምጥማ ባለቤቷን ብትማፀን ሊደበድባት አይችልም:: ከዚህ የተነሳ ማጀትና ምሰሶ የሴቶች ደሴት ናቸው ማለት ይቻላል:: ሴትዮዋ ካልኖረች በቀር ወንድየው ከማጀት ገብቶ ምንም ነገር እንዳያወጣ ባህሉ ይገድበዋል::

ግድግዳው ቁሞ ባጡ /ጣሪያው/ ከተዋቀረና ከተማገረ በኋላ መጠነኛው ወይም ዝቅተኛውም ሆነ አዳራሹ ቤት የሳር ወይም የመስኖና የገብስ ብዕር ይከደናል:: በዚህ ላይ ግን ለክዳን የሚሆኑት የሳር አይነቶች ሰንበሌጥ /ስርስራ/ እና ዘባ ሲሆኑ፣ ለደጋማው ደግሞ የገብስ ብዕር ነው:: በተለይ ሰንበሌጥ ሳር የሚከደነው ቤት ትልቁ አዳራሽ ነው:: ሰንበሌጡ ሳር ውድና ተመራጭ ስለሆነ ሀብታሙ ነው የሚከድንበት:: የሰንበሌጥ ሳር አከዳደንን

በምናየበት ጊዜ ሳሩ የሚበቅልበት ወይም ቂጡ ከታች ይሆንና ጫፉ ወደ ላይ ተጋድሞ በድግር እንጨት ወይም በጣውላ ከቂጡ እየተመታ ክፍክፍ ክዳን ይሆናል:: ይህም እርስ በራሱ እየተወሳሰበ የዝናብ ፍሳሽ ካለማስገባቱም በላይ ለብዙ ዓመታት ጠግኑኝ ሳይል ይቆያል::

ሁለተኛው የሳር አይነት ዘባ የሚባለው ወይም ከፍሬው ብዛት የተነሳ ራሳም የሚባለው ለጎጆ ወጪና ለመለስተኛ ቤት ክዳን ይሆናል:: አከዳደኑ ዘባው ሳር የበቀለበት ቂጡ ከላይ የሳሩ ጫፍ ወደታች ይዘቀዘቅና በክፍክፍ መልክ ሳይሆን ለወቅታዊ የዝናብ መፍሰሻነት የሚያገለግል ነው:: ይህ ሳር ካሰንበሌጥ የሰር ክዳን አቀማመጥ በተቃራኒ የሚውል ነው:: እድሜውም አጭር ነው:: በተለያዩ ተባዮችም ለመበላት ይጋለጣል:: በተለይ በክረምት ቅንቡርስ የሚባል ትላትል በትኖ ይጥለዋል:: እናም በየጊዜው ጠግኑኝ በማለት ወጪን ያስወጣል:: ሆኖም ሁሉም ሳሮች የሚገኙት በቆላማውና ወይና ደጋማው አካባቢ ነው::

ለደጋማ ቤት መክደኛ የሚሆነው የገብስና የመስኖ ብዕር ነው:: ይህን የገብስ ብዕር ከቆረኑ በመንቀል ማሰባሰብ ነው:: ከዚያም ብዕሩን ከጣሪያው ላይ መክደን የሚቻለው የብዕሩ ቆረን ወደታች ይዘቀዘቅና የበቀለበት ቂጡ ከላይ ይሆናል:: ልክ እንደዘባ ሳር ነው:: ሆኖም ክዳኑ ሲጀመር ከጣሪያው ጫፍ ላይ የገብሱ ብር የተነቀለበት ከስር ይሆንና ቆረኑ ወደላይ ይጋደማል:: ከዚያም የብሩ መነቀያ ከላይ ሆኖ ዕየተሳግ ከስር ወደሾጣጣው ዐየተከደነ ይወጣል:: ይህን ሁኔታ በሻንጊ፣ በአቅላት፣ በወገም፣ እንዲሁም በገሳግስ ደጋማ ቀበሌያት ተዘዋውሬ በምልከታ አረጋግጫለሁ::

ከ16 ክንድ ቤት ጀምሮ እስከ 22 ክንድ ቤት የሚሰሩ ሰዎች ደርብ ቤት እንደሰራው ሁሉ በማህበረሰቡ ዘንድ የተለየ ክብር ይሰጣቸዋል:: የቤቱ ስፋት በሀብቱ መጠን እየጨመረ የሚሄድ በመሆኑ ማንም ደሃ ሰው ሊሰራው አይሞክርም:: ምክንያቱም የሀብት መጠኑ በዚያ አይሞላምና:: ስራውም ከአቅም በላይ የሆነ ድግስን ያስወጣል:: ይህም ማህበራዊ ደረጃን ይወስናል:: የደሀውና የሃብታሙ ማህበራዊ አቅም ይገመትበታል::

በአጠቃላይ አዳራሽ የቤት አይነት በወረዳዋ ባሉት ቀበሌያት በስፋት ይሰራ የነበር መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል:: መስሪያ ጥሬ ቁሳቁስም ሆነ የአሰራር ጥበቡ አካባቢያዊ ነው:: ከዚያው

የተገኙ ጥሬ ቁሶች ነበሩ::የቤቱን ውስጣዊ ክፍልፋይ፣ የግድግዳ፣ እንዲሁም የጣሪያ፣ የምሰሶና የወጋግራ ሁኔታን በገለፃ ለመሳየት ተሞክሯል:: ቀጥሎ ደግሞ እልፍኝ ቤትን ለማስተዋወቅ ይሞክራል::

እልፍኝ ቤት:- እልፍኝ ቤት የምትባለው በአሁኑ ሰአት በየትኛውም የወረዳዋ ክፍል እንደማትገኝ መረጃ አቀባዮች አረጋግጠውልኛል:: መረጃ አቀባዮች በገለጹልኝ መልክ የተሰራች ወይም ግልጋት የምትሰጥ እልፍኝ ቤት ምልከታ ለማድረግ በተዟዟርኩባቸው ቀበሌያት ማግኘት አልቻልኩም:: ሆኖም መረጃ አቀባዮችን ዋቢ በማድረግ ለመግለጽ እሞክራለሁ::

እልፍኝ ቤት መጠኗ እስከ 8 ክንድ /ከምሰሶው እስከ ግድግደዋ ድረስ 4 ክንድ/ሆና ትሰራለች:: ልክ ደረጃውን ጠብቆ እንደሚሰራ አዳራሽ ቤት ጣሪያዋ የሚከደነው ሰንበሌጥ ሳር ነው:: ይህች ቤት ንፁህ ወለል እንጅ ሌላ የተከፋፈለ ክፍል የላትም:: ለማብሰያነትም አይጠቀሙባትም:: "መደብ፣ አልጋ ምናምን የላትም:: መጋረጃ ብቻ ነው:: ይህች ቤት ንፁህ ወለል እንጅ ሌላ የተከፋፈለ ክፍል የላትም:: ይሄ ዳውጃ ወይም የበግ /የፍየል/ አጎዛ ብቻ ይነጠፍባታል" ብለውኛል አቶ ዳኛው ወርቅነህ:: ካስፈለገ ያለምሰሶ ማለትም ምሰሶው መሬት ሳይተከል በግድግዳው ላይ ባሻጋሪ ከሚጋደም እንጨት ላይ ምስሰዋ ያርፍና ልትሰራ ትችላለች::

እንደ አቶ ዳኛቸው ወርቅነህ አባባል "የእልፍኝ ክብር ባለስልጣን ሲመጣ ነው:: ባህል አለ አይደል፣ ደህና ደህና ሰዎች ሲመጡ ወረዳ ገዥዎች፣ ምክትል ገዥዎች፣ አጥቢያ ዳኞች፣ ጉልተኞች ሲመጡ እልፍኝ ይገቡና ቡና ይፈላለቸዋል አረቄው ጠላው ጠጁ ይጠጣበታል:: ምግቡም ይበላበታል:: ማንም ሰው አይገባባትም:: በመጋረጃው ተጋርደው ይቀመጡባታል:: አንዳንዴ ባለስልጣናቱ የሚያድሩ ከሆነ የጠፍር አልጋ ይገባላቸውና ሊያድሩባት ይችላሉ" ብለውኛል:: እልፍኝ ቤትን ማንም ተራ ሰው ሊሰራት አይችልም:: ለገዥዎች ማረፊያ የተመረጡ ሰዎች ብቻ እንደሚሰሯት ነበር የሚታወቀው::

አንድ ሰው እልፍኝ ካዳራሽ አለው ማለት በአካባቢው ሰው ቀርቶ በወረዳ ገዥዎችና አጥቢያ ዳኞች የተለየ ክብር ይሰጠው ነበር:: እንግዳ ሲመጣም "እከሌ የእንግዳ ማረፊያ እልፍኝ

አለው" ይባልና ወደሱ ቤት ይመራል:: በሀብት መጠኑም የተመሰከረለት ስልጣኑም ቢያንስ በአካባቢው ወይም በደብሩ ወይም በጎጡ ይኖረዋል:: በጠቅላላው እልፍኝ ቤት በአሁኑ ሰዓት የለችም:: ሆኖም ምን ትመስል እንደነበር መረጃ ሰጭዎችን ዋቢ በማድረግ ለመግለፅ ሞክሬያለሁ::

ጎጆ ቤት:- በአሁኑ ሰዓት በወረዳዋ በተዘዋወርኩባቸው ቀበሌያት በብዛት የምትገኝ ብትሆንም በመጥፋት ሂደት ላይ ናት:: የሳር ክዳኗ ተራውን አይነት ቢሆንም ሌላው አሰራሯ ከሌሎቹ ተመሳሳይ ናት:: የመጠን ትንሽነቷም ያመዝናል::ጉጆ ቤት በአሁኑ ሰዓት አዳራሽ ቤት በቆርቆሮ ሲለወጥ እንደማብሰያ ታገለግላለች:: ከዚህ ባሻገርም ለአብነት ጭድ፣ ገለባና ድርቆሽ ሳር መከመሪያ ናት:: አልፎ አልፎ ካሮጌ ቆርቆሮ ማብሰያን የሰሩ ሰዎች ቢኖሩም ጎጆ ቤት የሌለው አባወራ የለም:: ልክ እንደሌሎቹ ባህላዊ የቤት አይነቶች ሁሉ ግድግዳዋ ክብ ጣሪያዋ ደግሞ ሾጣጣ ነው:: ግልጋሎቷ ለማብሰያነትና ለክብት መኖ መከመሪያነት ነው::



ፎቶ 3 ጎጆ ቤት

በአጠቃላይ ቀያዊ ስያሜን መሰረት በማድረግ ደርብ፣ አዳራሽ፣ እልፍኝና ጎጆ ቤት በማለት የወረዳዋን ባህላዊ ቤቶች በማዋገን መግለፅ የተቻለ ይመስለኛል:: እናም አይነታቸውንና መስሪያ ጥሬ ቁሳቸውን በገለፃው ተንትኖ ለማሳየት ተሞክሯል:: በሚከተለው ሰንጠረዥ የቤት አይነቶችን መጠን ለማሳየት ይፈለጋል::

ሰንጠረዥ-1 የደጋ ዳሞት ወረዳ ባህላዊ ቤቶች አማካይ መጠን

የቤቱ አይነት	ስፋት	የግድግዳ ቁመት	የጣሪያ ቁመት	የጣሪያ ዙሪያ	የበር ቁመት	የበር ስፋት	የምሰሶ ቁመት	የወጋግራ ቁመት	የወጋግራ ብዛት
ደርብ ቤት	16 ክንድ /ከመሀል እስከ ግድግዳው 8 ክንድ/	14 ክንድ /ከምድር እስከ ፎቁ/	12 ክንድ ወይም	70 ክንድ	የፎቁና የምድሩ በሮች በተመሳሳይ 6 ክንድ	2ክንድ ከስንዝር	16 ክንድ	-	-
አዳራሽ ቤት	22 ክንድ /ከምሰ ሰው መሀል እስከ ግድግዳው 11 ክንድ/	8 ክንድ	14 ክንድ	80 ክንድ	6 ክንድ	3 ክንድ	14 ክንድ	10 ክንድ	16
እልፍኝ ቤት	8 ክንድ	6 ክንድ	11 ክንድ	50 ክንድ	5 ክንድ	2 ክንድ	11 ክንድ	-	-
ጎጆ ቤት	8 ክንድ	5 ክንድ /	10 ክንድ	40 ክንድ	4 ክንድ	4 ክንድ	11 ክንድ	-	-

•አንድ ክንድ በአማካይ 0.50 ሳ.ሜ ሲሆን፣ ሁለት ክንድ ደግሞ 1 ሜትር ነው።

4.1.2. የባህላዊ ቤቶች የአሰራር ሂደት

አንድን ነገር ለመስራት ራሱን የቻለ ሂደት አለው። ያለምንም ሀሳብና ዝግጅት የሚሰራ ነገር የለም። ስለሆነም በተለይ ደርብንና አዳራሽ ቤቶችን ለመስራት ረዘም ያሉ አመታትን ማሰብ ይጠይቃል። ምክንያቱም ጥንቃቄ የተሞላበት እንጨት መረጣና የድግስ ዝግጅት ጊዜ ይወስዳልና። ይህ ብቻ ሳይሆን ቤቶቹ የሚሰሩበትን ወቅትም መወሰን ይጠይቃል። ከዚህ አኳያ በወረዳዋ ተመራጭ የሆነው የቤት መስሪያ ወቅት ከየካቲት እስከ ግንቦት ባሉት አራት ወራት ውስጥ ነው።

እነዚህ ወራት ለቤት መስሪያነት የተመረጡበት ምክንያት አንድም የመኸር ምርት ተጠቃሎ የሚሰበሰብበት በመሆኑ አንድም የበጋ ወራት በመሆናቸው ዝናብ ያለመኖሩን ተከትሎ በመሆኑ፣ በሌላ በኩልም ለድግስ የሚሆን እህል የሞለበት፣ ትርፍ ጉልበትም የሚበዛበት መሆኑን መረጃ አቀባዮች ነግረውኛል። በአጠቃላይ ግን የባህላዊ ቤቶችን የአሰራር ሂደት በቅደም ተከተል ለማሳየት ሙከራ ይደረጋል።

መስሪያ ጥሬ ቁስ መሰብሰብ:- ቤት ለመስራት ማሰብን እንዳለ ይዘን የቤቶቹን መስሪያ ጥሬ ቁሶች ለመሰብሰብ እንደቤቶቹ መጠን ግማሽ ዓመትና ከዚያ በላይ ሊወሰድ እንደሚችል ይገመታል:: እንዲህ እንደ አሁኑ ጫካው ሳይወድም ለግድግዳ፣ ለምሰሶ፣ ለወጋግራ፣ ለማገር፣ ለክዳን የሚሆን እንጨትንና ሳርን ካንዱ ጉራ ወዳንዱ ጎራ እየተዟዟሩ በመቁረጥና በማጭድ ማሰባሰብ የተለመደ እንደነበር አቶ ይታይህ አላምንህ /03-09-2002/ አጫውተውኛል:: በተለይ ወይራ፣ ቀንጦ፣ ፅድና የኮሶ እንጨቶችን ለመሰብሰብ የተለየ ትኩረት ይሰጣል:: ምክንያቱም እነዚህ እንጨቶች የቤቱን ጥንካሬም ሆነ የዘመን ቆይታ የሚወስኑ በመሆናቸው::

ሌላው ለወጋግራም ሆነ ለምሰሶ እነዚህ የእንጨት አይነቶች ተመራጭ ናቸው:: እናም እንጨቶቹን በመግመስ ወይም በመፍለጥ ወይም በመፈልፈልና በሚመች መልክ በማዘጋጀት ማሰባሰብን ይጠይቃል:: እንዲሁም ለግድግዳም ሆነ ለጣሪያ ማገር የተለያዩ ጥሬ ቁሶችን ማሰባሰብ የማይታለፍ ነው:: ለክዳን የሚሆነውን ስርሰራ ሳርም ሆነ ዘባ ሳር፣ ለደጋ ቤት ክዳን የሚሆን የገብስና የመስኖ ብዕርን በማጨድና በመንቀል ማሰባሰብ ይገባል:: ሀረግ መዝዞ፣ ቱቻ ፈትሎ፣ ጎድር ጎንጉኖ፣ ከቀርቀሃ ወችን ጠምዞ ማሰባሰብ ሌላው ነው::

በዚህ ላይ ጥሬ ቁሶችን ለመሰብሰብ በቤተሰሪው ግለሰብ ብቻ የሚጠቃለል አይሆንም:: እንጨቱንም ሆነ ሳሩን ከቆረጠበትና ካጨደበት ቦታ የሚያሸካክመው የአካባቢውን ሰው በማስተባበር እንዲያግዙት ያደርጋል:: አልያ ግን በአንድ ትክሻ የማይታሰብ ነው:: ወይም በገበያ ቀን መንገድ ዳር በማቅረብ አልያም ቤተክርስቲያን ለመሳላም ሰብሰብ ተብሎ በሚዜድበት ቀን ቁሳቁሶችን ማሸከምና ማስመጣት የተለመደ ነበር::

ድግስ:- ባህላዊ ቤቶችን ለመስራት መስራያ ጥሬ ቁሶችን ከመሰብሰብ ጎን ለጎን የቤቱ ባለቤት ሚስት በተራዋ ለድግስ ትዘጋጃለች:: እናም የእንጨቱንና የሳሩን ተጠናቆ መሰብሰብ ስታረጋግጥ አስቀድማ የተዘጋጀችበትን ድግስ ታሰነዳዳለች:: ይኸውም አስቀድማ ከጎረቤቶቿ ጋር በመተባበር ጤፉንም ሆነ ገብሱን ትፈጫለች:: ደረቆቱን ትቆላለች፣ የጠላ ድፍድፉንም ትደፈድፋለች::ከዚያም እንጀራው ይጋገራል፣ ወጡም ይሰራል:: ጠላውም በጋን ይሞላል:: የተሞላው ጠላ በተለያዩ እንስራዎች እየተጠለለ ይቀመጣል:: የድግሱ መጠን እንደቤቱ ትልቅነትና ትንሽነት ይወሰናል:: ምክንያቱም የቤቶቹ መጠን ለስራ የሚሰባሰበውን ሰው

ብዛት ያመለክታልና:: ሆኖም ይህስም ይብዛ ጠላ፣ እንጀራና ወጥ የማይታለፍ የቤት ማሰሪያ ድግሶች ናቸው:: ከዚህ አኳያ ድግሱን የማዘጋጀት ስራ የሴቷ ሲሆን ቤቱን የመስራት ተግባር ደግሞ ለወንዱ ነው::

ቁሶችን ለግንባታ ማመቻቸትና ቦታ መረጣ:- ከላይ በተገለፀው የአሰራር ሂደት ላይ መስሪያ ጥሬ ቁሶችን መሰብሰብና መደገስ ተብሏል:: እናም የድግሱን መዘጋጀት ተከትሎ ለግድግዳ የሚሆነውን በአንድ ጎን ፣ ለምሰሶና ለወጋግራ ደግሞ በሌላ ጎን፣ እንዲሁም ለማዋቀሪያና ለማገር የሚሆነውን እንዲሁ ለግንባታ በሚመች መልኩ ማስቀመጥ ይገባል:: ለማገር ማሰሪያ የተሰባሰበውን ሀረግ ማድረቅና ውሃ በመንከር ማለዘብ ያስፈልጋል:: የሚጠራረበው ተጠርቦ፣ የሚቃጠጠው ተቃጥ ይዘጋጃል:: ሁሉም መስሪያ ጥሬ ቁሶች መልክ መልካቸውን ይዘው ይሰናዳሉ::

የቁሶችን ለግንባታ መመቻቸት በማጤን ቤቱ የሚሰራበትን ቦታ መረጣ ይካሄዳል:: ባለቤቱ አስቀድሞ እዚህ ላይ ብስራ ብሎ ያሰበው ስለሚሆን ከጎረቤቶቹ ጋር ሆኖ ረግረጋማ ያልሆነና የምስጥ ኩይሳ የማይወጣበትን ቦታ ተወያይተው ይመርጣሉ:: ቤቱ የሚሰራበት አዲስ ቦታም የሰላም፣ የጤናና የሃብት እንዲሆንለት በውስጡ ይፀልያል::
ግድግዳ ማቆምና መማገር:- የቤቱን መስሪያ ቦታ ከመረጠ በኋላ ግድግዳ የሚቆምበትን ጉድጓድ ለመቆፈር ይጀምራል:: በዚህን ዕለት የሰፈሩ ሰው በሙሉ ወንዱ ማለት ነው ይሰባሰባል:: ከዚያም ግድግዳው የሚቆምበትን ጉድጓድ ለመቆፈር መካከል ላይ እንጨት ይተከላል:: ልክ ምሰሶው በሚቆምበት ማለት ነው:: ከዚያም እንደቤቱ መጠን በክንድ ይለካና ከችካሉ ወደ ግድግዳው 11 ክንድ ወይም 4 ክንድ ይለካና ዙሪያውን በክብ መልክ ይቆፈራል::

ግድግዳው የሚቆምበት መሬት ወደታች አንድ ክንድ ከተቆፈረና አፈሩ ከወጣ በኋላ ወዲያውኑ የተዘጋጀውን ግድግዳ ዙሪያውን ማቆምና በማገር ማሰር ነው:: የግድግዳው ማገር ከድምድማቱ ጋር ወደ አራት ዙር እንደሚሆን ከላይ ተጠቁሟል:: ግድግዳው ተቆመና እስከ ድምድማቱ ተማግሮ ካለቀ በኋላ ቀጣዩ ስራ ምሰሶና ወጋግራ ማቆምና ጣሪያ ማዋቀር ነው::

ምሰሶና ወጋግራ ማቆምና ጣሪያ ማዋቀር፦ በዚህ የስራ ሂደት ከቤቱ መካከል በተተከለው ችካል ላይ ሁለት ክንድ ወደታች በመቆፈር ምሰሰውን ማቆም ነው:: ምሰሶው ከቆመ በኋላ አዳራሽ ቤት ከሆነ ወጋግራዎች ከምስሰው ራቅ ብለው ዙሪያውን ይተከላሉ:: ወጋግራዎቹ ድምድም መሸከም የሚያስችል ባላ ይኖራቸዋል:: በዚህ መካከል ከወጋግራዎች ላይ ዙሪያውን የሚደረግ ድምድማት ከቀጫጭን እንጨት ወፈር ተደርጎ ይሰራል:: ይህ የተሰራ ድምድም በክብ ቅርፅ ተጠቅሎ ወጋግራዎች ላይ በሚደረግ መልክ ይዘጋጃል::

ምሰሶው በትክክል መቆሙንና ወጋግራዎችም ቦታቸውን ይዘው መጥበቅ እስከሚችሉበት ድረስ በአፈርና በኮረት ድንጋይ መጠቅጠቃቸውን ማረጋገጥ ነው:: ከዚያም ለቤት ስራ የተሰባሰበው ሰው ዙሪያውን በመቆም በአቋም መቆፈሪያ እንጨት ድምድማቱን በማንሳት ከወጋግራዎቹ ላይ ያስቀምጠዋል:: በተለይ ድምድማቱን አንስቶ ወጋግራዎች ላይ ለማስቀመጥ የሚደረገው የህብረት ስራ እጅግ እንደሚማረክ መረጃ አቀባዮች ነግረውኛል:: መተባበር መቻል የተፈለገ ግብን ለመምታት ወሳኝ እንደሆነ ነው::

የምሰሶውንና የወጋግራዎችን በትክክል መቆምና የቤቱን ውቅር መልካምነት የሚያረጋግጥ ከዚያው ከሰሪዎቹ መካከል በብልህነቱ የሚታወቅ ሰው ይኖራል:: እናም በብልሁ ሰው እየተመሩ ውቅሩን በትክክለኛው እቅጣጫ ያዋቅሩታል:: ከተዋቀረ በኋላ ደራስ እንጨቶችን ወይም ቀርቀሃውን ምሰሶው ላይ ከሚቀመጠው ገበታ ጋር በመሮ ተበስቶ በቱቻ ወይም በካስማ በማያያዝ ከላይ ወደታች በደራሶቹ መካከል ሳጋዎችን እየሳጉ ጣሪያውን መማገር ነው:: ጣሪያው ተማግሮ ካለቀ አስቸጋሪው የቤት ስራ አብላጫውን እንደተጠናቀቀ ይቆጠራል::

እናም ጣሪያው ተሰርቶ በተጠናቀቀበት ቀን የቤት ስራው ድግስ የሚበለበት፣ ጎረቤትም ድግስ የሚያመጣበት፣ ቤቱም የሲሳይና የጤና እንዲሆን በሽማግሌዎች የሚመረቅበት ነው:: ይህ ቀን የፉከራ፣ የቀረርቶ፣ የዘፈንና የደስታ ምሽት ይሆናል:: ቀረርቶው፣ ፉከራውና ዘፈኑ ከተጠናቀቀ በኋላ ምግብ ይበላና ሽማግሌዎቹ ለምረቃ ይነሳሉ:: በምረቃ ወቅት ወጣቱ ሁሉ በመቆም የሚከታታል ሲሆን፣ ምንም እንኳን ማሳረጊያው ካህን ቢሆንም በዕድሜ ደረጃ መራቂዎች ይመርቃሉ::

ምረቃው "ተው ደህና ያዋለን በደህና ያሳድረን:: ምህረቱንና በጎነትን ያውርድልን:: ሀገራችንን ሰላም ያድርግልን ጎጣችንን ይባርክልን:: እንደምታዩት ይሄን የመሰለ ቤት ተሰርቷል:: ቤቱን የሰላምና የጤና ያድርግልን:: በመደቡ ልጅ፣ በጋጡ ከብት ይሙላበት:: የሲሳይ ቤት ይሁን:: ይሄን ከሰራሁ ሀብት አገኘሁ ጤና አገኘሁ ለማለት ያብቃችሁ" እየተባለ ሲደረደር ተቀባዩ በሙሉ "አሜን! ያድርግልን" ይላል:: እናም በዚህ መልክ ሁሉም መልካም ምኞቱን ለባለቤቶቹ ከገለፀ በኋላ ይሰነባበታል:: ቀሪውን ስራ ለቤተሰብና ለቅርብ ጎረቤት በመተው::

ጣሪያን ሳር ወይም የገብስና የመስኖ ብዕር መክደን:- የባህላዊ ቤትን ጣሪያ ለመክደን በአካባቢው የታወቀ ባለሞያ ይኖራል:: ይህ ባለሞያ በኑሮው ያን ያክል ያልሆነ መሬቱን የሚያርስበት በሬ የሌለው ደሀ አንደሆነ አቶ ዳኛው ወርቅነህ /28-08-2002/ ነግረውኛል:: እናም በገንዘብ ወይም በበሬ ጉልበት የቤቱን ጣሪያ ይከድናል:: በሙያውም በአካባቢው የተመሰከረለት መሆን አለበት:: ጣሪያ የመክደኑ ስራ አዳራሽ ከሆነ ስለሚያስቸግር ሁለት ሶስት ከዳኞች በአንድ ጊዜ ይከድናሉ:: ለክዳን የሚሆነው ሰንበሌጥና ዘባ ሳር እንዲሁም የገብስና የመስኖ ብዕር እንደሆነ አስቀድሞ ለመጠቆም ተሞክሯል::

ግድግዳ መምረግና ውስጡን መከፋፈል:- ግድግዳ መረጋው ጣሪያ ከመክደን በኋላ የሚመጣው በጣሪያው አለመከደን የተነሳ የተመረገውን ጭቃ ፀሐይና ውርጭ እንዳይሰነጥቀው ነው:: ስለሆነም ግድግዳ ለመምረግ የሰፈሩ ሴት ውሃ ከወንዝ ሲያመጣ፣ ወንዱ አፈር በመቆፈርና ጭቃውን ለማቡካት ይሰለፋል:: ለምርግ የሚሆነው ጭቃ በጭድ፣ በገብስ ገለባና በአተር ገለባ በደንብ ከተቦካ በኋላ ወዲያውኑ መምረግ ነው:: አውሎ አሳድሮ መምረግ እንደሚቻልም ይታወቃል::

የግድግዳውን መመረግ ተከትሎ የከብቶች ጋጥ፣ የበጎች ጓዳ /ጉርና/፣ የመኝታ ቆጥና አልጋ፣ መደቡ፣ ምድጃው፣ ማጀቱና የመሳሰለው ሁሉ ይከፋፈላል:: መከታ ለሚያስፈልገው መከታ ይሰራለታል:: ከዚህ በኋላ ቤት ማስዋብ ይከተላል::

ቤት ማስዋብ:- ውስጠኛው የቤት ክፍል በመልክ በመልኩ ይዋባል:: የምድጃው ቀርጽ፣ የመደቡ አመዳደብ፣ የአልጋና የቆጡ ዝግጅት በተገቢው መንገድ ይደራጃል:: ምሰሶውና

መከታው ላይ ጌጠኛ የእቃ ማስቀመጫ ጭጉቶች ከጭቃ ይሰራሉ:: ወለሉ ይደለደልና በጭቃ ይመታል:: ከዚያም በከብቶች እበት ይለቀለቃል:: የቤቱ መግቢያ በር ውጭኛው ይመረግና በአመድ ወይም በነጭ አፈር ይለቀለቃል:: የሰውን ቀልብ በሚሰብ መልኩ ከተዋበ በኋላ ለመግባት ዝግጅት ይደረጋል::

ቤት ማሰናዳትና መግባት:- ይህ የባህላዊ ቤት አሰራር የመጨረሻው ሂደት ነው:: የከብቶችን ጋጣ በጠፍጣፋ ድንጋይ መደለህ፣ የአህል ጎታዎችን ወደማጀት ማስገባት፣ የቤት መገልገያ ቁሳቁሶችን ቦታ ቦታቸውን የማስያዝ ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ መግባት ነው:: የዓመታት ድካም እረፍት ይደረጋል::

በአጠቃላይ በደጋ ዳሞት ወረዳ ባህላዊ ቤትን ለመስራት ለዓመታት ማሰብን እንደሚጠይቅ ቢታወቅም እንደመረጃ አቀባዮች ከሆነ የቤቶቹ መስሪያ ጥሬ ቁሶችን ከመሰብሰብ ጀምሮ ቤቱ ተሰናድቶ እስከሚገባበት ቀን ድረስ ወደዘጠኝ የስራ ሂደቶችን ማለፍ የግድ እንደሆነ ነው:: እንዲህ እንደአሁኑ የባህር ዛፍ ግድግዳንና ማገርን እንዲሁም አውራጅን ካንድ ቦታ ማሰባሰብና በአንድ ቀን የሚሰብሰ ዘመናዊ ቆርቆሮን መጠቀም በማይቻልበት ዘመን ውጣ ውረዱ አስቸጋሪ ቢሆንም ባህላዊ የስራ ተስተላልፎው ልዩ ትውስታን ይፈጥር እንደነበር መገንዘብ አያዳግትም::

4.1.3. ባህላዊ ቤቶቹ በመጥፋት ላይ ለመሆናቸው ተፅዕኖ ፈጣሪዎች

ለውጥ የማይነካው የተፈጥሮ ክስተትም ይሁን ሰው ሰራሽ ቁስ በአለም ላይ ሊኖር እንደማይችል በትወራዊ ዳራው ላይ አስቀድሞ ለመጠቆም ተሞክሯል:: እናም ለውጥ በባህላዊ የምህንድስና ጥበብ የተሰሩ ባህላዊ ቤቶችን እየለወጠ መሄዱ አልቀረም:: ሮበርት ውስጥ ዶርሰን (1972፣281) ሀገረሰባዊ ምህንድስናው እየደበዘዘም ሆነ እየተለወጠ መሄድ የጀመረው ከ20ኛ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደሆነ አስገንዝበዋል:: በዚህ ላይም የአሰራር ጥበቡን ጨምሮ እንደሚነካ ጠቁመዋል::

በደጋ ዳሞት ወረዳዋ ደጋማ ክፍል /ሻንጊ ደረቁ፣ ዝቋላ ወገም፣ ድኩልካና፣ አቅላት ወይበኝ፣ ገሳግስ ሸምብርማ ቀበሌዎች/፣ በወይና ደጋማው /ፈንካቲት ገንዳውሃ፣ አረፋ ማሲካና፣ ልጆንጉስ፣ ከፊል ብሀንዴ ጭዋኔ ቀበሌዎች/፣ በቆላማው ደግሞ /ከፊል ብሀንዴ

ጭማኔ፣ ከፊል አረፍ መድሃኒያለም፣ ጌንስ ተክለሃይማኖት ቀበሌዎች/ በመዘዋወር ባደረኩት ምልከታ ባህላዊ ቤቶቹ በመጥፋት ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ ችያለሁ። ከዚህ ምን መገንዘብ ይቻላል? ባህላዊ ቤቶቹ አሻራቸው በፎቶ እንኳን ሳይቀረስ ተረት መሰል አሰራራቸውን ለአሁኑም ሆነ ለወደፊቱ ትውልድ ልናወርስ መሆኑ ነው። ለዚህ ተጽእኖ ፈጣሪዎች በርካታ ናቸው። ለአብነት ግን የደን መጨፍጨፍ፣ ዘመናዊ ኢንዱስትሪ የፈጠራቸው ቆርቆሮና ምስማር መመረት፣ የእሳት አደጋ መበራከት፣ ሀገር በቀል ያልሆነው ባህር ዛፍ በየግለሰቦች ጓሮ መተከል ተጠቃሽ ናቸው።

የሳር ቤት እንደድሮው ይሰራል? ይገኛል? በማለት የጠየቋቸው አቶ ዳኛው ወርቅነህ /28-08-2002/ እንዲህ ነበር ያሉኝ:-

> *አይ አሁን ቀንሷል። ምንድነው ቆርቆሮ ሰለመጣ እየቀረ ነው። ትልቅ ቤት /አዳራሽ/ እንዲያውም ቀርቷል አሁን። አሁን በገጠር አልፎ አልፎ መለስተኛና ጎጆ ቤቶች አሉ። እንጂ ሌላው ቀርቷል። ደርብም የሚራ የሰም። በጭቃ ጡብና በእንጨት የሚሠራ ቀረ እንጅ ይሄ በሰሚንቶ፣ በብረት፣ በባህር ዛፍ እንጨት የሚሰራ አለ። ሳር ቤት አብራኛ ነው። መቀት ይከላከላል፣ ቅዝቃዜም ይከላከላል። ሰንት ነገር ይከላከል ነበር። አሁን ዘመኑ ሰውም እሳት ነው። በዚህ ምክንያት አሁን ቀርቷል። እንጅ ሳርቤት እሚቀር አልነበረም።*

ከመረጃ አቀባዬ ንግግር የቆርቆሮ መምጣት፣ የብረታብረትና የሲሚንቶ መመረት፣ እስከፊው የእሳት ቃጠሎ በፈጠሩት ጫና ባህላዊ ቤቶች እየጠፉ ያሉበትና እንዳንዶቹም ሙሉ አሻራቸውን ማግኘት እንዳልተቻለ ነው። የአቶ ዳኛው ወርቅነህን ሀሳብ አቶ ይታይህ አላምንህ፣ አቡሃይ ጥሩነህ መርሻና ቄስ አጥናፉ ለማ እንደሚጋሩት በቃለምልልሳችን ወቅት አረጋግጠውልኛል።

ለግድግዳ፣ ለወጋግራ፣ ለምሰሶና ለክዳን የሚሆኑ እንጨቶችና ሳር የሉም ብለውኛል። "አልፎ አልፎ በየቤተክርስቲያኑ ይሄ ጥዱ ወይራው አለ እንጂ ጫካው ጠፍቷል። አሁን ሰንበሌጥ ሳር የለም። አሁን ይሄ ምስማር የተካቸው ለመማገሪያነት የሚያገለግሉት የጎድርና የቱቻ ሳሮች ጠፍተዋል። ሀረጉም ከጫካው ጋር አብሮ ወድሟል። አሁን በርሃ እየሆነ" ነው በማለት ነግረውኛል።

ከመረጃዎች በመነሳት ሀገር በቀል ዛፎችን ባህር ዛፍ ስለተካቸው ለግድግዳም ለምሰሶም ለማገርም በብቸኝነት ግልጋሎት ላይ ይውላል:: ምንም እንኳን በከተሞች እሱም እየቀረ መሆኑ ቢስተዋልም:: ሌላው የሳርና የገብስ ብዕር ክዳን በቆርቆሮ ተቀይሯል:: ማገር ለማሰሪያ ይውሉ የነበሩት ሀረግ፣ ቱቻ፣ ጎድርና ወች በምስማር ተለውጠዋል:: ለውጡ ጥሬ ቁሶችን ብቻ ሳይሆን የአሰራር ጥበባቸውንም ጨምሮ እየነካቸው መሆኑን ሮበርት እና መሰል ምሁራን ንድፍ ሀሳበቸውን እንዳጋሩን ከላይ ተጠቅሷል::

ግድግዳቸው ክብ፣ ጣሪያቸው ሾጣጣ የነበሩና ውስጣዊ አከፋፈላቸው ሁሉ በተለየ ቀያዊ እውቀት ወይም በራሳቸው ፈቃድ የተማሩ ባህላዊ ባለሞያዎችና ብልህ ሰዎች የተሰሩት ቤቶች እየጠፉ መሆናቸውን ማሳወቅ ይቻላል:: ክብና ሾጣጣ ቅርፅ ቤቶች በአውሮፓ ሰራሽ ሞዴሎች ተቀይረዋል:: ማጀት የሚሉት የለም:: አሁን እቃ ቤት እንጅ ማጀት ቀርቷል:: የሴቷ ጥገኝነት መጠየቂያ ወይም ዋስትና የነበረው ማጀት ቀርቶ በእቃ ቤት ተቀይሯል:: እቃ ቤት ደግሞ ወንድም ይገባል:: ማጀት የተደፈረበት ወቅት መሆኑንም ለመጠቆም ይፈለጋል::

በአጠቃላይ በወረዳዋ ይሰሩ የነበሩ ባህላዊ ቤቶች በደን መጨፍጨፍና በበረሃማነት መስፋፋት የተነሳ የመስሪያ ጥሬ ቁሶች አቅርቦት መቀነስ፣ እንዲሁም የኢንዱስትሪ አብዮት መከሰት የቆርቆሮ ምርት፣ ምስማርና ብረታ ብረት በገፍ መቅረብ በፈጠሯቸው ተፅዕኖዎች የተነሳ እየቀነሱ መሄዳቸውን መረጃዎች ጠቁመዋል:: ከተለያዩ ሀገራት ሮበርት ውስጥ ዶርሰን (1972:282) እንዳሉት የተለያዩ የህንጻ ፕላኖች በህዝባዊ ጋዜጦች፣ በንግድ አህዝቦቶችና በመንግስታዊ ኤጀንሲዎች አማካይነት መሰራጨት የተነሳ ሀገር በቀል የአሰራር ቅርፃቸውም እየተለወጡ ሂደዋል::

4.1.4. የደጋ ዳሞት ወረዳ ባህላዊ ቤት ሰሪዎችና ማህበራዊ ደረጃ

በወረዳዋ ሁሉም ቀሌያት ባህላዊ ቤትን ለመስራት ከቤት ከደናና ውቅርን ከማዋቀር አኳያ የተለየ ሙያን የሚጠይቅ ካልሆነ በስተቀር በቤተ ሰሪው መካከል የሙያ ልዩነት የለም:: በተለይ የቤት ግድግዳን ለማቆምና ለመማገር በወንፈል ወይም በማህበር ነው:: የሁሉም ሰው ሙያ ያርፍበታል:: ሆኖም ጣሪያውን ሳር ለመክደንም ሆነ ውቅር ለማዋቀር የተለየ

ብልሃተኛ ሰው ያስፈልጋል:: አቶ ዳኛው ወርቅነህ /28-08-2002/ "ውቅር የሚባል አለ:: ከምሰሰው ጋር የሚዋቀር:: ድህና ቁም መሆኑን ለይቶ የሚነግር ብልሃተኛ ሰው አለ:: አያ ገሌ ነው የሚያዋቅር እሱ ይሻላል ይባልና ተለምኖ ይመጣል:: ክፍያ ግን አይከፈለወም:: በነፃ ነው:: እናም ዝም ብሎ አይዋቀረም ብልሃተኛ ሰው አለ" ብለዋል::

በሌላ በኩል አቶ ይታይህ አላምንህ /03-09-2002/ "ጣሪያውን የሚከድነው ሰውየ ባለሞያ ነው:: በተፈጥሮ የለመደው እንጅ ያልተማረ ነው:: ይህ ሰው ደሃ ነው:: ደሃ ስለሆነም ገንዘብ ወይም ለእርሻ በሬ ልትሰጠው ትችላለህ" ብለውኛል:: የባህላዊ ቤት ሰሪዎችን ማህበራዊ ደረጃ በምናይበት ጊዜ ክዳን ከሚከድነው ባለሞያ በስተቀር በዝቅተኛነት የሚታይ የለም::ውቅሩን በማዋቀር ብልሃቱ የሚፈለገው ሰው እንደዚህ ነው ተብሎ አይሰየምም:: ለዚያም ነው ያለምንም ክፍያ በነፃ የውቅርን ብልሃት የሚያማክረው:: እንዲያውም በብልሃቱ ተመራጭ ሰው ነው:: ጣሪያን በክፍክፍ የሚከደነው ሰው ግን በድህነቱ የታወቀ ነው:: እንደ እጀ ሰሪዎች የሚዋረድ ባይሆንም በኑሮ ደረጃው ግን ዝቅተኛ ግምት የሚሰጠው ነው:: ድሃ ተብሎም ጉልበቱን ለገንዘብና ለእርሻ በሬ እየሸጠ ይጠቀም እንደነበር መረጃ ሰጭዎቼ ነግረውኛል:: ደሃ በመሆኑም ማህበራዊ ደረጃው ዝቅተኛ ነው::

በአጠቃለይ ባህላዊ ቤትን በአንድ ላይ ተሰባስቦ መስራት፣ መደገስና መጫዎት የወረዳዋን ህዝብ የእርስ በርስ ግንኙነት ከማጠንከሩም በላይ ከቤቱ ቁስ ጋር የተለየ የጋራ የሆነ ትስስርን ይፈጥራል:: ቤት በራሱ የኑሮ ተምሳሌት ነው:: ቤቴ ማለት ህይወቴ፣ ኑሮዬና ትዳሬ እንደማለት ነው:: እናም ባህላዊ ቤት መስራት የወረዳዋ ህዝብ ማህበራዊ የትስስር መገለጫ ነበር ማለት ይቻላል::

4.2. በመጥፋት ላይ ያሉ የእጅ ስራ ቁሶች

የእጅ ስራ ቁሶች ብራውሴር በድረገፃቸው እንዳሉት በዘመናዊ ማሽን ሳይሆን በእጅ ብቻ የሚሰሩ ለየቀን ተግባር የሚውሉ ናቸው:: ባህላዊ ፍላጎትን ባገናዘበ መልኩ እንደሚሰሩም ፕሮን (2009:2) ጠቅሰዋል:: የእጅ ስራ ቁሶቹ በሀገራችን መሰራት የጀመሩት ከታሪክ ውልደት ጀምሮ እንደነበር ፓንክረስት ገልፀዋል::

በዚህ ርዕስ ስር ባህልን መሰረት ተደርገው ለየቀን ተግበር መገልገያ ይሆኑ ዘንድ በአካባቢው ሙያ የተሰሩ የእጅ ስራ ቁሶች በየምድባቸው በመመደብ መግለፅና መተንተን

ይሆናል:: ገለፃው ከምን እንደተሰሩና፣ እንዴት እንደሚሰሩ እንዲሁም አገልግሎታቸውን የሚመለከት ነው:: በሌላ በኩል ትንተናው የተመረጡ የእጅ ስራ ቁሶችን ስነቃላዊ ግጥሞችን በመጠቀም ባህላዊ፣ ማህበራዊና ታሪካዊ ጠቋሚነታቸውን ወይም 2.2.3. ላይ በተጠቀሱት የመተንተኛ ሞዴሎች አንፃር ትኩረት ያደርጋል::

የእጅ ስራ ቁሶችን የመመደቢያ መስፈርቶች ማርቼስ (1984) ፕሮን (2009) እና ግላሲ (1991) ተግባር፣ ከባቢያዊ ስያሜ፣ ቅርፅ፣ መለያ ፀባይ፣ ባህልና ታሪካዊ ጠቀሜታ እንደሆኑ ጠቁመዋል:: ለዚህ ጥናት ለመመደቢያ መስፈርትነት የወሰድኩት ማርቼስ ውስጠ ማዮ (1984:15) ግለሰባዊ ብልሃንተን ነው:: ስለሆነም መስሪያ ጥሬ ቁሳቸውን ተጠቅሜ ከድንጋይ፣ ከቆዳና ከሳር በማለት ልመድባቸው ችያለሁ::

ከድንጋይ /የቤትና የውሃ ወፍጮ/፣ ከቆዳ/አንቀልባ፣ ኸርንዲ፣ መጫኛ፣ አቁማዳ፣ ላመነት፣ ጠፍር፣ መርገጭ፣ ማንጠቢያ፣ ለምድ፣ ደበሎ፣ ምናር፣/፣ ከሳር /ዳውጃ፣ የሸቆጥላና ገሳ/ በማለት:: እንዲሁም የስፌት ቁሶቹ ምንም እንኳ መስሪያ ጥሬ ቁሳቸው ከሳር ቢሆንም አገልግሎታቸው የተለያየ በመሆኑ የተጠቃለለ ስያሜ መስጠት ስላልተቻለ ማርቼስ (1984) የአሰራር ብልሃት አንዱ የመመደቢያ መስፈርት ነው ባሉት መሰረት በአሰፋፍ ብልሃታቸው የስፌት እቃዎች በማለት መመደብ ችያለሁ::የስፌት እቃዎቹ/ሞሰበ ወርቅ፣ሞሰብ፣ቀለምሻሽ፣ወራንታ፣ላዳን፣ቁና፣ወስከምቢያ፣አገልግል፣ወንፊትና ሰፌድ/ናቸው::

እነዚህ የእጅ ስራ ቁሶች በዚህ መልክ ተመርጠው የቀረቡት በወረዳዋ ውስጥ ካሉት ቁሶች ውስጥ ይበልጥ የመጥፋት አደጋ ያጠላባቸው በመሆናቸው ነው:: በመጥፋት ላይ መሆናቸውንም በቃል አቀባዮችና በምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል:: እናም የእጅ ስራ ሰሪዎችን ማህበራዊ ደረጃ ከመተንተንም ባሻገር በመጥፋት ላይ ለመሆናቸው ተፅዕኖ ፈጣሪዎችንና የመታደጊያ ስልቶችንም ለመዳሰስ ይሞክራል::

4.2.1. የድንጋይ ወፍጮዎች

በዚህ ርዕስ ስር የድንጋይ ወፍጮዎቹ ከየት እንደሚገኙ፣ እንዴት እንደሚሰሩ፣ አገልግሎታቸው ምን እንደሆነ ለማሳየት የሚቻልበት ነው:: በተለይ የውሃ ወፍጮን

በተመለተከተ በአካባቢያዊ የእውቀት ስርዓት ለመሰራቱ መረጃ በማሰባሰብ ሂደት የተለያዩ አስተያየቶች አጋጥመውኛል:: እነዚህን አስተያየቶች በማረቅ የጥናቱ አንድ የዕይታ የጉዳይ ላደርገው ችያለሁ::

ይኸውም የውሃ ወፍጮ ተከላ ሙያን ተሞክሮ ከየት አገኛችሁት ብዬ ስጠይቃቸው መምህር እንዳሻው ቻሌ እምሩ /02-07-2002/ አቶ አስናቀ ይሁኔ አላምንህ /03-07-2002/ "በዚያን ወቅት ፍኖተ ሰላም አካባቢ ላህ ከሚባል ወንዝ ላይ አንድ አረብ ተክሎ ነበር:: እናም ከዚያ አረብ ሰውየ ተሞክሮውን እንዳገኙ ሲያወሩ ሰምተናል" የሚል ምላሽ ሰጥተውኛል:: በሌላ በኩልም አቶ ዳኛው ወርቅነህ ባይነስ /28-08-2002/ የእነ መምህር እንዳሻውን ሀሰብ በመጋራት ከሌላ ሀገር ተሞክሮ መገኘቱን አውርተውኛል::

ሆኖም አቡነ እዝራ የደቂቀ እስጢፋኖስ መምህር የሆኑት ኢትዮጵያዊ በአባታቸው ደቂቀ እስጢፋኖስ የእምነት ሁኔታ በህዝቡ ዘንድ አመኔታ አጥተው እየተከሰሱ ከንጉሱ ዘንድ ይቀርቡ በነበረበት ጊዜ ስለተግባር ዕድ ችሎታ እንዳለቸው ተጠይቀው "የማውቀውን ጥቂቱን ስለ አህያ /የደንጋይ/ ወፍጮ፣ ስለውሃ ወፍጮ፣ ስለነፋስ ወፍጮ..." /ጌታቸው ኃይሌ 1996:3001/ እያሉ መናገራቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረ መሆኑን ፍንጭ የሚሰጥ ይመስላል::

አቡነ እዝራ ስለአህያ ወፍጮ በተግባር ሰርተው ካሳዮ በኋላ ንጉሱ "ከሮም፣ ከህንድ፣ ከግበፅ፣ ከቱርክ፣ ከፈረንሳይ፣ ከፋርስ፣ ከሊባኖስ፣ ከየሀገሮቹ ሁሉም መጥተዋል:: አንዱም አንተ እንደሰራኸው የሰራልን የለም::" /1996:304/ በማለት መናገራቸውን የጽሁፍ ታሪክ ያስረዳል:: እናም የውሃ ወፍጮ በዚያን ዘመን በኢትዮጵያ መሠራቱና ከተጠቀሱት ሀገራትም የሚያውቅ አንድም ግለሰብ አለመኖሩ ሀገራዊ የስራ ፈጠራ ለመሆኑ ማስረጃ ይመስለኛል:: የሆነ ሆኖ የውሃ ወፍጮን የመትከል ሙያ የኢትዮጵያም ሆነ የሌላ ሀገር ለጥናቱ እካል ማድረግ ችያለሁ::

.የቤት ወፍጮ

የቤት ወፍጮ በወረዳዋ ላለውና ለነበረው ማህበረሰብ ጥንታዊ ቁስ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ:: ታሪካዊ አመጣጡ ከዚህን ዘመን ጀምሮ ነው የሚል ወሰን የለውም:: "እንዲሁ ነው እኛም ስናውቅ የጥንት ነው:: ከአያት ከቅድመ አያት የቆየ ነው:: አመጣጡን በትክክል

አላውቀውም:: ብቻ የጥንት እንደነበር ነው ሲነገር የሰማሁት" ብለውኛል የ63 ዓመት የዕድሜ ባለፀጋው አቶ ይታየህ አላምንህ /19-07-2002/ በእሳቸው አባባል ሌሎች በርካታ አቀባዮችም ይስማማሉ::

የቤት ወፍጮ በወረዳዋ ቆላማ አካባቢ ይገኛል:: በተለይ በብሀንዴ ጭዋና ቀበሌ ልዩ ስሟ ገንቢች በምትባል ጎጥ ነው:: ከዚህ በተጨማሪም በአረፋ መድሃኒያለም ሽሜ አካባቢ በግንባራ ወንዝ ደገታማ ቦታዎች አንደሚገኝም ከመረጃ አቀባዮች ንግግር ለመረዳት ችያለሁ:: የደጋማና የወይና ደጋማ ቀበሌያት ነዋሪዎች አብዛኛውን ጊዜ በነዚህ አካባቢዎች ያሉት ሰዎች የሚያወጡትን ወፍጮ እየገዙ ይወስዳሉ::


አቶ እንየው አንለይ በብሀንዴ ጭዋኔ ገንቢች የተወለዱና ያደጉ ናቸው:: አሁን የ69 ዓመት አዛውንት ናቸው:: ከግብርና በተጓዳኝ ወፍጮ በማውጣት ስራ ላይ የተሰማሩ ነበሩ:: "የድንጋይ ወፍጮን ማውጣትና አስተካክሎ ለመፍጨት በሚያስችል መልኩ ለመስራት ከዚያው አካባቢ ከነበሩት አባቶቼ ነው የለመድኩት:: ወፍጮውን እያወጣን እናስቀምጠዋለን:: ከዚያ ይዤ ወፍጮ የሌለበት አካባቢ ሰው እየመጣ ይገዛናል:: በተለይ ከደጋው ገሸት ስላሴ፣ ሻንጊ ደረቄ፣ ፈንካቲት ገንዳውሃ እና ሌሎች ቀበሌዎች ይመጣሉ:: እንዲያውም ስንቅ ይዘው ተሸኝተው አድረው እየገዙ ይወሰዱ ነበር" ብለውኛል:: /07-07-2002/


የቤት ወፍጮን ከመሬት ውስጥ ቆፍሮ ለማውጣት የሚጠቀሙበት መሳሪያ ኪት[9] ማረሻ ነበር:: ተቆፍሮ የወጣውን የቤት ወፍጮ አይን መኖሩንና አለመኖሩን ለማወቅ በመዶሻ ፈልጦ ማረጋገጥ ነው:: ምክንያቱም ወፍጮው በራሱ ባለአይናማ ድንጋይ ነውና:: ልሙጥ ደንጋይ ከሆነ አላስፈላጊ ነውና ይተዋል::

የቤት ወፍጮ አገልግሎቱ መፍጨት ቢሆንም እንደ እህሉ አይነት በሁለት ይከፈላል:: እነሱም አይናማና ጥቃቅን አይኖች ያላቸው ናቸው:: የጤፍና የጥራጥሬ በመባልም ይታወቃሉ:: የጤፍ አይነቱ ወፍጮ አይኑ ድቅቅ /ሸክክ/ ያለ ሲሆን፣ የጥራጥሬው ደግሞ አይኑ ቦግ ቦግ ያለ ነው:: የሚለያዩት በአይናቸው ነው:: አወጣጣቸው ያው ነው:: የሚገኙበት ቦታም ይለያያል:: "የጤፉን ጀርም ከሚባል አካባቢ ስናወጣው፣ የጥራጥሬውን

[9] ኪት ማለት በአካባቢው አባባል ለብዙ አመታት አርሰውበት በማለቅ ላይ ያለ ግን ለእርሻ የማይጠቀሙበትን ማረሻ ነው /አቶ እንየው አንለይ፣ 07-07-2002/

ደግሞ ጉማራ ከሚባል ወንዝ ዳገታማ ቦታ ነው::" በማለት አጫውተውኛል አቶ ተፈራ ሽታ ዋሴ የ65 ዓመቱ የቀየዋ ተወላጅ /06-07-2002/





ፎቶ 4 የጥራጥሬ ወፍጮ ፎቶ 5 የጤፍ ወፍጮ

በሌላ በኩል የገብሱና የጥራጥሬው ወፍጮ በመጠን ይለያያሉ:: የጥራጥሬው ከበድ ያለና ትልቅ ሲሆን፣ የጤፍ ግን ቀላልና መለስ ያለ ነው:: በተፈጥሮው የጤፉ ደንጋይ ክብደቱ ቀላል ነው:: ወፍጮዎቹ እናትና ልጅ ናቸው:: እናቱ ከስር የሚሆን ልጁ ግን ከላይ ተይዞ የሚፈጭበት ነው:: የእነዚህ መጠንም "እናቱ ከበድ ያለ ነው:: ልጁ ግን ይቀላል:: ደህና ወፍጮ የሚባለው የእናቱ እርዝመት አንድ ክንድ ወይም ግማሽ ሜትር ይሆናል:: ወርዱ ግን የክንድ ግማሽ ነው:: ልጁ በወርዱ ከእናቱ እኩል ነው:: በቁመቱ ግን ከእናቱ ያጥራል:: ልጁ ከመኝታ ትራስ ይመሳሰላል:: እናቱን እስከ ስድስት ሰው ሲሸከመው የገብስ ወፍጮውን መጅ /ልጅ/ ግን ሁለት ሰዎች ሊይዙት ይችላሉ" በማለት መረጃውን የነገሩኝ አቶ አወቀ አደመ ወርቁ /07-07-2002/ ናቸው:: ከዚህ አኳያ በጤፍ ወፍጮና በጥራጥሬ ወፍጮ መካከል የክብደት ልዩነት የመኖሩን ያህል በእናቱና በልጁ መካከልም ተመሳሳይነት አለው::

የቤት ወፍጮዎችን በማውጣትና በማስተካከል እናትና ልጁን እስከ 10 ብር በኋላም እስከ 40 እና 50 ብር እየሸጡ መጠቀማቸውን መረጃ አቀባዮቹ ነግረውኛል:: "ትዳር መስርቼ በነበር ወቅት የራሴን ወፍጮ አውጥቼ እናትና ልጅ በማድረግ ተጠቅሜያለሁ:: ከዚያም ኃይለ ስላሴ ወድቀው ደርግ ስልጣን ሲይዝ ጎጆ ወጪ ግብር ይክፈል በማለቱ የምከፍለው በመጣቱ ከአባቱ በለመድኩት መሰረት እያወጣሁ ሸጬ ግብሬን እከፍል ነበር" ብለዋል አቶ አወቀ አደመ::

የቤት ወፍጮ መፍጨት በሚያስችል መልክ ተወቅሮ ከተስተካከለ በኋላ ከቤት ጓሮ ወይም ከቤት ውስጥ በሚተከልበት ጊዜ በሁለት የመትከያ ቁሶች ላይ እንዲቀመጥ ይደረጋል። አንደኛው አራት ባላ ያላቸው እንጨቶች ይቆረጡና ይተከላሉ። በእነዚህ ላይ ከፊትና ከኋላ እንጨት ይጋደማል። በዚያ ላይ እናቱ ይደረጋል። ሁለተኛው አተካከል ደግሞ ትላልቅና ጠፍጣፋ ድንጋዮችን ከፊትና ከኋላ በመትከል በነዚያ ላይ እናቱን ማስቀመጥ ነው። እናቱ ወፍጮ በዚህ መልክ ከተቀመጠ በኋላ ጭቃ ይቦካና በጭድ ታሽቶ የእናት ወፍጮውን ዙሪያ ይመረጋል። መመረጉ ጥሬውንም ሆነ ዱቄቱን እንዳያፈሰው ነው። ከኋላ የጥራጥሬው ማስቀመጫ፣ ከፊትም የዱቄቱ ማጠራቀሚያ ቋት ይሰራል። በመጨረሻም ለመፍጫነት የተዘጋጀው መጅ /ልጅ/ ከእናቱ ላይ ይደረጋል። የአፈጫጭ ሂደቱም ከፊት ወደ ኋላ በመሳሳብና ወደፊት በመግፋት ይከወናል።

የቤት ወፍጮን የማውጣትና ከቤት የማድረስ ስራ የወንድየው ነው። ጫካ ሄዶ ገደላማ ቦታዎችን ወጦ ወርዶ የሚያመጣው ስለሆነ የውጪ ስራ ነው። እናም መፍጨት እስከቻለበት የስራ ሂደት ድረስ የወንዱ ድርሻ ነው። ወፍጮውን ለመትከል በሚደረገው የስራ ተግባርም ይሳተፋል። የእሱ ወንድነት የሚለካው እስከዚህ ድረስ ብቻ ነው። ለዚህም ይመስላል "ወፍጮውን እንደሆን አባወራው ያምጣው፣

የሚፈጨውን ገብስ ሚስቲቱ ታምሰው" መባሉ።

በወረዳዋ ማህበረሰብ ዘንድ በቤቱ ወፍጮ ያልተከለ ወንድ እንደሰነፍ ይቆጠራል። እንዲያውም ሚስቱ እህል ለመፍጨት በየሰፈሩ በምትሄድበት ጊዜ በባለወፍጮዎቹ አባወራዎች የምትደፈርበትም ሁኔታ ይፈጠራል። ሁኔታውን በስነቃላቸው ገልፀውታል። አንዷ የቤት ወፍጮ የሌላት ሴት ከጎረቤቷ በመሄድ ሌት ስትፈጭ በመካከል የቤቱ አባወራ ሌት ይነሳና ለግንኙነት ይጠይቃታል። የአባወራው ሚስት ትሰማለች ብላ በመፍራት መቃወም አልቻለችም። እናም እንዲህ እያለች የሰውየውን ጥያቄ መቀበል ግድ ሆነባት። "በል በለኝ የወፍጮ አይገዛ፣ አይተክል ሚስት ነኝ" በማለት። ከዚህ አኳያ ወፍጮን በቤት መትከል የወንዶችን ኩራት ይገልፃል። የሚስቱንም ክብር ይጠብቃል።

በሴላ ጎኑ ወፍጮ መፍጨት የሴቷ ድርሻ ብቻ ነው:: ከቀን የውሎ ስራ ጋር በተደራቢነት ሌትም ሲፈጩ የሚያድሩት ሴቶች ናቸው:: መፍጨት የሴት ብቻ እንደነበር አቶ ምን ይችል ዘወልድ ጀምበሬ የ52 አመት ጎልማሳ /05-07-2002 ቁልቋል/ የሚከተለውን ብለዋል:: "አይ ወንድ አይፈጭም:: ሴቶች ብቻ ናቸው:: ሴቶች ሌት ይፈጫሉ፣ ይፈትላሉ፣ ይወቅጣሉ ስራቸው ይሄ ነበር:: ስሪቱ ምን እንደሆነ ባላውቅም የወፍጮ ስራ የሴት ብቻ ነው::" የአቶ ምንይችልን ሀሳብ ወ/ሮ የኔአየሁ ዘለቀ አየለ /22-08-2002/ እንዲህ በማለት ይጋራሉ::

"አይ ወንድ አይፈጭም:: ወንድ በዳሪ /በውጪ/ ስራ ነው:: ሴቶች በቤት ስራ ነው የተመደብን:: እንደዚያ ስለሆነ ወንዶች በዳሪ አዘጋጅተው ማምጣት ነው እንጅ ከቤት አይፈጩም:: የማይፈጩበት ምክንያት ከላይ የመጣ ነው:: ወንዶይ ለማረስ ለማግባት እኛ ሴቶች ለቤት ስራ ወንዶይ ለዳሪ ስራ ነው የተመደብን" ብለውኛል:: የወ/ሮ የኔአየሁ ዘለቀን አባባል እሙሃይ ብሏየሁ አስረስ ዘገየ /26-08-2002/፣ ወ/ሮ ያልጋ ደስታ ጌታወሁን /28-08-2002/ እንደሚጋሩት ከንግግራቸው መረዳት ችያለሁ::

ከእነዚህ ሴት መረጃ አቀባዮች ንግግር መረዳት እደሚቻለው የመፍጨት ሙያን ከእናቶቻቸው ወርሰዋል:: ይሄም መፍጨት የሴት ብቻ መሆኑ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው ይላሉ:: ከዚህ አኳያ የስራ ክፍፍሉ ለሴቶች መድበታል:: መፍጨት ከወንድ በተለየ ለሴቶች ይሁን እንጅ ከሴቶችም በድሮው አባባል "የገረድ" ስራ ነው:: ለዚያም ነው ገረዷ

"ወፍጮው ፍጨው ፍጨው ቋቱ ሙላ ሙላ

ካልሰሩ አይገኝም የሰው ቤት እንጀራ" የሚለውን ስነቃላዊ ግጥም እያንጎራጎረች መፍጨቷ:: ይህ የሚያሳየው ለሆዷ ብቻ የተቀጠረች ሴትን ነው:: ታልፈጨች ምግብ የማታገኝ ይመስላል:: ስራው ድሃንና ሀብታምን በመደብ ይለይ እንደነበር መገንዘብ አያዳግትም::

የወረዳዋ ማህበረሰብ በቤት ወፍጮ የእለት ምግቡንም ሆነ እዳ ለማውጣት እህልን በመፍጨት ሕይወቱን ይመራበት ነበር:: ሴቶችም በመፍጨት ሙያ ላይ መከፋታቸውን፣ ጥላቻቸውንና ፍቅራቸውን በእንጉርጉሮ/በዘፈን/ ይገልፁ እንደነበር ታሪካዊነት አለው:: የሴቶች የስሜት መተንፈሻ እንደነበርም ታሪክ አይዘነጋውም::

በሌላ በኩል በቤት ወፍጮ በህብረት መስራትን ይገልፀበት ነበር:: ማህበራዊ ትስስሩና መረዳዳቱ በጉልህ ይታይ እንደነበር ነው:: ደብተራ ተመስጌን ካሳ ጥሩህ /13/07/2002፣ ገሳግስ ማሪያም/ "ድሮ ሰርግም ስናሰርግ ተስካርም ስናወጣ ድግስ ሲኖር ለዳንላዳን እህል በየጎረቤቱ እየተናኘ /እየተሰጠ/ ያ እየተፈጨ እንጀራውን ጋግራ ይዛ ትመጣ ነበር:: ሰርዳታ ተብሎ ነው:: እህሉ የሚወጣው ከባለእዳው ነው:: ጉልበት ስለሚያጥር:: እናም የሴቶች የስራ ህብረት በጣም ደስ ይል ነበር" ብለዋል:: ወ/ሮ የኔ አየሁ ዘለቀ በሌላ በኩል "አስቀድሞ ፈጭቶ ማጠራቀም ካልተቻለ ከጎረቤቶቻችን ጋር ተባብረን በመፍጨት እዳ እናወጣ ነበር" ብለውኛል:: በዚህ መልክ የቤት ወፍጮ የማህበራዊ ተስተጋብሮ መገለጫ ነበር ማለት ይቻላል::

የቤት ወፍጮ እንዲህ እንደ አሁኑ ዘመናዊነት ሳይስፋፋ ለእለት ደራሽ ቁስ ነበር:: ሆኖም ዘመናዊ የሞተር ወፍጮ በከተማም ሆነ በገጠር በመስፋፋቱ ግልጋሎት መስጠቱን አቁሟል:: በመጥፋት ላይም ነው:: ሴቶችም ስለማይፈጩ ውስጣዊ ስሜታቸውን ይገልጹባቸው የነበሩ ስነ ቃሎች አብረው እየጠፉ ነው:: አሁን ወፍጮ ማውጣት አቁማችኋል? በማለት የጠየኳቸው አቶ አወቀ አደመ "አዎ አናወጣም::ድሮ አፍ ተጅ ስለነበር ጥቅም ስለሆነ እናወጣም ይፈጭበተም ነበር::የዚያን ጊዜ የሞተር ወፍጮ የለ::አልመጣም:: አሁን መንግስት ዘመናዊ ወፍጮን እደጃችን ድረስ አመጣልን ገበሬው አንድም ሁለትም ሦስትም እሆነ እየተከለው ነው:: መፍጨት ቁሟል:: በጓሮ ዝም በለን አስቀምጠነዋል" (07/07/2003)የሚል ምላሽ ሰጥተውኛል::

በአጠቃላይ የቤት ወፍጮ ከየት እንደሚገኝ፣ እንዴት እንደሚወጣ፣ እንዴት ለመፍጨት እንደሚዘጋጅና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውን፣ እንዲሁም በሰዎች መካከል ማህበራዊ ልዩነትን እንዴት እንደሚያሳይ ለመዳሰስ ተሞክሯል:: በስነ ቃላዊ ግጥሞችም ወፍጮ የሴቶች ብቻ፣ ከነዚህ ውስጥም "ለገረድ" የስራ ድርሻ እንደሆነ፣ በሌላ መልኩም ሴቶች ውስጣዊ ስሜታቸውን የሚተነፍሱበት እንደሆነ በትንታኔው ተገልጿል:: በመጥፋት ላይ መሆኑንና በምን እነደተተካም ለመጠቆም ተችሏል::

. የውሃ ወፍጮ

የውሃ ወፍጮ ከቃሉ እንደምንረዳው በውሃ ኃይል የሚፈጭ ማለት ነው:: ሆኖም የወፍጮ ድንጋዩ አይነት ከቤት ወፍጮው አይለይም:: በአሰራሩ ካልሆነ በቀር የሚቆፈረውና የሚወጣውም እንደቤት ወፍጮ ሁሉ ከመሬት ነው:: ሌላው ስለውሃ ወፍጮ ታሪካዊ አመጣጥ ግልፅ የሆነ መረጃ እንደሌለ ከላይ ተጠቅሷል:: ምንም እንኳን የወረዳዋ መረጃ አቀባዮች አንዳንዶቹ ተሞክሮው ከሌላ ሀገር መጣ ቢሉም ከጽሑፍ በተገኘው መረጃ ግን ሀገራዊ እነደሆነ ያሳያል፡፡

በወረዳዋ መተከሉን አስመልክተው አቶ ይታየህ አላምንህ "ልምድ ከየት እንደመጣ የማስታወሰው ነገር የለም ሆኖም መጀመሪያ ከ1940 ዓ.ም በፊት ፊታውራሪ በዛብህ የተባሉ ግለሰብ የግንባራ ወንዝን ጠልፈው ደብተራ ላይ መትከላቸውን ሲወራ ሰምቻለሁ::" /19-07-2002/ ብለዋል:: መምህር እንዳሻው፣ አቶ አስናቀ ይሁኔና አቶ ዳኛው ወርቅነህ ግን ከ1942-1948 ባሉት ዓመታት አቶ አንተነህ በየነ ተሞክሮውን ፍኖተሰላም ላህ ከሚባል ወንዝ ላይ ተክሎ ከነበረ አንድ አረብ ሰውዬ እንዳመጡና ሸሜ አካባቢ በግምባራ ወንዝ ላይ እንደተከሉ ይስማማሉ:: ያም ሆነ ይህ በወረዳዋ የተተከለ የውሃ ወፍጮ ታሪካዊ አመጣጥ ይህን ይመስላል::

በወረዳዋ ውስጥ ይተከሉ የነበሩ የውሃ ወፍጮዎችን የሚያወጡ ከይሁኔ ወላ በፊት አባ ሸዋ የሚባሉ ሰውዬ ነበሩ:: ከአባ ሸዋ ቀጥለው ደግሞ ይሁኔ ውላ መጡ:: ሁለቱም የአካባቢው ተወላጅ አይደሉም:: በተለይ "ይሁኔ ወላ ያካባቢው ተወላጅ ሳይሆኑ በልጅነታቸው ከሌላ ቦታ ተገዝተው የመጡ ነበሩ" ይባላል:: እሳቸው ከ1944 ዓ.ም ጀምሮ በዚህ ስራ ላይ ተሰማርተው ነበር:: ሆኖም አሁን በህይወት የሉም:: መያውን የወረሰው የእሳቸው ልጅ አስናቀ ይሁኔ የ42 ዓመት ጎልማሳ ናቸው፡፡ በእሳቸው መረጃ መሰረት መጀመሪያ የውሃ ወፍጮ ሲወጣ አራት እኩል ቦታ ተከፍሎ ነበር::

> *"ለማንገዝ እንዲያመች አራት እኩል ተከፋፍሎ ነበር የሚወጣው:: አራቱ ድንጋዮች ልክ አንድ ደቦን ለአራት እንደምንቆርሰው ሁሉ እኩል ተሰንጥቀው ይወጣሉ:: እናም እነዚህን አራት ክፍሎች ወፍጮው ከሚተከልበት ቦታ ሲደርሱ በወቅቱ ረጥባ የሚባል ማሰሪያ ብረት ነበር:: በዚያ ይታሰራሉ:: በዚህም ሁለቱን ለእናቱ ሁለቱን*

ለመጹ ይታሰራሉ:: ከታሰሩ በኋላ በቸንካር ይመታሉ:: ይሄ እንግዲህ ሰው ስላልለመደው ነው:: ሲለመድ ግን እናትና ልጁን አንድ በአንድ መሸከም ተጀመረ"/አቶ አስናቀ ይሁኔ 03-07-2002/ ብለዋል::

በተገኘው መረጃ መሰረትና እኔም በምልከታ እንደረጋገጥኩት ይህ አይናማ የውሃ ወፍጮ ድንጋይ የሚገኘው ሽሜ ጊዮርጊስ አካባቢ በግንባራ ወንዝ ዳገታማ ቦታዎች ነው:: የአወጣጥ ሂደቱ እንደተባለው በሁለት መንገድ ነበር:: በመጀመሪያ ለሸክም እንዲያመች ተብሎ ለአራት እኩል ተሰንጥቆ፣ እየተለመደ ሲሄድ ግን እንዳለ በድጅኖ ብረት እየተፈነቀለ ልጁና እናቱ በየራሳቸው በመዶሻ ተጠርበውና ተስተካክለው ይወጡ እንደነበር ነው:: አወጣጡ በድጅኖው መሬቱ ይቆፈርና ድንጋዩ ይገኛል:: ያንን ድንጋይ ለማውጣት በድጅኖው እየተነሳ ከስር ድንጋይ ይጎርሳል:: ድንጋይ መጉረሱ ቀስ በቀስ ለመፈንቀል እንዲመች ነው:: በድንጋይ እየተንተራሰ ይፈነቀልና ሲወጣ በመዶሻ እየተፈለጠ አይኑ ይወጣል::

የውሃ ወፍጩው አይን ከወጣና ክብ ሆኖ ከተጠረበ በኋለ መሀሉ ይበሳል:: ከዚያም ልክ እንደ ዘመናዊ ወፍጮ በወፍጮው መካከል ቦይ ይወጣለታል:: ዱቄቱን አያስፈተለከ እንዲያወጣው ነው ቦዩ የሚወጣው:: ይህም በመሮ እየተፈለፈለ ይቀረፃል:: ከተቆፈረበት ቦታ ላይ በዚህ መልክ ከተስተካከለ በኋላ በወቅቱ እናትና መጹን እስከ 50ና 60 ብር በኋላ ግን እስከ 300 ብር በመሸጥ ወደሚተከልበት ይጓጓዛል:: መምህር እንዳሻው ቻሌ እምሩ እንዳጫወቱኝ ከሆነ በግምት እናትና ልጁ "ሁለት ቶን" ይመዝናሉ:: የወፍጮው ዙሪያ በግምት አንድ ሜትር ተኩል ሲሆን ስፋቱ ደግሞ አንድ ሜትር ነው::

ይህን ያክል ክብደት የነበረውን ወፍጮ ከተቆፈረበት ወደ ሚተከልበት ቦታ ለማጓጓዝ እስከ አንድ መቶ እና ከዚያ በላይ ሰው ያስፈልግ እንደነበር ነው::

"የሸክሙ ሁኔታ ያው ሰው ይሰባሰባል:: በጥሩምባ ማለት ነው:: አያክሌ ወፍጮ አማጡኝ ብሏቸኋል ይባላል:: ሰው ከተሰበሰበ በኋላ ምሰሶው በሚገባበት ቀዳዳ ወፍራም እንጨት ይገባና በመጫኛና በገመድ ይታሰራል:: በወፍራሙ እንጨት ግራና ቀኝ ሌሎች ረጃጅም የመሸከሚያ እንጨቶች ይታሰራሉ:: ከዚያም ሁለቱንም እናቱንና መጹን ማለት ነው በአንድ ጎን 50

በሌላ ጎን 50 በድምሩ 100 ሰው ይሸከማል:: እንግዲህ እየተጋገዘ ለመሸከም እስከ 150 ሰው ይሳተፍበታል"

/መ/ር አንዳሻው ቻሌ፣ 02-07-2002/ በወረዳዋ አጎራባች ቢቡኝ ወረዳ፣ ሞሰባ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚያስተምሩበት ቦታ ሂጀ ባነጋገርኳቸው ወቅት ይህን ብለውኛል:: የእሳቸውን ሀሳብ አቶ አስናቀ ይሁኔ፣ አቶ ምንይችል ዘወልድ፣ አቶ ይታይህ አለምነህ፣ አቶ ልይህ ወርቅነህ፣ አቶ ዳኛው ወርቅነህና ሌሎችም ይጋሩታል::

የውሃ ወፍጮው ተጓጉዞ ከመምጣቱ በፊት፣ የውሃ ወፍጮ ለመትከል የፈለገ ግለሰብ የት ቦታ ላይ ወፍጮ መትከል እንደሚችል ያስባል:: በተለይ በወረዳዋ ውስጥ ግንባራ የሚባል ወንዝን የመሰለ ለውሃ ወፍጮ መትከያነት የሚያመች ቦታ የለም:: ውሃውን በወቅቱ በቀላሉ ጠልፎ ለማውጣት የሚቻልበት ሁኔታ ነበር:: ከዚያም የመትከያ ቦታውን ከመረጠና ውሃው ከየት ተጠልፎ የት እንደሚደርስ ከወሰነ በኋላ የውሃ ቦዩን መቆፈር ይጀምራል:: ውሃውንም ከሚወርድበት ሸረፍ አድርጎ ትላልቅ እንጨት ይተክልና በአጋም እሾህ ይልገዋል:: ከላገ በኋላ በድንጋይ ካብ በማስደገፍ ሳር ያለበትን አፈር በኪት ማረሻ እየቆረሰ በካቡ ላይ ይደርፋል:: ከዚያም ውሃውን በተቆፈረው ቦይ ያንፎለፉለዋል::

ውሃው በዚህ መልክ ወጣ ማለት ነው:: ወፍጮው የሚተከልበት ቦታ ረባዳ መሬት ሆኖ ውሃውን ሊያንደረድር በሚያስችል ሁኔታ የተመረጠ ነው:: ከረባዳ ቦታው ላይ የወፍጮው መትከያ ዛኒጋባ ሳር ቤት ይሰራል:: ከካርታውና ከምሰሶው ወይም ዋንጫዋ ካነጣጠረችበት የበርሚል ጫፍ፣ ከኩሻኔታዋና ከሳሙናዋ በላይ በአግድም በባላ ላይ የሚደረደር ትላልቅ እንጨት ይደረጋል:: በዚያ ላይ ደግሞ የወፍጮው መፍጫ ቦታ ወለል ነገር ይሰራል:: ከዚያም ከአካባቢው የሚገኙ አንደ ዋንጫ፣ ሙቀጫ /ቶርቤል/፣ መስቀል፣ ሳጠራ /ቅምባ/፣ ማገጃ፣ ሳሙና፣ ሳር ያሉትን መስሪያ ጥሬ ቁሶች አሰባስቦ መጠበቅ ነው:: በዚህ ላይም ከአካባቢው የማይገኙና የማይመረቱ በርሚል፣ ካርታ፣ ምሰሶ፣ ኩሽኔት /ጠጠር/ የመሳሰሉት ከከተማ ተገዝተው ይመጣሉ:: በዚህ መልክ ይሰናዳና ለተከላ ይዘጋጃል::

እናት የውሃ ወፍጮ ልጅ የውሃ ወፍጮ



ፎቶ 6. የእናትና ልጅ የውሃ ወፍጮ

የአተካከል ሂደቱን መረጃ አቀባዮቹ በሚከተለው መልክ ገልፀውታል:: በተለይ መ/ር እዳሻው ቻሌ የእነ አንተነህ በየነን የውሃ ወፍጮ በመፍጨት ይተዳደሩ ነበር:: ግን ወፍጮው መፍጨት ሲያቆም ወደ መምህርነት የተዛወሩ ናቸው:: እናም እንዲህ ብለዋል::

> ቦዩን እንቆፍርና ውሃውን በማምጣት ወደ ሃያ ሁለት የሚጠጉ በርሚሎች ተሰካክተው ቁልቁል በተቀመጡበት ሁኔታ ይለቀቃል:: ውሃው ከመለቀቁ በፊት ከበርሚሉ ጫፍ ላይ ከእንጨት የተጠረበ መቀጫ /ቶርቤል/ ይኖራል:: ይሄ መቀጫ ውሃውን በካርታው ላይ በማነጣጠር እንዲመታ አጥብባ የምታስወጣውን ዋንጫና በርሚሉን አስሮ የሚይዝ ነው:: ዋንጫዋ ደግሞ በዋንጫ ቅርፅ ከእንጨት ተጠርባ የምትሰራ ናት:: ይህችን የአንጨት ዋንጫ ከላይ ውሃው በሚገባበት የበርሚሉ አፍ ላይ በገመድ አስረን እንለቃታለን:: መጨረሻ መቀጫው ላይ ስትደርስ አስተካክለን እናስቀምጣታለን:: ከዚያም ውሃውን ስንለቀው ይንደረደርና ጫፍ ሲደርስ በዋንጫዋ ይታፈናል:: በዋንጫዋ የታፈነው ውሃ ካርታውን ሲመታው ወፍጮውንና ካርታውን ያያያዘውን ምሰሶ ያዞረዋል:: ምሰሶው በኩሽኔት/ በጠጠር ኮረት/ ይታሰራል:: እናም በቀላሉ ይዞራል:: ጠጠሯና ምሰሶው የሚታሰሩት የሳሙና ቅርፅ ባላት የተጠረበች እንጨት ወይም ብረት ውስጥ ነው:: ምሰሶው ይወጣና ወፍጮዎች መካከል ተቦርቡሮ ከገባው መስቀል ጋር ይታሰራል:: ከዚያም ካርታው ሲዞር መስቀሉን ይዞት ይዞራል::ወፍጮው ሲፈጭ ዱቄቱ እንዳይደፋ ከበርሚል ቁራጭ ወይም ከእንጨት ከባቢ ቋት ይሰራል:: የዱቄቱ መቀበያም ይዘጋጃል:: ከወፍጮው በላይ ጥሬ እህሉን የሚሸከም ጥራር ቂጡ ተበስቶ ይቀመጣል:: በዚህ ላይ እህሉን ለማላምና ለመሸርከት ማሻ የሚባል አለ:: ማሻው ሲጠብቅ ይልማል ሲነሳ ይሸረክታል:: በዚህ መልክ ነው የውሃ ወፍጮው ተከላ የሚከናወነው:: /መ/ር እንዳሻው ቻሌ እምሩ 02-07-*2002/*

ከዚህ እንደምንረዳው የውሃ ወፍጮን ለመትከል ውጣ ውረዱ የበዛ እንደሆነ ነው:: በዚህ የስራ ሂደት የህዝቡን የስራ ተባባሪነት ማየት ይቻላል:: ድግስ ተደግሶ፣ በጥሩንባ ታጅቦ

ነው የሚጓጓዘው:: በማጓጓዝ የስራ ሂደት የተሳተፈው ሁሉ በወቅቱ አንዳንድ ጭልጌ /ከከብት ቆዳ በሚሠራ አቁማዳ/ እህል በነፃ ያስፈጫል:: ከአንድ በላይ ግን በነፃ ማስፈጨት አይቻልም::ሌላው በወቅቱ መጠቀስ ያለበት ሚዛን አለመኖሩ ነው:: ሚዛን ስላልነበረ በአይን ግምት ነበር ገንዘብ የሚቀበሉት::

> *በዚያን ወቅት አንድ ጭልጌ /አቁማዳ/ ከ50 ሳንቲም እስከ 1 ብር ይፈጭ ነበር አሉ:: አንዱ ጭልጌ በግምት እስከ 110 ኪሎ እንደሚይዝ ነው:: በወቅቱ ሚዛን የለም ነበር:: በአይተሽ ነው:: እየቆየ ግን እኔ መፍጨት እስክቻልኩበት 4 እና 5 ብር ድረስ እናስከፍል ነበር:: በመጨረሻ ሲቆም ሲል በ1980ዎቹ መጨረሻ ላይ እስከ 8 ብር ፈጭተናል:: ቀድሞ እንደነገሩኝ ከሆነ የሚያስፈጨው ሰው 5 ሳንቲም ብትጎልበት አንድ ጭልፋ ዱቄት፣ አስር ሳንቲም ብትጎድልበት ደግሞ ሁለት ጭልፋ ዱቄት ከፍሎ ይሄድ እንደነበር ነው" በማለት መረጃውን ሰጥተውኛል:: /እንዳላይኛው/*

የውሃ ወፍጮ ስራ እንደቤት ወፍጮ ሁሉ ለሴቶች የተሰጠ አይደለም:: የወንዶች ነው:: ፈጭታው ቁጭ ብሎ መላምና መሸርከቱን መከታተል ነው:: ምክንያቱም ወፍጮው የሚፈጨው በውሃ ኃይል ስለሆነ እንደ ቤት ወፍጮ ሁሉ አጎንብሶ መፍጨትን አይጠይቅም:: አብዛኛውን ጊዜም ለማስፈጨት በአህያ ጭኖ የሚሄደው ወንድየው ነው::

በሌላ ጎኑ ሀብታም እንጅ ድሃ አይተክለውም:: የገንዘብ አቅምን ስለሚፈታተን:: እናም የሀብት ደረጃ መለያ ነበር:: ለዚህም ነው በ1948 ዓ.ም ሽሜ አካባቢ የግገባራ ወንዝን ጠልፈው ከተከሉት አቶ አንተነህ በየነ ቀጥሎ ወፍጮ የተከሉት አባ ይታየው የተባሉት ሰውዬ

> "በጠራ ሜዳ ውሃ አንደርዳሪ
> ከነአባ አንቱ ጋር ተወዳዳሪ" ብለው ፎከሩ የሚባለው::ወፍጮ መትከል የሀብት ተወዳዳሪነት እንደሚፈጥር ከአባይታየው የፉከራ ስነቃላዊ ግጥም መረዳት ይቻላል::

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ለውሃ ወፍጮ መትከያነት የግንባራ ወንዝ ግንባር ቀደም ነው:: በዚህ ወንዝ ላይ ከ1940 ዓ.ም በፊት ጀምሮ ተተክሎበት ነበር:: ውሃው አረፋ ማሲካና፣ ብሀንዴ ጭዋኔ፣ አረፋ መድሃኒያለምና ሽሜ በሚባሉ ቀበሌዎች መካከል እያቋረጠ የሚሄድ ወንዝ ነው:: በነዚህ ቀበሌዎች ፊታውራሪ በዛብህ፣ ፊታውራሪ እንግዳ፣ አቶ መኮንን ሰዋገኝ፣ አቶ ወርቅነህ ባይነስ፣ አቶ ደስታ አለሙ፣ አቶ ቢረሰው ብዙነህ፣

አቶ አንተነህ በየነ፣ አቶ መለሰ በየነና ቄስ ታገለ የሚባሉ ሰዎች በግምባራ ወንዝ ላይ የውሃ ወፍጮ ተክለው አብዛኛውን የወረዳው ማህበረሰብ ግልጋሎት ይሰጡ ነበር::

ከዚህ በኋላ የውሃ ወፍጮ በተለይ ከ1970-1980 ዓ.ም እየተስፋፋ ሲሄድና ሁሉም ወፍጮ ለመትከል በተነሳሳበት ወቅት በሌላው የወረዳዋ ክፍል ባለ "ጉማራ" በሚባል ወንዝ ላይ አልፎ አልፎ አንዳንድ ግለሰቦች መትከል ጀመሩ:: ከነዚህ ውስጥ አቶ አያሌው በላይ፣ አቶ አያሌው ብዙነህና አቶ ታረቀኝ ከፋለ ነበሩ:: ውሃው ገሸት ስላሴን፣ ቆላ ሻንጊን፣ ዳምባን፣ ቡሎን፣ ከፊል የዘለይ አቦንና ከፊል ብሀንዴ ጭዋኔ ቀበሌዎችን አቆራርጦ የሚሄድ ነው::

በወረዳዋ ያለው ህዝብ በሙሉ የሚያስፈጨው በነዚህ ወፍጮዎች ነበር:: የሁለት ቀን ጉዞ በማድረግ የሚያስፈጨ እንደነበር መረጃ አቀባዮች ነግረውኛል:: በተለይ ወረፋው ወይም ተራው ያልደርሰው ከሳምንት በላይ ስለሚቆይ ስንቁ አልቆበት ካስፈጨት ሰዎች ዱቄት እየተበደረ በብረት ነገር ላይ እያነሳተ ይመገብ ነበር:: ማስፈጨቱ አድካሚ ቢሆንም በወቅቱ ሰፊ ድግስ ለማዘጋጀት የሴቶችን ችግር ይቀርፍ ነበር ማለት ይቻላል:: ሆኖም እንደ ቤት ወፍጮ ሁሉ የውሃ ወፍጮ በዘመናዊ የሞተር ወፍጮ በመተካቱ ሙሉ በሙሉ አገልግሎቱ ተቋርጧል:: በተጨማሪም በደን መጨፍጨፍ የተነሳ በተከሰተው የጎርፍ ብዛት የውሃው ቦይ ወደውስጥ በመጥለቁ ጠልፎ ማውጣት አልተቻለም:: በርሃማነት በመስፋፋቱም ውሃ መጥፋቱን በምልከታ ወቅት አረጋግጫለሁ::

በአጠቃላይ የውሃ ወፍጮ ድንጋይ ከየት እንደሚገኝ፣ እንዴት እንደሚወጣ እንዴት እንደሚተከልና አገልግሎት እንዴት እንደሚሰጥ ለመግለፅ ተሞክሯል:: በዚህ ላይም ወፍጮን ለመትከል የነበረውን ማህበራዊ ግንኙነት መዳሰስ ተችሏል:: ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውም ተጠቁሟል::

ሰንጠረዥ 2- የቤትና የውሃ ወፍጮ አማካይ መጠን ማሳያ ሰንጠረዥ

የወፍጮ አይነት		ርዝመት	ስፋት	ውፍረት	ዙሪያ	ክብደት	ቅርፅ
የቤት ወፍጮ	እናት	1 ክንድ ተስንዝር	1 ክንድ	አንድ ክንድ አነስ ያለ	-	ከ50-70 ኪ.ግ	ከቂጡ ዘርጠጥ ብሎ ሾጠጥ ያለ
	ልጅ/ መጅ	1ክንድ ተስንዝር	1 ክንድ	አንድ ስነዝር	-	ከ25-30 ኪ.ግ	የትራስ ቅርፅ
የውሃ ወፍጮ	እናት	-	2 ክንድ	2 ስነዝር	3ክንድ ከስንዝር	ከ7000ኪ.ግ በላይ	ክብ
	ልጅ/ መጅ	-	2ክንድ	1 ስንዝር	3ክንድ ከስንዝር	ከ5000 ኪ.ግ በላይ	ክብ

•ክብደት የመረጃ አቀባዮች ግምታዊ አሰጣጥ ነው::

•1ክንድ 0.50 ሳ.ሜ ሲሆን 1ስነዝር ደግሞ ወደ 0.20 ሳ.ሜ ይደርሳል::


4.2.2. ከቆዳ የሚሰሩ ቁሶች

ከቆዳ ጥሬ ቁስ እየተሰሩ የደጋ ዳሞት ወረዳ ማህበረሰብም ሆነ የሀገሪቷ ህዝብ ለተለያየ ግልጋሎት የሚጠቀምባቸው የእጅ ስራ ቆሶች እንደነበሩ ታሪክ ይመሰክራል:: የቆዳ ጥሬ ቁስ በሀገሪቷ ኢኮኖሚ የማይናቅ ጥቅም ነበረው:: "Hides ad skins were of considerable importance in the traditional Ethiopian economy..." (ፓንክረስት 1964:230) ማለታቸው ለኢትዮጵያ ባህላዊ ኢኮኖሚ ቆዳና ሌጦ ጉልህ ድርሻ እንደነበራቸው ጠቋሚ ነው::

ከጥንት ጀምሮ ከቆዳ ውጤቶች ለመኝታ፣ ለማዘያ፣ ለልብስ፣ ለጓዝ መያዣ፣ ለእህል መክተቻ፣ ለመጫኛ፣ ለግብርና ሙያ እና ለመሳሰሉት መጠቀም የተለመደ ነበር:: እስከ አሁንም ቢሆን በተወሰነ መልኩ በተለመደው ሀገራዊ እውቀት መሰረት በእጅ ተሰርተው ግልጋሎት ላይ መዋላቸው ይስተዋላል:: ይሁን እንጂ በማዳበሪያ ኩንታል ትልታይና በዘመናዊ የኢንዱስትሪ ምርቶች እየተተኩ በመጥፋት ላይ ለመሆናቸው መረጃዎች ያመላክታሉ:: በመጥፋት ላይ ለመሆናቸው በ4.2.5 በስፋት የሚተነተኑ ሲሆን ከዚያ በፊት ግን አሰራራቸውን ለማሳየት ይሞከራል:: እነዚህ የተለያየ ግልጋሎት የሚሰጡ የእጅ ስራ

ቁሶች በመስሪያ ጥሬ ቁሳቸው ተመሳሳይነት በአንድ ክፍል ተመደቡ እንጅ የየራሳቸው የአሰራር ሂደት አላቸው:: ሆኖም ጥሬ

ቆዳው እንዴት እንደሚዘጋጅ አስቀድሞ መግለፁ ይጠበቃል:: ምክንያቱም መነሻ ሂደታቸው አንድ ነውና::




ፎቶ 7 ጥሬ ቆዳ

በየትኛውም ቦታ ከብቶች ይታረዱና ቆዳውን ገፍፎ በማድረቅ ለጥሬ ቁስነት ማቅረብ የተለመደ ነው:: ቆዳውን ገፎ ከማድረቅና ከማቅረብ በኋላ ያለውን የአሰራር ሂደት እንዲነግሩኝ አቶ በላይ አለሸኝ ወንድምን ጠይቄያቸዋለሁ:: አቶ በላይ የአርባ አመት ጎልማሳ ሲሆኑ ተወልደው ያደጉት ሻንጊ ደረቄ ቀበሌ ቆላማ አካባቢ ነው:: የቆዳ ሙያን የለመዱት ከአባታቸው ነው:: በዝርያ የወረሱት ሙያ እንደሆነም ነግረውኛል:: አሁን የሚኖሩት ፈረስ ቤት ከከተማው ነው:: ከከተማ የኪራይ ቤታቸው አነጋግረያቸው እንዲህ ይላሉ::

ሂደቱ የከብት ቆዳ ተገፎ ይደርቃል:: የደረቀውን ቆዳም ገበሬው አምጥቶ ይሸጥልናል:: የደረቀውን ቆዳ ውሃ ውስጥ ለሶስት ቀን እንነክረዋለን:: ከተነገረበት እናወጣና ፀር ለዳሩን በካራ ቀደን ጀሮ እናወጣለታለን:: ከዚያም ፀጉሩን በስር አድርገን በተስተካከለ መሬት ላይ እንዘረጋና በካሰማ እንቀትረዋለን:: ካሰማው ከእንጨት አሸለን የምናዘጋጀው ነው:: ከተቀተረ በኋላ ስጋ ስጋውን በካራ እየገፈፍን እናነሳዋለን:: እየፋቅን ድራቢ ስጋውን እንሞልጨዋለን:: የምንፍቀው በደንብ ሁና በተሳለች መጥረቢያ ነው:: እስኪ ደርቅ ድረስ ተቀትሮ ይቆያል:: ተፍቆ ካለቀ በኋላ መልሰን በውሃ እንነክረዋለን:: ከዚያ ይወጣና ፀጉሩን ለመክላት ደንቡለቡሽ ቀብተን እናደብነዋለን:: ድንቡሽ ቡሻ ማለት ከዱር ከሚገኝ ሀረግ ላይ የምናወጣው እንቧይ የመሰለ ፍሬ ነው:: ከመሬት የተቆፈረ አይደለም:: በገጠር ሰው ልብስ ያጥብበታል:: በድንቡቡሻ ሲደበን ፀጉሩን ይበላዋል:: ፀጉሩ በድንቡሽቡሹ ከከላ በኋላ መልሰን በካሰማ እንቀትረዋለን:: እንደተቀተረ ጫቅማ /ጉሎ/ ቀብተን እናደርቀዋለን:: የደረቀውን ውሃ እየጀበጀብን /እያርከፈከፍን/ በእግራችን እናሸዋለን:: ስናሸው እየላመ

እየላመ ይሄዳል:: ደሞ እናሳድርና በበነጋው እናሸዋለን:: የጫቅማውን ቅባት እንዲበላውና እንዲለሰልስ መላልሰን እናሸዋለን:: እንዳይከር ማለት ነው:: ከዚያ በኋላ እንደገና ምጥጥ አድርጎ ቅባቱን ጠጥቶ ከለሰለሰ በኋላ በካስማዎች መልሰን ቀትረን እንስበዋለን:: ከዚያ ተወጥሮ ከደረቀ በኋላ ለሚፈለገው ሁሉ እናደርገዋለን:: /አቶ በላይ አለኸኝ 11-07-2002/

የአቶ በላይ አለኸኝን ሀሳብ ወጣት ጥላሁን ምንውየ እንየው /13-09-2002/ እና አቶ የደሜ ብርሃኑ እምሩ /14-07-2002/ ባደረኩላቸው የቃል መጠይቅ እንደሚስማሙ አረጋግጠውልኛል:: ጥላሁንም ሆነ አቶ የደሜ የቆዳ ስራ ሙያን ከትውልድ እንደወረሱት ነግረውኛል::



ፎቶ 8 የተቀተረ ቆዳ

ከላይ መረጃ አቀባዮቼ የነገሩኝ የአሰራር ሂደት ለገርንዲ፣ ለአቁማዳና ለአንቀልባ የሚዘጋጀውን ነው:: ከነዚህ ውስጥም የአንቀልባው በተለይ የሚጨመረው የአሰራር ሂደት አለው:: ይኸውም እንደገርንዲ ሙሉ ሂደቱን ከተሄደ በኋላ መልሶ ውሃ በመንከርና በማውጣት በካስማ መቀተረ ነው:: በካስማ ከተቀተረ በኋላ በቀጋ እሾህ ጠጉር ነገር እንዲወጣው መጣጀት /መቧጨር/ ነው:: አቶ አለኸኝ "የምንጣጀው መልክ እንዲያወጣ ነው:: ጠጉር ነገር እንዲመስል ነው:: እንደሚዶ /ማበጠሪያ/ እንዲቀሰቅሰው ነው:: በእሾህ የሚጣጀው በስጋው በኩል ነው:: ከዚያ ጫቅማ ይቀባል:: ያንን እናሸና ሲበቃው ቀትረን ቀለም እንቀባዋለን" ብለውኛል:: /እንደላይኛው/

ሌላው ለመጫኛ፣ ለጠፍር፣ ለምናር፣ ለማንጠቢያና ለመርገጫ የሚሆነው የስራ ሂደቱ እንደዥንዲው ቢሆንም ፀጉሩ ብቻ ነው የሚወገደው:: አቶ የደሜ ብርሃኑ እምሩ "የዥንዲውና የመጫኛው አፋፋቅ ለየቅል ነው:: የመጫኛው ቆዳ ጠጉሩ ብቻ ከልቶ ነው

ILS LIBRARY


እሚቀዳድ ጠጉሩ ከከላ በኋላ ቅባት እየቀባን ሶስት ጊዜ አራት ጊዜ እናሸዋለን::" /14-07-2002 ፊረስ ቤት 01 ቀበሌ / በማለት ገልፀዋል::

በዚህ የቆዳን ለግልጋሎት ቁስነት የመስራት ሂደት ላምነት የሚባለው የመተኛ ቁስ በስጋው በኩል እንጅ ፀጉሩ አይነካም:: ይህም የሚለየው በፀጉሩ አለመነሳት ነው:: ምክንያቱም የወረዳዋ ማህበረሰብ በክረምት ወቅት ቫርንዲው ስለሚቀዘቅዝ ፀጉር ያለውን ላምነት መጠቀም የተለመደ ነውና:: ሌላው ለደበሎና ለለምድ /ለቃባ/ የሚሆነው ቆዳ የበግ ሌጦ ነው:: ይህም የራሱ የአሰራር ሂደት አለው::ስልቻን በተመለከተም ከፍየል ቆዳና ከጥጃ ቆዳ ስለምትሰራ በእጅ ባለሞያዎች የስራ ሂደት አንደደበሎና ቃባ ሁሉ አትሰራም:: እህል ለመክተቻነት እንደአቁማዳ ብታገለግልም የቆዳ ጥሬ ቁሷና አሰረሯ ይለያያል:: ይኸውም ፍየሏን /ጥጆዋን/ እንዴ መግፈፍ እንደሚቻል አቶ በላይ አለኸኝ እንደሚከተለው ይገልጹታል::

> *ስልቻ እንግዲህ የፍየል ቆዳ ነው:: ፍየሏ አንገቷ ትባረካለች:: አንገቷ ትባረክና የኋላ አግሯን ሁለቱን ሰንዝሮ በቁጡ ይወጣል:: የኋላ እግሯን አንዱን ገፎ ማንጠልጠል:: ከዚያም ዙሪያውን እየገፈፈ መውረድ ነው:: ከፊት እግሯ ጉልበቷ ላይ ቆርጦ እንደሴት ጥብቆ ወደራሷ ማሸለክ ነው:: ከዚያም በእርሾ ይደበንና ፀጉሩን ከልቶ በቅባት እየታሸች ትደርቃለች:: ከዚያም የአህል መያዣ ማድረግ ነው:: /11-07-2002/*

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ መግለፅ የተሞከረው ጥሬ ቆዳውን እንዴት ወደ እጅ ስራ ቁስነት ለመቀየር የተደረገ የስራ ሂደት ነው:: ነገር ግን እያንዳንዱ ቁስ ራሱን ችሎ የተገለፀበት ሁኔታ የለም:: ምክንያቱም ከቆዳ ቁሶቹ ብዛትና አንዱን በአንዱ መግለጽ የሚቻል ስለሆነ:: ለዚያም ነው በጥቅል ለመግለጽ የተሞከረው:: እናም በናሙናነት መርጨ አሰራራቸውንም ሆነ ማህበራዊ ጠቀሜታቸውን በተመረጡ ስነቃሎች በማስተንተን ለማቅረብ እሞክራለሁ:: በናሙናነት የመረጥኳቸውም አንቀልባ፣ አቁማዳ፣ ማንጠቢያና ደበሎ ናቸው::


ፎቶ 9. የተፋቀው ቆዳ



•አንቀልባ፦ አንቀልባ የሚባለው የእጅ ስራ ቁስ ለልጅ ማዘያነት በወረዳው ቀርቶ በመላ ጎጃም ውስጥ የጥንት ነው:: አሰራሩን አስቀድሞ ለመግለፅ ተሞክሯል:: ለአንቀልባነት የተፋቀውን ቆዳ ቀለም ይቀባል:: ቀለሙ ከገበያም ይገዛል:: ከዚያውም መስራት ይቻላል:: በዚህ ላይ አቶ በላይ አለኸኝ "አረብ ቀለም ይቀባል:: የቆዳ ቀለም ነው:: ከደንበጫ ነው የምናመጣው:: ግን እኛም መስራት እንችላለን:: ቀረጥ የሚባል ዛፍ አለ:: ልጡን እንቀረፋና በካራ ፍቀን እናመጣዋለን:: ደሞ ከዱር እንደእንሶስላ የምትቆፈር ስራ ስር አለይ:: ያችን ወቅጠን ስናቦካት ቀለም ትፈጥራለች:: ከዚያ ቀለሙን መቀባት ነው:: ወጪም ይቀንስልናል" ብለዋል:: ይህን ሀሳብ እነ የደሜ ብርሃኑም ይጋሩታል::

ቀለም ቀብቶ ከተዘጋጀ በኋላ ገርንዲውን በሦስት ክንድ ከሰንዝር ለክቶ ሁለት እኩል መቅደድ ነው:: አንድ ቸርንዲ ለሁለት አንቀልባ ይሆናል:: ዳር ለዳሩን ለመቀተሪያነት ጆሮ የወጣለትን አካባቢ በመተው ለአንቀልባ ይቆረጣል:: በዚህ ላይ አንቀልባው እንዴት እንደሚዘጋጅ አቶ በላይን ጠይቂያቸው የሚከተለውን ነግረውኛል::

> *ገርንዲውን ለሁለት በካራ ከቀዳድን በኋላ ሦስት ክንድ ከሰንዝሩን ለአንድ አንቀልባ እናደርገዋለን:: በአንገቱ በኩል በሚሆነው ላይ እሚዘመዘም አንድ ግርባን /እጥፋት/ በማጠፍ በወስፌ እንሰዋለን:: ከዚያም አንድ ክንድ የሚሆነውን ዝቅዝቅ በስለት እንሸነሽነዋን:: በቤሳ /በምላጭ/ ማለት ነው:: ከ35-40 ሸንሸን ይሆናል:: ዝቅዝቅ ጣት ጣት ይወጣለታል:: ጆፌ እንዲሆን ይህም ዶቃ /ማርዳ/ና ዛጎል ይደረግበታል:: ዝም ብለንም እንሸጠውና የገዙት ጌጡን ያደርጉበታል:: እኛም ብንሆን በግርባቱ ላይ ቁልፍ ለጌጥ እንዲሆነው እንተክልባትና ይጠቀሙበታል:: ያለቁልፍና ዘጎል ከ60-80 ብር እንሸጠዋለን:: ቁልፍ፣ ዛጎልና ማርዳ አድርገን ከሚላነው እስከ 150 ብር እንሸጠዋለን:: ድሮ ግን እስከ 15 እና 20 ብር ይሸጥ እንደነበር ሰምቻለሁ:: /03-09-2002/*



ፎቶ 10. የተዘጋጀ አንቀልባ

አንቀልባ በዚህ መልክ ይዘጋጅና ለልጅ ማዘያ ይሆናል። ምንም እንኳን በአሁኑ ሰአት ልብሳችንን ያበላሻል ያሸተናል እያሉ በዘመናዊ የጨርቅ ቁራጭ እየተለወጠ ቢሆንም። በቀደም ግን ሴቶችን እርስ በርስ ከማበላለጥ አልፎ የባሎቻቸውን ተወዳጅነትም ይገልፅ ነበር። አቶ በላይ "ቀሚስ ከሚገዛላት ባለሻሿቱ አንቀልባ ቢገዛላት ትወዳለይ። የውስጧን ትታ ሴቱ በዚያ ባንቀልባ ነው የሚቀና። ይኸን ገዛልኝ እያሉ ይረባበሻሉ። እኔም ይህን አይነት አስገዛዋለሁ እየተባባበሉ ይቀናናሉ። ባልና ሚስት ተጣልተው ትዳር የሚፈርስበት ሁኔታም ያጋጥማል። ታልገዛላት ተጣልተው ትዳራቸው ይፈርሳል። እንዲገዛም ተረቡ ያስገድደዋል" ይላሉ።

ከአቶ በላይ ንግግር እንደምንረዳው አንቀልባ መርጦ መግዛት የወረዳዋን ሴቶች ቀልብ እንደሚይዝ ነው። አንቀልባ ከሌለ ትዳር እንደሚፈርስም ያሳያል። ማህበራዊ ተቀባይነቱ የጎላ ነበር። ልጅ ወልዶ ያለ አንቀልባ ማዘል የማይቻል ይመስላል። ለዚህም ይመስላላል

"ሽጋ ሴትነቷን የምታስታውቀው፣
ህንፃን ልጅ በመውለድ አዝላ ስትወጣ" ነው መባሉ።

የሴትነት ቁንጅና ጐልቶ የሚወጣው በአንቀልባ አዝሎ በመታየት እንደሆነ ነው የሚያስረዳው። አንድም በወረዳው ልጅ መውለድ ፀጋ ነው ተብሎ ስለሚታመን ይህን ፀጋ በተዋበ አንቀልባ ማዘል ለሴቷ ድርብ ቁንጅናን እንዲሁም ሴትነቷን ትገልፅበታለች። በሌላ በኩል ያገባች ሴት ትወልዳለች ተብሎ እንቀልባ ተገዝቶ ብትጠበቅ ትዘገያለች በዚህን ጊዜ

"ኧረ ጉዴ በዛ ኧረ ጉዴ በዛ፣

ልጁ ሳይወለድ አንቀልባው ተገዘ፣

ይወለዳል ብለን መቼም እንደዋዛ" በማለት ስጋቷን ገልፃለች:: ይህም ልጅ ለመውለድ ምን ያህል እንደሚያጓጓ ነው:: ከዛሬ ነገ አርግዤ ወልጄ እንደሰፈርቼ ሴቶች እሆናለሁ ስትል መዘግየቷ ያሳስባታል:: ይህም አንቀልባና ልጅ መውለድ ምን ያህል የተሳሰሩ መሆናቸውን መገመት አያዳግትም:: በአንቀልባ ማዘል የሴትን ልጅ ቁንጅና ከማጉላቱም በላይ የሴትነት መገለጫም ነው:: ወንዱም ለአንቀልባ የተለየ ፍቅር ያሳያል:: ይህም ሴትን ከአንቀልባ ለይቶ ለማየት የሚቸግር ይመስላል:: ውበቷን ከአንቀልባው ማግኘት እንደሚቻል ነው::

ከቆዳ ቁስ የሚሰራው አንቀልባ ለልጅ ማዘያነት ከማገልገሉም ባለፈ የሴትነት ውበት መገለጫ እንደነበር ይታመናል:: ወ/ሮ የኔአየሁ ዘለቀ አየለ "ያለ አንቀልባማ ምኑን ልጁን ታዘለው:: ለመሆኑ ከመቼ ወልጄ እከሊት ያዘለችበትን አንቀልባ አዝየበት ብለን ነው የምንጓጓው:: ባልየው ለሚስቱ ያለውን ፍቅርም በሚገዛላት አንቀልባ ይገለፃል:: ልብስ መልበሴ ሳይሆን የማዝልበት አንቀልባ የበለጠ የሚያደምቀኝ ይመስለኛል" /22-08-2002/ ይሉታል:: እናም ይህ አንቀልባ ልጅ ለመውለድና ለማዘል ተምሳሌታዊ አንድምታ እንደነበረው ነው:: ልጅ ተወለደ ማለት አንቀልባ ተገዛ ነው:: መውለድና አንቀልባ መግዛት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ነበሩ ማለት ይቻላል:: የአቅም ልዩነትንም ይፈጥራል:: እንዲያውም ትዳርን እንደሚበትን በአቶ በላይ የተገለጸውን መረዳት በቂ ነው:: ሆኖም በዘመናዊ ማዘያ እየተተካ በመሆኑ ይህን ለዛውን ይዞ በመጥፋት ላይ ነው::

በአጠቃላይ ከአካባቢው እውቀትና ጥሬ ቁስ የሚሰራው አንቀልባ በወረዳዋ ላሉት ሴቶች ምን ያህል ተፈላጊ እንደነበር፣ እንዲሁም የሴት ልጅ የውበት መገለጫነቱን ለመግለፅ ተሞክሯል:: የአሰራር ሂደቱንም ለማሳየት የተቻለ ይመስለኛል::

• አቁማዳ አቁማዳ ባህላዊ የኢትዮጵያ የእህል መክተቻና ማጓጓዝ የቆዳ የእጅ ስራ ቁስ ነው:: ለዚህም ነው ፓንክረስት "...leather sacks for holding personal luggage while traveling by mule" (1964:233) ያሉት:: እንደለስላሳ የመኝታ ቆዳ ሁሉ

የአቢሲኒያ ሰው ለጓዝ መያዣና በበቅሎ ላይ ለማጓጓዝ አቁማዳን ይጠቀም እንደነበር ነው በጥናታቸው ያመለከቱት::

ጥሬው ቆዳ ለገርንዲነት እስከተዘጋጀበት ድረስ ያለው የስራ ሂደት አቁማዳን እንደሚመለከተው አስቀድሞ መጠቆም ተሞክሯል:: ቫርንዲውን ራሱን አቁማዳ ማድረግ ነውና:: በዚህ ላይ የደሜ ብርሃኑ እምሩ የሚከተለውን ብለዋል:: "ተወጥሮ ከደረቀ በኋላ በካራ እንቀድና በክንዳችን ሰፍረን ክንድ ተስንዝሩን ቆርጠን እናወጣዋለን:: ክንድ ተስንዝሩ ለማር ሲሆን ክንድ ተጋቱ ለእህል ይሆናል:: እናም በአንድ በኩል ክፍት እንተውና ቂጡንና ቁመቱን እንሰፋዋለን:: ከዚያም በአፉ በኩል ክፍት ይሆናል:: የምንሰፋው በራሱ በከብት ጅማት ሆኖ በወስፌ እየወጋን ነው:: ከዚያም ከቂጡ መሀል ላይ ማሰሪያ ጠፍር ወይም ገመድ ይደረግበትና ለእህል መከተቻ ይሆናል" ይላሉ:: /14/07/2002/



ፎቶ 11. ያረጀና እህል የተሞላ አቁማዳ

አቁማዳው በዚህ ሁኔታ ተሰርቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ለተጠቃሚ ገበያ ይቀርባል:: ቀደም ሲል መገበያያው ነጭ ሽልንግ ስለነበር እስከ ሶስትና አራት ሽልንግ ይሸጥ ነበር:: ሆኖም ህብረተሰቡ በአቁማዳ መጠቀም እያቆመ ሲሄድ በእውቅ በመስራት (ማለትም ስሩልኝ ተብሎ ሲጠየቅ ይሰሩና) አንድ መቶና ከዚያ በላይ ይሸጡታል:: የዋጋ ውድነቱም ጨምሯል:: አንድ አቁማዳ በሚገዛበት እስከ 15 ማዳበሪያ መግዛት ስለሚቀል ማህበረሰቡ ወደማዳበሪያ ኩነታሉ አዘነብሏል::

አቁማዳ ወይም ስልቻ ለአብሲኒያ ህዝብ ተወዳጅ ነበር እንዳሉት ፓንክረስት የወረዳዋ ህዝብ እህልን ከአውድማ ለማንሳት የተለየ ክብር ይሰጡት ነበር:: እህል ከሆነ እስከ መቶ ኪሎ፣ ማር ከሆነ ደግሞ እስከ ሁለት መቶ ኪሎ የሚይዘው አቁማዳ እሱ የነካው እህል "ረድኤት"

ነበረው የሚል አምልኮ በማህበረሰቡ ዘንድ መኖሩን ማረጋገጥ ተችሏል:: በዚህ ላይ እሙሃይ ብሂየሁ አስረስ ዘገየ ቃላቸውን ሰጥተዋል::


እሙሃይ ብሂየሁ የ70 ዓመት መነኩሲት ናቸው:: ፈንካቲት ሚካኤል ተወልደው ቢያድጉም ገና ስራ ሳይለምዱ በህፃንነታቸው /ጨቅላ ነበርኩ ሳገባ ይላሉ/ ለባል ተድረው ጭዋኔና ብሐንዴ ቀበሌ ልዩ ስሟ ገንቢች ወልደው ከብረው ይኖራሉ:: አሁን ባለቤታቸው መተው ከልጆቻቸው ጋር ናቸው:: እናም በደከመው አንደበታቸው "አሁን የማዳበሪያ ኬሻ ነው የምንጠቀም:: የአሁኑ ደግሞ ከልበ ቢስ /በረከት የለሽ ማለታቸው ነው/ እንጂ አቁማዳ ቀረ እንጅ ረድኤት የነበረው:: አቁማዳ ሽጋ ነበረ:: ትልቅ ክብር ነበረው::" ብለዋል:: /26-08-2002 ገንቢች/

የእሙሃይ ብሂየሁ አስረስን ሀሳብ ብዙዎቹ መረጃ አቀባዮች ይስማሙበታል፤ ሆኖም የቆዳው መወደድና የማዳበሪያ ኬሻው መርከስ እየታየ አቁማዳን ትተውታል:: እናም አቁማዳ በወረዳዋ ማህበረሰብ ዘንድ ትልቅ ክብር ነበረው:: እስሌ ይህን ያህል ጭልጌ /አቁማዳ/ እህል አስገባ ሲባል የተለየ አድናቆት ይሰጠው ነበር::

- **ማንጠቢያ፦** "...all straps that with us are made of a single piece of leather..." (ፓንክረስት፣ 1964:233) ከጥቅሱ እንደምንረዳው ሁሉንም ጠፍሮች ከቁርጥራጭ ቆዳ መስራት እንደሚቻል ነው:: እናም ማንጠቢያ አንዷ የጠፍር አካል ናት:: ገበሬው በሬዎችን በቀንበር ሲጠምድ በማነቂያው ላይ ታስራ የሚያነጥብባት ናት:: ማንጠቢያ ጉልበታሙን በሬ ሁሉ አስራ የምትይዝ ናት:: የማንጠቢያ አሰራር ከመጫኛና ሌሎች የጠፍር አይነቶች ጋር ያመሳስላታል::
የመጫኛ ቆዳን አሰራር ከላይ ለመጠቆም ተችሏል:: በዚህ ላይም ማንጠቢያ ከመጫኛው አካል ተቆርጣ ስለምትወጣ ጠቅለል ያለ መግለጫ ላቅርብ:: በቅባት የለሰለሰውን ቆዳ በመሳብና በመዘርጋት በካራ እየተለተሉ ማውጣት መቻል ነው:: ለመጫኛው አስራ ሁለት ክንድ ወይም ስድስት ሜትር ይቆረጣል:: ከመካከል ላይ ገበያ የሚባል ቋጠሮ ይቋጠራል:: ይህ የመጫኛው የገበያ ቋጠሮ ግራና ቀኝ የአህያውን ሆድና የተጫነውን አቁማዳ እንዳይዋኝ ወጥሮ የሚይዝ ነው::

የመጫኛውን ግማሽ ወይም ለጠንካራ ገበሬ ከሆነ ሙሉ መጫኛውን ጫፉ ላይ ቀዳዳ በማበጀት መፍተልና በማክረር ምናር ማድረግ ይቻላል:: የተከረረውን የመጫኛ ጠፍር ሶስትዮሽ ይገመድና በምናር ልክ ይዘጋጃል:: "የምናሩን ግማሽ ወይም ሶስት ክንዱን በመቁረጥ ወገልና ድግሩን ከሞፈሩ ጋር በማሰር እንዲረግጡበት መርገጭ ይደረጋል:: እናም ለመጫኛ የተዘጋጀውን እናከፋፍልና ለምናር፣ ለመርገጫ፣ ለማንጠቢያ እንሸጠዋለን:: ሁሉም የጠፍር ዓይነቶች የሚወጡት ከመጫኛው ተቆራርጠው ነው::" /አቶ በላይ አለኸኝ 03-09-2002/ በማለት መረጃውን ሰጥተውኛል::

ማንጠቢያ ትንሽ ነገር ናት ተብላ ማንኛውም የእጅ ሙያ የሌለው ገበሬ ሊያዘጋጃት አይችልም:: እንደትነሽነቷ የምትታይ ሳትሆን እንደገቦንዲ፣ አቁማዳ፣ አንቀልባና መጫኛ ሁሉ የቆዳ አሰራር ሂደትን በእጅ ባለሞያዎች ማለፍ አለባት:: ማንጠቢያን እናንተ አታዘጋጂትም ወይ? ያልኳቸው አቶ ሰፋኔ ዘለቀ ወርቅነህ አስተያየታቸውን ሰጥተውኛል:: አቶ ሰፋኔ ዘለቀ የ52 ዓመት ጎልማሳ ሲሆን ጭዋኔ ብሃንዴ ቀበሌ ልዩ ስሟ ገንቢች ከምትባል ቦታ ተወልደው የኖሩ ናቸው:: አሁንም እዚያው ያሉና አራሽ ገበሬ ናቸው:: እዚያው ከቤታቸው ነው ያነጋገርኳቸው:: "አይ እሽ አትለንም:: አትለፋልንም አትሰምርልንም እሽ ብላ:: ከራ ነው የምትቀረው:: ቶሎም ትቆረጣለች እኛ አልፍተን ብናነጥብባት:: ስለዚህ ባለሞያ ካልሰራት እኛ አንችልበትም::" /22-08-2002/ ብለዋል::



ፎቶግራፍ 12. ማንጠቢያ ጠፍር

ይህች ቀጭን አጭር ከበሬ ቆዳ ተቆርጣ የምትዘጋጀዋ ማንጠቢያ ከሌለች እርሻን ማረስ አይቻልም:: ከገበሬዎች የእርሻ እቃ እንደዋና የምትቆጠር ናት:: ምን ያህል እንደምትፈለግም በስነቃል ግጥም እንዲህ በማለት ይገልጿታል::

“የበሬዎች እቃ አስራ ሁለት ነው
ማንጠቢያ ከሌላ መበዘኑ ነው::”

በዚህ ስነቃላይ ግጥም ከአስራ ሁለቱ የበሬዎች እቃ እንደአንዱ እንደምትቆጠርና ያለ ማንጠቢያም ስራ ፈትቶ እንደሚዋል ነው:: እንደ አንድ የበሬ እቃ የምትቆጠረዋ ማነጠቢያ ከቆዳ ጥሬ ቁስ ተሰርታ የእለት ተእለት የእርሻ ስራን መከወኛነት ውላለች:: በሬና ገበሬን አስማምታ የምታውል ነበረች:: ሆኖም ከማዳበሪያ ትልታይ በተፈተለ ቀጭን ገመድ እየተተካች አገለግሎት መስጠት እያቆመች ነው::

• ደበሎ ማለት የበግ ቆዳ ተለፍቶ በደንብ ለምልሞ ከነፀጉሩ የሚለበስ መሆኑን መሪጌታ ጥዑመልሳን መለስ ነግረውኛል:: በሌላ በኩል “ደበሎ ማለት ከነጠጉሩ ከተለፋ በኋላ በካባ ቅርፅ ተቀጣጥሎ የተሰፋ የቆሎ ተማሪዎች የሚለብሱት የበግ ቆዳ ነው” /አማርኛ መዝገብ ቃላት፣ 1993፣ 464/ በደጋ ዳሞት ሻንጊ ደረቄ፣ ዝቋላ ወገም፣ ድኩልካና፣ አቅላት ወይበኝ፣ ጣዕመ አባኪዳን፣ ፍላጢት አቀቢት፣ ገስግሶ ሽምብርማ፣ ቀበሌዎች ወይም 75 ፐርሰንት ደጋማው የወረዳዋ ክፍል ህዝብ ደበሎን ያለበሰ የለም:: ከሴቶች በስተቀር::
አባ አዳሙ ደስታ ከሳ ይባላሉ:: ሻንጊ ደረቄ ቀበሌ ተወልደው አድገዋል:: አሁን የ75 ዓመት የእድሜ ባለፀጋ ናቸው:: ቁስ የነበሩና አሁን ግን ያፈረሱ ናቸው:: በአካባቢው አጠራር ያፈረሱ ደብተራ ናቸው:: ደበሎ ሰፍተው ይለብሱ ነበር:: ገንዘብ አያስከፍሉም እንጂ ሰፍተው ለሎች ይሰጣሉ:: እሳቸውን በ(11-07-2002 ዓ.ም) ደጋ ሻንጊ ካለችዋ ጥንታዊት የማሪያም ቤተክርስቲያን አስቀድሰው ሲወጡ በዕለተ ሰንበት በጓሮ በኩል እናግሬያቸዋለሁ:: ለመሆኑ ደበሎ ተለበሰ የሚባለው ከመቼ ጀምሮ ነው ሲባል ሰምተዋል ብያቸው “ኧራ... /አይናቸውን አጥብበው በማሰብ/ እንዲያው ለምድና ህዝብ ተለያይቶ አይታወቅም:: ደበሎም እንደዚሁ:: ከድሮ ወይም የወትሮ ነበር:: በዚህ ዘመን ነው ተብሎ አይታወቅም:: ሱሪ የለ ምን የለ አሁን ደህናው ወደላ ያለሱሪ አሁን አኔ የብልቴ ጠጉር እስኪበቅል ድረስ ሱሪ የለኝም ነበር:: ኮትም የለኝም ነበር:: ከዚያ ደበሎ ይሰፋና እለብሳለሁ:: የቆሎ ተማሪው ሁሉ ያንን ለብሶ ይሄዳል:: በደጋው ግን የሁሉም ልብስ ነበር” ብለዋል:: ደብተራ ተመስጌን ካሳ ጥሩነህ /13-07-2002/:: አቡሀይ በሻህ አይቸህ ዋሴ /15-07-2002/፣ መሪጌታ ጥዑመልሳን መለሰ /12-07-2002/ የአባ አዳሙን ሀሳብ ይጋራሉ::

ይህ የጥንት የደጋ ዳሞት ደጋማ ክፍል ህዝብ እና የጥንት ቆሎ ተማሪ በልብስነት ሲገለገልበት የቆየው ደበሎ ከበግ ጥሬ ቆዳ ይሰፋ ነበር:: ለደበሎ የሚሆነው በግ በጣም ያላነሰው በጣምም ያላረጀው ቢያንስ ሁለት ዓመት ሲሆነው የሚታረደው እንመዲሻል ነው:: የበጉ ቆዳ በጥቁር ፀጉር የተሸፈነ ከሆነ ደበሎውን ተመራጭ ያደርገዋል:: አልያ ግን ዳንግሌም ሆነ ነጭ ከጥቁሩ ጋር ተቀላቅሎ ቢሰፋ ችግር እንደሌለው መረጃ ሰጪዎች አረጋግጠውልኛል::

ደብተራ ተመስጌን ከሳ ጥሩነህ የተባሉትን የ62 አመት ሽማግሌ ገሳግስ ሽምብርማ ቀበሌ ልዩ ስሟ ገሳግስ ማሪያም በመሄድ የደበሎን አሰራር ሂደት እንዲነግሩኝ ጠይቄያቸው የሚከተለውን ብለውኛል:: የእሳቸው ምላሽ ግን የሌሎችንም ቃል አቀባዮች ሀሳብ የሚያጠቃልል ይሆናል::

> *መጀመሪያ በጎ ትታረዳለች:: ቆዳው ከስጋዋ ይለያያል:: ከዚያ በቀጫጭን የእንጨት ከሳማ ተዘርግታ ትቃቃና በፀሀይ ትደርቃለች:: ከደረቀይ በኋላ በአንትም/በወተት/ ሆነ በሊጥ እርሾ ይደበናል:: ከተደበነ በኋላ ይለፋል:: በደንብ ይለፋና ለመስፋት ይዘጋጃል:: ደበሎው እንደለባሹ የቁመትና የውፍረት መጠን ይወሰናል:: ከልጅ እስከ አዋቂም የሚለፋውን ቆዳ ብዛት ይመጥነዋል:: እናም ከአራት እስከ ስድስትና ሰባት የተለፋ የበግ ቆዳ ሰፍቶ መልበስ ይቻላል:: እዚህ ግን የፍየል ቆዳ ደበሎ አይሆንም:: የበግ ቆዳ ብቻ ነው:: ለምሳሌ 6ቱን ቆዳ ደበሎ ብናደርገው 2ቱ ዳርና ዳር አቋም፣ መሀሉ ደግሞ ሁለት አውራጅ፣ በዳር ደግሞ አንድ ሌላ አውራጅ ከዚያም ከላይ በአንገት ማስገቢያው በኩል ከፍ የሚይዝ አንድ ቆዳ ተጨምሮ ይሰፋል:: ከዚያም ለመልበስ ይዘጋጃል ማለት ነው:: /13-07-2002 ገሳግስ ማሪያም/*



ፎቶ ግራፍ 13. የተሰፋ ደበሎ

የደበሎ የአሰራር ሂደት ይህን ይመስላል:: በዚህ ላይ ግን ደበሎን የሚያሰፋ እንደ ቆዳ ሰሪ ሁሉ ባለሞያ አይደለም:: ማንኛውም ሰው ሊሰፋው ይችላል:: ሆኖም እንደ ቤት ሰሪ የተለየ ችሎታ ያለው መኖሩ አይቀርም:: በተለይ ቀሳውስት ይስፉት ነበር:: ውሏቸው ከደበሎ ጋር ስለነበር ይመስለኛል:: ቃለመጠይቅ ያደረኩላቸው ሰዎች አብዛኞቹ የቆሎ ተማሪ የነበሩ ናቸው:: አባ አዳሙ ከሳ "አብዛኛው ይሰፋዋል:: ግን የሚችልም አለ:: የማይችልም አለ:: እኔ ግን እሰፋ ነበር:: የቆሎ ተማሪዎች ይሰፉታል:: የቅኔው የአቋቋሙ ተማሪ ይሰፋዋል:: እንደፋቂዎች ግን አንታይም:: ለምደነው እንጅ በዘር የለብንም" ብለውኛል::

ደበሎን በመስፋት ተጨማሪ የገቢ ምንጭ የነበራቸው ግለሰቦች ነበሩ:: እናም ደበሎን እየሰፉ ገበያ ላይ ይሸጡ ነበር:: "አንድ ደበሎ ተሰፍቶ ተለፍቶ በቀድሞ ጊዜ እስከ 20 ብር እንሸጥ ነበር:: ወደአሁኑ እየቀረ ሲሄድና ቆዳው ሲወደድ ግን እስከ አንድ መቶ ሃያ ብር ወሰደብን" ብለውኛል መረጃ አቀባዮች:: የቆዳው ዋጋ እየጨመረ መሄድ አሁን አሁን የማይለበስበት ደረጃ ላይ ተደርሷል:: በመጥፋት ላይም ነው::

በሌላ በኩል ደበሎ ለወንድ እንጅ ለሴት ልብስ ሆኖ አያውቅም:: የሚከለክል ህግ ባይኖርም በአካባቢው እንደነውር ስለሚቆጠር ሴት ደበሎ መልብስ አትችልም:: ይህም ሴቶች ሙቀት ልብስ ለብሰው ራሳቸውን ከብርድ እንዳይከላከሉ አድርጓቸዋል:: የደበሎ ዋናው ጥቅሙ መሙቀት መፍጠር ነውና:: ቄስ አጥናፉ ለማ መሸሻ የ36 ዓመት ወጣት ናቸው ዝቋላ ወገም ቀበሌ ወገም ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ከዋናው በር ዘወር ብለን ሰው ከሚያርፍበት ካብ ላይ ተቀምጠን የሴቱን መልበስና አለመልበስ ጠይቄያቸው ነበር:: የሚከተለውን መልሰዋል::

"ሴቶይ አይለብሱትም:: በባህላችን የለም /ለምንድን ነው?/ አይ ሴት ሲለብስ እኛም አላየንም፣ ሲያወሩም አልሰማንም:: ህግ አልከለከላቸውም:: ስለሚከብዳቸው ይሆን አላውቅም:: አሁን ቄስ አጥናፉ ለማ ለምሽቱ ደበሎ አሰፉ ቢባል በዚህ በሀገሩ መሳቂያ ነው የምሆነው:: ያልተለመደ ባህል ስለሆነ ይሳቅብኛል:: በወንዶይ ነው የቆየ" /29-08-2002/ መቼም ሴቶችን የማይለይ የለም:: አስቸጋሪውን ስራ ለይቶ ቢሰጥ ለሴቶች:: መብላት የሌለባትን፣ መልበስ የሌለባትን ባህሉ ይወስንላታል:: ለዚያም ነው ደበሎ ሴቶች እንዳይለብሱ በባህል የተገደበው::

ደበሎ ከማህበረሰቡ ውስጥ ሴቶችን ለይቶ ተጠቃሚ ባለማድረግ ልዩነትን ይወክላል:: ይህን አጢኖ ይመስላል ስለሰረት ከዘጠኙ የመተንተኛ ሞዴሎች ውስጥ ቁሶች ባህላዊነት ይንጸባረቅባቸዋል ያለው:: ሴቶች ይህን ይልበሱ ወንዶች ያን ይልበሱ የሚል የተጻፈ ህግ የለም:: ሆኖም በየትኛውም ማህበረሰብ ዘነድ የሴቶችን ተጠቃሚነት የሚገድብ ባህል አለ:: ባህሉ በፈጠረው ጫናም በወረዳዋ ያሉት ሴቶች ደበሎን እንዳይለብሱ ተለይተዋል:: ለዚህም ነው ደበሎ ልዩነትን ይወክወላል ያልኩት::

ደበሎ ለሴት አለመሆኑን በሚከተለው ስነቃላዊ ግጥም አፍቃሪ ሀሳቧን ገልፃለች::

"ደበሎ ለብሼ ገበያ ብወጣ

የተቀናበቱ ሰውየው የት መጣ::" ብላለች:: ሴቶችን በቅናት የሚያጋጨው ሰውዬ ደበሎ ለብሼ ከገበያ ብወጣ ሸሸኝ እንደማለት ነው:: አንቀልባ ሴቷን እንደሚያሳላ ሁሉ በተቃራኒው ደበሎ የሴቶችን ውበት ደበቂ ነው ማለት ነው:: ቁስ አጥናፉ ለማ እዳሉት "ታሳፍራለች" ማለት ነው:: አንቀልባ ለብሳ የምታኮራውን ያህል ደበሎ ብትለብስ ግን ታሳፍረዋለች የሚል ይመስላል:: ይህም ባህላዊ ለይነት ነው::

የደበሎ ቁስን መሰረት ያደረጉ ስነቃሎች ይወረወራሉ:: ስለመከፋት፣ ስለፍቅር፣ በሽላላ ወይም በዘፈን ስሜታቸውን ይገልፃሉ:: የተበደለ የተገፋ ወንድ በሽለላ ውስጣዊ ስሜቱን ይገልፃል:: ወደፊት መበደሉን እንደሚካስ በቀረርቶው ይገጥማል::

"ሲሆን ጋቢ ልብስ ሳይሆንም ደበሎ

ቀን ሳይወጣ አይቀርም እንዲህ ብሎ ብሎ" ይህ የተከፋ ወንድ ነጭ ጋቢ ለብሶ ከሰው ጋር ተቀምጦ ባያወጋ ባይጫወት ደበሎውን ለብሶ ብርድና ቁር ሳይበግረው ቂሙን ለመወጣት እንደሚሸፍት የሚጠቁም ይመስላል:: አንድ ቀን ይሳካልኝና ብድሬን መልሼ ማለቱ ነው:: በተለይ በብቀላ የሚያምነው የዳሞት ህዝብ እንደዚህ ያሉ ስነቃላዊ የሽለላ ግጥሞችን በየተገኘበት ሁሉ መወርወርና መዛት የተለመደ ነው::

ሌላው በደበሎ ሴቶች የፍቅር ፍላጎታቸውን በግጥም ይገልፁበታል:: የምትወደውን ወንድ እንደምትፈልገው ታንጎራጉራለች:: "ደበሎ ሳልገዛ ሳያከረሰሰኝ

አምወደው ዘንዳ ምንድን ልብስ ያድርሰኝ"

“የጥቁር ደበሎ ጥፊህ ከቂጥህ
ይች ልጅ አበደች ታሰኘኛለህ”

በጀመሪያዎቹ ስንኞች ከምትወደው ወንድ ዘንድ ለመድረስ ደበሎ ባለመግሏታ በዝናብ የመበስበሷን ስጋት መግለጿ ነው:: ሌላው ደበሎ የወንድ ልብስ ብቻ ስለሆነ ያንን ለብሽ ከውዴ ዘንድ እንዳልሄድ ደበሎ አልገዛሁም ማለቷ ነው:: ይህም ከመንገድ የሚጠልፋት ወንድ እንዳያጋጥማት ወንድን ተመስላ ለማሳሳት መፈለጓን ያሳያል:: የ"ፍቅር እስከ መቃብሯ"ን ሰብለ ያስታውሷል:: በዚህ ስነ ቃል ደበሎ ለሴቶች ከአንዱ ቦታ ወደ አንዱ ቦታ ለመሄድ እንደ ሽፋን ማገልገሉን የሚጠቁም ይመስለኛል:: አደጋን የመሻገሪያ ሽፋን ነው::

በሁለተኞዎቹ የስነ ቃል ስንጮች ደግሞ የጥቁር በግ ፀጉር ያለበት ደበሎ ለብሰህ በፍቅር አሳበድከኝ ማለቷን ያሳያል:: በሰው ዘንዳም ፍቅሬን አጋለጥክ እንደማለት ነው:: ይህ የሚያሳየው የጥቁር በግ ፀጉር የተሻለ ተመራጭ መሆኑን ነው:: ጥቁሩ የበግ ፀጉር ጥቁር ካባን ስለሚመስል የተለየ ክብርን ይገልፃል:: አሰፋፉም ካባን ይመስላልና:: እናም ደበሎ የተለየ የክብር ደረጃን ያሳያል::

በሌላ ጎኑ ደበሎ የእድሜ ደረጃን ያሳያል:: ልጅ ሁለት ሦስት የበግ ቆዳን ነው የሚለብሰው:: አሰፋፉ እደሜውን ይወስናል:: ልቡ ሴትን የመፈለግ አዝማሚያ ቢኖረውም በሴቶች ዘንድ በእድሜ አለመድረሱ ይተወቅበታል:: ለዚያም ነው በሚከተለው ስነ ቃላዊ ግጥም ልጅነቱን ቢያምንም ወደፊት ሊጎለምስ እነደሚችል ደበሎን በመጠቀም የነገራት::

“ደበሎ ለብሼ ብቆነጥጣት
በጥፊ ቃጣችኝ አያድግም መስሏት
እኔ ግን አድጋለሁ እመለመላለሁ
ከርሞም እህን ጊዜ አንችን አህላለሁ::” በማለት ያዜምላታል:: ተይ ልጅ ነው ብለሽ አትናቂኝ:: ደበሎዬ ልጅነቴን ቢያረጋግጥም አንችን ማከሌ አይቀርምና የተለየ ስሜት አይኑርሽ መለቱ ይመስላል::


ደበሎ መጥፋት ላይ ያለ ሀገርኛ የእጅ ስራ ቁስ ሲሆን ባህላዊ ልዩነትን የሚፈጥር ሙቀትና ተመራጭ ልብስ ነበር፡፡ የእድሜ ደረጃንና አካላዊ መጠንንም ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ የደበሎን አሰራር፣ ግልጋሎት፣ እንዲሁም ማህበረ ባህላዊ ሁኔታ በዚህ መልክ ለመጠቀም ተችሏል::

4.2.3. ክሳር አይነት የሚሰሩ ቁሶች

ክሳር አይነት የሚሰሩ ቁሶች ሲባል የሳር ቤትንም የስፌት እቃዎችንም እንደሚመለከት ይታወቃል:: ምክንያቱም መስሪያ ጥሬ ቁሳቸው ተመሳሳይ ስለሆነ:: ነገር ግን የሳር ቤት የሚለው በሀገረሰባዊ የምህንድስና ቁስ ራሱን ችሎ መታየት ስላለበት እዚህ ውስጥ ማስገባቱ አስፈላጊ አልመሰለኝም:: የስፌት እቃዎችን በተመለከተም ከአገልግሎታቸውና አሰራር ብልሃታቸው አኳያ በተፈጠረው ልዩነት በራሳቸው እንዲታዩ ተፈልጓል:: ምደባውም የስፌት እቃዎች በሚል ተጠቃለዋል::

በዚህ ርዕስ ስር የሚዳሰሱት ግን ክሳር አይነት የሚሰሩ ቁሶች ሲሆኑ ዝናብ ለማባረያነትና ለምንጣፍነት የማገልገላቸውን ያህል በአንድ ምድብ ሊታዩ ችለዋል:: የሸቆ ጥላ የምንለው የዝናብ መከላከያ ቁስ በአገልግሎቱ ከገሳ ጋር የሚመሳሰል ስለሆነ በዚህ መልክ አብሮ ለመመደብ ተቻለ እንጅ ከቀርቀሃ ተክል ጥሬ ቁስ እንደሚሰራ ይታወቃል፡፡ ዳውጃም ከነዚህ ጋር አብሮ መታየቱ የሳር አይነት በመሆኑና ከገሳ ጋር ስለሚቀራረብ ነው:: ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዳቸውን ለመግለፅ ሙከራ ይደረጋል::

• ዳውጃ፡ ዳውጃ የሚባለው የእጅ ስራ ቁስ ከጥንት የነበረና ለምንጣፍነት የሚያገለግል መሆኑን መረጃዎች ያስረዳሉ:: በወረዳዋ የተለያዩ ቀበሌያት ባሉ ቤተክርስቲያናትና ለሃብታም ሰዎች በተለየ የሚነጠፍ ነበር:: ጥሬ ቁሱ በወረዳዋ ባሉ የተለያዩ ረግረጋማ ቦታዎች ላይ የሚበቅል ቁጤማ የሚሉት የሳር አይነት ነው:: ከቀጤማው በተጨማርም አውራ ልጥና ውልከፋ ልጥ በጥሬ ዕቃነት ይቀርባል::



ፎቶግራፍ 15. የደረቀ ቁጤማ ጥሬ ቁስ

ደብተራ ተመስጌን ካሳ ጥሩነህን ደውጃ ማለት ምን ማለት ነው? ከመቼ ጀምሮስ አገልግሎት ላይ ነበር? ብዬ ጠይቄያቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውኛል:: "ዳውጃ ማለት ከቁጤማ ሳር የሚሰራ ለቤተክርስቲያን፣ ለሀብታሞች፣ ለደጀዝማቾች፣ ለፊታውራሪዎች፣ ለቀኛዝማቾች ምናጣፍነት የሚሆን ነው:: ከመቼ ጀምሮ ላልከኝ እኔ አላስታውሰውም:: ጥንትም ነበር ሲባል ነው የሰማሁት:: ጥንታዊ ምንጣፋችን ነው ዳውጃ" ብለውኛል:: /13-07-2002፣ ገሳግስ ማሪያም/ ዳውጃን ጥንታዊ የወረዳዋ መገልገያ ቁስ ነበር ማለት ይቻላል:: አሰራሩን በተመለከተም አቡሀይ በሻህ አይቸህ ዋሴን ጠይቄያቸው ነበር::

አቡሃይ በሻህ አይቸህ የ65 አመት አዛውንት ናቸው:: አቡሃይ የተባሉት ባለቤታቸው መተውባቸው ሁሉን ነገር ትተው የአቅላት ማሪያም ቤተክርስቲያንን እቃ ቤት ለመጠበቅ መነኩሰው ስለተቀመጡ ነው:: በአካባቢው ባህልም የመነኮሰ ሰው ለወንድ "አቡሃይ" ለሴት ደግሞ "እሙሃይ" ማለት የተለመደ ነው:: ተወልደው ያደጉትም እዚያው አቅላት ማሪያም ነው:: ያነጋርኳቸው ቤተክርስቲያን ውስጥ ባሉበት ወቅት ነው:: የአሰራር ሂደቱንም በተግባር አሳይተውኛል::



ፎቶግራፍ 15. የዳውጃ አሰራር ሂደት

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ቁጤማው በውሃማ መሬት ላይ ይበቅላል:: ይህ ቻክ ወይም ረግረግ የምንለው ውሃ አዘል መሬት አለ አይደለ? በዚያ ላይ ይበቅላል:: ከዚያ ላይ በተለይ በነሀሴ ወር ላይ ይነቀልና መስከረም ላይ ይደርቃል:: ከዚያም ለመስሪያነት የሚያያገለግል አውራ ልጥ ይቀርባል:: አውራ ልጡ ከቀጫጭን የዛፍ አይነት የሚላጥና ተሞልፍፎ ውስጠኛዋ ለስላሳዋ ክፍል ናት:: ይች ትደርቅና በውሃ እየተራሰች ትፈተላለች:: አውራ ልጥ ግን ድሮ ነበር:: አሁን ጠፍቷል:: እናም ከውልክፉ ዘፍ ላይ እንልጥና ሞልፍፈን ለስላሳ ክፍሏን አምጥተን እናደርቃታለን:: ከደረቀይ በኋላ በውሃ እየተራሰይ በጭናችን እንፈትላለን:: ከሁለት መቶ ከሶስት መቶ በላይ የሚሆን በጭናችን አንፈትላለን:: ልጡን ካዘጋጀንና ቁጤማውን ካቀረብን በኋላ ሁለት ባላ ያላቸው እንጨቶች እዚያና እዚያ እንተክላለን:: ከባላዎች ላይ ደግሞ አግድም ገመዱ እንዲወጠር እናደርጋለን:: በዚያም የፈተልነው ገመድ ዝቅዝቅ ይንጠለጠልና ቁጤማውን እያስገባን እንጎነጉነዋለን:: አውራ ልጡ ለስራው እንደ እውራ ይሆናል:: ልክ አንደጋቢ አሰራር ማለት ነው:: ይሄ ግን በእጅ እየተጎነጎነ እንጅ እንደሸማ ስራ አይደለም:: ቁጤማው ደግሞ መስሪያ ነው:: የተፈተለው የአውራ ልጥ ፈትል እንደዘሀ ሲሆን፣ ቁጤማው ደግሞ እንደማግ ይሆናል:: ከዚያም ከላይ ወደታች አውራ ልጡ ከስር ይደበቅና ቁጤማው ጎላ ብሎ እንዲወጣ በማድረግ እንሰራዋለን:: እንግዲህ አሰራሩ ይህን ይመስላል:: የርዝመትና የወርድ መጠኑ እንዲሁኔታው ነው:: ይረዝማልም ይጠባልም:: እንደፈላጊው ነው:: /15-07-2002፣ አቅላት ማርያም ቤተክርስቲያን/

በዚህ መልክ እንዲሰራ የተለየ ባለሞያ የግድ ባይኖርም ልዩ ጥበብ ያላቸው ሰዎች በተለይ ይሰሩታል:: ከግብርና ስራው ላይ የማይተጉ ሰዎችና መነኮሳት ይሰሩት ነበር ይባላል:: ሆኖም ሁሉም ሰው ከተማረው ሊሰራው እንደሚችል መረጃ አቀበዮች ነግረውኛል:: በግልጋት በኩልም አብዛኛውን ጊዜ ለቤተክርስቲያንና ለሃብታሞች ተባለ እንጅ ሌላው እንዳይጠቀምበት የሚከለክል ህግ የለም:: ማንኛውም ሰው ሊጠቀምበት ይችላል:: ሆኖም ለሀብታሞች፣ለባለስጣናትና ለቤተክርስቲያን በተለየ እንደሚጠቀሙበት መረጃዎች ያሳያሉ::



ፎቶግራፍ 16. ተሰርቶ የተጠናቀቀ ዳውጃ

ዳውጃን መነኮሳትና ቀሳውስት እየሰሩ ይሸጡ ነበር:: እንዲያውም በድሮ ጊዜ እስከ 20 ሽልንግ እየሸጡ ይጠቀሙ ነበር፡፡ ወደአሁኑ ግን ቁጤማው እየጠፋ ሲሄድና በዘመናዊ ምንጣፍም እየተተካ በመሆኑ እስከ መቶ ብርም እንደማይገኝ መረጃ አቀባዮቼ አጫውተውኛል::

የዳውጃ ቁስ ለአካባቢው ማህበረሰብ የተለየ ተምሳሌታዊ ይዘት ነበረው:: ይኸውም ዳውጃ ታቦታት ከመንበራቸው ሲወጡ በተለይ በጥምቀት ካህናቱ ስብሀቱ እግዚአብሄርን የሚያወርዱበት ነው:: የተከበሩ ሰዎችና መኳንንቱ ይቆሙበታል:: እናም ምንጣፍነቱ ከሌሎች የአካባቢው የምንጣፍ ቁሶች በተለየ ይከብራል፡፡ ታቦታቱንም ያከበራል:: ከእምነት ጋር አያይዘው የሚመለከቱትም አይጠፉም::የእግዚአብሄርን ታቦት ተሸክመው የቆሙበትን ዳውጃ እንደፈለጉ መርገጥ ያስፈራል፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሄር ከብሮበታል ብለው ስለሚያምኑ፡፡

ዳውጃ ከለምለም ቁጤማ ስለሚሰራና ራሱም ለምለም ስለሆነ ካህናቱን ኮረዶች በስነቃላዊ ግጥም እንዲህ ይሏቸዋል “ዲያቆኑ ዲያቆኑ ኧረ ቁሱ ቁሱ

ከዳውጃው ነው ወይ እጅህ መለስለሱ፡፡” በዚህም ዲያቆናትና ቀሳውስት ከቤተክርስቲያን አገልጋይነታቸው ጋር ተያይዞ የሚከበሩበት ነው:: የእጃቸውን መለስለስ በዳውጃ መስለው ይነግሯቸዋል:: ዳውጃና ቀሳውስት የነበራቸውን ጥብቅ ግንኙነት ያሳያል:: የእጅ ልስላሴያቸው የቤተክርስቲያን አገልጋይነታቸውን እንጅ ስራ አለመስራታቸውንም ያሳያል፡፡

ሌላው ዳውጃ የልምላሜና የውበት መገለጫ መሆኑን በማጤን በእሱ ላይ መተኛትን ይመርጣሉ:: ሰውነታቸው እንደዲያቆኑ እጅና እንደ ዳውጃው እንዲለልስና እንዲዋብ::

“አንተ የኔ ቅባት ጌጤና ህይወቴ

በደውጃ ላይ ነው የኔማ ውበቴ” የዳውጃ ውበት ገላጭነትን ይመሰክራሉ:: የዘመኑ ኮረዶች የሚያፈቅሩትን ዲያቆን በዳውጃ መስለው በስነቃላዊ ግጥም እየደረደሩ ያሞካሹ ነበር::

ዳውጃ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ እንደመንፈሳዊ ነገር ይቆጠር የነበረ መሆኑንም ስነቃላዊ ግጥሞች ያሳያሉ:: ዳውጃ ከቤተክርስቲያን ቁሶች አንዱ ነው ተብሎ ይታመናል:: ለዚህም ይመስላል “ዳውጃ ሲነሳ ቁሶች ይመስክሩ

እንኳንስ ተሰርቶ ለምለም ነው ከሳሩ::” የሚባለው:: ይህም ከላይ እንደተጠቀሰው ዳውጃና ቁስን ለያይቶ ማየት እንደማይቻል ነው:: የዳውጃን ጉዳይ ከቁሶች የበለጠ የሚያውቅ የለም እንደማለት ይመስላል:: ይህ የሚያሳየን ከጥንት ጀምሮ ቤተክርስቲያናቱ ለምንጣፍነት ይጠቀሙ የነበረው በደውጃ መሆኑን ነው:: ከህዝቡ ልብ ጋር የተወሀደ ስለነበር ይመስላል በስነቃላዊ ግጥም መጠቀሚያነት የዋለው::

የዳውጃ ቁስ በሌላ በኩል በሰርግ ጊዜ ለሙሽራ መርገጫነት በማገልገል ለምለምነቱን በመዘከር ያወዱሱታል:: የዳውጃ ለምለምነትን እንደተምሳሌት በመያዝ የሀብትና የልምላሜ መገለጫ ያደርጉታል:: ለዚያም ነው በሰርግ ላይ “ሆ በል ሙሽራ ..ሆሆ

እርገጥ ዳውጀ

እንዲሆን ቤቱ የላም የጥጃ... ሆሆ” በማለት የሙሽራ ሚዜዎቹ በሆታ ላይ ግጥሙን ያወረዱት:: ዳውጃ ረግጦ ማግባት ሙሽራዋ የወጣችበትን ቤትም ሆነ የምትገባበትን ሀብት እንዲሞላበት፣ ላሙና ጥጃው እንዲራባበት ከማሰብ የመነጨ ምኞት ነው:: እናም ሙሽራዋና ሙሽራው ዳውጃ ላይ ቁመው በአባቶቻቸውና በሽማግሌዎች ይመረቃሉ:: “እንደ ዳውጃው ለምለም ሁኑ ውለዱ ክበዱ” ይባላሉ:: ቁጤማ ከኖህ ጀምሮ የልምላሜና የምስራች መሰረት መሆኑ በታላቁ መጽሀፍ ቅዱስ ተጠቅሷል:: ለዚህም ነው ከቁጤማ ጥሬ ቁስ የተሰራውን ዳውጃ የልምላሜ፣ የብልፅግናና የሃይማኖት ተምሳሌት ተደርጎ በወረዳዋ ሁሉም ቦታ የሚታየው::

በአጠቃላይ ዳውጃ በአካባቢው በሚገኝ ጥሬ ቁስና በአካባቢያዊ እውቀት የሚሰራ በምንጣፍነት የሚያገለግል የእጅ ስራ ቁስ ነው:: የተለየ ሃይማኖታዊና ኢኮኖሚያዊ ተምሳሌትነት እንዳለውም መረዳት ይቻላል:: የልምላሜና የብልፅግና ወይም የሀብት ተምሳሌትም ነው ዳውጃ::

• የሽቆ ጥላ፡ የሽቆ ጥላ ከጥንት ጀምሮ በተለይ የቀርቀሃ ተክል በሚበቅልባቸው የወረዳዋ ደጋማ ቀበሌያት እየተሰራ የዝናብ ማባሪያነትና ለፀሀይ መከላከያነት ይውል እንደ ነበር ነው መረጃዎች የሚያሳዩት :: እንዲህ እንደአሁኑ በዘመናዊ ጥላ ግልጋሎቱን ከመነጠቁ በፊት በቀላሉ ከጓሮ ካለው የቀርቀሃ ተክል ተገፎ በሳር ቤት ክዳን ቅርፅ ተሰርቶ ግልጋሎት መስጠቱን መረጃ አቀባዮች ነግረውኛል:: እናም መስራያ ጥሬ ቁስ የሚሆነው የቀርቀሃ አንጓ መሸፈኛነት የሚውለው ሰፋፊ ሳር ነው:: ለእጅ መያዣነትም ከዚያው ከቀርቀሃው ተሰንጥቶ በማጭድ ልስልሶ ወይም ቀጠንና ቀጥ ያለውን ቀርቀሃ ቆርጦ በማበጀት ነው:: እንደወራጅና ማገርም ያው የቀርቅሀው ስንጣቂ ነው:: ከዚህ ውጪ የሽቆ ክዳኑን ከጣሪያው ማገር ጋር ለመስፋት ክር ይጠቀማሉ::



ፎቶግራፍ 17. የሽቆ ጥላ ጅማሮ ስራ

የአሰራር ሂደቱ በፎቶና በቪዲዮ የተደገፈ ሲሆን ይህን በተመለከተ አባ ድልነሳ አላምንህ በላይን አነጋግሬያቸዋለሁ:: አባ ድልነሳ የ80 ዓመት ባለፀጋ ሲሆኑ ተወልደው ያደጉት አቅላት ወይበኝ ቀበሌ ልዩ ስሟ "አባይ ውሃ" ከምትባል ጎጥ ነው:: ከቤተሰብ ሲወራረስ የመጣ የቅርቀሀ ጫካ አላቸው:: ቤተሰቡ /አወለዱ/ በጋራ የሚጠቀምበት:: እናም በቤታቸው ሽቆ ጥላውን ከወጣቶቹ ጋር ሁነው እየሰሩ ቃለምልልስ አድርጌያቸዋለሁ::

ሽቆውን ከቀርቀሃው ገፈን እናመጣዋለን:: ከዚያም መያዣ የሚሆን ቀርቀሃ እናበጃለን:: መያዣ ቀርቀሀው እንደአቋም ወይም እንደምሰሶ ይሆንና ይቆማል:: በዚህ በምሰሶ አምሳያ

በቆመው ቀርቀሀ ላይ እንደቤት ውቅር አድርገን ሌላ የተሰነጠቀ ቀርቀሀ እናዋቅርበታለን:: የተሰነጠቀውን ቀርቀሀ ካዋቀርን በኋላ ዙያውን እንደቤት ማገር ወይም እንደቤት ጣሪያ እንማግረዋለን:: ማግረን ከጨረስን በኋላ ማገሩ ቢያንስ ሶስት ዙር ይሆንና በላዩ ላይ በየማገሩ ያስቀመጥነውን የቀርቀሀ ሸቆ በክር እናደርግና በመርፌ ወይም በሹል እንጨት እንሰፋዋለን:: ማገሩን የምንማግረው ግን በአውራ ልጥ ነው:: ይህን አድርገን እንደጥላ እንጠቀምበት ነበር:: የዝናብም የፀሀይም መከላከያ ይሆናል:: /16-07-2002/

በአባ ድልነሳ አላምንህ ሀሳብ ሁሉም መረጃ ሰጭዎች ይስማማሉ:: በዚህ ላይ ግን የሸቆ ጥላን ለመስራት የተለየ ሙያን አይጠይቅም ብለውኛል:: ማንኛውም ሰው ይሰራዋል:: ሆኖም በወረዳዋ ደጋማ ክፍል ያለው ህዝብ ብቻ ነው የሚጠቀመው:: ገበያ ወጥቶም እንደ ማይሸጥ አረጋግጫለሁ:: እንዲያውም የሸቆ ጥላ አሰራሩ እንዲታጠፍ ሆኖ ያልተሰራ በመሆኑ በቀላሉ ይጎዳ እንደነበር ነው:: ገበያ ይዘውት ሂደው ዋጋቸውን ከውነው እስኪ መለሱ በየሀገራቸው የገበያ መውጫና መግቢያ መንገድ ዳር ላይ ያስቀምጡት ነበር:: በዚህ ጊዜም በቀላሉ ይሰባበራል:: አንዱ የአንዱን መውሰድ ግን የተከለከለ ነው::



ፎቶግራፍ 18. ተሰርቶ የተጠናቀቀው የሸቆ ጥላ

እንዳገኘሁት መረጃ ከሆነ የሸቆ ጥላ ግልጋሎት እየቀረ የሄደው እንደልብ ሊተጣጠፍ ባለመቻሉ ሰዎች በፈለጉበት ቦታ ላይ ይዘውት መቀመጥ ባለመቻላቸውና ዘመናዊ ጃንጥላ ስለተካው ነው:: በአጠቃላይ ያለምንም ወጪ ሁሉም በየጓሮው ካለው ቀርቀሀ እየገፈፈ በመስራት ዝናብና ፀሀይን ይከላከል እንደነበር ይታወሳል::

• ገሳ፦ ገሳ[10] እንደሸቆ ጥላ ሁሉ ለዝናብ ማባሪያነት ለእረኞችም ሆነ ለገበሬዎች የሚያገለግል ነው:: ለፀሀይ እንደማያገለግል ግን ይታወቃል:: የገሳ ቁስ ጥንት ጀምሮ የዝናብ ማብሪያነት ግልጋሎት ውሏል:: ገሳን "የአባቶቻችን ነበር" ይላሉ ቃል አቀባዮች::

እርሻ ስንሄድ ከብት ስንጠብቅ በክረምት ያለገሳ ከቤት አንወጣም:: ገሳ የሚሆነው ይሄ ፊላው ነው:: እንደቁጤማ ሁሉ ረግረጋማ ቦታ ላይ ነው የሚበቅለው ከቻኩ ላይ:: ይሄን እናመጣና በፀሀይ እናደርቀዋልን:: ከደረቀ በኋላ ፊላውን ዘርግተን እንደዳውጃ እንሰራዋለን:: መስሪያው ወይም ፊላውን እንደማገር:: የምንማግረው በውልክፉ ልጥ ነው ከሰራን በኋላ ወደጫፉ ስንደርስ እንደፋዋለን /እንቀልሰዋለን/ በተደፋው ላይ የውልክፍ ልጥ ማጠናከሪያ እንዲሆነው እያጠፍንም እናደርግና እንሰራዋለን:: ከዚያም ዝናቡ በክረምት ሲበረታ ለገበሬውም ለእረኛውም ያገለግላል:: /አባ ድልነሳ አላምንህ፣16-07-2002/



ፎቶግራፍ 19. የተሰራ ገሳ

የገሳ ቁስ ከዝናብ ማባሪያነት ውጪ የተለየ ትርጉም የለውም:: ሴትም ሆነ ወንድ ይለብሰዋል:: ማንኛውም ሰው ይሰራዋል:: ገበያ ላይም ይሸጥ እንደነበር ነው:: በዚህ ጥናት የተካተተበት ዋናው ጉዳይ ግን የአሁኑ ዘመናዊ ጥላና ከዩሪያና ዳኘ ማዳበሪያ የሚወጣው ላስቲክ ሳይመጣ የወረዳው ህዝብ ራሱን ከዝናብ ይጠለልበት የነበረ በመሆኑ ነው:: ስለሆነም ሙሉ በሙሉ ከመጥፋቱ በፊት በፎቶግራፍ የተደገፈ ታሪካዊነቱን መግለፅ ይጠበቃል:: በአጠቃላይ የዳውጃን፣ የሽቆጥላንና የገሳን አሰራር፣ ጠቀሜታን ከባቢያዊ ቁስ መሆናቸውን ለመጠቆም ተሞክሯል::

[10] ገሳ ጠርዙ እንደ ሰይፍ ስለትና ስፋት ያለው ከረግረግ ቦታ የሚበቅል የሳር አይነት ከገሳ የሚሰራ የእረኞች ልብስ /የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ 1993፣464/

4.2.4. ባህላዊ የስፌት እቃዎች


ባህላዊው የደጋ ዳሞት ወረዳ ማህበረሰብ ለምግብነት የሚያውለውን እህል ለማበጠር፣ ለመንፋት፣ ለመስፈር፣ ለማደራረጊያ፣ እንዲሁም ምግቡን ለመመገቢያና ጥራጥሬውን ለመብያ በቀየው በተገኘ ጥሬ ቁስ በመስፋት ይገለገል ነበር:: ከመቼ ጀምሮ መስፋት እንደተቻለ የማይተወቅ ሲሆን እንዲሁ ከዘመን ዘመን ሲሸጋገር የመጣ የሴቶች የስፌት ሙያ ነው::


የስፌት እቃዎች ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ውጤቶች በመሆናቸው በአካባቢው ጥሬ ቁስና ቀያዊ እውቀት የሚሰሩ የቁሳዊ ባህል መገለጫ ናቸው:: ከዝርያ ወደዝርያ ወይም ከትውልድ ወደ ትውልድ በሚተላለፍ አይቶ በመልመድ እውቀት እንጅ በትምህርት ቤት በሚገኝ ስልጠና ወይም ትምህርት ያለመሆኑን የተለያዩ ምሁራን ንድፈ ሀሳቦችም ሆኑ መረጃ አቀባዮች አረጋግጠዋል::

የኔአየሁ ዘለቀ አየለ የተባሉት የ40 አመት ወይዘሮ ተወልደው ያደጉት ልጅ ንጉስ ሲሆን፣ በልጅነታቸው ወደትዳር አለም በመግባታቸው አሁን የሚኖሩት ጭዋኔ ብሀንዴ ቀበሌ ልዩ ስሟ ገንቧች ከምትባል ጎጥ ነው:: ባለትዳርና የዘጠኝ ልጆች እናት ናቸው:: የሚተዳደሩትም በግብርና ነው:: ወይዘሮ የኔአየሁን የስፌትን ሙያ ከየት ተማሩት ማን ነውስ ፈጠረው ሲባል የሰሙት ብየ ጠይቂያቸው "ከመቼ ጀምሮ መስፋት እንደተቻለ አላውቅም:: መቼም እንዲሁ ነው:: ሲሰፉ ነው የማውቀው:: ያው ከጥት ከእናቶች የመጣ ይመስለኛል:: እኔም የስፌት ሙያን ያሳየችኝ እናቴ ናት:: እይው እንዲህ ብሎ ነው የሚሰፋ እያለች ነው ያሳየችኝ:: በሰፈርም እናቶችና የእድሜ እኩዮቸ ሲሰፉ በማየት ለመድኩ:: በማየትና በማስተዋል ነው:: በሀገራችን የስፌት ሙያ የሌላት ሴት ማን ይፈልጋታል" በማለት መልሰውልኛል:: /22-08-2002፣ ገንቧች/

የወ/ሮ የኔኤአየሁ ዘለቀን ሀሳብ እማሆይ ብሏየሁ አስረስ ዘገየ /26-08-2002 ገንቧች/፣ ወ/ሮ ያልጋ ደስታ ጌታሁን /28-08-2002 ገንቧች/፣ ወ/ሮ የኔውብ ወተቱ ዘለቀ/03-09-2002 ፈረስ ቤት/ እና ወ/ሮ መልካም የኔነህ አላምነህ /27-08-2002 ሙዞ በረት/ እንደሚጋሩ በቃለምልልሱ ወቅት ቃላቸውን ሰጥተዋል:: ሁሉም መረጃ አቀባዮች የስፌት ሙያን ከእናታቸውና ከሰፈር ሴቶች በማየት መልመዳቸውን ማረጋገጥ ተችሏል::

የስፌት መገልገያ የሆኑት የስፌት ቁሶች የሚሰፉት ከግራምጣ፣ ከሰበዝ(ሰንደዶ)፣ ከዝርማ ፣ ከስርስራ(ሰንበሌጥ) ሳር እና የዘምባባ እንጨትን በመሰነጣጠቅ ነው:: ጥሬ ቁሶቹ ግራምጣ ከጫካ የሚገኝ ሲሆን በየጓሮውም የሚተከልበት ሁኔታ አለ:: አክርማና እንዲሁም ስርስራ ሳር ግን በየመስኩና በየግለሰቦች በአጥር በታጠሩ ጥብቅ ወይም ከለላ ቦታዎች ይገኛሉ:: ምሰበ ወርቅንና ሞሰብ ስፌቶቹን ለማሰዋብ ደግሞ ግራምጣውን ሾነ ዝርማውን የለሰላ ቀለም መንከርና ማቅለም የተለመደ ነው:: መስፊያ መሳሪያውም ኮተቤረ ተሚሰራ በአካባቢው አጠራር ወስፌ የሚባል ነው:: የሚሰፋውም በእጅ ብቻ ነው ::






ለሰላ የተነከረ ዜምጣ ግራምጣ

ሰበዝ

ፎቶግራፍ 20. የስፌት ጥሬ ቁሶች

ባህላዊ የስፌት እቃዎች ከሳር ላይነት ጥሬ ቁሶች የተገኙ በመሆናቸውና በስፌት መያ በአንድ ምድብ ማስቀመጥ ተቻለ አንጅ ከአገልግሎት አኳያ ግን ይለያያሉ:: ከልዩነታቸው የተነሳም በርካታ ስያሜና ቅርፅ እንዲሁም መጠን አላቸው:: ከዚህ አኳያ በመጥፋት ላይ ያሉትን መሰቦ ወርቅ፣ ሞሰብ፣ ቀለምሻሽ፣ አገልግል፣ ወራንታ፣ ላዳን፣ ቁና፣ ወንፊት፣ ሰፊድ፣ የሰታቴ ድስትም ሆነ ለቀለምሻሽ ክዳን የሚሆን ወስከምባይ፣ የአገልግል ክዳን በማለት መሰየም ተችሏል::




ፎቶግራፍ 21. ሁሉም የስፌት አቃዎች ያሉበት ፎቶ

የስፌት ሙያ ለሴቶች የተተወ ነው:: ወንድ በወረዳዋ ማህበረሰብ ዘንድ መስፋት እንደማይችል ባህሉ ገድቦታል:: የሴትነት መለኪያ እንጅ ወንዱ ቁጭ ብሎ አንገቱን የሚያቀረቅርበት ሁኔታ የለም:: "ወንዶች የዳሪውን /የውጭውን/ ሴቶች የቤቱን" የሚሉት እናቶች በሴትነታቸው የስፌት ቁሶችን የመስፋትና ግልጋሎት ላይ የማዋል የእነሱ ብቻ እንደሆነ አምነዋል:: እንዲያውም ከላይ የፈጣሪ ስራ ድልድል እንደሆነ ነው የሚገነዘቡት:: በዚህ ገለፃ ላይ ትኩረት የተደረገው አጠቃላይ የሆነ የስፌት እቃዎችን በሚመለከት ነው:: የስፌት እቃዎቹ መስሪያ ጥሬ ቁሶች፣ የእቃዎቹ አይነት፣ ታሪካዊ አመጣጣቸው፣ ማን እንደሚሰፋቸው፣ እንዲሁም የተለያየ መጠንና ቅርፅ እንዳላቸው የተመለከተበት ነው:: ይህም እያንዳንዱን የስፌት አይነት በራሱ ብቻ ከመግለፅ አጠቃላይ ዳራ በመስጠት ቀጥሎ በገለፃም ሆነ በትንታኔ ለማሳየት በናሙናነት ለመምረጥም ያመቻል:: በናሙናነት መርጦ ለማየት የተፈለገው ወደ አስር የሚደርሱትን የስፌት አይነቶች ዝርዝር መግለፅ ስለማይቻል ነው:: በሌላ መልኩ የመጠን መለያየትና የአገልግሎት ልዩነት ነው እንጂ በአሰፋፍ ስራው አንዱ በአንዱ ይገለጣል:: ስለሆነም ሞሰበ ወርቅ፣ ወራንታ፣ ወንፊትና አገልግል የሚባሉ የስፌት አይነቶችን ቀጥሎ ለማቅረብ ተፈልጓል::

• **ሞሰበ ወርቅ፦** ሞሰበ ወርቅ[11] ከስሟ መረዳት እንደሚቻለው በአካባቢው አሰያየም እንደወርቅ የምታበረቅርቅ ውብ የሆነች የስፌት ቁስ እንደማለት ነው:: ፕሮን (2009)

[11] ሞሰበ ወርቅ ልዩ ልዩ ቀለማት ባላቸው አለላዎች ተጊጦ የተሰፋና ረዘም ወይም አጠር ያለ እግር ያለው /የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ 1993፣51/

እንዳሉት ባህላዊ ፍለጎትን ባገናዘበ መልኩ የአካባቢው ማህበረሰብ ከስፌቶች ሁሉ በተለየ በአለላ ቀለም በተነከረ የአክርማ ሳር አዝጎርጉረውና አስውበው ሰፍተዋታል:: በወርቅ መገለፀም በባህላዊው አስተሳሰብና ፍላጎት መሰረት እጅግ ልዩ እቃ መባሏን የሚያሳይ ነው:: ሞሰብ የሚለውን ስያሜም ያገኘችው በመጠን ይለያዩ እንጂ በቅርፅና በአሰፋፍ ጥበብ ከምሰብ ጋር ተመሳሳይ በመሆናቸው ነው::



ፎቶግራፍ 22. ሞሰብ ወርቅ

የ25 አመታን ወጣት ወ/ሮ የኔውብ ወተቱ ዘለቀን ሞሰበ ወርቅን እንዴት ነው የምትሰፏት ብየ ጠይቁያት ነበር:: የኔውብ ተወልዳ ያደገችው ጭዋኔ ብሀንዴ ቀበሌ ልዩ ስሟ ብሀንዴ ስላሴ ነው:: ከቆዳ ሰሪው ባለቤታ አቶ በላይ አለኸኝ ጋር ነው ከቆላ ሻንጊ ወደ ፈረስ ቤት ከተማ የመጡት:: እሷም በዘሯ የቆዳ ሰሪ ልጅ ናት:: የስፌት እቃዎችን በመለጎምና በመስፋት ትተዳደራለች::

> *ምጅምር መደቢን ዘርግተን እንሰፋታለን:: መደቢ ማለት ጥራጥሬም ይሁን ዳቦ ቆሎ ለማስቆረስ የምናደርግበት ነው:: እና መደቢን ከሰፋን በኋላ እንሰብራታለን:: የምንሰብራት መደቡን ለመስፋት የተጠቀምንበትን ሰበዝ ለሁለት እንከፍልና ወደታችና ወደላይ ለምንሰፋበት እንከፍለዋለን:: ወደታይ የተከፈለው የመሶበ ወርቁን እግር ለመስፋት ይሆነናል:: ከዚያም ሰበዝም ሆነ ሰንበሌጥ ሳር እየሰበዝን አለላ በተቀለመ አክርማና ባልተቀለመው እያዝጎረጎርን በወስፌ እንሰፋታለን:: እግሯን ከመደቢ ስብር ጀምረን ወደታች እየሰፋች ትሄዳለች:: እግሯን ከጨረስን በኋላ ደግሞ መደቡን ጨርሰን ወደላይ የተውነውን ሰበዝ እንሰፋለን:: ወደ ላይ የሚሰፋው እንግዲህ የምንፈልገውን ነገር እንዲይዝልን ነው:: ሞሰቢን ሰፍተን ከጨረሰን በኋላ ግጣም እንሰፋላታለን:: ግጣሚን ደግሞ በትንሿ እንወጥንና የሞሰቢን አፍ በመግጠም ልክ እየሰፋን ማውረድ ነው:: ከዚያም ልንጨርስ ስንል ከሞሰቢ አፍ ጋር ጥብቅ እንድትል የምንሰፋውን ሰበዝ ለሁለት ከፍለን ወደ ላይ አንድ ዙር ወደታች አንድ ዙር ሰፍተን እንቆርጣታለን:: ከዚያ በቃ ሞሰበ ወርቅ*

ተሰፋች ማለት ነው:: የሞሰብ መርቂ አሰፋፍ ሁኔታ የሞሰቡንና የቀለም ሻሹን ይመስላል:: በመጣናቸው ነው የሚለያዩት ክዳኗም ብትሆን እንዳገልግል ግጥምና እንደ ሞሰብ ናት:: መጠን ነው የሚለያቸው እንጅ አንድ ናቸው:: /03-09-2002፣ ፈረስ ቤት ክተማ/

የወ/ሮ የኔውብ ወተቱን ሀሳብ ሁሉም እንደሚጋሩት በቃለ መጠይቅ ወቅት አረጋግጫለሁ:: የሁሉም ሀሳብ መደጋገሙ ስለማያስፈልግ ነው የተውኩት:: በዚህ ላይ ግን የሞሰብን፣ የቀለምሻሽንና የአገልግል ክዳን የአሰፋፍ ተመሳሳይነት ማጤን የሚገባ ይመስለኛል:: ባህላዊ ሙያው ምን ያህል እንደሚስብ መረዳት ይቻላል::

የሞሰበ ወርቅ መጠን አነስተኛ እንደሆነ ተገልጿል:: የእግር ቁመት 0.20 ሳ.ሜ ሲሆን የአፍ ቁመት ደግሞ 0.15 ሳ.ሜ ነው:: የእኩሯ ስፋት 0.78 ሳ.ሜ ነው:: የአፏ ደግሞ 0.85 ሳ.ሜ :: መደቢም 0.18 ሳ.ሜ ነው:: የክዳኑ ቁመት 0.18 ሲሆን ዙሪያዋ 0.85 ሳ.ሜ ነው::

ሞሰበ ወርቋ በአካባቢው ማህበረሰብ ትልቅ ክብር ይሰጣታል:: "ሞሰበ ወርቅ በአለላ ተንቆጥቁጣ ትሰቀላለይ:: መከታ ላይ ነው የምትሰቀለው:: ክብር ናት:: አገልግሎቷ ጥሬይቱን ቆሎይቷን ዳቦቆሎይቱን ማስቆረሻ ናት:: ተዝጎርጉራ ተሰፍታ ለቤተክርስቲያን እናስገባታለን:: እጣን ምናምን ፀናፅል ያስቀምጡባታል" ብለውኛል እማሆይ ብሂየሁ አስረስ ዘገየ /26-08-2002/

ተንቆጥቁጣ መከታው ላይ መንጠልጠሏን አጢነው ይመስላል በስነቃል ግጥም ሰፊዋን የሚያሞግሷት::"ያች ሞሰብ የማን ናት ከግድግዳው ላይ

ያች ሽጋ ቆንጆ ጠላልፋት ነው ወይ":: የሞሰቧን ውበት የተመለከተ ሰው ነው ይህን ስነቃላዊ ግጥም በዘፈን ያዜመው:: የሞሰቧ የአሰፋፍ ጥበብ ማርኮት ሰፊዋን ያች ሽጋ ቆንጆ በማለት ያሞገሳት:: ባህላዊ ቁሶች የአካባቢውን ባህል በሚያንፀባርቅ መልኩ በመሰራታቸው የተነሳ ሰዎች ባህላዊ እሴታቸውን አዋህደው ይገልፁበታል:: የሞሰቧን ውበት ከሴቷ ውበት ጋር አዋህደው ሲገልፁ ይታያል::

“ሴት ሁኖ ተወልዶ ሲያወሩ ተማፈር
ይሻለኝ ነበረ ሞሰቤን ማጥበርበር”

ሞሰበ ወርቅን መስፋት የሴት ልጅን ክብር ይገልፃል:: ስለሆነም ስፌት የሴት ልጅ መገለጫ ይሆናል:: ስፌት መስፋት የማታውቅ ሴት ከሴቶች ጋር ለመመደብ እንደሚያሳፍራት በግጥሟ ውስጣዊ ስሜቷን ገልፃለች:: እንደ ሴቶች መስፋት አለመቻል ያሳፍራል:: እናም የሚሻለው የተጥበረበረ ሞሰብን መስፋት ነው በሚል መግለፅ ይቻላል::


ሞሰበ ወርቅ በቤተክርስቲያን ግልጋሎት ላይ የሚውሉ እቃዎች ማስቀመጫነት የክብር አቃ ናት:: እንዲያውም በወርቅ መሰየማቸው የእመቤቱ ተምሳሌት አድርገው በማየታቸው ይመስለኛል:: “ሞሰብ እሰፋለሁ እኔ በህይወት
የእመቤትን እቃ የማኖርበት” ተብሎ መገጠሙ በቅድስት ድንግል ማርያም መመሰሏን ያሳያል:: የእመቤቱ እቃ መቀደሻ፣ ፅናፅል፣ እጣን ማስቀመጫነቷን በግልፅ ያሳያል:: የወረዳዋ ህዝብ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን እንደመሆኑ እመቤቴን ልጅ በመውለድ ጊዜ መማፅኛው ናት:: ሴቶች ለእመቤቴ ያላቸው ፍቅር የተለየ ነው:: ለዚያም ነው በህይወት ዘመኔ የእመቤቴ እቃ የሚቀመጥበት ሞሰብ መስፋት አለብኝ ማለቷ::

በአጠቃላይ መሶበ ወርቅ የተባለችዋ የክብር፣ የጌጥና የአምልኮ ቁስ ከሌሎቹ የስፌት እቃዎች በተለየ በማህበረሰቡ እይታ ወይም ባህል ላይ ልዩ ስፍራ ተሰጥታለች:: ማህበራዊው ህይወትም የሴቶችን የሙያ ብቃት ይለይበታል:: ሆኖም ይህች ሞሰበ ወርቅ በአሁኑ ሰአት ቅርጿን ሳትቀይር መስሪያ ቋሷን ለውጣለች:: ይኸውም በክር እና በማዳበሪያ እያኸርጎረጎሩ መስፋት ተለምዷል:: እናም ለውጧ የቅርፅ ሳይሆን የመስሪያ ጥሬ ቁስ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል::

• ወራንታ፦ ወራንታ የሚባለው የስፌት ቁስ በቤት ውስጥ ደረቆት ሲቆላና ሲፈጭ፣ ጤፍ ሲበጠር፣ ብቅልና ጌሾ ሲወቀጥ ለማቀራረቢያ፣ ለመስፈሪያና ለመገደቢያ ያገለግላል:: መገደቢያነቱ እናቶች በቤት ወፍጮ ሲፈጩ ከቋቱ እየሞላ የሚወርደውን ዱቄት ማጠራቀሚያ ማለት ነው:: በጥንት ዘመን የወረዳዋ ማህበረሰብ ወራንታን ከግራምጣ፣ ከሰበዝ /ከስንደዶ/ እና ሰበዝ ከጠፋም ከሰንበሌጥ ሳር በመስፋት ግልጋሎት ያውል ነበር:: ይህም እዚያው በቀየው በተፈጠረ እውቀት የተሰፋ የየዕለት የስራ መከወኛ ነበር ማለት

ይቻላል:: በዚህ ላይም አሰፋፉን በተመለከተ ወ/ሮ የኔውብ ወተቱ የሚከተለውን ተናግራለች::

ወራንታው ሰፊ ነው:: በተለይ ከላዳን ይበልጣል:: መደቡ ሰፊ እንዲሆንና በትንሹ እንዳይታጠፍብን የወራንታውን ድርብ እንለዋለን:: መደቡ /ቂጡ/ እንደሰፈድ ሰፋ ይላል:: ከዚያ ሰፋ ብሎ ሰበር እያለ ይሰፋል:: የላዳኑ ግን መደቡ ጠበብ ይልና ስብሩም እንደወራንታው ዘርጋ ሳይል ጠቅለል ብሎ ይሰፋል:: ቂጡ ከጠበበ ወራንታ አይሆንም:: እና በቁመትም ከላዳን ይበልጣል:: የቁና አሰፋፍም በዚህ መልክ ነው:: ግን ጠባብና በጣም ትንሽ ናት:: ይህችዋ ደግሞ ከላዳንም በጣም ታንሳለች:: ለጥሬ መብያ ናት:: ለህጻናትም ምግብ መብያ ትሆናለች:: ለወራንታ እስከ 50ም 60ም ዙር እንሰፋለን:: ያው እንደወረንታው ነው:: ቀጠን አድርገን የምንሰፋው ከሆነ የዙሩ ቁጥር ይጨምራል ካወፈርነው ግን ዙሩ ያንሳል:: ከወፈረ በ40 ዙር ላይ እንቆርጠዋለን:: በዚህ ሁኔታ ተሰፍቶ አንዳንዴይ በቆዳ ይለጉመታል፣ አዳንዴይ ደግሞ ቂጡንና አፉን ለጉመው ለማቀራረቢያነት ይጠቀሙታል:: /03-09-2002፣ ፈረስ ቤት ከተማ/



ወራንታ ላዳን ቁና

ፎቶግራፍ 24. ወራንታ፣ ላዳንና ቁና

ወራንታ ራሱን የቻለ ቅርፅና መጠን አለው:: ቅርፁ ከቂጡ /መደቡ/ ሰፋ ብሎ ከቁመቱ እየሰፋና እየተዘረጋ የሚወጣ ነው:: ከመደቡ ሰፋ ማለቱ ነው እንጅ በጋሻ መልክ ወይም ቅርፅ የተሰፋ ነው:: መጠኑን በምናይበት ጊዜ የአፉ ዙሪያ 2 ሜትር፣ የመደቡ ሰፋት 0.30 ሳ.ሜ እና ቁመቱ 0.21 ሳ.ሜ ነው:: ወራንታ በየትኛውም የወረዳዋ ክፍል የሌለበት የለም ነበር:: አሁን በተለያዩ የላስቲክ ምርቶች ግልጋሎቱ እየተቀማ በመሄዱና የግራምጣና

LS LIBRARY

የሰበዝ ጥሬ ቁስ እየጠፋ በመሄዱ መስፋቱ እየቀነሰ ነው:: ለዚህም ነው በሚከተለው የስነቃል ግጥም የተገለፀው::

"አሁን በመጣችው ትንሽ ቁጥር ሰሀን
ከመመላለስህ ስፈር በወራንታህ
ባያት በቅድመ አያት በድሮው ርሰትህ::" ከዚህ የምንረዳው ወራንታ ትልቅና ሰፊ በመሆኑ እህል ለመስፈር ባንዴ ለማጠቃለልና ስራን ለማቀላጠፍ መጥቀሙን ነው:: የፋብሪካ ውጤት በሆነችው ትንሽ የላስቲክ ሰሀን እየቆነጠርክ ጊዜህን ከማባከንና ጉልበትክን ከመጨረስ ከአያት ከቅድመ አያትህ በወረሰክው የእጅ ስራ መስፈሪያ ቁስ ተጠቀም ማለቱ ነው::

"ወራንተየን ወስደሽ ሰፍረሽ ቶሎ ቶሎ መልሽው
በቃሉም አይገኝ የዘመኑ ሰው" በማለት ትጉኋ ሰፊ የተዋሰቻትን ሴት ትነግራታለች:: የዘመኑ ሰው ከተዋሰ በቶሎው እይመልስምና ሳይረሳ አምጭልኝ ማለቷ ነው:: በዚህም ወራንታ መስፈሪያነቱ በስነቃል ተነግሯል:: መዋስን የተመረረችዋ ሴት ደግሞ

"ወራንታ እሰፋለሁ ሁሉን ነገር ትቼ
ያን መንከራተቱን ሰጡኝን ጠልቼ" ትላለች:: ካለው መዋዋስ የወረዳዋ ዋና የባህል እሴት ቢሆንም /ቃለ አቀባዮች እንደነገሩኝ/ የራስን ሰፍቶ ለመዋስ ከመንከራተቱ ስራንም ከመፍታት ያድናል የሚለው ብሂል ለሰነፍ ሴቶች ለመንገር የተዜመ ስነቃላዊ ግጥም ነው::

ወራንታ ሰፊና ትልቅ ስለሆነ የመስፋት ትዕግስትን ይጠይቃል:: እናም ሰነፍ ሴት አይሰፋውም:: በዚህ የተነሳም ሰነፏን ሴት ጎበዝ ሴቶች በዚህ መልክ ይተርቧታል::

"በወር ዙር በወር ዙር አንድ ወራንታ ቆርጣ
እናትና አባቷ ሞቱባት በደስታ" ይሏታል:: አንድ ዙር በወር ሰፍታ ከአመት በኋላ ወራንታ በቆረጠችው ልጅ እናትና አባቷ ደስታ ሞቱ መባሉ ሽሙጥ እንጅ መገሳ አይደለም:: ስፌት አይተው አያውቁ አይነት ስነቃላዊ ተረብ ነው:: በአሽሙር ጎሸም ሲያደርጓት ነው::

ወራንታ መስፋት ትጉህነትን ስለሚጠይቅ በስነ ቃላዊ ግጥም ቅልጥፍናን መግለፅ ይቻላል።

"ግራምጣ ገዝቼ ወራንታ እሰፋለሁ

ጀምበር እስኪገባ እጨርሰዋለሁ።" ይህች ሴት እንግዲህ በወር አንድ ዙር ከምትሰፋዋ ሴት ጋር አወዳድራት። ጎበዟ በጀንበር ግባት ወይም በቀን ውሎ አንድ ወራንታ ስትሰፋ፣ ያችኛዋ ደግሞ በአንድ ወር አንድ ዙር። ጎበዟ በቀን 40 እና 50 ዙር ስትሰፋ ሰነፏ በወር አንድ ዙር። እናም የመጀመሪያዋን ሴት ከእናትና አባቷ ጋር ምን ያህል እንዳሸሞሯት መገንዘብ አያዳግትም። ይህም በአካባቢው በሚሰሩ ቁሶች ምክንያት ስሜት መግለፅ እንደሚቻል ነው። ቁሶች የማንነት መገለጫዎች ናቸው። በአጠቃላይ የወራንታ የአሰፋፍ ሂደትና አገልግሎት በዚህ መልክ የተገለፃና የተተነተነ ይመስለኛል።

• ወንፊት፦ ከስፌት ቁሶች ውስጥ በዋናነት የምትመደበው ወንፊት[12] ናት። ወንፊት እንደ ሞሰበ ወርቅ ሁሉ የቅርፅ ሳይሆን የመስሪያ ጥሬ ቁስ ነው ለውጧ። ስለሆነም በአሁኑ ሰአት በብረት በተሰራ ወንፊት ተቀይራለች። ግለጋሎቷም ለመንፊያነት ነው። ያለ ወንፊት እህልን አስፈጭቶ ወይም ፈጭቶ መብላት አይቻልም።

> *ወንፊትማ ያለወንፊትማ አይሆንም። ወንፊትማ እሱ ነው የሚያጣራልን ሁሉን ነገር። ብቅልም ሆነ ጌሾም ሆነ ሰንወቅጥ ያለሱ መለያ የለንም። ጥሬውን ጤፍም ሆነ ዱቄቱን ስናጣራ ያለ ወንፊትማ መቼ ይሆናል። ወንፊትና ሰፌድ አንድ ናቸው። ሰፌድን የሚተካው የለም። ዋና እብቁን እያንገዋለልን የምንለይበት ነው። እስከ አሁንም ያልተለወጠ በዚህ በአካባቢያችን ሰፌድ ነው። ወንፊት ግን በብረት እየተቀየረ ነው /የኔአየሁ ዘለቀ አየለ፣ 22-08-2002፣ ገንቢች/*


በማለት የተናገሩላት ወንፊት ልዩ ግልጋሎት ስለነበራት ነው። በማሽን ተሰርታ ባትመጣ ኑሮ እንደሰፌድ ሁሉ የማትተው ነበረች።

ወንፊት እንዴት እንደምትሰፋ ሂደቱን እስኪ ንገሪኝ በማለት የኔውብ ወተቱን ጠይቂያት "ግራምጣ እንሰነጥቅና በውሃ አርሰን እንፈትላለን። ፈትለን እናጠራቅምና መንፊያ መደቡን ሊያስነፋ በሚችል ልክ እንጎነጉነዋለን። መደቡን ከስንዝር በሚበልጥ ሁኔታ እንጎነጉነውና ዙሪያውን እየጠቀለልን እህሉን ደግፎ የሚይዝ እንሰፋለን። ከዚያ ወደ ላይ ስድስት ዙር እንሰፋለን። በመደቡ ደግሞ ዳር ለዳር ለማስቀመጫ እንዲሆን ሁለት ዙር እንሰፋለን። ከዚያ

---

[12] ወንፊት እህልን ወይም ዱቄትን ለመንፋትና ተፈላጊው ከማይፈለገው ለመለየት የሚያገለግል ከአክርማ፣ ከስንደዶ፣ ከግራምጣ የሚሰራ እቃ /አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ 1993፣413/

በቃ እንነፋበታለን::" /03-09-2002/ መደቡ ለመንፊያነት ሲሆን ከመደቡ ዙሪያ ወደላይ ስድስት ዙር የሚሰፋው ደግሞ እህሉን ደግፎ ለመያዣ ነው::



ፎቶግራፍ 24. ወንፊት

የወንፊትን የጎላ ጠቀሜታ በመገንዘብ ማህበረሰቡ በስነቃላዊ ግጥም ስሜቱን ይገልፃል:: እንዲህ በማለት "ዱቄቱ ተፈጭቶ እህል ተበራይቶ

ያለ ወንፊት አይሆን በጎታ ተሞልቶ::" ዱቄቱም ሆነ እህሉ በጎታ ቢሞላ ያለወንፊት ማዘጋጀትና ለምግብነት ማዋል እንደማይቻል ነው::

"ዘረር አርገህ ንፋው አደራ ወንፊት

መቼም ያላንተ አይሆን የእንጀራው ውበት" ይባልለታል:: የእንጀራው ውበት የሚወጣው ቆሻሻውን ሁሉ ወንፊት ሲያጣራው ነው:: ያለወንፊት ግን አሰሩ ሁሉ አብሮ ይቦካና የእንጀራውን ውበት ያደበዝዛዋል:: "ሰፊፍ የመሰለ እንጀራ" ሲባልላት ነው የምትወደው ሴቷ:: በዚህም የሴቶችን ጠንቃቃነትና ባለሞያነት መግለፅ ይቻላል:: ለዚያም ነው

"የወንፊቱ ሙያ እያለ በጃችን

ምነው ያልተነፋ እህል መብላታችን" መባሉ::

በወንፊት የስፌት ቁስ ብዙ ተብሏል:: በቁሷ አማካይነት የሰዎች ውሽታምነት ወይም ሚስጢር አባካኝነት ይገለፃል:: ፊት ለፊት ከመናገር ይልቅ በእጅ በተሰራ ቁስ አንድን ሰው ባህሪውን መንገር የሚቻልበት ሁኔታ በማህበረሰቡ ተለምዷል::

"ሚስጢርክን ለባይድ ምነው የነገርከው

ወንፊት ውሃ ይዞ የትሲደርስ አየኸው" መባሉ ባይድ ሚስጢር አይጠብቅም ማለቱ ነው:: ውሃ በወንፊት የማይቻል ነው:: እናም ሚስጢሬን ለባይድ ብነግረው ለሌላ ሰው አሳልፎ አወራበኝ ቢለው ውሃን በወንፊት በመያዝ መስሎ ሲነግረው ነው ከግጥሙ

የምንረዳው:: በሌላ በኩል "እሱ ወንፊት ነው" ከተባለ ሚስጢር አይጠብቅም፣ ባገኘበት ሁሉ ይናገራል ለማለት ነው:: በወንፊቷ ሙያ የሰውየውን ነገር አፍሳሽነት ይነግሩበታል::

በአጠቃላይ ወንፊት እንዴት እንደሚሰፋና ከሌሎቹ የስፌት ቁሶች በተለየ ለማህበረሰቡ የሰጠችውን ግልጋሎት መግለፅ ተችሏል:: ከወንፊት ሙያ ተነስተው እንዴት ሀሳባቸውን እንደሚገልፁም በስነቃል ከቀረቡት ግጥሞች ተንትኖ ለማሳየት ተሞክሯል:: እናም ወንፊት በወረዳዋ ማህበረሰብ ዘንድ የተለየ ድርሻ እንዳላት መረዳት የሚቻል ይመስለኛል::

• **አገልግሉ** አገልግል ከግራምጣ፣ ከሰበዝና ከአለላ /አክርማ/ የሚሰፋ የስፌት ቁስ ነው:: ይህ የስፌት ቁስ በድሮ ጊዜ ለፈትል፣ ለጥጥ፣ ለልብስና ለስንቅ መያዣነት ያገለግል ነበር:: እንዲሁም ሻንጣና ቁምሳጥን ሳይመጣ አገልግል ለልብስ መያዣነት ተመራጭ ነበር:: ሴቶች የአምልኮ መግለጫቸውን ቁሳቁስ ያስቀምጣሉ ይባል ነበር:: እናም አገልግልን የጥንት ሰዎች ለጦርነትም ሆነ ለስራ ከቤት ሲወጡ የስንቅ መቋጠሪያ ያደርጋሉ:: ሆኖም በአሁኑ ሰአት በመጥፋት ላይ ነው:: በሳጥን፣ በሻንጣና በመሳሰሉት ዘመናዊ ቁሶች እየተለወጠ ነው::

አገልግል ራሱን የቻለ የአሰፋፍ ሂደት አለው:: የአሰፋፍ ሂደቱን በተመለከተ የኔውብ ወተቱ የሚከተለውን ብላለች::

> *አገልግል ምጅምር መደቡን እንሰፋለን:: መደቡን ሰፍተን ስንጨርስ ሰፋ ካለ ለትልቅ ጠበብ ካለ ለትንሽ አገልግል እናደርገዋለን:: መደቡን ሰፍተን ስንጨርስ ሰበር አድርገን መያዣውን ወደላይ እንሰፋለን:: ዘጠኝ ዙር ወደላይ ሰፍተን እንቆርጠዋለን:: ከዚያም የአገልግል ክዳኑን እንሰፋለን:: የክዳኑ አሰፋፍ ደግሞ ጠበብ አድረገን እንወጥናታለን ያችን እንደወስከንቢያ ሰፋ ሰፋ እያደረግን እንሰፋታለን:: እታይ ስንደርስ ልንቆርጣት ስንል አንዷን ሰበዝ ወደ ላይ አድርገን አንድ ዙር እንሰፋለን:: ወደታች የተውናትን ደግሞ ለመግጠም እንዲመች አድርገን አንድ ዙር እንሰፋለን:: ከዚያ ስንጨርስ መቁረጥ ነው:: በኋላም የምንፈልገውን ጥጡን፣ ፈትሉን እናስቀምጥበታለን /የኔውብ ወተቱ 03-09-2002/*



ፎቶግራፍ 26. ለልጉም የተሰፋ አገልግል

አገልግል ለስንቅ መያዣነቱን ከላይ ተጠቁሟል:: በተለይ ከወረዳዋ የገጠር ቀበሌያት ከዛሬ 30 አመት በፊት ወደዋናዋ ከተማ ፈረስ ቤት እየመጡ የሚማሩ ተማሪዎች በአገልግል የሳምንት ቀለባቸውን ይዘው ነበር:: በእርግጥ አሁንም ቢሆን በወረዳዋ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ብቻ በመኖራቸው ከገጠር ወደ ከተማዋ መምጣት አይቀርም:: በተለይ ቅድመ ዩኒቨርሲቲ የሚማሩት ከከተማዋ ብቻ ስለሆነ ስንቅ ማጓጓዙ ይጠበቃል:: እናም ተማሪዎች አገልግሏን በተመለከተ ስነቃላዊ ግጥም ገጥመውላታል::

"እንጀራው ዳቦውን የራት የምሳዬ
እናት አንችን ሰጠኝ ፈጣሪ ጌታዬ"
"ሌላ እህል አትቀምስም ወይ በሶ ወይ ገንፎ
በእንጀራ በዳቦ ሆዷ ተቆልፎ"
"አንጀቷ ሰፊ ነው ሆዷ ጎርጓዶ ናት
ሁሉን በሆዷ ነው አገልግል የኔ እናት"

በነዚህ ሦስት ጥንድ ስነቃላዊ ግጥሞች ተማሪዎች የአገልግልን ጥቅም ገልፀዋል:: አገልግልን በእናት መስለው ነው እየተናገሩ ያሉት:: እንጀራና ዳቦውን በአገልግል ይገር ባልመጣ ኑሮ ራትና ምሳየን ከየት እበላ ነበር የሚል ነው:: በሌላም ያለ እንጀራና ዳቦ በስተቀር በሶ ወይም ገንፎ ሊያዝባት እንደማይችል ወይም ተማሪዎች እንደ ቤት ልጅ ገንፎን የመሰለ የቅንጦት ምግብ እንዳማያገኙ የገለፁበት ይመሰለኛል:: እኛ የምንፈልገውን ሁሉ ልክ እንደእናት ትይዝልናለች በማለት ነው::

ከዚህ በዘለለ ጠለቅ ብለን ስንመረምረው አገልግል የእናት ተምሳሌት መሆኗን ነው:: እናት ሁሉን ቻይና የሆድ ቀልብ ናት:: እርሀብ አስታጋሽ ዳኛሽ ናት:: ለዚያም ነው "እናት ካለች

ባይበላስ" የሚባለው:: እናት ካለች ምግብ አለ:: አገልግል ካለች ስንቅ ይቋጠራል:: እራትና ምሳ ይበላል:: ከዚያም ያሰቡት ቦታ መድረስ ይቻላል:: ልክ እንደ እናት አለኝታነቷን ገልፀዋታል የሚል ሀሳብ አለኝ:: በዚህ ላይ አገልግልን ሲያንገላቷት የተመለከተ ተማሪ

"ኧረ እናንተ ልጆች በጣም ሸወዳችሁ

እሱን መከረኛ አትንኩት ባካችሁ

እንጀራ በውስጡ ስለያዘላችሁ" በማለት የተከላካይነት ሚናውን ሲጫወት ማየት ይቻላል::

አገልግልን ለተለያየ የቁሳቁስ ማስቀመጫነቷን አይተናል:: በሌላ መልኩ ግን በአካበቢው ማህበረሰብ አንዳንድ ሴቶች "የአምልኮ እቃ" ማስቀመጫ ያደርጉታል:: ለህመም መከላከያ ተብሎ የተሰራ ቀይ፣ ጃኖው ቦግ ያለ ቀሚስ /ጥብቆ/ ይቀመጥበታል:: ጨረቃ ጠልሰሙ የብር ሀብሉ በአጠቃላይ ጨሌው ይቀመጥበታል:: በዚህ መልክ ስናየው የአምልኮ ቁሶችን ማስቀማጫነትም ይጠቀሙበት ነበር:: የአምልኮ ጨሌ ያለበትን ሙዳይ ያለእናቲቱ በስተቀር የሚነካው የለም:: "የእሷ ቆሌ አይን ያጠፋል" ተብሎ ይታመናልና::

በዚህ ላይ ወ/ሮ የኔአየሁ ዘለቀ አየለ እንዳሉት "ለዛር መውረጃ ተብሎ የተቀመጠ ልብስ ሙዳይን ከፍቶ ማየት ክልክል ነው:: እኔ ልጆቹን እንዳይነኩ ባላደርግም የእኔ እናት ግን የቅቤ ቅሏንና አገልግሏን እንድንነካባት አትወድም ነበር:: ለእሷ ህመም ብቻ ሳይሆን እኛን አንድ ምናምን ወይም ቆሌው ይደነብቅበኛል /ይመታብኛል/ ብላ በመስጋት ነው" /22-08-2002፣ ገንቧች/ ከዚህ የምንረዳው በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ የአምልኮ ጨሌ መቀመጫነት ማገልገሉን ነው::

በአጠቃላይ አገልግል ለወረዳዋ ማህበረሰብ ይሰጥ የነበረውን አገልግሎትና የአሰራር ሂደቱን እንዲሁም በተመረጡ ስነቃሎች በአገልግሉ አማካይነት ሊተላለፍ የተፈለገውን ጉዳይ ተንትኖ ለማሳየት ተችሏል የሚል ግምት አለኝ:: በመቀጠል የስፌት እቃዎችን አማካይ መጠን በሰንጠረዥ ለማሳየት ይሞክራል::

ሰንጠረዥ 3 የስፌት ዕቃዎች አማካይ መጠን ማሳያ

የስፌት አይነት		ቁመት		ዙሪያ		የመደብ ስፋት	የስፌት ዙር ብዛት
		እግር	አፍ/ክዳን/	እግር	አፍ/ክዳን/		
ሞሰበ ወርቅ	ዋና	0.25ሳ.ሜ	0.18ሳ.ሜ	0.30ሳ.ሜ	0.85ሳ.ሜ	0.18ሳ.ሜ	-
	ክዳን	-	0.16ሳ.ሜ	-	0.85ሳ.ሜ	-	-
ሞሰብ	ዋና	0.50ሳ.ሜ	0.25ሳ.ሜ	1.80ሳ.ሜ	1.60ሳ.ሜ	0.40ሳ.ሜ	-
	ክዳን	-	0.30ሳ.ሜ	-	1.60ሳ.ሜ	-	-
ቀለምሻሽ	ዋና	0.30ሳ.ሜ	0.7ሳ.ሜ	1.23ሳ.ሜ	1.63ሳ.ሜ	53 ሳ.ሜ	-
	ወስከምቢያ	-	0.30ሳ.ሜ	-	1.63ሳ.ሜ	-	-
አገልግል	ዋና	0.22ሳ.ሜ	-	-	1.56ሳ.ሜ	-	-
	ክዳን	-	0.30ሳ.ሜ	-	1.56ሳ.ሜ	-	-
ወንፊት		0.3ሳ.ሜ		1.10ሳ.ሜ		0.25ሳ.ሜ	6
ሰፊድ		-		1.70ሳ.ሜ		0.50ሳ.ሜ	15-20
ወራንታ		0.21ሳ.ሜ		2.ሜ		0.30ሳ.ሜ	40-60
ላዳን		0.16ሳ.ሜ		1.40ሳ.ሜ		0.15ሳ.ሜ	20-30
ቁና		0.6ሳ.ሜ		0.60ሳ.ሜ		0.8ሳ.ሜ	8

4.2.5. ባህላዊ የእጅ ስራ ቁሶች በመጥፋት ላይ ለመሆናቸው ተጽዕኖ ፈጣሪዎች

በዚህ ጥናት የተመለከትኳቸው ባህላዊ የድንጋይ ወፍጮዎች፣ ከቆዳ የሚሰሩ ቁሶች፣ ከሳር አይነት የሚሰሩ ቁሶችና ባህላዊ የስፌት እቃዎች ባህላዊ የእጅ ስራ ውጤት መሆናቸውን ለመጠቆም ተሞክሯል:: ለዘመናትም የወረዳዋን ማህበረሰብ የለት ተለት የስራ ተግባር መከወኛነት ሲያገለግሉ ነበር:: አሁንም ቢሆን አንዳንዶቹ በተወሰነ መልኩ በግልጋሎት ላይ ናቸው:: ሆኖም ለውጥ እያንጎበጎባቸው ለመሆኑ በአካላዊ ምልከታና በቃል አቀባዮቹ በኩል ለማረጋገጥ ችያለሁ::

ለውጡ የቅርፅ፣ የጥሬ ቁሰ፣ ጨርሶም የመጥፋት ነው:: ለውጥ ለምን መጣ ማለት እንደሌለብን ባህላዊ ቤቶችን ባየንበት ወቅት ለመጠቆም ተችሏል:: ምክንያቱም ለውጥ

የተፈጥሮ ህግ ስለሆነ:: የሰው ልጅም የአስተሳሰብ አድማስ ባለበት አይቆምም:: አካባቢውን የበለጠ እየተረዳና እያወቀ በሄደ መጠን ይጠቀምባቸው የነበሩ ቁሶችን ባሉበት የማሻሻል ወይም እንዳሉ ለውጦ በምትካቸው ስራ ሊያቀላጥፉ የሚችሉና ቀላል ቁሶችን ማምረቱ ይጠበቃል::

የዚህ ጥናት ዋና ጉዳይም ለምን ተለወጡ አይደለም:: ነገር ግን ሲለወጡ አሻራቸው አለ ወይ? የተካቸውስ ምን ቁስ ነው? ተጽእኖ ፈጣሪዎችስ ምን ምን ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ ማስፈለጉን በማጤን ነው::

- **የደን መጨፍጨፍ:-**

ይህ የተፈጥሮም ይሁን ሰው ሰራሽ ክስተት በበርካታ ባህላዊ የእጅ ስራ ቁሶች ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል::በትወራ ዳራው ለይ ለማንሳት እንደተሞከረው የደን ውጤት የሆኑት እንጨት፣ ሳርና ሀረግ የመሳሰሉ ጥሬ ቁሶች እየጠፉ መሆናቸውን አይተናል:: የእንዚህ ጥሬ ቁሶች አለመኖርም በእጅ ስራ ቁሶች ለውጥ ላይ ያነጣጠሩ ተፅዕኖዎችን ደቅነዋል:: በደን መጨፍጨፍ የተነሳ ለዳውጃ እንዲሁም ለባህላዊ የስፌት እቃዎች የሚሆነው የሳር አይነት እየቀነሰ ሄደ:: ምክንያቱም ለገሳና ለዳውጃ የሚሆኑት ፊላና ቁጤማ የሚበቅሉበት ረግረጋማ መሬት ደረቀ፤ ሳሩንም ከብቱ በላው:: መሬቱም ለእርሻ ዋለ::

በሌላ በኩል በድርቅ መስፋፋት የተነሳ በቁጤማና በፊላ የሳር ቁሶች የሚሰሩ ዳውጃና ገሳ እየጠፉ ነው::

> *ቀጤማውም ሆነ ፊላው እንደልብ አይገኝም:: ድሮ ሜዳው ሁሉ ያበቅል ነበር:: ከብቱም እንደልቡ ይበላ ነበር:: አሁን ግን ድርቅ ሆነ:: ድርቅ ሲሆን ጊዜ ረግረጉ ደረቀ:: ከብቱ እንደልቡ እየገባ በላው:: ከብቱ ተራበና በላው:: አንዳንድ ሰዎች በየጓሯቸው እንደአትክልት ተክለው የሚንከባከቡት ናቸው እንጅ ጠፍቷል:: በዚህ የተነሳ ዳውጃና ገሳ መስራት ቀንሰናል:: እንደልብ የለም /አቡሃይ በሻህ አይቸህ፣ 15-07-2002፣ እቅላት ማሪያም/*

በደን መጨፍጨፍና በበርሃማነት መስፋፋት የተነሳ ዳውጃና ገሳን መስራት ያለመቻሉን ያህል በደኑ ውስጥ ለውስጥ የሚበቅለው ግራምጣ የሚባለው ለመስፊያነት የሚያገለግለው ጥሬ ቁስ አብሮ ጠፍቷል:: ሰበዙና አክርማውም ከብቱ አማራጭ ሲያጣ ጊዜ እየበላው ነው::

የህዝብ ብዛቱም በመጨመሩ ጫካውንም ሆነ የሳር መሬቱን አረሰው:: በዚህ ምክንያት ባህላዊ የእጅ ስራ ቁሶችን መስራት እየቀነሰ ሂዷል::

የደንጋይ ወፍጮን በተመለከተ በተለይ የውሃ ወፍጮ በአሁኑ ሰአት ሙሉ በሙሉ መተከል ያቆመው በደን መጨፍጨፍ የተነሳ ጎርፍ መሬቱን በላውና የወንዙ ውሃ ይሄድበት የነበረው መሬት ጥልቀቱ ጨምሮ ውሃውን ማውጣት ባለመቻሉ ነው:: በርሃማነትም በመስፋፋቱ ምክንያት ውሃው በተለይ በበጋ እያነሰ ሂዷል:: አካላዊ ምልከታ ባደረኩበት ወቅት በርካታ ወፍጮዎች ይተከሉበት የነበረው የ"ግንባራ ውሃ" ለድንችና ለሽንኩርት እንኳን በመጥለፍ ሳይሆን በዘመናዊ ሞተር ፖምፕ እየወጣ ነው ሲሰራ የተመለከትኩት::

መ/ር እዳሻው ቻሌ የውሃ ወፍጮ መትከል የተቋረጠበትን ምክንምያት በሚከተለው መልክ በስፋት ገልፀውታል::

> *በውሃ ወፍጮ መፍጨት ያቆምንበት ምክንያት በተለይ ዋናው የተፈጥሮ መዛባት ነው:: በፊት የነበረን የውሃ መጠን በጣም በከፍተኛ ነበር:: እናም በጋ እስከክረምት የምንፈጭበት አካባቢ ነበር:: አሁን ግን ውሃው በጣም እየቀነሰ ነው የመጣው:: የምንጠጣውም እያጣን ነው:: ሁለት ቶን የድንጋየ ወፍጮ የሚያዞር ቀርቶ የሚጠጣም እያጠጠ የመጣበት ወቅት ላይ ነን ያለነው:: ይህም የበረሃማነት መስፋፋት ነው:: ጫካው ጠፍቷል:: እየተመነጠረ ወደ እርሻ ተለውጧል:: ጎርፉም በረታና የውሃውን መውጫ በጣም ጥልቅ አደረገው:: ምንጮች ባህር ዛፍ እየተተከለባቸው ደርቀዋል:: የህዝብ ቁጥርም በዕለት ተዕለት እየጨመረ ሄደ:: በዋናነት እንግዲህ የተፈጥሮ መዛባት ነው:: /02-07-2002፣ ምሰባ 1ኛ ደ/ትቤት/*

በመምህር እንዳሻው ሀሳብ የውሃ ወፍጮ ባለቤት የነበሩት አቶ ልይህ ወርቅነህ፣ አቶ ምን ይችል ዘወልድ፣ የውሃ ወፍጮ አውጭው አቶ አስናቀ ይሁኔ ይስማማሉ:: በተለይ አቶ ልይህ ወርቅነህ የአባታቸውን የአቶ ወርቅነህ ባይነስ አይቸህን የውሃ ወፍጮ ወርሰው ነበር የሚሰሩት:: እናም ክረምት ሲሆን በጎርፍ ብዛት የተነሳ በበጋ የገደቡትን የውሃ ጎተራ ጠራርጎ እየወሰደባቸው አድካሚ የስራ ጊዜን አሳልፈዋል:: "በበጋ ጊዜም ውሃው እጅግ በማነሱ ምክንያት የውሃ ወፍጮ ሙያ ቀርቷል:: ጉልበታችንን ጨረሰብን:: ውሃውም ደረቀ:: ሌላው ከላይ ያለው ሰው ውሃውን እያወጣ ድሮ ተጠቅሞ የማያውቀውን ድንች

ሽንኩርት በመትከል ተጠቀመበት:: ውሃው በዚህ የተነሳ አነሰ:: በየጊዜው ብንከስም አልተቻለም:: ኑሮው ሲወደድ ጊዜ ሰው ተጫማሪ አትክልትን መጠቀም ፈለገ" /05-07-2002፣ ሸባ/ ብለውኛል::

በአጠቃላይ የደን መጨፍጨፍ በርሃማነትን አስከተለ:: ለደን መጨፍጨፍም የህዝብ ቁጥር መጨመር ነው:: በዚህ የተነሳ ከሳር አይነት የሚሰሩ ቁሶችንና በተለይ የውሃ ወፍጮ ቁስን ለመስራት እየቀነሰ የሄደበት ሁኔታ ተፈጥሯል:: ስለሆነም ለእጅ ስራ ቁሶቹ በመጥፋት ላይ መሆን እንደዋና ተፅዕኖ ፈጣሪነት ማየት የሚቻል ይመስለኛል:: የመስሪያ ጥሬ ቁሶች አቅርቦት መቀነስ በቁሳዊ ባህሎች ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ በደን መጨፍጨፍና በበረሃማነት መስፋፋት የተነሳ መሆኑን ከዚህ ጋር አብሮ ማየት ይቻላል::

- **የኢንዱስትሪ አብዮት መከሰትና የምርቶች በገፍ መመረት:-**

የኢንዱስትሪ አበዮት ተለይ ባደጉ ሀገራት የተጀመረው በ18ኛውና በ19ኛው ክፍለ ዘመን መሆኑ ይታመናል:: ይሄ የኢንዱስትሪ አብዮት መስፋፋት የእጅ ስራ ሙያን ወደ ፋብሪካ ወይም ወደ ማሽን ስራ ለወጠው:: ፋብሪካዎችም በገፍ ማምረት ጀመሩ:: ሮበርት ውስጠ ዶርሰን (1972) እንዳሉት ወደ ገጠራማው ክፍል መጉረፍ ጀመሩ:: ወደገጠራማው ክፍል በመጉረፍም በርካሽ ዋጋ ቀረቡ:: በዚህ ምክንያትም በየሀገራቱ በባህላዊ የእጅ ሙያ ተሰርቶው በሚሸጡ ቁሶች ላይ የገበያ ፍላጎት መቀነስን አስከተሉ:: የእጅ ስራ ባለሞያዎችንም ከተወዳዳሪነት ውጪ አድርገዋቸዋል::

የፋብሪካ ምርቶች መመረት የስፌት ቁሶችን በሀገራዊ እውቀት መሰራት ቀንሷል:: ግላሲ (1999:240) እንዳሉት ቁርጥራጭ ብረቶችና ለስላሳ የፕላስቲክ ምርቶች የስፌት እቃዎችን እየለወጡ ነው:: እነዚህም ተፈጥሯዊ ትውስታን እንደሚያጠፉ ይታመናል:: ስለሆነም ሳህን መሰል የፕላስቲክ እቃዎች በእጅ የሚሰፋውን የአካባቢ ቁስ ቁናን ተኩ:: በቁና መብላት ቀረ:: ሌላው ሞሰብና ቀለምሻሽ በትሪ ተለውጧል:: እንደመረጃ አቀባዮቹ ከሆነ ትሪውን ጠረጴዛ ላይ አድርጎ መመገብ ስለተቻለ ሞሰብንና ቀለምሻሽን መስፋት አላስፈለገም:: ወራንታንና ላዳንን ሳፋ መሰል ፕላስቲኮች ለወጡት:: ለመስፈርም ሆነ እህል ለማቀራረብና ለመያዝ ሳፋን በቀላሉ ገዝቶ መጠቀም ተቻለ::

የወረዳዋ ህዝብ በገበያ ቀን ዋጋ ይለዋወጥበትና እየሰፈረ ይሸጥበት የነበረው ላዳን አሁን በብረት ጣሳና በፕላስቲክ ጆግ ተቀየሯል:: ይህን ጉዳይ በገበያ ቀን ባደረኩት ምልከታ አረጋግጫለሁ:: መረጃ አቀባዮቹም ምልከታዬን ተጋርተውታል:: እህልን ወይም ዱቄትን ለመንፋትና ተፈላጊውን ከማይፈለገው ለመለየት የምታገለግለው ተፈላጊ ወንፊትም በሰበዝና በግራምጣ መስፋት ቀርቶ ከብረት መመረት ቻለች:: እናም ቅርጿን ባትለውጥም ጥሬ ቁሷን አጥታለች::

ሌላው ሞሰበ ወርቅን፣ ሞሰብን እንዲሁም ወሰክንባይ ነገሮች በክርና በማዳበሪያ ትልታይ እየተሰፉ ነው:: እነዚህም የቅርፅ ሳይሆን የመስሪያ ጥሬ ቁስ ለውጥ ይታይባቸዋል:: ሆኖም ግልጋሎታቸው ቀንሷል:: ለምግብ ማቅረቢያ ሳይሆን ወደጌጥነት ተለውጠዋል:: በዚህ ላይ የአገልግሎት ለውጥንም ማየት ይቻላል::

ከሳር አይነት የሚሰሩ ቁሶችንም የፋብሪካ ምርቶች እየተኳቸው ነው:: ዳውጃን ዥንጉርጉር የስጋጃ ምንጣፍ፣ የሸቆ ጥላንና ገሳን ዘመናዊ ጃንጥላና የዩሪያና የዳፕ ማዳበሪያ ላስቲክ ተክታቸዋል:: ከዝናብም ሆነ ከፀሀይ በጃንጥላ መከላከል ተችሏል:: ይህም የዘመኑ ኢንዱስትሪ የወለደው ምርት ምን ያህል ተፅዕኖ እያሳደረ እንደሆነ መገመት አያዳግትም::

የውሃ ወፍጮንና የቤት ወፍጮን በተመለከተም ዘመናዊ የሞተር ወፍጮ መጥቶ ከግልጋሎትና ከስራ ውጪ አድርጓቸዋል:: ወፍጮው በፋብሪካ ተጋግሮ መመረት ጀመረ:: ለመፍጨትም የሰው ጉልበትና የውሃ ኃይል አላስፈለገም:: ዘመናዊ ሞተር ያሸከረክረዋል:: ስራን በማቀላጠፍም አቻ አልተገኘለትም:: ሆኖም ነዳጅን /በገጠር/ ስለሚጠቀም በዋጋ ላይ ያመጣው ጫና የበዛ ነው:: ከአንድ ሽልንግ ወደ አርባና ሃምሳ ብር ሊለውጠው ችሏል:: በውሃ ወፍጮ ማስፈጨት እየቀረ የሄደው ከ1980ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ መሆኑን መረጃ አቀባዮቼ ነግረውኛል::

ከቆዳ የሚሰሩ ቁሶችንም ዘመናዊው ምርት ጫና ፈጥሮባቸዋል:: በቆዳ ምርቶች ላይ በተለይ ተፅዕኖ የፈጠረው ይሄ የማዳበሪያ ኬሻ ነው:: የማዳባሪያ ኬሻ የማይሆነው የለም:: አብዛኛውን ቁስ እየተካው ያለው ይሄ ነው:: አቁማዳን፣ ስልቻን፣ ምናርን፣ ማንጠቢያን፣ ገርንዲንና ላምነትን እየተካ ነው:: ይህም የፋብሪካ ምርት ውጤት ነው:: የማዳበሪያ ኬሻውን

/ከረጢቱን/ በመተርተርና በመፍተል ለማንጠቢያ፣ ለመጫኛነት፣ ለምናርነት መጠቀም ተችሏል:: ለእህል መክተቻነቱም ተመራጭ ሁኗል:: ገለባ ከትቶ እየተሰፋም ገርንዲንና ላምነትን በመተካት ለመኝታነት ውሏል:: አንሶላን በማነጠፍ መጠቀም እንደሚቻል መረጃ አቀባዮች ነግረውኛል:: እኔም በአካል አይቻለሁ:: ባደርኩባቸው የገጠር ቤቶች በገርንዲ ሳይሆን በማዳበሪያ ፍራሽ ላይ ነው የተኛሁት::

አቶ በላይ አለኸኝ "ኮሸኮሽ ያለበት የማዳበሪያ ኩንታል ከመጣ ጀምሮ አቁማዳ መስራት ትተናል:: እየቀነሰ ሄዷል:: ኮሸኮሽ ያለበትን ማዳበሪያ ማር ይጭኑበታል:: ነጋዴው ከከተማ ያመጣዋል:: የጠላ ማድረጊያ፣ የደፍድፍ መደፍደፊያ፣ የልጉስ መለጎሻ፣ ለእዳ የሚሆን ጠላ መጫኛና ለውሃ መቅጃ ያደርጉታል:: ገበሬው አቁማዳን ትቶ ወደዚያ ተሰማርቷል:: ስለዚህ አቁማዳ መሰራቱን አቁመናል::" ብለውኛል /11-07-2002/

ሌላው በመቀቱ መልካምነት "ከልብስ ደበሎ ከመብል ድጉሎ" ይባልለት የነበረው ከበግ ቆዳ ይሰራ የነበረው ደበሎ በጎጃም አዘነ ልብስ ተቀይሯል:: ጎጃም አዘነው በፋብሪካ በሚመረተው ጥለት በሸማ ሰሪዎች የሚሰራ ነው:: በፋብሪካ ተመርቶም ፎጣ ተብሎ ይቀርባል:: ደበሎ መልበስ እየቀረ የሄደው በደርግ ጊዜ በየህብረት ሱቁና በየገበያው ይመጣ በነበረው የፋብሪካ ፎጣ ሲሆን፣ በኢህአዴግ መንግስት ግን ጎጃም አዘነ የሚባለው መጣና እንዳለ አስቀረው:: አይደለም ደበሎን ዘመናዊ ብርድልብስንም እየተቀናቀነው ነው:: በተለይ በደጋ ዳሞት ወረዳ የቀንም የሌትም ልብስ ነው::

በአጠቃላይ የዘመናዊ ኢንዱስትሪ በመስፋፋቱ የተነሳ በወረዳዋ ያሉ የእጅ ሙያተኞችን ከገበያ ውድድር ውጪ ከማድረጉም በላይ ባህላዊ የደንጋይ ወፍጮዎችን፣ የቆዳ ቁሶችን ከሳር አይነት የሚሰሩ ቁሶችንና የስፌት ዕቃዎችን በሀገር በቀል እውቀት እንዳይሰሩ አድርጓል:: የለውጥ ተዕዕኖው የቅርፅ፣ የመስሪያ ጥሬ ቁስ፣ የአገልግሎትና ጨርሶ የማጥፋት እንደሆነ ለማየት የተቻለ ይመስለኛል::

- **ባህላዊ ቁሶች የኋላቀርነት ምልክት ተደርገው መወሰዳቸው:-**

በሀገረሰባዊ ቁሶች ላይ የጥሬ ቁስ አቅርቦት መጥፋትና በዘመናዊ የኢንዱስትሪ ምርቶች ከገበያ ውጪ የመደረጋቸውን ያህል ዘመናዊው ትውልድ የጥንት የአባቱን መገልገያ ቁሶች

የኋላቀርነት ምልክት ናቸው በማለት እንደሚንቃቸው የቃል አቀባዮች መረጃ ያሳያል:: በጥንቱ ሞሰብና ቀለምሻሽ ሳይሆን ምግቡን የሚበላው በትሪና በፕላስቲክ ነው:: በተለይ የከተማ ሰው በእንግድነት ከቤቱ ቢሄድበት በድሮ ለሹማምንት ያቀርብበት የነበረውን ሞሰብ በጓሮ ጥሎ ከቤቱ ባይኖር እንኳ ከጎረቤት ትሪ እየተዋሰ እንደሚያቀርብ እሙሃይ ብሏየሁ አስረስ አጫውተውኛል::

በባህላዊ የደጋ ዳሞት ማህበረሰብ ዘንድ ትንሿ የስፌት ቁና ለልጅ ምሳና ጥራጥሬ መብያ ነበረች:: አሁን ግን እማሆይ ብሏየሁ እንዳሉኝ "በሰሀኔ ነው የለወጥነው:: ማን ነክቶልን በቁና:: የድሮውን አይበላበትም:: እኛም በቁና አናቀርብም:: በኮለል /በጥራር/ ነው በምን ያቀረባችሁልን ይላሉ:: በተለይ የተማሩትና ከተማ ያሉት ናቸው የሚንቁት:: ቁናውን ናቁብን" /28-08-2002፣ ገንቧች/ ከዚህ መረዳት እደተቻለውም በጥንቱ የስፌት ዕቃ መመገብ የኋላቀርነት መለያ ሁኗል::

በሌላ በኩል ደበሎ ከበግ ቆዳ በመሰራቱና በግም ያልጠፋ በመሆኑ ለምን አይለበስም ብዬ የጠየቋቸው አባ አዳሙ ካሳ "አይ ህዝቡ ትቶታል:: ልቦናው እየኮራ ሰው ሌላ ሌላ ልብስ ይለብሳል እንጂ ይህንስ ትቶታል::" ብለውኛል:: /12-07-2002፣ ሻንጊ ማሪያም/ "ልቦናው እየኮራ" ነው ያሉት አባ አዳሙ:: ይህም ለቀየው ምርት ያለውን ንቀት ያሳያል:: አባ አዳሙ አክለውም "ደበሎ አትልበሱ የሚል ህግ ባይኖርም የፋብሪካ ምርቶች ደበሎን ያስንቃሉ:: እናም ህዝቡ የተሻለውን ስላገኘ ደበሎውን ናቀው" ብለዋል:: ደበሎ መልበስ የኋላቀርነት ምልክት ነው ማለት ይቻላል በቃል አቀባዮች ሀሳብ መሰረት:: የቆሎ ተማሪ መለያ የነበረውን ደበሎ ትቶ ጎጃም አዘነን ለበሰ:: "የቆሎ ተማሪ እንዲያውም ራሱ እየጠፋ ወደ ዘመናዊ ትምህርት እየገባ ስለሆነ ለቤተክርስቲያንም አገልጋይ ላይገኝ ነው" ብለዋል ቄስ አጥናፉ ለማ:: ለቤተክርስቲያን አገልጋይ ማን እንደሚተካ አሳሳቢ መሆኑንም መረዳት ይቻላል::

የሴትነት መለያ የነበረውን የቆዳ ውጤት አንቀልባ ስንት ትዳር እንዳላስፈረሰ ሁሉ አሁን በፎጣው፣ ከከተማ በሚሄድ ጀሮና ማሳሪያ ያለው ጨርቅ ማዘያ ስለተካው ይከረፋኛል የሚል ስሜትን እንደፈጠረ ለመረዳት ችያለሁ:: እንዳስተዋልኩት ከሆነ የአካቢው እጀ ሰሪዎች የሰሩትን ቆዳ ቅባት ቀብቶ መልበስ እየተናቀ የሄደበት ሁኔታ አለ:: ማህበረሰቡ

የኋላቀርነት መለያችን ነው ብሎ የተወው ቁሳዊ ባህል የሀገርን ክብር ካለመገንዘብ የመጣ ሀሳብ ይመስለኛል::

- **የባህላዊ ቁስ ባለሞያዎች ሙያውን ለልጆቻቸው ማውረስ ያለመፈለግና ልጆችም ሙያውን መናቃቸው:-**

ይህን ርዕሰ ጉዳይ በትወራዊ ዳራው ላይ እንዴት እንደተገለፀ ማየት ይቻላል:: ስለሆነም ትውልዱ የሀገሩን የእጅ ስራ ምርት እየናቀ የሚሄደ ከሆነ በዚህ ዘመናዊ ዓለም ማን ሙያውን ለልጁ ያስተምራል:: ልጁስ ዘመናዊ ትምህርት ተምሮ ራሱን ይለውጣል እንጅ ለምን በአባቱ ሙያ ይሰማራል:: እነዚህ አስተሳሰቦች በፈጠሩት መጥፎ ስሜት የተነሳ ሀገር በቀሉ ሙያ እየጠፋ ነው:: የቆዳ ስራ እየተተወ የሄደ ይመስላል:: እርስዎ እንደነገሩኝ ከሆነ አባት ለልጁ ማውረስ ካልቻለ አይረሳም ይላሉ ያለኳቸው አቶ የደሜ ብርሃኑ የሚከተለውን መልሰውልኛል::

> *አዎ ይረሳል እንጅ:: አሁን የእኔ ልጆች ወደዚህ ሙያ የዞረ የለም:: ሁሉም ተማሪዎች ናቸው:: እኔ የተማርኩት ካባቴ ነበር:: አሁን እኔ ከምትኩ ማን ይቀበለኛል:: ልጆቼ እንደሁ ሙያውን አያውቁትም:: ተምረውም ቦታ ይቀይራሉ:: ከዚያ በኋላ ያባትን ሙያ ማን ያነሳዋል:: የእኔ ብቻ እኮ አይደለም:: ዘመኑ የትምህርት ስለሆነ የገጠሩ ሁላ እየተማረ ነው:: እናም የምናወርሰው የለም:: /14-07-2002፣ ፈረስ ቤት ከተማ/*

እንደ አቶ የደሜ ብርሃኑ ከሆነ ስጋታቸው የሚገባ ነው:: እንዲያውም በዚህን እለት በመስሪያ ቤታቸው ጓሮ ቃለ መጠይቅ እያደረኩላቸው እያለሁ ሴት ልጃቸው ከርቀት ላይ ሁና ስትረብሻቸው እንደነበር ተመልክቻለሁ:: ለቆዳ ሙያ ምን ያህል የሀፍረት ስሜት እንደተሰማት መረዳት አያዳግትም:: እናም ልጆቻቸው ሙያቸውን በመናቅ እንደተውባቸው ማረጋገጥ ችያለሁ::

የደንጋይ ወፍጮዎች፣ የስፌት እቃዎችና የሳር አይነት የእጅ ስራ ቁሶች ሰሪዎች ግን በሙያው አፍረውበት ሳይሆን ዘመናዊው አለም ባመጣው የቴክኖሎጂ ውጤት መተካት ስለቻለባቸው ነው:: እናም በወረዳዋ ቀበሌያት በተዘዋወርኩበትና ከቃል አቀባዮቼ ባገኘሁት መረጃ መሰረት ሙያዬ ብሎ ቁጭ ብሎ የሚሰፋና የሚፈጭ አላጋጠመኝም:: ሴቶች ወደ

ቀለም ትምህርት እየገቡ መማር እንጅ እንደድሮው ፈጭታ እና ሰፊታ ተብላ ለባል የምትሰጥበት ሁኔታ የለም:: የሆነ ሆኖ እነዚህ የእጅ ስራ ቁሶች በዘር ሳይወራረስ ቀርተው መሥያው እንደሚጠፋ ግን ልብ ማለት ይገባል::

- ባህላዊ የእጅ ስራዎች እንደተጨማሪ ስራ መታየታቸው:-

ሮበርት ውስጠ ዶርሰን ባህላዊ የእጅ ስራ ባለሞያዎች የግብርና ስራን እንደተጨማሪ ስራ ያዩ የነበረ መሆኑን ጠቁመዋል:: በተመሳሳይም ላጵሶ ጌድልቦ የሀገራችን የእጅ ባለሞያዎች ከእርሻና ከእንስሳት እርባታ ጋር አጣምረው መስራታቸውን ገልፀዋል::/1983:231/ ድሮውንም ቢሆን ባህላዊ እጀ ሰሪዎች በእጅ መሥያቸው ብቻ ሳይሆን በተጓዳኝ በግብርና ላይ የመሰረተ ነበር::

አሁን የሚታየው ሁኔታ ግን የተለየ ነው:: ምክንያቱም እንደወረዳዋ እጀ ሰሪዎች ከሆነ ከደርግ ጊዜ ወዲህ በመሬት ላራሹ መርህ መሰረት የተሻለ መሬት በማግኘታቸው የኑሮ መሰረታቸው ግብርና ሆኖ የእጅ ስራውን በተደራቢነት ይዘውታል:: ይህም ከዘመናዊነቱ ጋር ተዳምሮ የቆዳ ስራውን ወደ መተው ያዘነበሉ ይመስላል:: እናም ባህላዊ የእጅ ስራ መሥያን እንደተጨማሪ ማየቱ የጎላ እንደሆነ ማረጋገጥ ይቻላል:: በቁሶቹ ላይ የሚመጣው ተፅዕኖም ቀላል አይደለም::

በአጠቃላይ በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ውስጥ የተገለፁትና የተተነተኑት በመጥፋት ላይ ያሉ ባህላዊ የድንጋይ ወፍጮዎች፣ ባህላዊ የስፌት እቃዎች፣ ከሳር አይነት የሚሰሩ ቁሶችንና ከቆዳ የሚሰሩ ቁሶች ከላይ እንደተገለፀው የመጥፋት አደጋ ተጋርጦባቸዋል:: በሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ቁሶች ላይ ያለው ለውጥ በብዛት እየተከሰተ የሄደው በኢህአዴግ መንግስት እንደሆነ መረጃ አቀባዮቼ አረጋግጠዋል:: እኔም በምልከታዬ እንዳስተዋልኩት ከሆነ ጫካው ሁሉ ተመናምኖ በርሃማነቱ ተስፋፍቷል:: ብቻ ሁሉም ለቀየው ባይተዋር ሁኗል ማለት ይቻላል:: በዚያ ላይ ወደ ወለጋ፣ በምራብ ጎጃም አዊ ዞን በምስራቅ ጎጃም ደግሞ የጁቤ ጫካ ለመመንጠርና ለማረስ ገበሬው ፣ተማሪው፣ ነጋዴው፣ ሴት ወንዱ ያዙኝ ልቀቁኝ ሲል ተመልክቻለሁ:: ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ምን ምን እንደሆኑ በዚህ ሁኔታ ለመጠቆም ተሞክሯል::

4.2.6. የደጋ ዳሞት ወረዳ ባህላዊ የእጅ ስራ ሰሪዎች ማህበራዊ ደረጃ

በ4.2. ንዑስ ምዕራፍ ስር የተለያዩ ባህላዊ የእጅ ስራ ቁሶችን የአሰራር ሂደትና መስሪያ ጥሬ ቁስ እንዲሁም አገልግሎታቸውንና ታሪካዊ አመጣጣቸውን ለመግለፅ ተሞክሯል። በሌላ በኩልም የእጅ ስራ ቁሶችን መሰረት ተደርገው በሀገሬው ማህበረሰብ የተገጠሙ ስነቃሎችን በመምረጥ የተወሰኑ ቁሶችን ያላቸውን መልዕክት በመተንተንም ለማሳየት ጥረት ተደርጓል።

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ስር ደግሞ ባህላዊ የእጅ ስራዎችን ማን ሰራቸው? እነዚህ እጀሰሪዎችስ ያላቸው ማህበራዊ ደረጃ ምን ይመስላል? የሚሉት አንኳር ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የሚሞክርበት ነው። እጀ ሰሪዎች ከጥንት ጀምሮ የሀገሪቱን ህዝብ በማገልገል ቆይተዋል። በ3.6 "የቁሳዊ ባህል ሰሪዎችና ማህበራዊ ደረጃ" በሚል በቀረበው ርዕስ ላይ ፓንክረስት ከአክሱም ዘመን ውድቀት በኋላ ኢትዮጵያ ከማንም ጋር ላለመገናኘት የባህር በሯን በዘጋችበት ወቅት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት እንደነበሩ ማስታወሳቸውን መጠቀም ተችሏል። እንዲያውም የኢትዮጵያን የእጅ ስራ ከታሪክ ውልደት ጋር አብሮ የመጣ እንደሆነም በጥናታቸው አሳይተዋል።

እንግዲህ የኢትዮጵያ ብሎም የደጋ ዳሞት ወረዳ የእጅ ሰሪዎች ከታሪክ ውልደት ጋር አብረው ብቅያሉ መሆናቸውን መረዳት የሚቻል ይመስለኛል። ሆኖም ከሌላው ዜጋ በተለየ የማስተዋልና አካባቢያቸውን የበለጠ የመረዳት ብቃታቸው ተነስተው የእለት ከዕለት የኑሮ ውጣውረድ መከወኛ ቁሶችን በመስራታቸው የተለየ ግምት ሲያሰጣቸው ኑሯል። ባህላዊው የጥንት ትውልድ እጀ ሰሪዎች የሚሰሩትን ቁስ እየተጠቀመ ከእነሱ ጋር ለመጋባትና ለመዛመድ ግን ራሱን ሲያከብር መኖሩ ታሪክ አይረሳውም። ነገር ግን የእሱ አካባቢውን የመረዳትና ለአካባቢው ምላሽ የመስጠት አቅሙ የተዘጋ መሆኑን አላስተዋለም ማለት ይቻላል።

በተለይ በቆዳ፣ በሸማና በብረት ስራ ላይ የተሰማሩትን ብልህ እጀ ሰሪዎች ሲያገላቸውና ሲያንቋሸሻቸው ኑሯል። እነሱም የእለት ህይወታቸውን ማቆየት አለባቸውና ዝቅተኛነታቸውን አምነው ተቀብለው ሀገርኛ የጥበብ አሻራ ያረፉባቸውን ቁሶች ከማምረት

አልተገቱም:: በዚህ ጥናት ትኩረት አድርጌ የምመለከተው የቆዳ ሰሪዎችንና በዚህ ጥናት የተካተቱትን በመጥፋት ላይ ያሉ ቁስ ሰሪዎች ብቻ ይሆናል::

"... እጁ ምናምን ስራ የማያውቀው ሰነፍ ብልሁን እየሰደበ አስቸገረ..." /ተክለ ፃድቅ፣ 1983 591/ በማለት አጼ ሚኒልክ ያወጡትን አዋጅ ስንመዝነው ምንም ሙያ የሌለው ሁሉ ጥበበኞችን ያንቋሸሻል የሚል ነው:: በዚህ ላይም በቆዳ ቁሶች ላይ በዋና መረጃ አቀባይነት የተጠቀምኩባቸው አቶ በላይ አለሽኝ፣ አቶ የደሜ ብርሃኑና ወጣት ጥላሁን ምንውየ ሙያውን በዘር ውርርስ ከቤተሰብ እነደወረሱት ቃላቸውን ሰጠውኛል:: እንደ እጅ ባለሞያዎች ከሆነ አባቶቻቸውና አያቶቻቸው ሲያወሩ እንዳሰሙት በማህበረሰቡ ዘንድ ይሰጣቸው የነበረው ግምት እጅግ የወረደ እንደነበር ነው:: "ጥበባችንን ወደው እኛን ያንቋሸሹናል:: ፋቂ፣ ትከረፋለህ፣ ትሸታለህ" ያሉናል ብለውኛል::

እንዲያውም አቶ በላይ አለሽኝ በ/3.6/ ላይ እንደጠቀሱት ከቆላ ሻንጊ ተወልደው ካደጉበት ቦታ በሰፈርተኞቻቸው ጫና ምክንያት አንደተፈናቀሉ ነው:: ወጣት ጥላሁን ምንውየ አየነውም "የቆዳ ስራውን በዘር የወረሰኩት ስለሆነ ብወደውም ትምህርት ቤት ገብቼ ስማር በጓደኞቼ መንቋሸሼና የፋቂ ልጅ መባሌ በስራው እንዳልገፋበት እያደረገኝ ነው:: አንዳንዶች በተለይ አሁን ሰው ሁሉ በነቃበት ዘመን ሲሳደቡ ያሳማምሉ" /13-07-2002፣ ፈረስ ቤት ከተማ/ ብሏል:: ይህ ልጅ ገና የ23 አመት ወጣት ቢሆንም የአባቱን ሙያ እየተገበረ ነው ያለው:: ግን ጫና እየተፈጠረበት መሆኑ አያጠራጥርም:: እናም በማህበረሰቡ የሚሰጣቸው ግምት የበታችነት እንዲሰማቸው አድርጓል:: ከዛሬ አንድ መቶ አመት በፊት አፄ ቴዎድሮስም ሆኑ አፄ ሚኒልክ ያሰሙት የነበረው መከላከል እስካሁንም ያን ያህል ስር እንዳልሰደደ ነው በምልከታዬና በውይይት ወቅት የተረዳሁት::

የቆዳ እጅ ሰሪዎች በማህበረሰቡ ዘንድ የነበራቸው ማህበራዊ ደረጃ የወረደ ስለነበር በጋብቻ፣ በመሀበረና በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ይገለሉ ነበር:: እንዲያውም በአካባቢው ማህበረሰብ "እጅ ሰሪዎች በፈጣሪ ዘንድ ሲፈጠሩ የጎደሉና የረከሱ ናቸው" ተብሎ ስለሚታመን የቤተክርስቲያን ትምህርት ተምረው ቁስ የመሆን እድል የላቸውም ነበር:: "አጥንተ ሰበራ ናቸው" ብለው ስለሚያምኑ ቁስ ሁነው በነሱ መባረክ ክልክል ነበር::

(እንደዚህ ጥናት አጥኝ እማኝነትም ተወልጄ ባደኩበት አካባቢ የእጅ ሰሪ ዝርያ ያለበት ሰው ቁስ ሲሆን አላጋጠመኝም::)

ሌላው በዚህ ጥናት ከታዩት ውስጥ የስፌት፣ የድንጋይ ወፍጮና ከሳር አይነት የሚሰሩ የእጅ ስራ ቁሶች ሰሪዎቻቸው እንደ ቆዳ ሰሪዎች የማይንቋሸሹበት ሁኔታ ነው ያለው:: በዚህ ላይ በተለይ የስፌት እቃዎችን የሴት ሙያ ብቻ ነው የሚል ሁኔታ አለ:: ባህሉ ለሴት ሙያ ብሎ የለየው እንጂ ስፌት የሚሰፉ ሴቶች እንዲያውም ተመርጠው ለባል ይዳሩ ነበር:: ረቂቅ የስፌት ሙያ ያላት ሴት ከሌሎች ሴቶች የተለየ በማህበረሰቡ ዘንድ ትከበራለች:: የተዋጣላት ሰፊ ናት ከተባለች ራሷን ብቻ ሳይሆን ዘመዷን፣ አገቡኞቿን፣ ባለቤታንም ታኮራለች::

በዚህ ሁኔታ የስፌት ሙያ ለሴት ተብሎ ይታይ እንጅ ማህበራዊ ደረጃቸው ጥሩ ነው:: እንዲያውም ለሚስትነት የምትታጭ ልጃገረድ ስፌት ትችላለች? መፍጨት ትችላለች? ተብላ መጠየቋ የማይቀር ነው:: ይህም ስፌትና መፍጨት ለሴቶች መመረጫነት ያገለገሉ ሙያዎች ነበሩ:: በእርግጥ ስፌትም ሆነ መፍጨት ከሴቶችም በተለየ በማህበረሰቡ ዘንድ በድህነትና "በአባተ ጎደሎነት" እሳቤ የዝቅተኛው መደብ ሴቶች ስራ ነው ይባል እንደነበር ነው:: ከዚህ ውጪ ግን "ወንዶች ከውጭ አዘጋጅተው ማምጣት ሴቶች በቤት ውስጥ መፈጫጨት እንጅ መፍጨት የወንዶች ስራ አይደለም" በማለት እንደተናገሩት ሁሉ መፍጨትና መስፋት የሴትነት መገለጫ ነው:: ይሄ ግን የሚከለክል የፈጣሪም ሆነ የሰው የተጻፈ ህግ ኑሮ ሳይሆን ባህሉ የፈጠረው ጉዳይ ነው:: ባህልን መጣስ ደግሞ ቁስ አጥናፉ ለማ መሸሻ እንዳሉት በማህበረቡ ዘንድ መሳቂያና መሳለቂያ ያደርጋል::

ደበሎን፣ የሸቆ ጥላን፣ ዳውጅን፣ ገሳንና የቤት ወፍጮን እንዲሁም የውሃ ወፍጮን መስራት በሰሪዎች ላይ የሚያመጣው ጫና የለም:: በተለይ እነዚህ የእጅ ስራ ቁሶች የሚሰሩት በወንዶች ብቻ ነው:: ዳውጅን በተለየ ስራ የማይበዛባቸው መነኮሳትና ቀሳውስት ቢሰሩትም ሌላው እንዳይሰራው የሚከለክል የለም:: እናም እከሌ ዳውጅ ሰራ፣ ደበሎ ሰራ፣ ወፍጮ አወጣ ተብሎ አይናቅም:: እንዲያውም ደብተራ ተመስጌን ካሳ ጥሩነህ ደበሎ የቆዳ ውጤት ነው:: እስዎ ግን ደበሎን ይሰራሉ:: በዚህ ስራዎ የተለየ ስም ይሰጥዎታል? ብዬ ጠይቄያቸው "እኔ የቆሎ ተማሪ እያለሁ ከቁሶች ነው የተማርኩት:: ሆኖም ይሄ የጨዋው

መ·ያ እንጂ የቆዳ እጀ ሰሪዎች አይደለም:: ጨዋውም ይሰራዋል:: እኔም ተምሬ እንጅ በዝርያ ያገኘሁት አይደለም" ማለታቸው የሚያሳፍር አለመሆኑን አመላካች ነው::

በአጠቃላይ በደጋ ዳሞት ወረዳ ያሉ ባህላዊ እጀሰሪዎች በመ·ያቸው የተለየ ስም የሚሰጣቸው፣ በሴትነት ደግሞ ይህ የእሷ መ·ያ ነው ተብሎ በባህል የሚሰጣት መሆኑ ታይቷል:: በተለይ የቆዳ ሰሪዎችን ስናይ ማህበራዊ ደረጃቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ተመልክቷል:: ሆኖም የወረዳዋን የእጅ ስራ ቁስ በመስራት ከታሪክ ውልደት ጀምሮ ለህዝቡ ያበረከቱትን ተግባር ታሪክ ሊረሳው አይችልም::

ምዕራፍ አምስት

5 ማጠቃለያና ይሁንታ

5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በአማራ ክልል፣ በምዕራብ ጎጃም ዞን ካሉት ወረዳዎች አንዷ በሆነችው በደጋ ዳሞት ወረዳ የተሰራ ነው። ጥናቱ "በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች በደጋ ዳሞት ወረዳ" በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን፣ ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳውም በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች አሰራርና ብሎም በምን ተጽእኖና እንዴት እየጠፉ እንዳሉ በመግለፅ ማሳየት ነው። በዋና ዓላማው ስር ያሉ ስድስት ዝርዝር ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ በቃል መጠይቅና በምልከታ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ እንዲሁም ጥናቱን የተሟላ ለማድረግ የጽሁፍ መጠይቅን፣ ናሙና ጥናትንና የተተኳሪ ቡድን ውይትይን በአጋዥነት መጠቀም ተችሏል።

ከቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በፊትም ካልዐይ መረጃዎችን ከቤተመጽሐፍትና ከዓለም አቀፍ ድረገፆች ማሰባሰብን በዘዴነት ተጠቅሜያለሁ። በዚህ ዘዴ ጥናቱን ለመተንተንና ለመግለፅ የሚውሉ የተለያዩ ትውሮችንና ወረዳዋን የሚመለከቱ ጥሬ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የታተሙ መጻሕፍትን፣ ያልታተሙ ጽሑፎችንና ከኢንተርኔት ለማንበብ ተሞክሯል ። በቃለ መጠይቁ በአብዛኛው ከ 30 ዓመታት በላይ ዕድሜና የተለያየ ያታ ካላቸው 20 ዋናና 14 ተራ በድምሩ 34 የወረዳ መረጃ ሰጪ ነዋሪዎች ጋር መወያየት ተችሏል።

ቃለ መጠይቁንና ምልከታውን ተጨባጭ ለማድረግ የፎቶግራፍና ቪዲዮ ካሜራዎችን፣ ቴፕ ሪከርደርና ማስታወሻ ደብተርን ለመጠቀም ተሞክሯል። በዚህም ፎቶግራፍና የቪዲዮ ውጤቶችን እንዲሁም የቃል አቀባዮችን ንግግር በካሴት መያዝ ተችሏል። መረጃዎች በዚህ መልክ ከተሰባሰቡ በኋላ ሀገረሰባዊ ቤቶችንና የእጅ ስራ ቁሶችን በሁለት ንዑስ ርዕስ ስር የስከለረት ዘጠኝ ሞዴሎችን በማስታወስ ለመተንተንና ለመግለፅ ሙከራ ተደረጓል። ገለፃና ትንተናውን ለመስጠት ይቻል ዘንድም ቁሶችን አካባቢያዊ ስያሜን፣ ግለሰባዊ ብልሃትንና አሰራር ጥበብን ተጠቅሜ ለመመደብ ችያለሁ።

ከጥናቱ ገለፃና ትንተናም የቤቶችን ዓይነት፣ የአሰራር ሂደት ደረጃዎችንና ማህበራዊ ተስተጋብሮውን፣ የቤቶችን መጠንና ቅርፅ፣ ይህን ተከትሎም የባለቤቶችን የኑሮና የክብር ደረጃ ለማሳየት ተችሏል። የእጅ ሥራ ቁሶችንም በተመሳሳይ መልኩ መግለፅና መተንተን የተቻለ ሲሆን፣ የሀገረሰባዊ ቤቶችም ሆኑ የእጅ ሥራ ቁሶች በመጥፋት ላይ መሆንና ለዚህ ደረጃ መድረስ ተፅዕኖ ፈጣሪዎችን ለማመላከት ተሞክሯል። በዋና ተፅዕኖ ፈጣሪነት የተመለከቱትም የደን መጨርጨፍ፣ የኢንዱስትሪ ምርቶች በገፍ መመረት፣ ባህላዊ ቁሶች የጎላ ቀር ምልክት ተደርገው መውሰድ፣ እንዲሁም የቁሳዊ ባህል ሰሪ ባለሞያዎች መ.ያቸውን ለልጆቻቸው ለማውረስ አለመፈለግና ልጆቻቸውም ከአባቶቻቸው ለመወረስ ፍላጎት አለማሳየት ናቸው።

ቁሶች መጀመሪያ ከተሰሩለት አገልግሎት ባሻገር አንዳች መልዕክትን ማሳየት መቻላቸውን ለመጠቆም ሲባል የተመረጡ ቁሶችን በስነቃሎች መሰረት ተንትኖ ለማሳየት ተሞክሯል። ለአብነት ደበሎ፣ አንቀልባ፣ ዳውጃና ማንጠቢያ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የተለየ ማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳን እንደሚገልፁ ተጠቁሟል።

በሌላ መልኩ የአካባቢው ቁስ ሰሪዎች ማህበራዊ ደረጃ እንዴት እንደሆነ፣ ማህበረሰቡ እንዴት እንደሚገልፃቸው ለማሳየት ተችሏል። በዚህም የቆዳ ቁስ ሰሪዎች በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ዝቅተኛ ግምት ሲሰጣቸው፣ የቤት፣ የስፌት፣ የሳር ዓይነትና የድንጋይ ወፍጮ ቁሶችን የሚሰሩ የአካባቢው ባህላዊ ባለሞያዎች ግን የተለየ ግምት አይሰጣቸውም። ሆኖም ቤት የመክደን ችሎታ ያላቸው ግለሰቦች በድህነታቸው ዝቅተኛ ሲሆኑ ጉልበታቸውን ለበሬና ለገንዘብ እንደሚሸጡ ጥናቱ ያሳያል።

ከጥናቱ ማጠቃለያዎች በመነሳት ሀገረሰባዊ ቤቶችም ሆኑ የእጅ ስራ ቁሶች በመጥፋት ላይ መሆናቸውን መደምደም ይቻላል። ይህም ቁሶቹ ጨርሰው የመጥፋትና አሻራቸውን ያለማግኘት፣ አሻራቸው ቢኖርም አገልግሎት አለመስጠትና አገልግሎት የመቀየር፣ የቅርፅና የጥሬ ቁስ ለውጥም ታይቶባቸዋል። ከጥናቱ የድምዳሜ ሀሳብ በመነሳትና በፅሑፍ መጠየቁ አማካይነት የተገኙትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ አጥኝው የሚከተሉትን የ "ይሁንታ" ሀሳቦች ለመጠቆም ችሏል።

5.2 ይሁንታ

በጥናቱ ትኩረት የተደረገባቸው ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች በመጥፋት ላይ መሆናቸውን ከድምዳሜ ላይ ተደርሷል። በመጥፋት ላይ መሆናቸውም የደጋ ዳሞት ወረዳ

ማህበረሰብ የቀደመ አስተሳሰብና ማንነት ገላጭ ጥበባዊ እሴቱ አብሮ እንደሚጠፋ ይታመናል ። መጪው ትውልድም የቀደመ አባቶቹን ማንነትና ጥበብ ሊወረስ አይችልም። ከዚህ አኳያ በመጥፋት ላይ ያሉትን ቁሶች በመታደግ መጪው ትውልድም የቁሶችን የአሰራር ጥበብ አሻራ ይወርስ ዘንድ የሚከተሉትን የይሁንታ ነጥቦች ለመጠቆም ተችሏል።

- ባህላዊ ቁሶቸን ከነፈጠራ አውዳቸው በመቅረስ መጠበቅና ለቱሪዝም መስህብነት እንዲውሉ ቢደርግ፣
- የወረዳዋ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤቱ ባህላዊ ቤቶችን ጥበቃ በሚደረግባቸው መሥሪያ ቤቶችና በተለይም በትምህርት ቤቶች ውስጥ ቢሰራና በቅርስነት ቢይዛቸው፣
- የጽሑፍ መጠይቁን በሞሉበት ወቅት ስለባህላዊ ቁሶች ግንዛቤው ቢኖራቸውም በወረዳዋ ያሉትን ቁሶች ግን የመለየትና የመመዝገብ ሥራን በተለያዩ ድራሽ ሥራዎች ምክንያት እንዳልሰሩ አረጋግጠዋል። ሆኖም የባህልና ቱሪዝም ተቋም በወረዳዋ መቋቋሙ ተቀዳሚ ተግባሩ በአካባቢው ማህበረሰብ የተሰሩትን ቀደምት ባህላዊ ቁሶች መለየት፣ መሰብሰብያ ሙዚየም ሰርቶ ማስቀመጥ ነውና የተጣለበትን ኃላፊነት በቁርጠኝነት ቢወጣ፣
- በወረዳዋ ሙዚየምን ለመስራት የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊነት ብቻ አለመሆኑን በመረዳት የወረዳዋ አስተዳደርና የአካባቢው ማህበረሰብ በጋራ የሚተባበሩበትን መንገድ መፍጠር ቢቻል፣
- ዘመናዊው የሀገራቱ የምህንድስና ጠበብትና ተቋማት አውሮፓ ሰራሽ ህንፃዎችን ከባዕዳን ሀገራት እያመጡ ከመስራትና ከመማር ባሻገር የሀገራቸውን የቀድሞ ባህላዊ የቤት አሰራር ሂደትና ጥበብ በማጥናት ለዚህ ትውልድም ሆነ ለቀጣዩ ትውልድ የሚያወርሱበትን መንገድ ቢቀይሱ፣
- ሀገረሰባዊ የእጅ ሥራ ባለሞያዎችን በማደራጀት ከመንግስትም ሆነ ከረጅ ድርጅቶች የገንዘብም ሆነ የስልጠና ድጋፍ በማድረግ ባህላዊ ሙያቸውን የሚያስቀጥሉበትን መንገድ መቀየስ ቢቻል፣
- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥር ያሉና የቁሳዊ ባህል ጉዳይ የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ተከታታይና ሰፊ የሆነን የምርምር መርሃ ግብር በመቅረፅ በመጥፋት ላይ ያሉ ቁሳዊ ባህሎችን ጥናት ቢያደርጉ የሚሉ ይሁንታዎችን አጥኝው አቅርቧል።

ዋቢ ጽሑፎች

ላጵሶ ጌ. ድልቦ(1983) :: የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓት ጅምር ካፒታሊዝም 1900-1966። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት (ሁለተኛ እትም)::

ሔለን አላምረው (1999) :: "ባህላዊ ሽመናና ቆዳ ሥራ በደንበጫና አካባቢዋ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ለኢትዮጵያ ሥነፅሁፍና ፎክሎር ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ (ያልታተመ)::

ተክለ ዓድቅ መኩሪያ(1983) :: አፄ ምኒሊክና የኢትዮጵያ አንድነት:: አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት::

አስቴር ሙሉ(2000) :: "ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሠሩ የቤት ቁሶች በዘጌ ባህረ ሰላጤ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ለኢትዮጵያ ሥነፅሁፍና ፎክሎር ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ (ያልታተመ)::

አበበ መርዕድ(2000) :: "በጉባ ወረዳ የኦሮሞ ብሔረሰብ የመመገቢያ ቁሳቁስ አሠራር፣ አገልግሎትና ባህላዊ ፋይዳ ትንተና" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ለኢትዮጵያ ሥነፅሁፍና ፎክሎር ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ(ያልታተመ)::

ዋልተንጉስ መኮንን(2000) :: "የሽመናና ጥልፍ ትውፊት በአክሱም::" አዲሰ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ለኢትዮጵያ ስነጽሑፍና ፎክሎር ለኤም ኤ ዲግሪ ሚሟያ የቀረበ (ያልታተመ)::

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል(1993) :: አማርኛ መዝገበ ቃላት።።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ÷ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።።

የደጋ ዳሞት ወረዳ ማስታወቂያና ህዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት "ዳሞት መጽሄት":: (1997) ፊረስ ቤት /ያልታተመ/::

ዐቢዩ አስማማው (2000) :: "የአርጉባ ብሔረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች፣ በአማራ ክልል፣ደቡብ ወሎ ዞን፣ አርጉባ ልዩ ወረዳ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ለኢትዮጵያ ሥነፅሁፍና ፎክሎር ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ (ያልታተመ)::

ፊረስ ቤት 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት "50ኛ ዓመት የወርቅ ኢዮሌልዮ በአል መጽሄት":: (1994) ፊረስ ቤት /ያልታተመ/::

ፊቃደ አዘዘ (1991) :: የስነ ቃል መምሪያ:: አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተመያ ድርጅት::

Ames, L.Kenneth(1984). "Material Culture as Non Verbal..." American Material Culture The Shape of Things Around Us. Bowling Green, Ohio 43403; Bowling Green State University Popular Press.

Braussieur, Ray(1999). "Article Essays/ Creosle- art- folkcraft- hand html" http://www/louisiana/folk/life/org.

Federal Democratic Republic of Ethiopias Population Sensus Commission(2008). "summary and Statically Report of the 2007 Population and Housing Census, Population age and Sex". Addis Ababa Printed by Unite Nations Population Fund; December.

Fekadu Gedamu(2003). "The Gurage House: Its Construction and Socio-Economic Significance", In Proceedings of the 16th International Conference on the History of Ethiopian Art. Addis Ababa University(pp.430-439).

Fosster I. LL, and L. Alchock (ed)(1963). *Culture and Environment.* Routledge and Kegan Pawl, London.

Girma Kidane(1994). "The International Ways of Buildings Houses with in Wolayta Society". 12th Interational Conference of Ethiopian Studies. Michigan State University, The Red sea Press inc.(pp.834-857).

Glassie, Henry(1999). *Material Culture.* Bloomington; Indiana University Press.

Hoben, Alen(1970). "Land Tenure and Social Mobility Among the Damot Amhara". Proceeding of the 3rd International Conference of Ethiopian Studies. Addis Ababa, III Institute of Ethiopian Studies Hailesellassie I University. (pp. 62-88).

Jenkins J. Geraint(1972). "The use of Artifacts..." In Folklore and Folk life: An Introduction. Dorson Richard's ed; Chicago and London; The University of Chicago Press.

Marchese T. Ronald(1984). "Material Culture and Artifact Classification",in *American Material Culture the Shape of Things Around Us.* Mayo Edith's ed; Bowling Green, Ohio 43403; Bowling State University Popular presss.

Mayo, Edith(1984). *American Material Culture the Shape of Things Around Us.* Bowilng Green. Ohio 43403; Bowling State University Popular Press.

Pankhrst, Richard. "History of Ethiopian Handicrafts and Handicraft Workers". In Pado Dieci and Clavdio Viezzoli (eds), Resettle and Rural development in Ethiopian Socio and Economic Research, Training and Technical Assistance in the Bless Valley.

Prown, J. David(2009). "Mind in Matter: An Introduction to Material Culture Theory and Method." Online Available at:http://www.jstor.org/about/terms.html.

Pankhrst, Richard and Rita (1964). "History and the Art Published in Ethiopia and Britain", Ethiopian Observer Journal of Independence Opinion, Economic, History and the Art. Published in Ethiopia, vol. Viii, No 3.

Robert, E. Warren(1972). "Folkcrafts" In Folklore and Folk life: An Introduction. Dorson, Richard's ed; Chicago and London; The University of Chicago Press.

Schlereth J. Thomas (1980). "Understanding the Nine Models of Material culture Interpretation."Online Available at: http://wwweducators/btnep.org.

_____(1980). Artifacts the American Past. American Association for State and Local History; Mashvive.

Silverman A. Raymond.(1999) *Ethiopian Tradition of Creativity.* Michigan University Museum: University of Washington Press.

The Encyclopedia Britannica(1768). Knowledge in Depth, Macropaedia Vol 7, Published with the Editorial Advice of the Faculties of the University of Chicago. (15th ed).

Tolstykh, V.E(1988). "The Policy of the State of Ethiopia in the Spare of Industrial Development". Proceeding of the 9th International Congress of Ethiopian Studies. Moscow; Nuaka Publisher.

አባሪ 1

የዋና መረጃ አቀባዮች መግለጫ

ሙሉ ስም	ፆታ	ዕድሜ	ብሄር	መኖሪያ አካባቢ	ቀበሌ	ስራ	የመረጃው ርዕሰ ጉዳይ	መረጃው የተሰበሰበበት ቀን
አቶ ዳኛው ወርቅነህ ባይነስ	ወ	65	አማራ	ፈረስ ቤት	01	ንግድ	ባህላዊ ቤቶች	28-08-02
አቶ ይታይህ አላምንህ የስጋት	ወ	63	አማራ	ገንቢች	ጭዋኔ ብሀንዴ	ግብርና	- ባህላዊ ቤቶች - የደንጋይ ወፍጮ	19-07-02 03-09-02
መ/ር እንዳሻው ቻሌ እምሩ	ወ	38	"	ሞሰባ	ሞሰባ /ቢቡኝ ወረዳ	መምህር	- የውሃ ወፍጮ	02-07-02
አቶ በላይ አለኸኝ ወንድም	ወ	40	"	ፈረስ ቤት	01	ቆዳ ስራ	- የቆዳ ቁሶች	11-07-02 03-09-02
ወ/ሮ የኔውብ ወተቱ ዘለቀ	ሴ	25	"	ፈረስ ቤት	01	ስፌትና ልጉም	የስፌት ቁሶች	03-09-02
አቶ አስናቀ ይሁኔ አላምንህ	ወ	42	"	ሸሜ	አረፋ መድሃኒያለም	ግብርና	የውሃ ወፍጮ	03-07-02
ወ/ሮ የኔ አየሁ ዘለቀ አየለ	ሴ	40	"	ገንቢች	ጭዋኔ ብሀንዴ	ግብርና	- የቤት ወፍጮ - የስፌት ቁሶች	22-08-02
አቶ የደሜ ብርሃኑ እምሩ	ወ	42	"	ፈረስ ቤት	01	ቆዳ ስራ	ከቆዳ የተሰሩ ቁሶች	14-07-02
እሙሃይ ብዟየሁ አስረስ ዘገየ	ሴ	70	"	ገንቢች	ጭዋኔ ብሀንዴ	ግብርና	- የቤት ወፍጮ - የስፌት ቁሶች	26-08-02

U.S. LIBRARY

ተማሪ ጥላሁን ምንውየ አየነው	ወ	23	"	ፈረስ ቤት	01	ቆዳ ስራ	- ከቆዳ የተሰሩ ቁሶች	13-07-02
ወ/ሮ ያልጋ ደስታ ጌታሁን	ሴ	55	"	ገንቢች	ጭዋኔ ብሄንዴ	ግብርና	- የቤት ወፍጮ - የስፌት ቁሶች	28-08-02
አባ ድልነሳ አላምንህ በላይ	ወ	80	"	አባይ ውሃ	አቅላት ወይበኝ	ግብርና	- የሻቆ ጥላ - ገሳ	26-07-02
አቶ እንየው አንለይ ቦጋለ	ወ	69	"	ገንቢች	ጭዋኔ ብሄንዴ	ግብርና	- የቤት ወፍጮ	07-07-02
አቶ ሰፋኔ ዘለቀ ወርቅነህ	ወ	52	"	ገንቢች	ጭዋኔ ብሄንዴ	ግብርና	- የቆዳ ቁሶች	22-02-02
ቁስ አጥናፉ ለማ መሸሻ	ወ	36	"	ወገም	ዝቋላ ወገም	የቅኔ መሪጌታ	- የሳር አይነት ቁሶች - ባህላዊ ቤቶች	29-08-02
ደብተራ ተመስጌን ካሳ ጥሩነህ	ወ	62	"	ገሳግሶ ማሪያም	ገሳግስ ሾምብርማ	ግብርና	- ደበሎ - የሳር አይነት ቁስ	13-07-02
አባ አዳሙ ካሳ ደስታ	ወ	75	"	ሙዞ በረት	ሻን 2 ደረቄ	ግብርና	- ደበሎ፣ ለምድና ወፍጮ	12-07-02
አቡሃይ በሻህ አይቸህ ዋሴ	ወ	65	"	ወንዳ ወንድ	አቅላት ወይብኝ	ግብርና	- ዳውጃ፣ ደበሎ	15-07-02
አቶ አወቀ አደመ ወርቄ	ወ	48	"	ገንቢች	ጭዋኔ ብሄንዴ	ግብርና	- የቤት ወፍጮ	07-07-02
አቡሃይ ጥሩነህ መርሻ ወንዴ	ወ	82	"	ዝቋላ	ዝቋላ ወገም	የቤ/ክ ዕቃ ጠባቂ	- ባህለዊ ቤቶች - ገሳና ደበሎ	29-08-02

- የመ/ር እንዳሻው ቻሌ፣ የአቶ በላይ አለኸኝ፣ የአቶ አስናቀ ይሁኔ፣ የአባ ድልነሳ አላምንህ፣ የአባ አዳሙ ከሳ፣ የአቡሃይ በሸህ አይቸህ የደብተራ ተመስጌን ካሳ መረጃ በቪዲዮና በመቅረፀ ድምፅ የተሰበሰበ ሲሆን፣ የተቀሩት ዋና መረጃ አቀባዮች ግን በመቅረፅ ድምፅመና በማስታወሻ ደብተር የተያዘ ነው::

አበሪ 2

ተራ የመረጃ አቀባዮች መግለጫ

ሙሉ ስም	ፆታ	ዕድሜ	ብሄር	መኖሪያ አካባቢ	ቀበሌ	ስራ	የመረጃው ርዕሰ ጉዳይ	መረጃው የተሰበሰበበት ቀን
አቶ ምንይችል ዘወልድ ጀምበሬ	ወ	52	አማራ	ቁልቋል	አረፋ ማሲካና	ግብርና	የውሃ ወፍጮ	05-07-2002
አቶ ልይህ ወርቅነህ ባይነስ	ወ	59	"	ሸባ	ጭዋኔ ብዜንዴ	ግብርና	የውሃ ወፍጮ	05-07-2002
መሪጌታ ጥዑመልሳን መለስ	ወ	29	"	ሙዞ በረት	ሻንጊ ደረቄ	የቅኔ መሪጌታ	- የሳር አይነት ቁስ - የበሎ	12-07-2002
አቡሃይ መንግሰቱ አሰጌ አለባ	ወ	65	"	ወንዳ ወንድ	አቅላት ወይባኝ	የቤቴክርስቲያን እቃ ጠባቂ	ደበሎ የሳር አይነት ቁስ	16-07-2002
አቶ ተፈራ ሽታ ዋሴ	ወ	65	"	ገንቧች	ጭዋኔ ብዜንዴ	ግብርና	የቤት ወፍጮ	06-07-2002
አቶ ገበየሁ ከበደ አላምነህ	ወ	70	"	ፎጨጭ	ጭዋኔ ብዜንዴ	ግብርና	የስፌት ቁሶች	22-07-2002
ወ/ሮ ውብርስት ካሳ አደጋ	ሴ	60	"	ፎጨጭ	ጭዋኔ ብዜንዴ	ግብርና	የስፌት ቁሶች	22-07-2002
ወ/ሮ በላይነሽ አስረስ አይቸህ	ሴ	65	"	አባይ ውሃ	አቅላት ወይበኝ	ግብርና	የሽቶ ጥላ	16-07-2002
ወ/ሮ መልካም የኔነህ አላምንህ	ሴ	50	"	ሙዞ በረት	ሻንጊ ደረቄ	ግብርና	የስፌት ቁሶች	25-08-2002
አቶ ፈንቴ አስረስ	ወ	68	"	ፈረስ ቤት ከተማ	ፈረስ ቤት 01	ነጋዴ	ባህላዊ ቤቶች	30-08-2002
አቶ ታሪኬ አድማሴ መላኩ	ወ	45	"	አቦ	አረፋ መድሃኒአለም	ግብርና	የቆዳ ውጤቶች	02-07-2002
ወ/ሮ አታሉ ዘለቀ ወርቅነህ	ሴ	40	"	ጫቶ	ጭዋኔ ብዜንዴ	ነጋዴ	የስፌት ቁሶች	05-07-2002
አቶ ወተቱ ዘለቀ	ወ	67	"	ብዛንዴ	ጭዋኔ ብዜንዴ	ቆዳ ሰሪ	የቆዳ ውጤቶች	20-08-2002
አቶ ላቃቸው ቢራራ ወርቅነህ	ወ	50	"	ገንቧች	ጭዋኔ ብዜንዴ	ግብርና	የቤት ወፍጮ	19-08-2002

- ከአቶ ምን ይችል እስከ አቶ ተፈራ ያሉት መረጃ አቀባዮች መረጃቸው በመቅረፀ ድምፅ የተሰባሰበ ሲሆን ከአቶ ገበየሁ ከበደ እስከ አቶ ላቃቸው ቢራራ ያሉት ደግሞ በማስታወሻ ደብተር የተሰበሰበ ነው::

አባሪ 3

የጽሁፍ መጠይቁን ሞልተው የመለሱ የወረዳዋ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት

ሙሉ ስም	ፆታ	የትውልድ ቦታ	የወረዳ ቆይታ	የትምህርት ደረጃ	የስራ ድርሻ
አቶ መልሰው በላይ	ወ	ደ/ዳሞት	8 ዓመት	10+3	የቅርስ ጥናት ባለሙያ
አቶ ውበቱ ምህረት	ወ	ደ/ዳሞት	ከልደት ጀምሮ	12+3	የመንግስት ስራ
	ወ	ደ/ዳሞት	22 ዓመት	12+3	የስነ ጽሑፍና ቲያትር አፊሰር
	ወ	ፈረስ ቤት	21 ዓመት	12+4	የቅር/መስ/ሃብ/ጥ/ል/ቁ/ አፊሰርና ተወካይ ኃላፊ

አባሪ 4

ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ናሙና ጥያቄዎች

በዚህ አባሪ ላይ የቀረቡና ሌሎች በዚህ ዝርዝር ያልተካተቱ ጥያቄዎች በ10 ካሴቶች የተቀረፁና የተጠቃለሉ ናቸው:: በተጨማሪም በመቅረፀ ድምፅ ያልተካተቱና በተገኘው አጋጣሚ የተነሱ ጥያቄዎች አሉበት::

I. ለሁሉም መረጃ አቀባዮች የቀረቡ አጠቃላይ ናሙና ጥያቄዎች

1. የቁሱ መጠሪያ ስም ምን ይባላል?
2. ቁሱ ከመቼ ጀምሮ ተሰራ? ታሪካዊ አመጣጡ እንዴት ነው?
3. ቁሱን ለመስራት ምን ምን ጥሬ ቁስ ትጠቀማላችሁ?
4. የቁሱ የስራ አጀማመርና አጨራረስ እንዴት ነው? ሂደቱን ቢግሩኝ::
5. የቁሱ መስሪያ ጥሬ ቁስ ከየት ይገኛል? ቁሱን ለመስራት የምትጠቀሙበት መሳሪያስ?
6. የቁሱን መጠን ለመወሰን መለኪያችሁ ምንድን ነው?
7. የቁስ ሰሪዎች ማህበራዊ ሁኔታ እንዴት ይገልጻል?
8. የቁሱ ጠቀሜታ ለምን ይውላል?
9. የቁሱ ዋጋ እንዴት ነበር? አሁን ካለበት ሁኔታ ይለያል?
10. የቁሱ መሰራትና አገልግሎት መስጠት እየቀነሰ ነው ይላሉ?
11. ቁሱ እየጠፋ ነው ካሉ ከመቼ ጀምሮ ነው?
12. ቁሱን እየተካው የሄደው ምን ቁስ ነው?
13. በቁሱ ዙሪያ ይነገሩ የነበሩ አባባሎችን ቢነግሩኝ?
14. በቁሶቹ እየጠፉ መሄድ ህዝቡ ምን ይላል? እርስዎስ ምን ተሰማዎት?
15. አካባቢያዊ ቁሶችን በምን መንገድ ማቆየትና መስቀጠል ይቻላል ይላሉ?

II. ባህላዊ ቤቶችን በተመለከተ የቀረቡ ናሙና ጥያቄዎች

1. ባህላዊ የቤት አይነቶች ስንት ናቸው? አይነታቸውን ቢነግሩኝ?
2. በደጋው፣ በወይናደጋውና በቆላው ለሚሰሩ በቶች የሚሆኑ ጥሬ ቁሶች ይለያያሉ?
3. ለቆላውና ለደጋው አካባቢ ለቤቶች ክዳን የሚሆነው የሳር አይነት ምንድን ነው?
4. የሳር ቤት አሰራር ማህበራዊ ግንኙነት እንዴት ይገለፃል?
5. የሳር ቤት እንዲጠፋ ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው?

6. የሳር ቤት እየጠፋ መሄድ በኑሮ ላይ ያወጣው ችግር አለ ከጤና ከሀብት ከክብር ከእምነት?

III. የቤትና የውሃ ወፍጮን በተመለከተ የቀረቡ ናሙና ጥያቄዎች

1. የቤትና የውሃ ወፍጮ የሚሆነው ምን አይነት ድንጋይ ነው?
2. የወፍጮ አይነቶቹ ልዩነት አላቸው?
3. የቤትና የውሃ ወፍጮ ይሸጥ ነበር?
4. ወፍጮ ከሚገዙት ጋር በምን ሁኔታ ትገናኙ ነበር?
5. ከገዥዎች ጋር ከተነጋገራቸሁ በኋላ ነው ወፍጮውን የምታወጡት ወይስ እውጥታችሁ ታስቀምጣላችሁ?
6. በእናትና በልጅ ወፍጮው መካከል የክብደትና መጠን ልዩነት አለ?
7. በቤት ወፍጮ የሚፈጨው ማን ነው?
8. የውሃ ወፍጮ በየትኛው ወንዝ ላይ ነው የሚተከለው?
9. የውሃ ወፍጮ ድንጋይን እንዴት ማጓጓዝ ይቻል ነበር?
10. የውሃ ወፍጮ ማውጣት ማቆማችሁ በኑሯችሁ ላይ ያመጣው ተፅዕኖ አለ?

IV. ለቆዳ ሰሪዎች የቀረቡ ናሙና ጥያቄዎች

1. የቆዳ ቁስ የመስራት ሙያን ከማን ተማሩት? በስንት አመትዎ?
2. ለመጫኛ፣ ለጠፍር፣ ለማንጠቢያ፣ ለምናር፣ ለአንቀልባና ለዥንዲ ቁሶች የሚሆነው የቆዳ አሰራር ሂደት ተመሳሳይ ነው?
3. የቆዳውን ፀጉር በምን ታነሱታላችሁ?
4. ደበሎን ከእጅ ሰሪዎች ውጪ ያለው ሰው ይሰራዋል?
5. የምን ቆዳ ነው ደበሎ የሚሆነው?
6. ምን ያህል ቆዳ ነው አንድ ደበሎ የሚሆው?
7. ደበሎን ማን ይለብሰዋል? በልባሾች መካከል ልዩነት አለ?

V. ከሳር አይነት ለሚሰሩ ቁሶች የቀረቡ ናሙና ጥያቄዎች

1. ዳውጃን ማን ይሰራዋል? የተለየ ሰሪ አለው?
2. ዳውጃን የሚጠቀመው ማን ነው? በተጠቃሚው ዘንድ የሀብትና የክብር ልዩነት ይታያል?
3. ዳውጃ በአካባቢው ዘንድ የተለየ ተምሳሌታዊነት አለው?
4. የሸቆ ጥላ ለዝናብ ብቻ ነው ወይስ ለፀሀይም መከላከያነት ይውላል?

5. ለገሳ የሚሆነው ሳር ምን አይነት ነው? ሳሩ ብቻ ነው ገሳ የሚሆው?

VI. የሰፌት ቁሶችን በተመለከተ የቀረቡ ናሙና ጥያቄዎች

1. የሞሰበ ወርቅ፣ የሞሰብና የቀለምሻሽ አሰፋፍ አንድ ነው?
2. ወራንታ፣ ላዳኑንና ቁና ተመሳሳይ የአሰፋፍ ጥበብ አላቸው?
3. ለየስፌቶቹ ስንት ዙር ነው የሚሰፋው?
4. አገልግልን ለመስፋት ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?
5. ሞሰበ ወርቅ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የተለየ ክበሬታ አላት?
6. ስፌት መስፋት የማን ሙያ ነው?
7. የስፌት ሙያን ከማን ተማሩት? በስንት አመትዎ?

አባሪ 5

ለደጋ ዳሞት ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ኃላፊና ባለሞያዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ

ስም ---------- ብሄር ---------- የትውልድ ቦታ -------- ያደጉበት ቦታ ----------

በወረዳዋ ያላቸው ቆይታ ---------- የስራ ድርሻ

1. በወረዳዋ ምን ያህል ቀበሌዎች አሉ?
2. በየቀበሌዎቹ ያሉት ነዋሪዎች የሚተዳደሩት በምንድን ነው?

   ሀ. ግብርና መ. ብረታብረት ስራ ሰ. ቅርጫት ስራ

   ለ. ሽመና ሠ. ሸክላ ስራ ሸ. ሌላ ካለ ይግለፁ---------

   ሐ. ንግድ ረ. እንጨት ስራ
3. በሀገረሰባዊ እጅ ስራ የሚተዳደሩት ቀበሌዎች የትኞቹ ናቸው?
4. በወረዳዋ በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች አሉ ብለው ያምናሉ:: አዎ☐ የሉም☐
5. ለጥያቄ ቁጥር አራት መልስዎ አዎ ከሆነ የትኞቹ በመጥፋት ላይ ናቸው?-------
6. በጥያቄ ቁጥር አምስት የዘረዘሯቸው ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች በመጥፋት ላይ የመሆናቸው ምክንያት ምንድን ነው ይላሉ? ----------

   ---
7. በመጥፋ ላይ ናቸው ያሏቸውን ቁሶች ምን ምን ተካቸው? ለእያንዳንዱ ቁስ ትክ ምላሽ ይስጡ:: ----------

   ---
8. በወረዳዋ ውስጥ ያሉ ቁሳዊ ባህሎችን መስረያ ቤታችሁ ለይቶ መዝግቧቸዋል? አዎ☐ የለም☐
9. ለጥያቄ ቁጥር 8 መልስዎ የለም ከሆነ በምን ምክንያት ----------

   ---
10. ቁሳዊ ባህሎችን ለመንከባከብም ሆነ በቅርስነት ለማቆየትና ወደ ቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ ምን ያህል እየጣሩ ነው? ስለቁሳዊ ባህሎችስ ያለዎት ግንዛቤ ምን ያህል ነው? ----------

    ---

11.የደጋ ዳሞት ወረዳ ባህላዊ ቁሶች በቅርስነት የሚካማቹበት መዚየም አላት?

አዎ☐ የለም☐

12.መልስዎ አዎ ከሆነ እንቅስቃሴው ምን ድረስ ነው? ----------


---------- ምን ምን ቁሶችን አካማችቷል?

በዝርዝር ቢጠቅሱልኝ:: ----------


13.ለጥያቄ ቁጥር 11 መልስዎ የለም ከሆነ ለምን? ----------

---------- ለማቋቋምስ እቅድ የላችሁም? ----------


አባሪ



ከአቶ በላይ አለኸኝ ጋር ቃለ ምልልስ ሲደረግ፡፡ አቶ በላይ የቆዳ ዕጀ ሰሪ ናቸው፡፡




ከአባ አዳሙ ከሳ ጋር ቃለ ምልልስ ሲደረግ፡፡ አባ አዳሙ ደበሎ ይሰፋሉ፡፡



ከደብተራ ተመስጌን ከሳ ጋር ቃለ ምልልስ ሲደረግ፡፡ ደብተራ ተመስጌን ዳውጃ ይሰራሉ፡፡

ከአቶ ይተይህ አላምንህ የስጋት ጋር ቃለ ምልልስ ሲደረግ። በባህላዊ ቤቶች ላይ መረጃ ሰጥተውኛል።






ከአቡሃይ በሻህ አይቸህ ጋር ቃለ ምልልስ ሲደረግ። አቡሃይ ዳውጃ ይሰራሉ።




ከአባ ድልነሳ አላምንህ ጋር ቃለ ምልልስ ሲደረግ። አባ ድልነሳ ገሳና የሸቆ ጥላ ይሰራሉ።


LIBRARY

ከሙሃይ ብዙአየሁ አስረስ ጋር ቃለ ምልልስ ሲደረግ። በስፌት ዕቃዎች ዙሪያ መረጃ ሰጥተውኛል።






ከመምህር ዕንዳሻው ቻሌ ጋር ቃለ ምልልስ ሲደረግ። ሞሰባ ት/ቤት ከቢሮአቸው በውሀ ወፍጮ ዙሪያ አነጋግሬያቸዋለሁ።




ከአቶ አስናቀ ይሁኔ ጋር ቃለ ምልልስ። በውሀ ወፍጮ ማውጣት ላይ አነጋግሬያቸዋለሁ።




ከአቶ ዳኛው ወርቅነህ ጋር ቃለ ምልልስ ሲደረግ። በባህላዊ ቤቶች ዙሪያ በተለይ በደርብ የቤት አይነት ላይ መረጃ ሰጥተውኛ ል።

ቀንበር ላይ ያለ ምናር።




ጠጠኝ፣ ድግሪንና ሞፈሪን የምታስረዋ መርገጭ።





ወስከምቢያ የቀለምሻሽ ክዳን።



ከነጠጉሩ የተዘጋጀ የመተኛ ላመነት።



ያረጀ ሞሰብ ይህን ይመስላል።



የደጋ ቤት ክዳን የገብስ ብር።




የቆሎ ተማሪዎች ጎጆ ቤት መኖሪያቸውን የገብስ ብር ሲከድኑ።

ባለ 11 ክንድ የደጋ ቤት፡






ወጋግራው፣ ምስሶው፣ መከታውና የውስጥ ጣሪያው የሚታይ ቤት።



የቆላ እህል ጎተራ።




የሸቆ ጥላ ሲሰሩ።



የሸቆ ጥላ።



ዳውጃ በመሰራት ላይ።




ጓሮ የተተከለ የጤፍ ወፍጮ።



ግምባራ ወንዝ ላይ ተተክሎ ስራውን ያቆመው የአንተነህ በየነ የውሀ ወፍጮ ከስር ከርተው ከላይ ወፍጮው::




መምህር እንደሻው እንዴት ዕንደሚዞር ሲያሳዩ::




መጫኛ




የደርቡ ቤት ሁለቱም በሮች ያሉበት አቅጣጫ።



የደርቡ ቤት የምድሩ በር።



የደርቡ ቤት የፎቁ በር።



ወገም ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በደበሎ ዙሪያ መረጃ የሰጡኝ ቄስ አጥናፉ ደበሎ ለብሰው::



የጥቁር፣ የዳንግሌና የአሻል ፀጉርማ በጎች ቆዳ የተሰፋ ከአባ መሰል ደበሎ::



ደበሎው ከጀርባ ዕንደተለበሰ ይህን ይመስላል::

መግለጫ

ይህ ቴሲስ (የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ) የእኔ ወጥ ስራ (Original) ሲሆን፤ ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩንቨርስቲ የዲግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም፡፡ ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸው መረጃዎች በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን አረጋግጣለሁ፡፡

አስመላሽ እስጢፋኖስ

ስም

ፊርማ

አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የካቲት 2003 ዓ.ም